# ከ
# ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ

## ፩ኛ ወዳጄ ልቤ
የሰውን ጠባይና ኑሮ በምሳሌነት የሚገልጽ

## ፪ኛ ለልጅ ምክር
ለአባት መታሰቢያ

## ፫ ሱካርና ወተት
የልጆች ማሳደጊያ

## ፬ የልብ አሳብ
የብርሃኔና የጽዮን ሞገሳ ጋብቻ

## ፭ አዲስ ዓለም
የቅኖችና የደግ አድራጊዎች መኖሪያ

**አዲስ አበባ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ.ም**

በአርቲስቲክ ፡ ማተሚያ ቤት ፡ ታተመ ።

# ወዳጄ ልቤ እና ሌሎችም

## ከብላቴ ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ

አዲስ አበባ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ.ም

በአርቲስቲክ ፡ ማተሚያ ቤት ፡ ታተመ ።

ISBN 978-99944-52-11-8

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

1. **ወዳጄ ልቤ፤ የሰውን ጠባይና ኑሮ በምሳሌ የሚገልጽ**
    - *መጀመሪያ* በ1915 *ዓ.ም ታተመ*
    - *ሁለተኛ* በ1918 *ዓ.ም ታተመ*
    - *ሦስተኛ* በ 1927 *ዓ.ም ታተመ*
    - *አራተኛ* በ1963 *ዓ.ም ታተመ*
    - እንደገና በ2000 *ዓ.ም ታተመ*
2. **ለልጅ ምክር ለአባት መታሰቢያ**
    - *መጀመሪያ* በ1910 *ዓ.ም ታተመ*
    - *ሁለተኛ* በ1923 *ዓ.ም ታተመ*
    - *ሦስተኛ* በ 1963 *ዓ.ም ታተመ*
    - እንደገና በ2000 *ዓ.ም ታተመ*
3. **ሱካርና ወተት የልጆች ማሳደጊያ**
    - *ሁለተኛ* በ1962 *ዓ.ም ታተመ*
    - *ሦስተኛ* በ 1963 *ዓ.ም ታተመ*
    - እንደገና በ2000 *ዓ.ም ታተመ*
4. **የልብ አሳብ የብርሃኔና የጽዮን ሞገሳ ጋብቻ**
    - *መጀመሪያ* በ1923 *ዓ.ም ታተመ*
    - *ሁለተኛ* በ1963 *ዓ.ም ታተመ*
    - እንደገና በ2000 *ዓ.ም ታተመ*
5. **አዲስ ዓለም የቅኖችና የደግ አድራጊዎች መኖሪያ**
    - *መጀመሪያ* በ1925 *ዓ.ም ታተመ*
    - *ሁለተኛ* በ1955 *ዓ.ም ታተመ*
    - እንደገና በ2000 *ዓ.ም ታተመ*



ከብላቴ ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ

# ማውጫ


መቅድም ........ 15

ክፍል ፩ ወዳጄ ልቤ ........ 16

ስለ መጀመሪያ ዛፍ ........ 16

ስለ ሁለተኛው ዛፍ ........ 18

ስለ ሦስተኛው ዛፍ ........ 20

ስለ ትዕቢትና ስለ ትሕትና መጣላት ........ 20

ስለ ንፍገት ተራራ ........ 23

ስለ ምእመን ሠርግ ........ 25

ምእመን ሞት ........ 29

ስለ ምእመን ሞት መርዶ ........ 32

ስለ ፍቅርና ስለ ተንኰል ........ 35

ስለ ፍቅርና መከራ ........ 39

ስለ ፍቅር ሕይወት ........ 44

ስለ አቶ እንደ ጊዜው ........ 45

ስለ ትምሕርት ቤት ........ 46

ስለ ወይዘሮ ዓለሚቱ ........ 50

ስለ አዝማሪው ........ 51

ስለ ንጉሥ መልእክት ........ 57

ስለ ማቴዎስና ስለ ሉቃስ፤ ስለ ሙሴም ጨዋታ ........ 59

ስለ ወዳጄ ልቤ ቁጣ ........ 63

ስለ ትልቅ አዳራሽ ........ 64

ስለ ትልቅ ኃዘን ........ 67

ስለ ደቡብ መንገድ ........ 72

ስለ መሰነባበት ........ 73

ስለ ወንጌል መሰነባበት ............................................ 74
ወንጌል በዘፈን ስለ ማሞገስ........................................ 76
ስለ ፍቅር መሰነባበት................................................ 82
ስለ ፍቅር ምክር....................................................... 84
ስለ መንግሥተ ሰማያት ወሬ....................................... 86
ስለ ጸሎት መጸለይ .................................................. 87
ስለ ሁለተኛው ዘፈን ................................................. 88
ስለ ሀገራችን መንገድ................................................ 94
ክፍል ፪ ለልጅ ምክር .................................................... 94
መቅድም ....................................................................... 94
መጀመሪያ ክፍል......................................................... 98
ሁለተኛ ክፍል.......................................................... 100
ሦስተኛ ክፍል .......................................................... 104
አራተኛ ክፍል .......................................................... 107
አምስተኛ ክፍል........................................................ 112
ክፍል ፫ ሱካርና ወተት ............................................... 114
ልጆቼ ሆይ፤ .......................................................... 114
ስለ አንድ ከበርቴ ሰው............................................ 115
ስለ ሁለት ባልንጀሮች............................................ 116
ስለ የብራማ ካህን .................................................. 117
ስለ የእስጳንያ ሰውና የህንድ ሰው ............................. 118
ስለ አንድ አንበሳና አንድ ቡችላ ................................ 118
ተረት ስለ ሚወድ ንጉሥ ......................................... 119
ስለ አንድ ጫማ ሰፊ............................................... 121
ስለ አንድ ሰውና ስለ አንድ ውሻ ................................ 122

ስለ አንበሳና ስለ አይጥ ............................................ 123
ስለ የሌት ወፍ....................................................... 124
ስለ ቀበሮና ስለ ፍየል ............................................... 125
ስለ የጦጣ ፍርድ..................................................... 126
ስለ አንበሳና ስለ ነብር፤ ስለ ጅብና አህያ ባልንጀርነት......... 127
ስለ አንድ ቅምጥል የበግ ግልገል .................................. 129
አንድ ዳውላ እህል ስለ ተሰረቀበት ሰው.......................... 130
ስለ እንግሊዝ ንጉሥ ጆርጅ ፫ኛ.................................. 130
ስለ የጀርመን ንጉሡስ ............................................... 131
ስለ አንድ ሽማግሌ ሰውና ስለ አንዲት ሴት ልጅ............... 132
ክፍል ፬ የልብ አሳብ .................................................... 133
የብርሃኔና የጽዮን ሞገሳ ጋብቻ .................................... 133
አቶ ክብረትና ገነሆይ ንጋቷ ጽዮን ሞገሳን ስለ መውለዳቸው 134
ስለ ጽዮን ሞገሳ እጮኛ - ስለ ብርሃኔ ............................ 137
ብርሃኔ ጽዮን ሞገሳን ለማግባት ቁርጥ አሳብ ስለ ማድረጉ ... 139
ጽዮን ሞገሳ ለትምሕርት ወደ ደብረ ሊባኖስ ስለ መውረድዋ 143
ጽዮን ሞገሳ ትምሕርቷን ጨርሳ ወደ ሀገርዋ ስለ መመለስዋ. 151
ስለ ብርሃኔና ጽዮን ሞገሳ የቃል ኪዳን ጋብቻ................... 155
ስለ ጽዮን ሞገሳ ልጅ መውለድ..................................... 159
ስለ ሥላሴ በዓል ዝክርና ስለ ብርሃኔ ሞት ...................... 163
ክፍል ፭ አዲስ ዓለም.................................................... 164
የቅኖችና የደግ አድራጊዎች መኖሪያ .............................. 164
ስለ ዓወቀ ትውልድና ወደ ፓሪስ ስለ መሔዱ.................. 166
ስለ አቶ እንደ ልቡ መታመምና መሞት.......................... 169
ስለ አቶ እንደ ልቡ ተዝካር......................................... 172

ስለ ተዝካር የተደረገ ጉባዔ........................................175
ዓወቀ በአባቱ መቃብር ላይ ጥርብ ድንጋይ ስለ ማቆሙ......180
ዓወቀ ዘመዶቹ ያጩለትን ሚስት አላገባም ስለ ማለቱ........182
ዓወቀ ራሱ የመረጣትን ሚስት አጭቶ ስለ ማግባቱ...........184
የዓወቀ ዘመዶች ከብዙ ቀን በኋላ አሳቡን ስለ መቀበላቸው .191
ስለ ዓወቀና ስለ መምሬ ሰባጋዲስ የዕርቅ ነገር ..................194
ስለ መምሬ ሰባጋዲስ ድንጋጤና ጥንቃቄ........................197
ስለ ሁለተኛው ጉባዔ ነገር .........................................198
ስለ መምሬ ሰባጋዲስ ስብከት .....................................202

# ማስተዋወቂያ

የሃያኛው ክፍለ ዘመን የመጀመርያ አጋማሽ ቀዳሚ ምእራፍ፣ በተለይ ከጦቢያ (**ልብ ወለድ ታሪክ**) መታምተም እስከ ጣሊያን መግባት፣ 1900 – 1928 ያለው ጊዜ ለአማርኛ ስነ ጽሑፍ የመሰረት መጣያ ዘመን ነው ተብሎ ይታመናል። በዚህ በተጠቀሰው ዘመን ተእንስተው የአማርኛን ስነ ጽሑፍ መሰረት ከጣሉና ካጠበቁ ደራስያን መሃል እውቁ የፖለቲካ ሰውና ዲፕሎማት፣ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ አንዱ ናቸው። ብላቴ ጌታ በዚሁ ዘመን ውስጥ ባነሱት ሃሳብ፣ በተመሰረቱበት ዘውግና በመረጡት የአጻጻፍ ቅጥ ለየቅል የሆኑ በርካታ መጻሕፍትን - የልብ ወልድ፣ የታሪክ የሕይወት ታሪክ፣ የጉዞ ማስታወሻ፣ የስነ ቃል፣ የመጻሕፍት ዝርዝር፣ የተግሳጽና የምክር መጻሕፍትን - አሳትመዋል።

ከእነዚህ፣ ደራሲው በሕይወት እያሉ ካሳተሟቸው መጻሕፍት መሃከል ደግሞ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ «ወዳጄ ልቤ»፤ «ለልጅ ምክር ለአባት መታሰቢያ»፤ «ሱካርና ወተት የልጆች ማሳደጊያ»፤ «ለልብ አሳብ የብርሃኔና የጽዮን ሞገሳ ጋብቻ» እና «አዲስ ዓለም የቅኖችና የደግ አድራጊዎች መኖርያም» የሚሉትን አምስት አምስት ድርሰቶች በአንድ ቅጽ ጠቅልሎ አሳትሟል። ከአምስቱ ድርሰቶች መሃል «ለልጅ ምጅር ለአባት መታሰቢያ» እና «ሱካርና ወተት የልጆች ማሳደጊያ» ለልጆች ታስበው የተጻፉ የምክር - የተግሳጽ እና የተረት መጻሕፍት ሲሆኑ ቀሪዎቹ ሦስት ድርሰቶች ደግሞ ልብ ወለድ ናቸው። ይህ መታሰቢያም በዋናነት ልብ ወለዶቹን የሚያስተዋውቅ ይሆናል። ልብ ወለዶቹን በተመሰረቱበት ሃሳብ እና በተከየኑበት መንገድ፤ «የልብ አሳብ»ን እና «አዲስ አለም»ን በአንድ ወገን፤ «ወዳጄ ልቤ»ን ደግሞ በሌላ ወገን አድርገን እንመልከት።

<u>አንደኛ፤ «የልብ አሳብ» እና «አዲስ ዓለም»፣ ማሕበራዊ ልብ ወለዶች፤</u>

እርግጥ ነው እነዚህን ከ75 ዓመት በፊት የተጻፉ ድርሰቶች ዛሬ ልብ ወለድን በምንመዝንባቸው ኪናዊ መለኪያዎች - በአተራረክ ቴክኒክ፣ በሙቼት አቀራረጽ፣ በገጽ ባሕርይ አሳሳል ጥበብ ወዘተ. - የምር እንመዝናችሁ ካልን መቸገራችን አይቀርም። ዳሩ ግን፣ አንድም በኪናዊ

ቸ

እሴቶቻቸው የሳሉ ቢሆኑም እንደምናባዊነት፣ ፈጠራዊነት ያሉ መሰረታዊ የስነ ጽሑፍ ባሕርያን በማሟላታቸው፤ አንድም፣ ደራሲው «አዲስ ዓለም» ለተባለው ድርሰት በጻፉት መቅድም በቀጥታ እንደሚነግሩን (ገጽ <u>፻፷፫</u>) በትክክል ከተደረጉና

ከሆኑ ገጠመኞች ይልቅ በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ልሆኑና ሊደርሱ በሚችሉ እውነታዎች ላይ በመመስረታቸው፤ በገቢር ከታዩና ከተሰሙ ጉዳዮች ይልቅ ከዓይነ ኅሊናና ከእዝነ ልቡና (በጥቅሉ ከምናብ) የመነጩ ስሜታዊና ሃሳብ ገጠመኞችን ምርጫቸው በማድረጋቸው የድርሰቶቹን ልብ ወለዳዊነት አምነን እንቀበላለን። ድርሰቶቹ የተጻፉበትን ዘመንና ሁኔታም ከግምት ማስገባቱ ተገቢ ይመስለኛል።

የልብ ወለዶቹ አቢይ ትኩረት የማሕበረሰቡ የእሴት ስርዓት እና የገጸ ባሕርያቱ ማሕበራዊ ማንነት ነው። በልብ ወለዶቹ ውስጥ፣ የማሕበረሰቡን ማሕበራዊ ተቋማት፤ በተለይም ጋብቻን፣ ቤተሰብን ዝምድናን ወዘተ. የሚመለከቱ ቤተ ዘመዳዊ ተቋማት እና ከሃይማኖት ከትምህርትና ከእደ ጥበብ ጋር ትስስር ያላቸው የባህል ተቋማት እንደየዓይነታቸው እና እርከናቸው የተነሱ ሲሆን በተቋማቱ ውስጥም ይሁን በተቋማቱ መሃል ያለ ትስስርም በመጠኑ ተብሎበታል። ግለ ሰብ ገጸ ባሕርያት ከተቋማቱ ጋር ካሏቸው ፈርጀ ብዙ መስተጋብሮች የሚወለዱ ስምምነቶችና ይልቁንም በአስተሳሰብ፣ በአመለካከት፣ በአኗኗር ፈሊጥ ልዩነት ምክንያት የሚፈለፈሉ ግጭቶቹ ያስከትሏቸው ማሕበራዊ ለውጦች (አንዳንዴም ቀውሶች) የእነዚህ ልብ ወለዶች የትኩረት ነጥቦች ናቸው።

ኅሩይ በእነዚህ ድርሰቶቻቸው የማሕበራቸውን ገበና በድፍረት ይገልጣሉ። ከጽኑነታቸው የተነሳ ድርስቶቹ ከተጻፉ ከ75 ዓመት በኋላ፣ ዛሬን ጭምር የዘለቁ አጓጉል ልማዶችን፣ ያለ እድሜ ጋብቻን፣ በቤተሰብ የሚታቀድና የሚቆረጥ ጋብቻን በድርፍረት (ጥበብና ብልሃት ባለዘቡት ድፍረት) ይተቻሉ። ኅሩይ የገነቡት ምናባዊ ዓለም ወላጅና ልጅ ተቻችለውና ተከባብረው የሚኖሩበት፣ የጾታ እኩልነት የሰፈነበት ጭምርም ነው። በተለይም በዘመኑ የነበረው የሴትነት እሴት ተነቅሎ

ኅ

የወደቀ እስኪመስል ሚስት ከባሏ እኩል በልጇ እጣ ፈንታ ላይ ትመክራለች። ሴት ልጅ ምርጫዋ ይከበራል፤ ፍላጎቷን ትፈጽማለች፤ ፈቃዷን ትሞላለች።

የኅሩይ ድርስቶች ማሕበራዊ ለውጥ ነው ግባቸው። ለውጥን ይናፍቃሉ፤ ለጥን ይጠራሉ፤ ለውጥን ያሰፍናሉ። ለአንዱ ድርሰታቸው በጻፉት መቅድም «አንዳንድ ሰዎች ብዙ ዘመን የኖረውን ልማድ ማሻሻል ማደስ እንደ ነውር ይመስላቸዋል። ይኸውም የቀድሞውንና የዛሬውን ታሪክ ካለማንበባቸውና ካለመረዳታቸው የተነሣ ነው --- (ገጽ ፻፴፫) የሚሉን ኅሩይ በሸንጎ፣ በሊቃውንቱ ፊት በሚደረግ ሙግት

አጓጉል ልማድ በለውጥ ሲረታ ያሳያሉ። ዳሩ ግን፣ በአዳዲስና ተራማጅ አስተሳሰቦች የሚመሰረቱት ጠቃሚ በሆኑ ነባር የማሕበሩ እሴቶች ላይ በመሆኑ ይህ ለውጥ ሙሉና እንግዳ ነው ለማለት እሴቶች ላይ በመሆኑ ይህ ለውጥ ሙሉና እንግዳ ነው ለማለት አንችልም። በዚህ ዓይነቱ ስርዓት የታነጹ፣ ወይም የዚህ ዓይነቱ እሴት ማደርያ የሆኑ ገጸ ባሕርያት፣ የምር ኢትዮጵያዊ ሆነው ነው የተቀረጹት፤ በአንድ በኩል ማሕበራዊ ለውጥ ይጠነስሳሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ባህልና ታሪክ ጠብቀው ያኖራሉ። በተጨማሪም ማሕበራዊ ለውጥ ማሕበራዊ ስርዓት ሳይናጋ፤ ማሕበራዊ ቀውስ ሳይፈጠር የሚመጣ ክስተት በመሆኑ ልብ ወለዶቹ የደራሲው በጎ ርእይ አድሮ የተገለጠባቸው ድርሰቶች ናቸው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል።

<u>ሁለተኛ፤ «ወዳጄ ልቤ»፤ አሊጎሪያዊ ልብ ወለድ፤</u>

በሀገራችን የስነ ጽሑፍ ትምህርት ውስጥ ዛሬም ድረስ ለአሌጎሪያዊ አጻጻፍ በምሳሌነት የሚጠቀሰ **ወዳጄ ልቤ** በዋናነት በመንፈሳዊ ወይም ሃይማኖታዊ እና ስነ ምግባራዊ እሴቶች ላይ ተመስርቶ የተጻፈ ልብ ወለድ ነው። የ«ወዳጄ ልቤ»ን ዓይነት ልብ ወለዶች (ክርስቲያናዊ አሌጎሪ /Christian allegory/ በመባል ይጠራሉ) አቢይ አላማና ተግባር የማሕበራቸውን መንፈሳዊ እሴቶች አንስተው የስነ ምግባር ትምህርት መስጠት በመሆኑ ብዙውን ጊዜ አንባቢያቸውን ለመማረክና ለማሸነፍ ይቸገራሉ። ዳሩ ግን በ«ወዳጄ ልቤ»፣ ደራሲው እያፈራረቁ

ነ

በተገለገሉባቸው ቴክኒኮች፣ እያሰባጠሩ በዘርዋቸው ፎክሎራዊ ቅርጾች እንዲሁም የታሪኩን ፍሰት በተቆጣጠሩባቸው «ጉዞ» እና «ፍለጋ» ባሉ ነባር ሚታዊ መባያዎች (mythological motifs) አማካይነት ወለዱን የታደጉት ይመስለኛል።

ልብ ወለዱ ሲጀምር እንዲህ ይላል፤ «በተወለድሁ **<u>በ፲፰ ዓመት ከዘመዶቼ ተለይቼ ወዳጅጄ ልቤን ብቻ አስከትዬ ከቤቴ ተነሣሁ።</u>** አሳቤም ይህን ዓለም (መጻሕፍትን) በምሥራቅና በምዕራብ፣ በሰሜንና በደቡብ እየዞርሁ ለማየት ነበር» (ገጽ ፫፣ አጽንኦት የእኔ)። በጥቅሱ ውስጥ ያሰርመርኩባቸው አራት ሃሳቦች ልብ ወለዱን በወጉ ለማንበብ (በተለይም ለሚታዊ ንባብ /mythological reading/ እጅግ ወሳኝ ይመስሉኛል። በልማድ እንደምናውቀው 18 ዓመት፣ ሰው ከልጅነት ወደ ጎልማሳነት ወደ ሙሉ ሰውነት የሚሸጋገርበት አካባቢውን ለመረዳት፣ ማሕበሩን ለመመርመር፣ ራሱን ለመፈተሽ፣ በጥቅሉም የሰው ልጅን የመኖር ምክንያት ፈልጎ ለማግኘት የሚቀሰቀስበት የሚተጋበት እድሜ ነው የ«ወዳጄ ልቤ» ገጸ ባሕርይ ከሰሜን እስከ

ደቡብ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ በተዘረጋው የመጻሕፍት ዓለም ውስጥ እንደ እውቀት፣ ጥበብ፣ እውነት ያሉ ጸናን ጉዳዮችን ፍለጋ ነው የሚጓዘው። ይህ ዓይነቱ ጉዞ በመመሰጥ፣ በማብሰልሰል፣ በማሰላሰል እና እነሱን በመሰሉ ጥብቅ ዲሲፕሊኖች የሚካሄድ በመሆኑ አካባቢን በመንፈስ መለየት፣ አካልን መቆጣጠርና በስጋዊ ፍላጎቶች ላይ መሰልጠን፣ ወደ ውስጥም ርቆ መጓዝ ይቻላል። (ይህንን ነው እንግዲህ ገጸ ባሕርይው፣ «ከዘመዶቼ ተለይቼ ወዳጄ ልቤን ብቻ አስከትዬ ከቤት ተነሳሁ» የሚለን። )

በጉዞ ውስጥ ከመለየት (departure) በኋላ የሚከትለው ምእራፍ ተጋድሎ ነው። ለረጅም ጉዞ የወጣ መንገደኛ ብዙውን ጊዜ ሊወጣው ከሚከብደው አስቸጋሪ ፈተና ውስጥ ይጣላል (ወይም ይገባል)። በምድር ላይ በሚፈጸም አካላዊ ጉዞ (exterior pilgrimage) ተጓዡ ከሰውና ከተፈጥሮ ክስተቶች ጋር ትንንቅ ይገጥማል። ከፍ ብዬ እንደጠቆምኩት፣ «ወዳጄ ልቤ» የተመሰረተው በንባብ አማካይነት በሚካሄድ አእምሯዊና መንፈሳዊ ጉዞ (interior pilgrimage) ላይ በመሆኑ ገጸ ባሕይው

ኘ

በመልክአ ምድር ትይዩ ያለውን **የመልክአ ልቡና** (inner landscape) «ጫካ» የማቋረጥ፣ «ተራራ» የመውጣት፣ «ባሕር» የመጥለቅ ግዴታ ነው የሚጣልበት። መልክአ ልቡና በትርጓሜ ካልሆነ በቀር በገሃድ የማይደረስበት የሰው ልጅ ኅሊናዊ ዓለም ነው። ይህ ዓለም ደግሞ የሰው ልጆች ስሜታዊ፣ ምግባራዊ እና እውቀታዊ ማንነት መኖርያ ወይም ማደርያ ነው። ይህ ነው እንግዲህ የድርሰቱ አቢይ ጉዳይ። ልብ ወለዱ እንደሚያሳየን የሰው ልጅ ረቂቅ ባህርያት **በአንድ ሰው ልቡና** ውስጥ **በአንድ ጊዜ** ተቃርነው፣ ተቀያይጠው ይመጣሉ። ትህትና የሚባል ጊዜ የጣለው የጨዋ ልጅ እና ትዕቢት የሚባ ሌባ ጌታ ድንቁርና በሚባል አገር አብረው ይኖራሉ (ገጽ ፳)። ፍቅር ገርነትን አግብቶ፣ ቅንነትን አሽከር ቀጥሮ ከቅናትና ከምቀኝነት ጋር ተጎራብቶ በአንድ አገር ይኖራል (ገጽ ፳)። ነጭ ለባሹና ሳቂታው ተንኮል አቶ ፍቅር ቤት በእንግድነት ያድራል (ገጽ ፳)። ይህ ዓይነቱ የተጠፋፊዎችና የተቃራኒዎች መገጣጠምና መቀያየጥ ነው የሰው ልጅን ስብእና የሚያወሳስበው፤ ፀባዩን፣ ፍላጎቱንና ምግባራዊ ማንነቱን እያደበላለቀ፤ አንድ ሰው ስለገዛ ራሱ፣ ሰው ስለ ጥቅሉ የሰው ልጅ፣ ሰው ስለ አለመ አለማቱ፣ ሰው ስለ አምላኩ ያለውን አመለካከት፣ ፍልስፍናና እምነት እያዛነቀ፣ ወዘተ። የልብ ወለዱ ማቀንቀኛ - ማጠንጠኛ ጉዳዮች እነዚህ ናቸው። ጉዳዮቹ የሰውን ልጅ አጠቃላይ ኑባሬ (human existence) የሚመለከቱ ኅሊናዊ ክስተቶች በመሆናቸው እጅጉን ይረቅቃሉ፤ ይጠልቃሉ፤ ይወሳሰባሉ።

ይህንን ጸናን እውነታ በመረዳት ይመስለኛ ደራሲው ልብ ወለዳቸውን ሙሉ በሙሉ በአሌጎሪያዊ የአጻጻፍ ቅጥ የከየኑት። በአሌጎሪያዊ አጻጻፍ ሰው ያልሆኑ ነገሮች፣ ረቂቅ ሃሳቦችና ግብሮች የሰው ልጅን ተግባርና ባህርይ ይወርሳሉ። አንደበት አውጥተው ይናገራሉ፤ አካል ገዝተው፤ ቅርጽ አበጅተው ይንቀሳቀሳሉ፤ ስሜት ሊያግቱ -- ሊያዝኑ፣ ሊደሰቱ፣ ሊከፉ፣ ተስፋ ሊያደርጉም ይችላሉ። «ምርምር» እና «ድንቁርና» የአገር ስሞች ናቸው። ትዕቢት አንበሳ፣ ንፍገት ደግሞ አቦሸማኔ ነው (ገጽ ፵፫)። ንፍገት ከርዝሙቱ የተነሳ «በጫፉ ላይ የቆሙ እንደሆነ ሰዉም፣ ከብቱም፣ ወርቁም ብሩም -- ጥቂት መስሎ» የሚታይበት ረጅም ተራራ ነው (ገጽ ፱)። በሰብዓዊ

አ

የእሴት ስርዓት ይመራሉ፤ ይተዳደራሉ። ትሕትና ወንበር ዘርግቶ ያስተምራል (ገጽ ፳፱)፤ «የበለው ጌታ» ለአቶ ቅናት፣ «የፍጀው ጌታ ለአቶ ተንኮል የተሰጡ የፈረስ ስሞች ናቸው። ተንኮልና ቅናት በጦር ልብሳቸው ደምቀው በፈረስ ስማቸው ይፎክራሉ፤ ይሸልላሉ፤ ያቅራራሉ (ገጽ ፴፰)። ረቂቆቹ ኅሊናዊ ክስተቶ በዚህ ልብ ወለድ ውስጥ ለዓይነ ልቡና እጅግ ቅርብ ሆነው ተስለዋል። ልብ ወለዱ የተከየነበት ቋንቋ ቅለትና የአቀራረቡ ቀጥተኛነት ደግሞ ጽንሰ ሃሳቦቹን ጭምር ገር አድርጓቸዋል።

ከወገን በመለየት የሚጀምረው «ወዳጄ ልቤ» ገጸ ባሕርይውን ወደ ተለያቸው «ዘመዶቹ» በመመለስ (return) ነው የሚቋጨው። በሚታዊ ጉዞ ውስጥ የገባ ገጸ ባሕርይ ወደ መኖርያው የሚመለስ ለተለየው ዓለሙ ከሚጠቅም አንዳች በረከት (boon) ጋር ነው። በ«ወዳጄ ልቤ» ውስጥ መሰረታዊው ጉዳይ በንባብ ምክንያት ወደ ግጭት የሚገባ ልቡና ነው። ከፍ ብለን እንደተመለከትነው በልቡና ውስጥ የሚከሰተው የተቃራኒና የተጠፋፊ ስሜቶች፣ ምግባሮችና አስተሳሰቦች መገጣጠም መደበላለቅ የሚፈጥረው ለባለቤቱ እንግዳ የሆነ ቀውስ አለ። ሰው ለራሱም ጭምር ድብቅና ሽሽግ ከሆነ ማንነት (ከፉም ሆነ ደግ) ጋር መተዋወቁ (self realization) ቀዳሚው በረከት ነው። (በስነ ልቡና ተራ እንናገር ከተባለ ይህ ጉዞ ንቁ ከሆነው የሰው አእምሮ ወይም ማንነት «the conscious self» በውል ወደማይታወቀው፣ ለባለቤቱ ጭምር እንግዳ ወደ ሆነው ማንነት «unconscious self» የሚደረግ ነው።)

ከዚህ ዓይነቱ መገለጥ፣ ከዚህ ዓይነቱ የራስ እውቀት በኋላ ሕይወት እንደወትሮዋ አትሆንም። ተለምዷዊው የኑሮ አዳምስ ያረጃል። ከነባር ጽንሰ ሃሳቦችና እሴቶች ፍቺ ይታጣል። በዚህ ምክንያት ሰው ከገዛ ራሱ ጋር ትንንቅ ይገጥማል፤ ራሱን ያሸንፋል፤ ከራሱ ጋር (ወይም በራሱ መሃል) እርቅ ያወርዳል። በስነ ምግባር ደንቦች ይታሻል፤ በስሜት ይበስላል፤ በእውቀት፣ በግንዛቤ ይልቃል። በአዲስ ማንነት

ይወለዳል፡፡ ሰው በጥቅሉ ለሰብእና ልእልና (transfiguration of personality) ይበቃል። በተራዛሚው ለሰርከ ሕይወቱም ለዘለለት ዓለሙም መታደስ (renovation of the world) ምክንያት ይሆናል። ይህ ነው ከረጅሙ ጉዞ በኋላ

ከ

ወደተለየው የሰርከ ሕይወት፣ ዘዘለለታዊ ማንነት ይዞ የሚመለሰው በረከት። ለዚህም ይመስለኛል በልብ ወለዱ ማብቂያ በሚመጡ ምእራፎች ውስጥ ከቀዳሚዎቹ ምእራፎች እጅግ በተለየ እንደ ትኅትና፣ ቸርነት፣ ይቅር፣ መባባል፣ ድኅነት ወዘተ. ያሉ በጎ እሴቶች የሚገኙት።

## <u>ለማሳረግ ያህል፤</u>

እስካሁን በመግቢያነት ያስተዋወቅኋቸው የማንበቢያ አንጻሮች እነዚህን፣ በአንድ ቅጽ ተጠቃለው የቀረቡ ሥራዎች ለማንበብ ብቸኛ መንገዶች አይደሉ፣፤ ፈጽሞ። ሥራዎቹን አናጥሎም ይሁን አዳብሎ ለማጣጣም የሚያስችሉ በርካታ የማንበቢያ አማራጮች አሉን። የደርስቶቹን ባሕርይ፣ ድርስቶቹ የበቀሉበትን ዘመንና ሥፍራ፣ እንዲሁም ከዘመኑና ከሥፍራው ጋር የሚናበቡ ማሕበራዊና ርእዮተ ዓለማዊ አንድምታዎችን ከግምት እስካስገባን ድረስ በየትኛውም የማንበቢያ አንጻር መገልገል እንችላለን። ሁላችንም እንደምናውቀው፣ ጥሩ ልብ ወለድ በጥበባዊ ኃይሉ ታግዞ ታላላቆቹን ሰብዓዊ እሴቶች ያነሳል፤ ሕይወትን ይመረምራል፤ ሕይወትን ይተረጉማል፤ የደረሰበንም ግኝት በቋንቋው ሀይል ይስላል። ወይም በሌላ አነጋገር ስለ ጽሑፍ ከፍ ብዬ በዘረዘርኳቸው ጉዳዮች ላይ በደራሲው የሚሰጥ አስተያየትና ትችት ነው። አንድን ልብ ወለድ ስናነብ ምናልባት - ምናልባት አስተያየቱና ትችቱ ሊጎረብጠን፣ ትርጓሜው ላይስማማን ይችል ይሆናል። የምናነበው ድርሰት ስነ ጽሑፋዊ ሥራ እስከሆነ ድረስ ግን ቅድምና የምንሰጠው ጉዳይ አከያየኑ መሆን አለበት። ስለዚህ ምናልባት ስብከቱ ያልጣመው፤ አስተምሕሮቱ ያልተዋጠለት ቢኖር እንኳ ቢያንስ ቢያንስ አለም ያታየችበትንና የተተችበትን፣ ሕይወት የተተረጎመበትን፣ የሰው ልጅነት የተበየነበትን **ጥበባዊ መንገድ** አድንቆ ይለፍ። መልካም ንባብ።

ቴዎድሮስ ግብሬ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሥነ ጽሑፍ

ትምህርት ክፍል መምህር

# መቅድም

ይህን መጽሐፍ የምትመለከቱ ሰዎች ሁሉ አስቀድማችሁ የራሳችሁን ጠባይና ኑሮ መርምሩበት።

ክፉ ጠባይና ክፉ ኑሮ ያለባችሁ እንደ ሆነ ግን ከእናንተ አውጥታችሁ ጥላችሁ መልካሙን ጠባይና መልካሙን ኑሮ ያዙ።

ነቢዩ ኤርምያስ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ የልባችሁንም ቆላፍነት አርቁ ብሏልና። ኤር. ፬፥ ፬።

የራሳችሁን ጠባይና ኑሮ ሳትመረምሩ የሌላውን ሰው ጠባይና ኑሮ ብትመረምሩበት ግን ሰነፎች ትባላላችሁ።

ዳግመኛም ነቢዩ ኤርምያስ እርሳቸው የሰነፉ ልጆች ናቸው፤ ያላስተዋሉም። ክፉ ለማድረግ ብልሀተኞች ናቸው፤ መልካም ለማድረግ ግን አያውቁም ብሏልና። ኤር. ፬፥ ፳፪።

ይህንም መጽሐፍ ስትመለከቱ ነገሩን በማስተዋልና በመመርመር ይሁን እንጂ፤ በመቸኰል አይሁን።

እንደዚህ ያደረጋችሁ እንደ ሆነ ከዚህ የበለጠ ጥበብ ታገኛላችሁ። ሰሎሞን ለብልሀተኛ ከጥበብ'ኸ ስጠው። ጥበብንም ያበዛል። ለጻድቅም አስተምረው እውቀቱ ይበዛል። የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ይላልና። ምሳ. ፱፥ ፱ - ፲።

እንደዚህም ማለቴ እውቀትን ለሚፈልጉ ሰዎች ነው እንጂ ለዋዘኞችና ለሰነፎች ግን ይህን ምክር መስጠት እንዳይገባ የታወቀ ነው።

ዳግመኛ ሰሎሞን ዋዘኛን የሚገሥፅ ለራሱ ስድብን ይቀበላል። ሕግ ተላላፊውንም የሚዘልፍ ነውርን ይወስዳል። ዋዘኛን አትገሥፅ፤ እንዳይጠላህ። ብልሃተኛን ብትገሥፅ ግን ይወድኻል፤ ይላልና። ምሳ. ፱፥ ፯ - ፰።

*0*

ነገር ግን የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት እንደ ሆነ የጥበብም መጨረሻ ፍቅር ነውና እርስ በርሳችን እንፋቀር።

ቅዱስ ጳውሎስም እንዲህ ብሏል። በመላእክትና በሰዎች ቋንቋ ብናገር ፍቅርም ባትኖረኝ እንደሚጮህ ናስ ወይም እንደሚጮህ ጸናጽል ሆንሁ። ትንቢትም ብናገር

ምስጢርንም እውቀትንም ሁሉ ባውቅ ተራራም እስካፈልስ ሃይማኖት ቢኖረኝ ፍቅር ከሌለኝ አንዳች አይደለሁም።

ገንዘቤንም ሁሉ ለድኆች ብመጸውት ሥጋዬንም ለመቃጠል ብሰጥ ፍቅር ከሌለኝ ምንም አይረባኝም። ብሏል። ፩. ቆሮ. ፲፫፥ ፩ -፬።

ስለዚህ መጣላትን ከኛ እናርቅ። ደግሞ ጉልበት ካገኘን ከሰይጣንና ከኃጢአት ጋራ እንጣላ እንጂ፤ ከወንድሞቻችን ጋራ ብንጣላ እኛንም ሰማያዊ አባታችን ይጣላናል። ማቴ. ፯፥ ፲፬ -፲፫።

ለዚህም ሁሉ የጥበብና የፍቅር አምላክ ይርዳን፤ አሜን።

### መሪ

አንባቢ ሆይ፤ በዚህ መጽሐፍ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ወደ ምሥራቅ ሔድሁ፤ ወደ ምዕራብ ተመለስሁ፤ ወደ ሰሜን ሔድሁ፤ ወደ ደቡብ ተመለስሁ እያለ ተጽፎ ይገኛል። ምሥራቅ ሲል መጻሕፍተ ሐዲሳት ማለቱ ነው። ምዕራብ ሲል መጻሕፍተ ብሉያት ማለቱ ነው። ሰሜን ሲል የሊቃውንት መጻሕፍት ማለቱ ነው። ደቡብ ሲል አዋልድ መጻሕፍት ማለቱ ነው። ዓለም ያለ እንደ ሆነ ግን መጻሕፍትን ሁሉ ማለቱ ነው። ይህንም ካስታወቅሁ በኋላ ምሥራቅ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ደቡብ የሚለው ሀገር እንዳይመስላችሁ። እግዚአብሔር ልጁን የክርስቶስን ብርሃን በልባችሁ ውስጥ ያብራላችሁ። አሜን። ጴጥ. ፩፥ ፲፱።

# ክፍል ፩ ወዳጄ ልቤ

## የሰውን ጠባይና ኑሮ በምሳሌ የሚገልጽ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

## ምዕራፍ ፩

## ስለ መጀመሪያ ዛፍ

በተወለድሁ በ፲፰ ዓመት ከዘመዶቼ ተለይቼ ወዳጄ ልቤን ብቻ አስከትዬ ከቤቴ ተነሣሁ።

አሳቤም ይህን ዓለም (መጻሕፍትን) በምሥራቅና በምዕራብ፤ በሰሜንና በደቡብ እየዞርሁ ለማየት ነበረ።

በምሥራቅ ስዞር መሪ ነበረኝ፤ በምዕራብ እኩሌታውን ያህል በመሪ ዞርሁ። በሰሜንና በደቡብ ግን ብቻዬን ነበርሁ። ያ ወዳጄ ልቤ ብቻ ስንቄን ተሸክሞ ተከትሎኝ ነበረ። እርሱ ስንኳ አንዳንድ ጊዜ እየተወኝ ይሔድ ነበረ።

ምርምር ወደ ሚባለው ሀገር ለመድረስ ጥቂት ሲቀረኝ አንድ ዛፍ አገኘሁ። የዛፉም ጥላ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነበረ። በጥላውም ውስጥ ብዙ ፍጥረታት የሰው ወገን፣ የእንስሳም ወገን፣ የአራዊትም፣ የአዕዋፍም ወገን ተሰብስበው አርፈዋል። እኔም በጥላው ጥቂት አረፍሁ። መዝ. ፻፶፫፥ ፲፫ - ፳፩።

ከዚያም ስነሣ ያ የመንገድ መሪ የሆነኝ ወደ እኔ ቀርቦ የዚህን የዛፉን ስም ታውቀዋለህን አለኝ።

ጌታዬ ሆይ፤ እንደዚህ ያለ ዛፍ አይቼ አላውቅምና የዚህን ስሙን አላውቅም አልሁት።

እንኪያስ እኔ ልንገርህ። ይህ ዛፍ እግዚአብሔር ይባላል፤ ነገር ግን የበቀለበትን ጊዜ የሚያውቅ ሰው የለም። ባባቶቻችንም ዘመን እንደዚሁ ነበረ አለኝ። መዝ. ፺፪፥ ፳፫፣ ፳፮ ፻፪፤ ዮሐ. ፩፥ ፬፣ ፯፣ ፶፯፣ ፩ዮሐ. ፩፥ ፩።

እኔም እጅግ ተደነቅሁ፤ ያስደነቀኝም የስሙ ነገር ነው። የተለመዱትና በጣም የታወቁት ዛፎች ስማቸው ጠንቋይ፤ አስማተኛ፣ ሟርተኛ፣ ዛር፣ ሐሰተኛ፣ ናዝራዊ ሐሰተኛ ባሕታዊ፣ ጋኔን ጐታች፣ ሞራ ገላጭ ነው።

ከነዚህም ዛፎች ለጊዜው የሚያምረውና የሚያስጐመጀው ጠንቋይ ነው። ነገር ግን ፍሬው እጅግ መራራ ነው። ከርሱም ፍሬ የቀመሰ የዘላለም ሕይወት አያገኝም።

ከዛፉም ሥር ተነሥቼ ብዙ መንገድ ከሔድሁ በኋላ በስተምሥራቅ ቆሜ ዘወር ብዬ ብመለከት፤ ያ ያየሁት ዛፍ ሦስት መስሎ ታየኝ። ማቴ. ፳፯፥ ፲፪። ቶሎ ብዬም ወደ ምዕራብ ዞርሁ። በዚያም ቆሜ ብመለከት ፍጹም አንድ መስሎ ይታያል። መነጽሬን አውጥቼ ብመለከት ግን ጥቂት ጥቂት ሦስት መስሎ ይታያል። ዘፍጥረት ፩፥ ፳፮።

ከዚያም ወደ ሰሜንና ወደ ደቡብ ዞርሁ። በዚያ ቆሜ ብመለከት ግን አንድ ጊዜ ሦስት አንድ ጊዜ አንድ እየሆነ ታየኝ። በዚህም እጅግ ተደነቅሁ።

ከዚያም ካለፍሁ በኋላ ዮሐንስ ታዓቃቢ የሚባል ሰው አገኘሁ የዛፉንም ነገር ያወቀው እንደ ሆነ ብዬ ጠየቅሁት። በጥላው አርፈህ ስትነሣ ምድርና ሰማይ ቢዞርብህ ነው እንጂ ዛፉስ ዘጠኝ ነው፤ አለኝ እኔ ግን ስቄበት መንገዴን ሔድሁ።

ጥቂትም መንገድ ከሔድሁ በኋላ፤ ሰባልዮስንና መሐመድን አገኘኋቸው። የዛፉንም ነገር ያወቁት እንደ ሆነ ብዬ ጠየቅኋቸው።

ዓይንህን አሞህ እንደ ሆነ ብዥ ብዥ እያለብህ ነው እንጂ፤ ዛፉስ አንድ ነው። በዚህ ነገር ምንም ጥርጣሬ አይግባህ አሉኝ። እኔ ስቄባቸው መንገዴን ሔድሁ።

ከዚህም በኋላ ከሰሜን ሀገር የመጡ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ቄርሎስ አትናቴዎስ ጐርጐርዮስ የሚባሉ ሰዎች አገኘሁ። ስለ ዛፉም ጠየቅኋቸው። እነርሱም ቶሎ ብለው ማስረዳት ወደምትባል እልፍኛቸው ነገር መርምሮ ገብተው ብዙ ጨዋታ ተጫወትን። በመጨረሻውም የዚህን የዛፍ ነገር መርምሮ ያወቀ የለም። አንተም መርምሬ አውቃለሁ ብለህ አትድከም። እኛም የዚህን የዛፍ ነገር እንመረምራለን ብለን ብዙ ደክመን ነበርን። ግን እንዲሁ አንተ እንዳየኸው አየን እንጂ ሌላ ነገር ምንም አላየንም አሉኝ። ጌቶች ሆይ፤ ይህን ስለ መከራችሁኝ ዋጋችሁ በሰማይ ይሁን። አሁንም ወደ ምሥራቅ ሀገር እሔዳለሁና መንገዱን አመልክቱኝ። በዘወርዋራ መንገድ እንዳልሔድ አልኋቸው።

ከፉ ምርምር የምትባለውን ከተማ ወደ ግራ እየተውህ፤ ቀኝ ቀኙን ሒድ አሉኝ።

ከዚህም በኋላ መንገዴን ሔድሁ። ያ ወዳጄ ልቤ ግን በግዕዝ ቋንቋ ተነከረ አእምሮትከ በላዕሌየ ጸንዐተኒ ወኢይክል ምስሌሃ እያለ፤ የዳዊት መዝሙር ይዘምር ነበር። መዝ. ፻፴፱፥ ፮።

# ምዕራፍ ፪

# ስለ ሁለተኛው ዛፍ

ከዚህም በኋላ ወደ ምሥራቅ ሀገር ዞርሁ። በዚህም ሀገር፤ ማቴዎስ ማርቆስ፣ ሉቃስ፤ ዮሐንስ፣ የሚባሉ ሰዎች ጌቶች ሆነው ይኖራሉ። ወደ እነርሱም ደጅ የማይደርስ ሰው የለም።

እኔም ወደ እነርሱ ስሔድ በመንገድ ዳር አንድ ዛፍ አገኘሁ። ይህም ዛፍ በቁመትም፣ በመልክም በፍሬም ያንን በመጀመሪያ ያየሁትን ዛፍ ይመስላል። ዮሐ. ፲፭፥ ፱።

በጥላውም ውስጥ ጥቂት አረፍሁ።

ከዚህም በኋላ ለመሔድ ተነሣሁ። ጥቂትም እንደ ሔድሁ፤ ዘወር ብዬ ብመለከት ያ ዛፍ ፍጹም ሰው መስሎ ታየኝ። ዕብ. ፪፥ ፱፣ ፲፬።

እስኪ ባላገሮችን ልጠይቃችሁ፤ ከቶ ይህ ዛፍ እንደ ምን ይሆን ብዬ ወደ መንደር መሮጥ ጀመርሁ። ወደ መንደርም ሳልደርስ ዳግመኛ ዘወር ብዬ ብመለከተው ፍጹም ዛፍ መስሎ ታየኝ። ዮሐ. ፲፥ ፴።

ከዚህ በኋላ ግን ያየኝ ሰው ይስቅብኛል ብዬ መንገዴን ሔድሁ። ያ የመንገድ መሪ የሆነኝ ሰው ከኔ ቀድሞ ሔዶ ነበርና ቶሎ ብዬ ደረስሁበት። የዛፉንም ስም ያወቀው እንደ ሆነ ብዬ ጠየቅሁት። እርሱም የዛፉ ስም ብዙ ነው። አማኑኤል ክርስቶስ ኢየሱስ ይባላል አለኝ። ማቴ. ፩፥ ፳፫።

እኔም እጅግ አደነቅሁ። ማድነቄም ምግብነቱ ከሀገሬ ምግብ ልዩ ስለሆነ ነው። ዮሐ. ፮፥ ፶፫።

የሀገሬ ምግብ እንጀራና የከብት ሥጋ ነው። ያውም ማታ በልተውለት ለጧት አይገኝም። እንዲህም እየተደነቅሁ ስሔድ ሐራ ጥቃ የሚባሉ ሰዎች አገኘሁ። ስለ ዛፉም ጠየቅኋቸው። እነሱም ጥንት በውነት ዛፍ ነበረ። አሁን ግን ዛፍነቱ ቀርቶ ሰው ሆነዋል አሉኝ። እኔ ግን ስቄባቸው ሔድሁ። ጥቂትም ከሔድሁ በኋላ አወጣኪን አገኘሁት ስለ ዛፉም ጠየቅሁት። እርሱ ግን ወደኔ ዘወር ብሎ ጤና የለህምን፤ ሰው መምሰሉ በቀረ በስንት ዓመቱ። ዛሬማ ፍጹም ዛፍ ሆኖ የለምን አለኝ። እኔም ስቄበት መንገዴን ሔድሁ።

ከዚህ በኋላ ሳላስበው በድንገት ወደ ሰሜን ዞርሁ። በሰሜን ያሉ ሰዎች የዛፉን ነገር ጠንቅቀን እናውቃለን ይላሉ። እኔም ወደ እነርሱ ሔጄ ጠየቅኋቸው። ነገር ግን አንድ ነው፤ ሁለት ነው በማለት ክርክር ይዘው ነበሩና እኔም ከቁም ነገር ስላልቆጠሩኝ የእነርሱ ክርክር መጨረሻ ሳይኖረው ጊዜ በዚህ ቆሜ ልቀር ነውን፤ ብዬ ወደ ምሥራቅ ዞርሁ በምሥራቅም ያሉ ሰዎች አንድ መሆኑን ዘወትርም ዛፍና ሰው መስሎ መታየቱን አስረዱኝና እጅግ ደስ አለኝ። ማቴ. ፫፥ ፲፯፣ ፩ቆሮ. ፰፥ ፮ ዮሐ. ፱፥ ፴፮ -፫-፰።

## ምዕራፍ ፫

# ስለ ሦስተኛው ዛፍ

በዚሁ በምሥራቅ ሀገር ከወዲያ ወዲህ ስመላለስ በነፋሻ ስፍራ የበቀለ አንድ ዛፍ አገኘሁ።

ይህም ዛፍ በልምላሜ በቅጠልም በርዝመትም አስቀድሞ ያየኋቸውን ሁለቱን ዛፎች ይመስላል። የበቀለበት ስፍራ ተራራማ ሆነ ነፋስ ይወዘውዘው ነበረ።

የዚህንም ነገር እየመረመርሁ ስሔድ መቅዶንዮስ አገኘሁት። የዛፉንም ነገር ያውቀው እንደ ሆነ ብዬ ጠየቅሁት። እርሱም እንዲህ የሚያስደንቅ የዚህ የዛፍ ነገር ነውን፤ ከዚህ የሚበልጡትን ሁልትቱን ዛፎች አይተህ በሆነ ምንኛ ባደንቅህ ኖሯል።

ይህ ዛፍ በሁለቱ ዛፎች ዘንድ የቁጥቋጦ ያህል ነው አለኝ። እኔ ግን ስቄበት ሔድሁ። ጥቂትም እንዳለፍሁ ዘወር ብዬ ብመለከት ያ ያየሁት ዛፍ እንደ ርግብ ክንፍ አውጥቶ ሲበር አየሁት። ከዚህም በኋላ እያደነቅሁ መንገዴን ሔድሁ። ያ ወዳጄ ልቤም ካማርኛ ይልቅ የግዕዝ ቋንቋ ያውቅ ነበርና ወመንፈስከ ቅዱስ ኢታውፅእ እምላዕሌየ። ወበመንፈስ አዚዝ አጽንዓኒ። አይቴኑ አሐውር እመንፈስከ እያለ የዳዊት መዝሙር ይዘምር ጀመረ። መዝ. ፶፩፥ ፲፩፤ ፻፴፱፤ ፯።

## ምዕራፍ ፬

# ስለ ትዕቢትና ስለ ትሕትና መጣላት

ከዚህ በኋላ ድንቁርና ወደ ምትባል ሀገር ደረስሁ። በዚያችም ሀገር ትዕቢት የሚባል ሌባ ጌታ ሆኖ ይኖር ነበር። ሌብነቱን ግን የሚያውቅበት አልነበረም። ደግሞ ትሕትና የሚባል ሰው የጨዋ ልጅ፤ ጊዜ ያዋረደው በዚያችው ሀገር ራሱን ቀብሮ ይኖር ነበር። እኔም ለሁለቱም ወዳጅ ሆኜ በሁለቱም ቤት ስበላ ስጠጣ ብዙ ቀን ተቀመጥሁ። ዳሩ ግን ትዕቢት ሌባ መሆኑን አላወቅሁም ነበር። ትዕቢትም በትሕትና ላይ ክፉ ክፉ ወሬ እያወራ ይነግረኝ ነበረ። ትሕትናም በሰማ ጊዜ ነገሩን እንዳልሰማ እየሆነ ዝም ይል ነበረ።

አንድ ቀን ትሕጥና ወደ ቤቱ ጠርቶኝ ትንሽ ጨዋታ ስንጫወት ትዕቢት እግረ መንገዱን ሲያልፍ አየኝና ተቆጥቶ ጨርቁን ባፍንጫው ላይ አድርጐ አለፈ። ጥቂትም እንደ ሔደ፤ ከሐሜት ጋራ በመንገድ ተገናኙ። ሐሜት ቶሎ ብሎ ጌታው አቶ ትዕቢት ከወዴት ይመጣሉ አለው።

ከወደ ሰይጣን ልብ አለው።

ምነው አዝነዋል አለው።

ኃዘን ይበዛብኝን? ሰው ሁሉ ወረተኛ ነው። ይህን ባጠገባችን የቆመውን ሰው ይህን ዓለም (መጻሕፍትን) ሲዞር አግኝቼው ወደ ቤቴ ወሰድሁት።

ደግሞ ሱሪህን እስከ ተረከዝህ አድርግ፤ ዓይንህን ተኳል፤ ጨርቅህን አፍንጫህ ላይ አድርግ፤ ሰላምታ ሲሰጡህ ዝም በላቸው ብዬ የሀገሩን ሥርዓት አስተማርሁት። አሁን ግን ሁሉንም ትቶት ከትሕትና ጋራ ሲጫወት አየሁት። ትሕትና ስንኳን እንግዳ የሚቀበልበት ራሱን የሚረዳበት ገንዘብ አያገኝም አለ።

ትዕቢትም ከሐሜት አፍ ይህን በሰማ ጊዜ ደስ አለውና ትሕትና የሚያውቀው እንግዳ መጥቶብኛልና እንጀራ አበድሩኝ ማለት ነው እንጂ፤ ባለ ገንዘብማ ከሆነ ልጆቹ ነቢያት፣ ሐዋርያት ጻድቃንና ሰማዕታት የሚበሉትና የሚጠጡት አጥተው በረኃብ ለምን ይተላለቁ ነበር አለ። ማቴ. ፩፥ ፯።

ትዕቢት ይህን ሁሉ ነገር ሲናገር ትሕትና ጆሮውን ጣል አድርጎ ይሰማ ነበርና በነገሩ ስለ ተናደደ በትሩን ይዞ ወደ ትዕቢት ቀርቦ አንተ ሌባ ነው ብችልህ እምቢ አልህ።

የዚያ የሐሰተኛ የዲያብሎስ ልጅ መሆንህን ረሳኸውን? ዳሩ ግን ምን ታደርግ ስደት ለወሬ ይመቻል። የኔ አባት ክርስቶስ ካገርህ (ከሰው ልብ) አስወጥቶ ቢሰድህ ወደዚች ድንቁርና ወደ ምትባል ሀገር መጥተህ ጌታ ሆነሃል። እውቀት የሚባል ከሳሽ አስነሥቼ ከዚህ ሀገር ሳላጠፋህ የቀረሁ እንደ ሆነ እያለ በዛቻ ወደ ቤቱ ተመለሰ። ትዕቢትም ለካ ሌብነቴ ታውቆብኛል ብሎ ዝም አለ።

ኋላ ግን ዘመዶቹ ተሰብስበው አሁንማ እንዴህ ዝም ብለህ ከቀረህ ማንም እየተነሣ ሌባ እያለ ሊሰድብህ አይደለምን በዳኛ ክሰስና ያዘው ሌብነትህን በማን ይረታሃል አሉት። ከዚህም በኋላ ትዕቢት ወደ ወዳጄ ልቤ መጥቶ ዳኛ አድርጌሃለሁና ትሕትናን አስመጣልኝ አለው ትሕትናም አሳቡን ጥሎ ተቀምጦ ሳለ ተከሰሃልና ቶሎ ድረስ የሚል ቃል መጣበት።

ከዚህ በኋላ ትዕቢትና ትሕትና ተቋቋሙ።

እኔም አስታርቃለሁ ብዬ ብዙ ደከምሁ፤ ነገር ግን ትዕቢት ዕርቅ እምቢ አለ። ትዕቢትም ዕርቅ

እምቢ ያለበት ምክንያት ለዳኛው ብዙ ገንዘብ እሰጥሃለሁ ብሎ ተስፋ ሰጥቶት ነበርና መቸም አይረታኝም ብሎ ነበር። በንግግሩም ይታወቃል።

ትሕትናም ሌባ መሆንህን ልርታህ አለው። ዳኛው ግን ለትዕቢት አድልቶ ነበርና ትዕቢት ሌባ አለመሆኑን ይርታ አለ። እንዲህ ማለቱ ለትዕቢት ብዙ ወዳጆች ነበሩትና ምናልባት እነዚያ ምስክር ተቆጥረው ትዕቢት ይረታል ብሎ ተስፋ አድርጎ ነው። ትሕትናም ነገሩ እንዳልሆነለት ባየ ጊዜ ተጠበቃዬ አለ። በስምንተኛውም ቀን ጳውሎስ የሚባል ነገር አዋቂ አግኝቶ ይዞ መጣ። ዳኛውንም ያንን ባየ ጊዜ እጅግ ፈራ። ስለዚህም ቀኙ ለትሕትና ይሁን ተባለ። ፈራጆቹም ትዕቢት ሌባ መሆኑን ትሕትና ይርታ እያሉ ፈረዱ። ጳውሎስም ትዕቢትን ሌባ አለው። አይደለሁም አለ። የዘላለም ኵነኔ እሰጥ አለው። አገባ አለ።

ከዚህም በኋላ ምስክሮች ተቈጠሩ። ምስክሮቹም ጴጥሮስ ማቴዎስና ያዕቆብ ነበሩ። ጳውሎስም እጁን ዘርግቶ ጴጥሮስ ሆይ፤ ትዕቢት ሌባ እንደ ሆነ እወቅልኝ አለው። ትዕቢትም በኔም አታውቅብኝ እኔ ሌባ አይደለሁም አለ። ጴጥሮስ ተነሣ፤ አለም። እንዲሁ እናንት ጐበዛዝት ለሽማግሎች ተገዙ፤ ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ ተገዙ፤ ትሕትናንም ልበሱ እግዚአብሔር ልባቸውን የሚያስታብዩትን ይጣላልና። ለትሑታን ግን ጸጋውን ይሰጣል፤ እንግዲህ ከጸናችው ከእግዚአብሔር እጅ በታች ዝቅ በሉ፤ በጊዜው ከፍ ከፍ ያደርጋችሁ ዘንድ አለ። ፩ጴጥ. ፭፥ ፭ -፯።

ጳውሎስ ነገረልኝ አለ። ትዕቢትም አዎን ነገረልህ አለ።

ዳግመኛ ማቴዎስ ሆይ፤ ትዕቢት ሌባ እንደ ሆነ እወቅልኝ አለ።

ትዕቢትም እኔ ሌባ አይደለሁም በኔም አታውቅብኝ አለ። ማቴዎስ ተነሣ ከናንተ የሚበልጥ ሎሌ ይሁናችሁ። ነፍሱን ከፍ ከፍ ያደረገ ዝቅ ይላልና። ነፍሱንም ዝቅ ዝቅ ያደረገ ከፍ ይላልና አለ። ማቴ. ፳፫፥ ፲፩ -፲፪።

ነገረልኝ አለው። ትዕቢትም አዎን ነገረልህ አለው።

ያዕቆብ ሆይ፤ ትዕቢት ሌባ እንደ ሆነ እወቅልኝ አለው።

ትዕቢትም በኔም አታውቅብኝ ሌባ አይደለሁም አለ።

ያዕቆብ ተነሣ እግዚአብሔር ልባቸውን የሚያስታብዩን ሰዎች ይቀጣል። ለትሑታን ግን ጸጋ ይሰጣል አለ። ያዕ. ፬፥ ፮።

ጳውሎስም ነገረልኝ አለ። አዎን ነገረልህ አለ። አንሣ አለው። አያስነሣኝም እነዚህ አሁን የመሰከሩት ሁሉም አብሮ አደጎችህ ናቸው አለ።

ዳኛውም እጁን ዘርግቶ ይህን ማለት በፊት ነበረ እንጂ፤ አሁንማ አንተው ወደህ ተቀብለሃቸው ነገር ካለቀ በኋላ እንዲህ ብትል መቼ ይሆናል፤ ይልቅስ አንሣ አለው።

ጳውሎስ ግን ተናደደና አሁን እንዲህ ማለትህ ሌሎች ምስክሮች አያገኝም ብለህ ይሆናል። እኔ መልካቸውን እንኳ ካላየኋቸው ከሽማግሎች ወገን ልቁጠርህ አለው።

ትዕቢትም ከዚያ ወዲያስ ብሞትም አይቈጨኝም አለ። ከዚህ በኋላ ሰሎሞንን ሕዝቅኤልን ቈጠረለት። ከፊተኞች ጋራ አምስት ምስክሮች መሆናቸው ነው። ጳውሎስም በቊጣ ቃል ሰሎሞን ሆይ፤ ትዕቢት ሌባ እንደ ሆነ እወቅልኝ አለ። ትዕቢትም በኔም አታውቅብኝ ሌባ አይደለሁም አለ።

ሰሎሞን ተነሣ። ሰውን ትዕቢቱ ያዋርደዋል፤ ነፍሱን የሚያዋርድ ግን ክብር ይቀበላል አለ። ምዕ. ፳፱፥ ፳፫።

ነገረልኝ አለው። አዎን ነገረልህ አለ። ሕዝቅኤል ሆይ፤ ትዕቢት ሌባ እንደ ሆነ እወቅልኝ አለው። በኔም አታውቅብኝ ሌባ አይደለሁም።

ሕዝቅኤል ተነሣ። የተዋረደ ይከብራል። የከበረውም ይዋረዳል አለ። ሕዝ. ፳፩፥ ፳፮።

ጳውሎስም አንሣ አለው። አነሣሁ አለ። ከዚህ በኋላ ትዕቢት ሌባ መሆኑ ትሕትናም ደኅና ሰው መሆኑ በሁሉ ዘንድ ታወቀ።

ትሕትናም ለዚህ ጳውሎስ ለሚባለው ተሟጋቹ በሮሜ የተሠራ ጥሩ ባ፥ሕረ ወጥ ሰይፍ አንሥቶ ሰጠው። ጳውሎስ ግን ሰይፉን ለአክሊል ለወጠው።

# ምዕራፍ ፭

# ስለ ንፍገት ተራራ

ከብዙ ዘመንም በኋላ ታምሜ ተኛሁ፤ በሽታዬም እጅግ ጽኑ ነበረ። ነፍሴን እየወጋኝ ከማኽል ራሴ ከክርስቶስ የሚለየኝ ነበር ጥቂትም በኀነት ባገኘሁ ጊዜ እያዘገምሁ መንገዴን ጀመርሁ።

በመንገዴም በስተ ግራ ረጅም ተራራ ነበረ። ስሙም ንፍገት ይባላል። አንዳንድ ሰዎችም ፍቅረ ንዋይ ይሉታል። እኔም በዚያ ላይ ወጥቼ ይህን ዓለም ለማየት አሰብሁ። ያ ወዳጄ ልቤ ግን ገመምተኛ ነህና አትችልም ብሎ ከለከለኝ። ይህንንም ስንነጋገር ጋዝ ከወደ ተራራው በተራራው ጫፍ ተሠርቶልኛል። አንተም ትንሽ ዛኒጋባ መሳይ አሠርተህ በዚያ ብትኖር ይሻልህ ነበረ አለኝ። ፩. ነገ. ፩፥ ፳ ፳፺።

እኔ ግን አሳቤ ይህን ዓለም (መጻሕፍትን) ለመዞርና ለማየት ነውና ሁሉንም ነገር ከወዳጄ ልቤ ጋራ ተማክሬ እነግርሀለሁ አልሁት። ለኔ ይመቸኝ ይሆንን፤ ብዬ ጠየቅሁት። ወዳጄ ልቤም ኸረ ወዲያ ምን ያደርግልኝ ብለህ ነው። እኔ አውቀው የለምን አለኝ። ኧኸ እንደ ምን ነው አልሁት።

የንፍገት ተራራ አሁን አንተ እንደምታየው እጅግ ረጅሙ ነው። ወጥቶ በጫፉ ላይ የቆሙ እንደ ሆነ በምድር ያለው ሁሉ ሰውም፤ ከብቱም፤ ወርቁም፤ ብሩም፤ እህሉም ጥቂት መስሎ ይታያል። ዳግመኛ የሚበቃ አይመስልም። ይልቁንም በንፍገት ተራራ የቆመ ሰው አባቱንና እናቱን፣ ወንድሙንና እኅቱን ዘመዱንና ወዳጁንም ለይቶ ማወቅ አይችልም አለኝ።

ይህን ሁሉ ሲነግረኝ ወጥቼ አያለሁ በማለት ልቡናዬ ተስፋ አልቆረጠም ነበር። ነገር ግን ባንድ ስፍራ ቆሜ ሳመነታ ጊዜው መሸ። ከኔም ጋራ ሰይፍም፤ ጋሻም፤ ጦርም አልነበረም። ያ የሚሰብረውን እሸቶ የሚዞረው አውሬ ቢመጣ ያፉ ጉርሻ ነኝ እንጂ የማመልጥበት ስፍራ አልነበረኝም። ፩ጴጥ. ፩፥ ፰።

እንዲሁም ስጨነቅ ከንፍገት ተራራ በስተቀኝ አንድ ቤት አየሁና ቶሎ ብዬ ወደዚያ ሔድሁ። አንድ ባላቴናም በደጅ ቆሞ አገኘሁ። ወዳጄ ሆይ፤ ስምህ ማነው አልሁት። አብሮ መብላት እባላለሁ አለኝ። ይህ ቤት የማነው አልሁት። የብላታ ቸርነት ነው አለኝ። እባክህ ንገርልኝ አልሁት። እርሱም ቅን ብላቴና ኑሮ ቶሎ ገብቶ ነገረልኝ። ብላታ ቸርነትም በሰሙ ጊዜ እጃቸውን ዘርግተው ሲበሩ መጡና ይዘውኝ ገቡ። ከገባንም በኋላ የሚያስፈልገኝን ነገር ሁሉ አቀረቡልኝ። የመኝታም ጊዜ ሲደርስ ወደ መኝታ ቤት ይዘውኝ ሔዱ። በዚያም መልካም ምቹ አልጋ አሳዩኝ። እኔም እጅግ ደክሞ ነበርና ቶሎ ተኛሁ። ወዳጄ ልቤ ግን እጅግም እንቅልፍ አልነበረበትምና ባጠገቤ ተኝቶ ያጫውተኝ ነበረ። በነጋም ጊዜ ለመንገዴ ስለ ቸኰልሁ ቶሎ ታጠቅሁ። ብላታ ቸርነትም ለመንገዴ የሚበቃ ስንቅ ስጡኝ። ዳግመኛም ወደ ንፍገት ተራራ መውጣት እንዳላስብ መከሩኝ። ምክንያቱም ብጠይቃቸው ከተራራው መርዘም የተነሣ ራስ እያዞረ ይጥላል አሉኝ።

እኔም ብላታ ቸርነት በሠሩልኝ ሥራ ሁሉ እጅ ደስ ስላለኝ ወደ ሀገሬ ስመለስ መጥቼ እሰናበትዎታለሁ ብያቸው መንዴን ሔድሁ።

## ምዕራፍ ፮

# ስለ ምእመን ሠርግ

ከዚህም በኋላ ምሥራቅ ምሥራቁን ለመዞር ተነሣሁ። በምሥራቅም ያላየሁት ሀገር አልነበረም። መንገዱ ግን እጅግ አስቸጋሪ ነበረ። ማቴ. ፯፥ ፲፫።

መሪ ባልነበረኝ ባንዱ ፈርፈር ውስጥ ወድቄ እቀር ነበረ እንጂ ወደ አሰብሁበት ስፍራ ባልደረስሁም ነበረ፤ ነገር ግን ከወጣሁ ቀኑ ብዙ ነበረና ስንቅ አለቀብኝ። ወዳጄ ልቤም ችግሬን አይቶ የሕይወት እንጀራ የሚሸጥበት ገበያ ሞልቶ የለምን፤ ሔድን እንግዛ አለኝ። ዮሐ. ፯፥ ፶።

ነገሩስ መልካም ነበረ። ነገር ግን የያዝነው ገንዘብ ጥቂት ነውና በዚህ ያህል ዋጋ የሕይወት እንጀራ አንሸጥም ብለው ቢመልሱን እንዲኤት እንሆናለን። እንዲህ በረኃብ ተጨንቀን ሳለን የመንገዱን ድካም እስኪ ተመልከተው አልሁት።

እንዲሁ ባንድ ሥፍራ ቆመን ይህን ስንነጋገር ወደ ሰሜን ብመለከት በምሥራቅና በሰሜን አዋሳኝ ብዙ ሰዎች ነጫጭ ልብስ ለብሰው በትልቁ አዳራሽ ደጅ ከወዲያ ወዲህ ሲመላለሱ አየሁ። እኔም ፈጥኜ ወደ እርሳቸው ሔድሁ። በደረስሁም ጊዜ ይህ አዳራሽ የማነው ብዬ ጠየቅኋቸው። የታላቁ ንጉሥ ቤት ነው። ነገር ግን አሁን በውስጡ ያለው ሰው ባለ ኪራይ ነው አሉኝ።

ሁላችሁ ነጫጭ ልብስ ለብሳችሁ ከወዲያ ከወዲህ የምትመላለሱት ስለ ምን ነው፤ ዛሬ ያመት በዓል ነውን አልኋቸው።

እንኳን እንኳን ይህን ቤት የተከራየው ሰው ልጁን ምእመንን ከወንጌል ጋራ ሊያጋባው ነው።

ስለዚኢህ አሁን ወደ ሠርጉ ለመሔድ ቸኩለናል። ነገር ግን ሠርገኞች እጅግ ጥቂቶች ሆነን ተቸግረናልና የሠርግ ልብስ እንዳለህ ከኛ ጋራ እንሒድ አሉኝ። እባካችሁ ጥቂት ቆዩኝና በከረጢቴ ትቂት ገንዘብ ባገኝ ወደ ገበያ ሔጄ፤ የሠርግ ልብስ ልግዛ አልኋቸው።

አይሆንም በጊዜ ግቡ ተብለናል። ጊዜው የመሸ እንደሆነ በሩ ይዘጋብናል። በሩም ከተዘጋ በኋላ፤ ከፈልቱልን ብንል የሚከፍትልን አናገኝም አሉኝ። ማቴ. ፳፭፥ ፲፩ -፲፪።

እኔም ጥንቱን ባልነገራችሁኝ እንኳ መልካም ነበረ። አሁን እንደምን ልሁን እያልሁ አለቅስባቸው ጀመር። እነርሱም አይዞህ አታልቅስ ንስሐ የሚባለውን ወንዝ ተሻግረው እንሔዳለንና ልብስህን በዚያ ታጥባለህ። እኛም አንድ ሰዓት ያህል እንቆይሃለን አሉኝ። እኔም እጅግ ደስ አለኝ። የደስታዬም ምክንያት ተርቤ ነበርና ከዚያ ከሠርጉ እንጀራ ለመብላት አስቢኤ ነው። ማቴ. ፬፥ ፲፯።

ከዚህም በኋላ በኋላ ንስሐ ወደሚባለው ወንዝ ደረስን። ቶሎ ብዬም ልብሴን አውልቄ ማጠብ ጀመርሁ። ነገር ግን የዘወትር ልብሴ ነበረና እድፉ ፈጽሞ የማይለቅ ሆነ። ኢዮብ. ፳፭፥ ፬፥ ፮።

ሠርገኞችም ትተውኝ የሚሔዱ ሆነ። እኔም ቶሎ ብዬ ለቅልቄ ሳይደርቅ እርጥቡን ለብሼ ተከተልኋቸው። ወደ ሠርጉም ቤት በደረስን ጊዜ ወደ ውስጥ አስገቡን ቢኤቱም እጅግ አጊጦ ነበረ፤ በውጭም በግቢም ፀሐይ የሚመስል መብራት ይበራ ነበር።

እድመኞቹም ከጥሩ ወርቅ የተሠራ ልብስ ለብሰዋል። የሙሽራዪቱ የወንጌል አባት ክርስቶም በመካከላቸው ተቀምጧል። እንደ ነፋስ የሚፈጥኑ አሽከሮች መላእክትም የሠርገኞቹን መሣሪያ እየተቀባበሉ ያገለግሉ ነበሩ።

ሠርገኞቹም መጡ በተባለ ጊዜ በውጭም በግቢም ፍጹም እልልታ ሆነ። እምቢልታም መለከትም ይነፉ ጀመረ። ይኸም ሁሉ ሲሆን እኔ እየተከናነብሁ አለቅስ ነበር። ያ ወዳጄ ልቤም ወደኔ ቀርቦ ስለምን ታለቅሳለህ አለ። እንዲህ በሥራት ሚስት ሳላገባ ዘመኔ ስላለፈብኝ ነው አልሁት።

ለሠርግም እንጂ መጠራት እጅግ መታደል ነው ወደ ሠርጉ የተጠሩ ያለመጡ ስንት ይመስሉሃል አለኝ። ማቴ. ፳፪፥ ፩፣ ፲፬።

ከኛ ወገን የነገር አባት ቶማስ ነበረ።

አንድ ሰዓትም የሚያህል ዝም ብለው አቶሙን።

ከዚህም በኋላ ምነው ቆማችኋል አሉ።

የሙሽራው የነገር አባት ቶማስ ቶሎ ብሎ ልጅ ታደርጉን ብለን

አለ። ዮሐ. ፫፥ ፭።

ጥቂትም ቆይተው እጃችሁ ከምን አሉ።

ከመቄረጥ አላቸው።

ከዚህም በኋላ የሴት ጌጥ አቀረበ።

የውስጥ ቀሚስ አሳዩን አሉ።

መደረቢያሳ አሉ።

የዋህነት አላቸው።

ጉትቻ አሉ።

ክፉ ነገር አለመስማት አላቸው።

ሌላም ብዙ ዓይነት ጌጥ አቀረበ።

ማደሪያችንን ንገሩን አሉ።

መከራ፣ ስደት፣ ረኃብ፣ ጥማት፣ መታሠር፣ መገረፍ፣ ጭንቀት

አላቸው። ዕብ. ፲፩፥ ፴፮።

ጥቂትም ቆይተው ጣል ጣል አድርጉበት እኮ አሉ። መሰደብ፣ መጠላት መመታት፣ መናቅ፣ መዋረድ አላቸው። ትቂጥም ቆይተው ጨምሩበት አሉ።

መሰቀል፣ መታረድ፣ መታነቅ፣ በመጋዝ መሠንጠቅ አላቸው።

ርስትሳ የለምን አሉ።

አባታችሁ አዳም ለልጆቹ ሁሉ ያወረሰው ሞት የሚባል ሰፊ ርስት አለን አላቸው። ሮሜ. ፩፥ ፲፪።

ከዚህ በቀር የላችሁምን አሉ።

መኖርስ መቃብር የሚባል ርስት አለን። ነገር ግን ዘወትር ካልቆፈሩት እህል አያበቅልም አላቸው።

የግል ገንዘብ የላችሁምን አሉ።

የቀድሞ አያታችሁን የጴጥሮስ ርስት ፍርሃት የምትባል የግል ገንዘባችን ናት አላቸው። ዮሐ. ፲፰፥ ፲፯።

ስለ ምን አሉ።

እናታችን ወይዘሮ ሰውነት አርጅተው ደክመዋልና እሳቸውን እንጦርበታለን አላቸው።

ከዚህም በኋላ ሁለቱ ሚዜዎች ሃይማኖትና ምግባር የሙሽራዪቱን ዓይንዋን ጥርሷን ለማየት ወደ እልፍኝ ገቡ። አይተውም በተመለሱ ጊዜ ቃል ኪዳን ተጋቡ። ወደ መብልም ቤት ገባን። ቤቱም እጅግ ያማረ ሰርፍና ወላንሳ የተነጠፈበት ነበረ።

እንጀራው በገበታ፤ ወይኑ በጽዋ፤ ተዘጋጅቶ ቀርቦ ነበር። በልተንም የምንጠግብ አልመሰለንም። ይልቁንም፤ ወዳጄ ልቤ በልቶ የሚጠግብ አይመስለውም ነበር።

ነገር ግን ሁላችንም በልተን ጠጥተን ጠገብን።

በነጋም ጊዜ ሙሽራዪቱን ተቀብለን ምሳችንን ተጋብዘን ወደ ሙሽራው ቤት ተመለስን።

የሚቀበሉንም ብዙ ሰዎች መጡልን።

እኛም ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ስቡሐ ዘተሰብሐ እያልን እንቀኝ ጀመር።

የሙሽራውም ሴት ዘመዶች እንዲህ እያሉ ይዘፍኑ ነበሩ።

እንዲያው ገበየንሽ፣

እንዲያው ገበየንሽ፣

አላየንሽ።

እንዲያው ገበየንሽ።

ሙሽራዪቱንም ተከትለው የመጡቱ ሴቶች እንዲህ እያሉ ይዘፍኑ ነበሩ።

ትዕቢት ትዕቢት አይዝሽሞይ፣

ትዕቢት አይዝሽሞይ፣

የክርስቶስ አይደለሽሞይ።

ትዕቢት አይዝሽሞይ፣

የማቴዎስ አይደለሽሞይ፣

ትዕቢት አይዝሽሞይ፣

የማርቆስ አይደለሽሞይ።

ትዕቢት አይዝሽሞይ፣

የነሉቃስ አይደለሽሞይ።

ትዕቢት አይዝሽሞይ፣

የዮሐንስ አይደለሽሞይ።

ትዕቢት አይዝሽሞይ፣

የነጴጥሮስ አይደለሽሞይ።

ትዕቢት አይዝሽሞይ፣

የጳውሎስ አይደለሽሞይ።

ትዕቢት አይዝሽሞይ፣

እንዲህም በዘፈንና በእልልታ ገባን።

በማግሥቱም ሁለቱ ሚዜዎቹ ሃይማኖትና ምግባር የምሥራቅ ለማለት ተለከው ሔዱ።

የሙሽራዪቱም የወንጌል አባት በሰማ ጊዜ፤ ለልጄ ለወንጌል ባል ለምእመን መንግሥተ ሰማይ የምትባለው ርስት ሸልሜዋለሁ አለ። ማቴ. ፭፥ ፫።

# ምዕራፍ ፯

# ምእመን ሞት

እኔም የሠርጉ ትርፍራፊ እስኪያልቅ በዚያው ሀገር ተቀመጥሁ።

ሙሽራዪቱ ወንጌል ግን እስከ አሥር ቀን ሳትታይ በጫጉላ ቤት ተቀምጣ ነበረና ባሥረኛው ቀን ከዘመድ ከወዳጅ ለመገናኘት መጣችና በሠርጉ አዳራሽ ቁጭ አለች።

ቤተ ዘመድም ጐረቤትም ተሰብስቦ ቢያያት ቀኝ አይንዋ የጠፋ፣ ቀኝ እጅዋ የሰለለ፣ ቀኝ እግሯ ያነከሰ ሆና ተገኘች። ማቴ. ፭፥ ፳፱፣ ፴።

ጉንጭና ጉንጭዋንም በጥፊ ሲመቷት አድጋ ኑራ ፍም መስሏል። ማቴ. ፭፣ ፴።

የቀረውም ሰውነቷ ረኃብ ያንገላታው የከፉ ቀን ሰው ይመስላል። ማቴ. ፳፥ ፯።

በዚያ ጊዜ ቤተ ዘመድ ቤተ ዘመዱ አፈረ።

ባዕድ ባዕዱ ግን ይስቅ ጀመረ።

ባሏ ምእመን ግን ይህን ሁሉ ባየ ጊዜ አንድ ጊዜ በቃል ኪዳን ካገቧት በኋላ ምንም መልኳ ቢከፋ አልፈታትም ብሎ ቆሞ ተናገረ።

እርሷም ከተቀመጠችበት ተነሥታ እኔ መልኬ ባያምር የኋላ ኋላ ለባሌ ተመቼ ደስም አሰኝቼ እኖራለሁ። ደግሞም አሁን እናንተ ብትንቁኝ የራስ ፀጉሬ ስንኳ ሊነካበት የማይወድ አባት አለኝ። ምን ትጐዱኛላችሁ። ብላ ተናገረች። ስለዚህ ሁላችንም አደነቀን። ማቴ. ፲፥ ፴።

ከዚህም በኋላ፤ ዘመዶቹ ሁሉ ተሰብስበው ይህችን ሴት ብትፈታ ፍታ፤ ባትፈታ ግን እኛ እንጣላሃለን። ያንተ ይቅርና በኛ ስንኳ ልጅ አዋቂው ይስቅብን ጀመረ። ያለእርሷ ሴት የለምን አሉ። ማቴ. ፲፥ ፴፭ -፴፮።

ቤተ ሰዎቹም እኛ ይህችን ሴት እመቤታችን ብለን አንኖርም አሉት።

እርሱ ግን ሚስቱን ወንጌልን ለብቻዋ ጠርቶ ሁሉም ፍታት አሉኝ ምን ማድረግ ይሻላል አላት።

እርስዋም አንተ ጠልተኸኝ እንደ ሆነ ፍታኝ። አልጠላኸኝ እንደ ሆነ ግን የእግዚአብሔር ሀገር ሰፊ ነውና ተነሥተን ወደ አንዱ ሀገር እንሒድ አለችው። ማቴ. ፲፥ ፳፫።

እርሱም በእውነት ይህ ነገር መልካም ነው። በዚህ የዘመዶቼ መዘባበቻ ሆኜ ከመኖር ሀገር ጥሎ መሔድ ይሻለኛል ብሎ ያለ ገንዘባቸውን ትተው ተሰደዱ።

እኔም ይህን ዓለም (መጻሕፍትን) ዞሬ ሳልጨርስ ወደ ሀገሬ አልመለስም ብዬ ነበርና ከዚያ ሀገር ተነሥቼ ወደ ደቡብ ሀገር ሔድሁ።

ከብዙ ቀንም በኋላ፤ አንድ ቀን ወደ ማታ ወዳጄ ልቤ ጠፍቶብኝ ብቻዬን ተቀምጬ ስጨነቅ በድንገት ከወደ ፊቴ ሲመጣ አየሁት። በቀረብኝም ጊዜ ወዴት ጠፍተህ ኖሯል አልሁት።

ወይዘሮ ዓለሚቱን ለመጠየቅ ሔጄ ነበረ አለኝ። ከርሱም ጋራ ይህን ስንነጋገር አንዲት ሴት መጥታ ባጠገባችን ቆመች። እኔም የማውቃት መሰለኝና እቴ ሆይ፤ አንተዋወቅምን አልኋት።

ጥቂት ጥቂት አለች።

ማን ትባያለች አልኋት።

እኔ ወንጌል ነኝ አለች።

በዚያን ጊዜ ራሴን ይዤ እጮህ ጀመርሁ።

ባልሽ ምእመንሳ አልኋት።

ምነዋ እርሱማ ከሞተ ብዙ ዘመን አይደለምን አለችኝ።

ምን ገደለው አልኋት።

ያን ጊዜ እንዳየኸው እኔን በማግባቱ ዘመዶቹም ወዳጆቹም አይንህን ላፈር አሉት። እርሱም ደስ ይበላቸው ብሎ ሀገሩን ጥሎ እኔን ይዞ ሔደላቸው።

ነገር ግን በዚያ በሔድንበት ሀገር ሰው ጠላኝ።

እኔም ውኃ አየቀዳሁ እግራቸውን ከማጠብ በቀር የበደልኋቸው በደል አልነበረም። ዮሐ. ፲፫፥ ፲፬፣ ፲፯።

አንድ ቀንም ባላገሮቹ ሁሉ ተሰብስበው ይህች ሚስትህ ምስጢር አትሰውርም፤ በጆሮዋ ቢነግሯት በሰገነት ላይ ቆማ ታወራዋለች፤ በጨለማ ቢነግሯት በብርሃን ታወራዋለች፤ እንዲያውም ሰውና ሰው ሳታጋድል አትቀርምና ይዘህልን ካገራችን ጥፋ አሉት። ማቴ. ፲፥ ፳፯።

በዚህ ምክንያት እኔን ይዞ ከወዲያ ወዲህ ሲል አንድ ቀን ሌሊት አውሬ መጣና ነጥቆ ወሰደው። ብጮህም የሚረዳኝ አላገኘሁም። በዚያው ብቻዬን ሳለቅስ አድሬ ጧት ያውሬውን ፈለግ ተከትዬ ብፈልግ አውሬው የበላውን በልቶ የተረፈውን የሰማይ ወፎች ሲናጠቁት አገኘሁ። መዝ. ፸፱፥ ፪።

ከዚህም በኋላ እርሚኤን አውጥቼ ካንዱ ወዳንዱ ሀገር ስዞር እስካሁን ቆየሁ አለችኝ።

ምነው ያባትሽ ቤት ስንኳን ላንች ለሌላስ ይበቃ የለምን፤ ይልቅ ወደ አባትሽ ቤት ብትመለሽ አይሻልሽምን አልኋት።

አዬ ወንድሜ ሆይ፤ እንግዲኢህ ወዲኢህ ባሌ ምእመን ሞቶ እኔ ተድላ ደስታ አድርጌ ለመኖር የማስብ ይመስልሃልን። እንዴሁ ከንዱ ሀገር ወዳንዱ ሀገር እየዞርሁ እኖራለሁ እንጂ፤ ወደ ሀገሬስ አልመለስም።

ደግሞ ሴት ነኝና ብቻዬን መኖር የማይሆንልኝ የሆነ እንደ ሆነ አንዱን እንደኔው ያለውን አግብቼ እኖራለሁ አለችው።

እቴ ይሆ፤ እኔም ጥቂት ቀን ካንቺ ጋራ ሆኜ ባስተዛዝንሽ እወድ ነበረ፤ ግን አሁን ለመንገዴ እቸኩላለሁ። እግዚአብሔር ቢፈቅድልኝ ስመለስ ያለሽበትን አስጠይቄ አንድ ሳምንት ያህል አነጋግርሻለሁ አልኋት። ይህንም ሁሉ ስንነጋገር እንባዋ በጕንጯ ይወርድ ነበረ።

# ምዕራፍ ፰

# ስለ ምእመን ሞት መርዶ

ወዳጄ ልቤም የሴቷን የወንጌልን መከራ አንሥቶ እየተጫወትን ስንሔድ እንደ ገና በስተኋላችን ስትመጣ አየናትና ቆመን ቆየናት።

በደረሰችም ጊዜ ምነው እቴ ሆይ፤ በደኅናሽ ነው አልኋት።

እኔስ ደኅና ነኝ። ነገር ግን ወደ ሀገር ቤት ትሔድ እንደ ሆነ የባሌን ሞት መርዶ ወደ ዘመዶቹ እንድታደርስልኝ ብዬ ነው አለች።

በቃሌ ነውን ወይስ በደብዳቤ አልኋት። ቢሆንማ ቀለምና ወረቀት ይዘህ እንደ ሆነ ቃሉን እየነገርሁህ ብትጽፍልኝ መልካም ነበረ አለች። እሺ ብዬ ቀለሜንና ወረቀቴን ተኪሴ አወጣሁና እየነገረችኝ ልጽፍ ጀመርሁ።

ይድረስ ካቶ እንደ ልቡ፣ ካቶ በፈቃዱ፣ ካቶ እንደ ጊዜው፣ እጅጉን እንዴት ናችሁ። እኔ ደኅና ነኝ። እግዚአብሔር ይመስገን። ወንድማሁ ምእመን ሞቷልና እርማችሁን አውጡ። ባልተቸገራችሁበት ነገር ወንድማችሁን ስለአስቀየማችሁት ይኸው እንዲህ በሰው ሀገር ወድቆ ቀረ።

ያሚሟቱም ነገር እንዲህ ነው። ከሀገራችን በወጣንበት ዕለት ጊዜ መሽብንና በዱር ውስጥ አደርነ። በዝያም ወምበዶች መጥተው ቀሚሳችንን ከነመደረብያችን ወሰዱብን።

በነጋም ጊዜ መንገድ አላፊች አገኙን። እነርሱም ትብትባቸውን ኍሉ አሸከመው ሁለት ምዕራፍ መንገድ ወሰዱን። ከዚያም በኋላ በጥፊ እየመቱ ወደ አደባባይ አቀረቡን። ማቴ. ፳፥ ፴፱ - ፵፪።

በዚያም ሌቦች ብለው ፈረዱብን። ከተፈረደብንም በኋላ ፴ ፴ ተገረፍን።

ከብዙ ቀንም በኋላ ሁሉ አላፊ ነው ወደ ምትባል ከተማ ደረስን። በዚያች ሀገርም ያሉ ሰዎች ለጊዜው በመልካም አቀባበል ተቀበሉን።

ካንድ ዓመት በኋላ ግን አንድ ምቀኛ ሰው ተነሥቶ ይህ ምእመን የሚባል ሰው ምንም እርሱ ደግ ቢሆን ሚዒስቱ ወንጌል ክፉ ናትና ሚስቱን ይዞ ካገር ካልወጣ ለሕዝቡ ሁሉ ጤና አይገኝም፤ ብሎ ላገረ ገዢው ነገረው።

በዚሁ ምክንያት ካገር እንድንወጣ ታዘዝን።

እኛም ቀን ለቀን የሔድን እንደ ሆነ ያው ምቀኛችን ያየንና ደግሞ አንድ ክፉ ነገር ተናግሮ እጃችንን ያሲዘዋል ብለን ስለ ፈራን በሌሊት ለመሔድ ተማከርን። ሌሊትም በሆነ ጊዜ አውራ መንገዱን ትተን ጠባቡን መንገድ ይዘን ሒድን። ማቴ. ፯፥ ፲፫ - ፲፬።

ነገር ግን የጨለማ ጊዜ ነበርና መንገድ ጠፍቶብን ዱር ለዱር ስንሔድ አውሬ በድንገት መጥቶ ባሌን ምእመንን ነጥቆ ወሰደብኝ። ብጮህም የሚደርስልኝ ሰው አላገኘሁም።

በማግሥቱም በራሴ ላይ ትቢያ ነስንሼ፣ ልብሴን ቀድጄ፣ እያለቀስሁ ብቻዬን ስሔድ መታመኔ በእግዚአብሔር ነው ወደ ምትባል ከተማ ደረስሁ።

የዚያችም ከተማ ንጉሥ በሰገነቱ ላይ ተቀምጦ አይቶኝ ኖሮ ያች ሴት ምንድር ናት፤ እስቲ ጠይቃት ብሎ አንድ አሽከር ላከልኝ።

እኔም ለመላከተኛው መከራዬን ሁሉ ከመጀመርያ እስከ መጨረሻው አጫወትኩት።

እርሱም ሔዶ በነገረው ጊዜ ብዙ አዘነልኝና ወደ እንግዶቹ ማደሪያ ቤት ውሰድዋት ብሎ አዘዘልኝ። በማግሥቱም ማኅበረ መላእክት የሚባሉትን ጭፍሮች ጠርቶ አጐበር ሥርታችሁ፤ አጐበሩን ወርቀ ዘቦ ግምጃ ለብሳችሁ፤ ጭፍሮችን ሁሉኡ

በየወገናችሁ ሰብስባችሁ፤ አልቃሽ አቁማችሁ ስለ ባሏ ስለ ምእመን አልቅሱላት ብሎ አዘዘ።

እነርሱም ጌታቸው እንዳዘዛቸው አጐበሩን ሠርተው በታላቅ ሜዳ አስቀመጡት። እኔም አጐበሩን እየዞርሁ አለቅስ ጀመርሁ። በዚያ ጊዜ ጭፍሮች ሁሉ ልዩ ልዩ ባንዲራቸውን ይዘው በክፍል በክፍሉ ሊመጡ ጀመሩ።

መጀመሪያ ማኅበረ ነቢያት የሚባሉት ጭፍሮች መጡ። ባንዲራቸውም ብጫ ሆኖ በውስጡ ዓይን ተሥሎበታል።

ቀጥሎም የንጉሥ ልጅ መጣ። የርሱም ባንዲራ ቀይ ሆኖ በውስጡ የመስቀል ምልክት አለበት። በስተኋላውም ማኅበረ ሐዋርያት የሚባሉት ጭፍሮች የጌታቸውን ባንዲራ የሚመስል ባንዲራ ይዘው መጡ።

ቀጥሎም ማኅበረ ሰማዕታት የሚባሉት ጭፍሮች መጡ። ባንዲራቸውም ቀይ ሆኖ ሰይፍ ተሥሎበታል።

ቀጥሎም ማኅበረ ጻድቃን የሚኢባሉት ጭፍሮች መጡ። የነሱም ባንዲራ ጥቁር ሆኖ በላይ የዱር አውሬ ተሥሎበታል።

ቀጥሎም ማኅበረ ምእመናን መጡ። ባንዲራቸውም አረንጓዲኤ ሆኖ በላዩ የዓለም ካርታ ተሥሎበታል።

ከነዚህም ሁሉ መካከል ዳዊት የሚባል በገና መቾ ክቡር ሞቱ ለጻድቅ በመቅድመ እግዚአብሔር። ጻድቅሰ ከመ በቀልት ይፈሪ፤ ወይበዝኀ ከመ ዘግባ ዘሊባኖስ እያለ በገናውን ሲደረድር ያየው ሰው ሁሉ በእንባ ይራጭ ነበረ።

እኔም ይህን ሁሉ ባየሁ ጊዜ የባሌ ኀዘን እየጸናብኝ ሔደ። በዚያ ጊዜ አልቃሾቹ እንዲህ ብለው አለቀሱ።

ዘመዶቹ ጠሉት እርሱም ተበደለ፣

የዱር አውሬ ሆኖ ሰው አልቀርብ እያለ።

ዋይ ዋዬ፤ ዋይ ዋዬ።

መቼ ክፉ ነበር እርሱ ለወደደው፣

ሰውስ ይቅርና አውሬ እንኳ ለመደው።

ዋይ ዋይ፤ ዋይ ዋዬ።

ምእመን ሰላምታ ሲጽፍ አየሁት፣

የተላከ ብሎ ይድረሱን ከሞት።

ዋይ ዋዬ፤ ዋይ ዋዴሌ።

እንዲህ ከጧት እስከ ማታ ስናለቅስ ውለን ፀሐይ ስትጠልቅ ተለያየን።

እኔም እንግዲህ ዓይናሁን ለማየት እንኳ ፈቃድ የለኝምና በዕለተ ምጽአት ለመፋረድ ያብቃን።

ዲዮቅልጥያኖስ በነገሠ ባ፫ ዓመት በሮምያ ከተማ ተጻፈ።

## ምዕራፍ ፱

# ስለ ፍቅርና ስለ ተንኰል

ከዚህም በኋላ ወደ ሰሜን ዞርሁ። የሰሜን ሀገር መንገድ በዚያም በዚህም ያስኬዳል። ግን ቶሎ ብዬ ወደ ደቡብ ሔድሁ። በደቡብም ወደ ምሥራቅ ተመለስሁ። በሰሜንና በደቡብ በምዕራብም ዞሬ ተመልሼ ማረፊያዬ በምሥራቅ ነበረ።

በምሥራቅም ሀገር ፍቅር የሚባል ሰው በጌትነት ይኖር ነበረ። ሮሜ. ፲፫፥ ፲።

እርሱም እጅግ መልካም ሰው ስለ ሆነ ወደ ቤቱ የሚመጡትን እንግዶች ሁሉ ይቀበል ነበረ።

ነገር ግን ቅናትና ምቀኝነት የሚባሉ ጐረቤቶች ነበሩትና እንግዶቹ ሁሉ ወደ ፍቅር ቤት ሲሔዱ ያዩ እንደ ሆነ ፍቅር ዛሬ በቤቱ የለምና ወደኛ ዘንድ መጥታችሁ እደሩ እያሉ ከደጅ ይወስዱዋቸው ነበረ። አንድ ቀንም በሩቅ ቆሜ ስመለከት፤ ተንኰል የሚባል ሰው ሦስት አጋሰሶች ጭኖ ሲመጣ አየሁት። ወደ ፍቅር ቤትም ለማደር አስቦ ኖሮ አቃንቶ ሔደ።

ፍቅርም ተንኰል ወደ ርሱ ሲመጣ ባየ ጊዜ ቅንነት የሚባለውን አሽከሩን ጠርቶ እንግዳ መጥቶአልና ወጥተህ ተቀበል አለው።

ጭነቱኡም እስትራገፍ ብዙ ቆዩ። በዚያ ጊዜ ቶሎ ብሎ ሚስቱን ገርነትን ጠርቶ ምነው እንግዶቹ ጠፉ ይሆን፤ እስኪ ብቅ በይና እያቸው ያልሆነ እንደ ሆነ እኔም እመጣለሁ አላት።

እሷም ገና ብቅ ስትል ተንኰል ጭኑቱን አራግፎ፣ ነጫጭ ልብሱን ለብሶ እየሳቀና ደስ እያለው ሲመጣ አገኘችውና ወደ ቤት አስገባችው።

የተጫነውም ምንም እንደ ሆነ አላወቁም።

ተንኰል ግን ፍቅርን ከዚያ ሀገር ለማጥፋት አስቦ ነበርና ምስክር የሚሆኑ ሰዎች በሣጥን ውስጥ አግብቶ ምግባቸውን ጨምሮ ቆልፎባቸዋል።

አሳቡም፤ ፍቅርን ክፉ ነገር ለማናገርና እነዚያን ሰዎች ምስክር ለማድረግ ነበር።

የራትም ጊዜ ሲደርስ ፍቅር ወደ ተንኰል ቀርቦ ጌታ ሆይ እባክህ እንግዴህ እህል እንቅመስ አለው።

ተንኰል መለሰ፤ ጌታው ምን ከፋኝ። ነገር ግን ጭነቴ በደጅ እንደ ወደቀ ነው። አስቀድሞ ጭነቱን አስገብተን ከዚያ በኋላ ለራት ብንቀመጥ መልካም ይመስለኛል አለ።

ፍቅርም አሽከሩን ቅንነትን ጠርቶ ምነው እንዲህ አደረግኸኝ ጭነቱን በጊዜ አታስገባም ኖሯልን አለው።

እመቤቴ ለእንግዳ እግር ውኃ አሙቅ ብለውኝ ነበረ አለ።

በል እኮ አሁንም በቶሎ ለራት ተቀመጡ።

እራትም ከበሉ በኋላ፤ ጨዋታ ጀመሩ።

ተንኰል በመጀመሪያ እንዲህ አለ።

ወዳጄ ፍቅር ሆይ፤ እኔ በሀገሬ ሳለሁ፤ አባትህ ክርስቶስ ከሞተ ወዲህ ከታናሽ ወንድምህ ከትሕትና ጋራ በዚህ ሀገር የመኖራችኍን ወሬ ሰምቼ ነበር። ነገር ግን፤ ወንድምህ ትሕትና እንዳንተ አልተመቸውም አሉ።

አሁንም እንዳንተ ያለ ሰው ለጌታ ሳያድር መኖር አይገባምና፤ ለዚህ ሀገር ገዢ ለሰይጣን አሽከር ብትሆን መልካም ነው። ቤትህም ይታፈር ነበር እንጂ፤ መቼ ለሁሉ መሣፈሪያ ትሆን ነበረ። ፍቅር ደግ ሰው ነው እያሉህ እውነት ይመስልሃልን። አትስማ፤ ሁሉሎም ትዳሩን እያበጀ ነው። እኔ ዛሬ ወዳንተ መምጣቴ ይህን ልመክርህ ነው እንጂ፤ ምንም ሌላ ጉዳይ የለኝም።

እንግዲያውማ ቅናትና ምቀኝነት ያባቴ የሄሮድስ የእኅቱ ልጆች አይደሉምን። እርሳቸውን ትቼ ወዳንተ መምጣቴ ለምን ይመስልሃል። ምክሬን ስማ እያለ ሊነግረው ጀመረ።

ፍቅርም እስቲ እኮ ለሁሉም ነገር እግዚአብሔር ያውቃል አለው። ከዚህም በኋላ ወደ መኝታ ቤት ሔዱ። በነጋም ጊዜ ከየመኝታቸው ተነሥተው ተገናኙ። ከሰላምታም በኋላ ቆመው ሲነጋገሩ ቅናት እግረ መንገዱን ሲያልፍ ተንኰልን ከፍቅር ጋር ቆሞ አየው። መዝ. ፷፪፥ ፬።

በቶሎም ወደ እርሱ ቀርቦ አንተ ተንኰል አይደለህምን አለው።

ነኝ እንጂ፤ አለው።

እስቲ ወዲህ ና አለው።

በሔድህም ጊዜ ምነው ወዳጄ ከእኔና ከፍቅር ማን ይቀርብህ ነበረ። መሰንበት እንጂ፤ ብዙ ያሳያል። እኔ አሽከሮች አይሁድና የፍቅር አባት ክርስቶስ ጠበኞች መሆናቸውን ሳትሰማ ቀርተህ ነውን።

እርሱ ስንኳ በእኔ ምክንያት ነው እንጂ፤ ሥር መሠረት የሆነ ጠብ የላቸውም ብሎ ተቆጣና ሔደ። የሐዋ. ፲፫፥ ፵፯።

ሔዶም ያየውን ሁሉ ለወንድሙ ለምቀኝነት ነገረው።

ምቀኝነትም መለሰ፤ ወንድሜ ቅናት ሆይ፤ ከቶ ይህ ፍቅር የሚባል ሰው በምን ታደለ።

እኛ በገዛ ሀገራችን ተንቀን፣ ተጠልተን መኖር፤ እርሱ ተከብሮ፣ ተወዶ መኖር ምን ይመስልሃል።

በል እስኪ ሌላውስ ይቅርና ያጐታችን የሄሮድስ ልጅ ተንኰል እንኳ ወደ ፍቅር ቤት ሒዶ ይደርን።

ይህን ሰው ከዚህ ሀገር ካላጠፋን ምን ኑሮ አለን። እንዲህማ ከሆነ፤ አሽከሮችስ፣ ሚስቶችስ ቢኖሩን ምን ይሆኑናል። ወደርሱ ቤት የሚመጡ ብዙ ናቸውና እነዚያን እያዩ እየተዉን ይሔዳሉ እንጂ፤ ከኛ ጋራ የሚኖሩ ይመስልሃልን እያለ ጣቱን ያጮህ ጀመረ።

ይህም ከሆነ በኋላ ተንኰል በፍቅር ቤኢት ዋለ አደረ። የሚሔድበትም ጊዜ በደረሰ ጊዜ ሔዶ በጭነቱ መካከል ተቀመጠ። ፍቅርንም ቆይታ አለኝ ብሎ ጠራው።

ፍቅርም በመጣ ጊዜ ተንኰል ነገረ ጀመረ።

ወዳጄ ፍቅር ሆይ፤ በዚህ ሀገር የምትኖረው ከቶ ስለ ምን ነው። ርስትህ ጉልትህ በምዕራብ ሀገር መሆኑን ሰምቼ ነበረ። ዘሌዋ. ፲፱፥ ፲፰።

ርስትህ ጉልትህን ለማንም ከብት መቋሚያ አድርገህ በዚህ ሀገር መቀመጥህ ለማን ደስ ይበለው ብለህ ነው። ከደግነት የሚቆጠርልህ መስሎህ ነውን አለ።

በዚያ ጊዜ ሞኙ ፍቅር ሆይ፤ እውነት መሰለውና ይልቁንም ተንኰል የቅናትና የምቀኝነት ያጐታቸው የሄሮድስ ልጅ መሆኑን ዘነጋውና የልቡን ምሥጢር ሁሉ ሊነግረው ጀመረ።

ተንኰል ሆይ፤ እንግዲህ አብረን በላን፤ አብረንም ጠጣን፤ ምን እሰውርሃለሁ።

እነዚህ ጐረቢቶቼ ቅናትና ምቀኝነት ጠላቶቼ ናቸው። እነርሱ ቤታቸው ቁጭ ብለው አሽከሮቻቸውን አይሁድን ከሳሽ አድርገው ልከው አባቴን ክርስቶስን አስገደሉት።

እኔም ያን ጊዜ ገና ልጅ ነበርሁ። አሁን ግን ሰውነቴ እያደገ ነገሩ ይቆጨኝ ጀመር።

ገዳዮችንም በጠቋሚ አገኘኋቸው። እነዚያንም ለመግደል ሳስብ የነፍስ አባቴ መምሬ እውቀቱ መጥተው በምን ነገር አይሁድ ልትገድል ታስባለህ። ጌቶቻቸው ምቀኝነት ቢያዙዋቸው እምቢ ይበሉ ብለህ ነውን አሉኝ።

ከዚህም በኋላ ቅናትና ምቀኝነት ያሉበትን ስፍራ እየጠያየቅሁ አገኘሁት።

አሁን እነርሱን ከሰሼ በፍርድ እንዳስገድላቸው ያገሩ ዳኛ ሰይጣን የሚባለው ጠላቴ ነው። ለነርሱ ግን አያታቸው ነው። ዮሐ. ፰፥ ፴፰።

ነገሩ ቢቸግረኝ ወደዚህ ሀገር መጥቼ ቤት ሥርቼ ተቀመጥሁ። አሳቤ ግን ሲመቸኝ ቢሆን እኔ ራሴ፤ ባይሆን እጅ አዛውሬ እነርሱን አስገድዬ ያባቴን ደም እወጣለሁ ብዬ ነው።

እንዲያውም አባታቸው ሰይጣን ያየ እንደ ሆነ ሀገር አስጨሆ ያሲዘኛል ብዬ ነው እንጂ፤ ቀን ለቀንም ገድያቸው ብሔድ አልፈራም ነበር።

የዚህ ሀገር ሰው ሁሉ እንዴት ጠልቷቸዋል ይመስልሃል። ሥራቸው ሁሉ ባልና ሚስት ማፋታ፤ አሽከርና ጌታ መለያየት፤ ድኃና ባለጠጋ ማጣላት፤ አባትና ልጅ ማረጋገም፤ ወንድምና ወንድም ማጋደል ነው። ማቴ. ፲፥ ፳፩።

እንዲህ እያደረጉ ሀገር አውከዋል እያለ ምሥጢሩን ሁሉ ዘረገፈለት።

ተንኰልም ይህን ሁሉ ምሥጢር በሰማ ጊዜ፤ ለካ እንደዚህ ነውን፤ እኔ ይኸን ሁሉ ነገር መቼ ሰማሁ እንዲህስ ከሆነ ያስብከው ይፈጸምልህ ብሎ ጭነቱን ጭኖ ተነሣና ተሰነባብተው ሔደ።

የፍቅር አሽከር ቅንነትም እስከ አውራው መንገድ ድረስ ሸኝቶት ተመለሰ።

ተንኰልም ወደ ጐድጓዳው ስፍራ ሲደርስ ጭነቱን አራግፎ ሣጥኑን ከፍቶ እነዚያን ሰዎች አወጣቸው።

ከዚህም በኋላ ፍጹም ሳቅ ሆነ።

ከሰዎቹ አንዱ «ቀን ለቀንም ገድያቸው ብሔድ አልፈራም ነበረ።» ብሎ ሲናገር ልስቅ ነበረ። አንድ እርምጃ መንገድስ የሚያስኬደው ኑሯልን። ምን ጉደኛ ሰው ነው አለ።

ተንኰል መለሰ፤ እኔስ የሚያስደንቀኝ የቀላልነቱ ነገር ነው። በሉ እስቲ ጥንት አንተዋወቅም፤ ይህን ሁሉ ምሥጢር መናገሩ ቀላል አያሰኘውምን። የሚያስለፈልፍ መድኃኒት ቀምሶ ይሆናል እንጂ፤ በጤናው አይመስለኝም አለ። የሐዋ. ፳፯፥ ፳፬።

ደግሞ ከሰዎቹ አንዱ መለሰ፤ እንደዚህ ይመስላችኋልን።

የቅናትና የምቀኝነት ውቃቢ ነው እንጂ፤ በሉ እስቲ በገዛ ሀገራቸው ተቀምጦ ሊገድል የሚያስብ እንዲያ ያለ ሰው ነው፤ ይህ ሴረኛ እንዲህ ሰውን ሁሉ አሲሮ አሲሮ ሊገድላቸው ኖሯል፤ ዛሬ ግን ተገለጠለት አላቸው።

እንዲሁም ሲጫወቱ ፀሐይ ጠለቀች።

## ምዕራፍ ፲

# ስለ ፍቅርና መከራ

ከዚህ በኋላ ቀኑ ሲጨልምላቸው አራቱ ሁሉ በፈረስ በፈረስ ተቀምጠው ወደ ቅናትና ወደ ምቀኝነት ቤት ሔዱ።

ተንኰልም እንግዶቹን በደጅ ትቶ እርሱ ቀድሞ ገባ። ቅናትና ምቀኝነትም ባዩት ጊዜ እንዲህ አሉት።

ተንኰል ኅሆይ፤ ከዘመድ ወገን አንድ አንተ ብቻ ቀርተኸን ነበር። እንዴት እኛን ትተህ ወደ ፍቅር ቤት ትገባለህ። ፍቅርና እኛ ጠበኞች መሆናችንን አጥተኸው ነውን፤

ያንተ አባት ሄሮድስ የቤተ ልሔምን ሕጻናት ሁሉ ያስገደላቸው በፍቅር አባት በክርስቶስ ምክንያት አይደለም። ማቴ. ፪፥ ፲፮ - ፲፰።

ነገር ግን ላንተ አባት ክርስቶስን መግደል ባይሆንለት እኛ አሽከሮቻችንን አይሁድን ከሳሽ አድርገን አስገደልነው። አሁንም አንተ የሄሮድስ ልጅ መሆንህን ፍቅር አውቆ በነበር በተኛህበት ስፍራ በማንጅራትህ አርዶህ ይሔድ ነበረ። እንግዴህስ የራት ጊዜ ነውና ወደ ሙብል ቤት እንሒድ አሉት።

ተንኰል መለሰ፤ የዚህስ ነገሩ ገና ነው። ይልቅስ እንግዶች አሉብኝና አስገቡልኝ አለ።

በፍጥነትም ወጥተው እንግዶቹን አስገቡለት።

ከዚህም በኋላ ለራት ቀረቡ። ሙብሉም ሲጋመስ መጠጥ ቀረበና ሁለት ሁለት ብርጭቆ ጠጅ እንደ ፈጁ ጨዋታ ተጀመረ።

ቅናትና ምቀኝነት ተንኰልን እንደዚህ ብለው ጠየቁ። ከቶ እኛን ትተህ ወደ ፍቅር ቤት የገባህበትን ነገር እባክህ ንገረን አሉት።

ተንኰል መለሰ፤ እንግዲህ ወዲህ ነገሩን አሳምሬ ልንገራችሁ።

በፍቅር አባት ለክርስቶስ ፲፪ አሽከሮች እንደ ነበሩት እናንተም ታውቃላችሁ። ማቴ. ፲፩፥ ፩።

እነርሱም ጌታቸው ከሞተ በኋላ ከወደ ምዕራብ ሀህገር የመጣ ጳውሎስ የሚባል ሰው ረዳት አድርገው ዘመዶቻችንን ሁሉ ፍጁዋቸው። እነዚያ ሁሉ ጀግኖች እነ ክህደትን፣ እነ መሠሪነትን፣ እነ ጸብን፣ እነ መከራከርን፣ እነ ሁከትን፣ እነ ስካርን፣ ከነዚህም ሁሉ የሚበልጥ ጣዖት ማምለክን ስንቱን ልንገራችሁ። እነዚህን ሁሉ ገድለው ዘራቸውን አጣፉት። ገላ. ፭፥ ፲፱ - ፳፩።

የነዚህንም ደም የሚመስል አንድ ልጅ ስንኳ መኖሩን እንጃ። አሁንም ባገሬ ሳልሁ የክርስቶስ ልጅ ፍቅር የሚባለው ቅናትንና ምቀኝነትን ለመግደል ባጠገባቸው ቤቱን ሠርቶ ተቀምጧል።

ጊዜውም ሲመቸው በተኙበት ስፍራ አርዷቸው ሳይሔድ አይቀርም እየተባለ ሲወራ ሰማሁ።

ከዚህም በኋላ ለሚስቴ ለወይዘሮ ክፋት፤ ወንድሞቼ ቅናትና ምቀኝነት ነገሩን ሳይውቁት ሊሞቱ ነውና፤ ምናልባት ሳይሞቱ ባገኛቸው ልሒድ ብዬ ነገርኋት።

እርስዋም በኅዘን ቃል በል እንግዲህ ብቻህን ቅረውና ዕረፈው። ቅናትና ምቀኝነትማ ከሞቱ ምን ቆሜያለሁ ትላለህ። አነሰ ሲሉት ተቀነሰ እያለች እያለቀሰች ትሎ ስንቄን ሰንቃልኝ ተነሣሁ።

እኔም አስቀድሞ ወደ እናንተ ቤት የመጣሁ እንደ ሆነ ጠላታችን ፍቅር ይጠረጥራል ብዬ ስለ ሥጋሁ ኸው ብዬ ወደ እርሱ ቤት ሔድሁ።

እነዚህንም ሰዎች የሚበሉትና የሚጠጡትን ጨምሬ በሣጥን ቆልፌባቸው ነበረ።

ማታ ማታ ግን እየከፈትሁ አወጣቸው ነበረ።

አንደኛው አሳቤ ነጋዴ እንመስልና እንዳልጠረጠር ነበር።

ሁለተኛው አሳቢኤ እርሱ ለሚናገረው ነገር ሁሉ ምስክር እንዲሆኑ ብዬ ነበረ።

ከዚህማ ወዲያ ያለውን ነገር እነዚህ ይንገሯችሁ እንጂ ምንትሉኛላችሁ አለ።

እነዚያም መለሱ፤ ኧረ ወዲያ አንተው እንደ ጀመርህ ንገራቸው እኛስ እንኳን ልንናገረው ስናስበው ልባችን ይንቀጠቀጣል አሉ። መዝ. ፴፫፥ ፲፩።

ተንኰል መለሰ፤ እንግዲያውስ እኔ ልንገራችሁ።

ወንድሞቼ ሆይ፤ ያልሞታችሁ ይመስላችኋልን። ሞታችኋል እኮ።

እርሱ ያሰበው ጊዜ ሲመቸው ቢሆን እርሱ፤ ባይሆንም እጅ አዙሮ ገድሏችሁ ሊሔድ ነበረ አላቸው።

የውነትህን ነው አሉት።

ነጉላ ቂል ሁሉ፤ የውነትህን ነውን ስትል አንገት አንገትን እያለ ይሔዳል አላቸው።

ቅናትና ምቀኝነትም ወይ እኛ ሆይ፤ ወይ እኛ ሆይ፤ ባባቱ ከተማ ልጁ ተቀማ። እንደሚባል ሁሉ በገዛ ሀገራችን ተቀምጦ ሊገለን ኖሯልን እያሉ ከቤት ወደ ደጅ፤ ከደጅ ወደ ቤት መመላለስ፤ ጣታቸውን ማጮህ ሆነ።

በዚያ ጊዜ ተንኰል ተናደደና አሁን ከቤት ወደ ደጅ፤ ከደጅ ወደ ቤት ብትሉ ምን ይሆናል። ይልቅስ ኑ ተቀመጡና እንማከር አላቸው።

እነርሱም መጥተው ተቀመጡ።

ከዚህ በኋላ ተንኰል ምክሩን ጀመረ።

ወንድሞቼ ሆይ፤ እንኳን ሳትሞቱ አገኘኋችሁ እንጂ፤ ባለፈ ነገር ለምን ታዝናላችሁ። አሁንም ነገ ማለዳ ተነስተን ነፍሰ ገዳይ ነው ብለን በዳኛ ላይ እንከሰሰው። ነገሩን ሐሰት ቢል በምስክር እንረታዋለን። ነገሩም መልካም ሆኖልናል አላቸውና ይሁን ብለው አደሩ። ሌሊቱም እጅግ በዛባቸው። ነግቶ ዓይኑን የሚያዩት አልመሰላቸውም ነበረ።

በማለዳም ተነሥተው ወደ ዳኛ ሔዱ።

ሀገሩም ሀገር፤ ነገሩም ነገር እንደሚባ፤ እነርሱ ከሳሾች አባታቸው ስይጣን ዳኛ ሆነ።

ዳኛውም ይህን ነገር በሰማ ጊዜ፤ እጅግ ተቆጣ። ልጆቹንም እንዲህ እያለ ይሰድብ ጀመር።

እናንተን ከመውለድ ልጅ የለውም መባል ይሻለኝ ነበረ ምናምንቴ ሁሉ፤ ይህን ስትሰሙ ጊዜ ሔዳችሁ አንገቱን ብላሁች አትገድሉትም ኖሮአልን አላቸው።

አንተን አባታችንን እንዳናሳማ ብለን ነው እንጂ፤ እንግዲያውማ እርሱ አቅቶን ነውን አሉት።

ከዚህ በኋላ ይዛችሁ አምጡ ተብሎ ተላከና ፍቅር ተይዞ ቀረበ።

በዚያ ጊዜ ቅናትና ምቀኝነት ቆመው ሊያሳጡት ጀመሩ። ወዲያውም ልትገድለን ሞክረሃል አሉት። ፍቅርም አሁንስ ጊዜ ባይመቸኝ ነው እንጂ መቼ እተዋችኋለሁ።

በሸንጐም የተቀመጡት ሽማግሎች ጀግንነቱን አደነቁ። ዳኛው ግን እጅግ ተቆጣና አንተ ደፋር ለጊዜው እንኳን ሐሰት ነው አትልም አለው።

ፍቅርም ሳይፈራ በድፍረት መለሰ፤ እኔ እንዳንተ መቼ የሐሰት አባት ነኝ። አንተ የእውነቱን ሐሰት፤ ሐሰቱን እውነት ስትል ትኖራለህ። ዮሐ. ፰፥ ፵፬።

አሁንም ካንተ የተወለደውን ሁሉ ቀስ እያልሁ ከምድር ላይ ሳላጠፋ የቀረሁ እንደ ሆነ ምን ተናገረ በለኝ አለው።

ሽማግሎችም እየተነሡ ፍቅር ሆይ፤ ጦጣ ትዘፍን ተይዛ የሚሉትን ተረት ደረሰብህ። አሁን በሰንሰለት ተይዘህ ይህን ከመናገርህ ይልቅ አጥፍቻለሁና ማረኝ ማለት አይሻልምን አሉት።

ፍቅር መለሰላቸው፤ የሞትሁ እንደ ሆነ ምን እጐዳለሁ። ሥጋዬን ነው እንጂ ነፍሴን አይገድሏትም። እውነቱን ተናግሬ የሆነ ይሁን አለ። ማቴ. ፲፥ ፳፰።

ከዚህም በኋላ ሊገድል ከመከረ ይሙት በቃ እየተባለ ተፈረደ።

ፍቅርም ይሙት በቃ ከተፈረደበት በኋላ፤ አሰበና ምሥጢሩን ያወጣበት ተንኰል እንደ ሆነ ትዝ አለው። ከሸንጐም ይዘውት ሲሔዱ በተንኰል እጅግ አዝኖ በግዕዝ ቋንቋ መዝሙረ ዳዊት እየደገመ ይሔድ ጀመረ።

እንዲህ እያለ

ጸላእከ እግዚኦ ኵሎሙ ገበርተ ዐመጻ።

ወትገድፎሙ ለኵኰሎሙ እለ ይነቡ ሐሰተ።

ብእሴ ደም ወጕኅላዌ ያስቆርር እግዚአብሔር።

ልበሙኒኢ ከንቱ።

ከመ መቃብር ክሡት ጐራዒቶሙ።

ወጸልሐዉ በልሳናቲሆሙ።

አድኅነኒ እግዚኦ እስመ ኅልቀ ኄር።

ከንቶ ይትናገሩ ፩ዱ ምስለ ካልዑ።

በከናፍረ ጕኅሉት ልበ ወብ ይትናገሩ።

ይሤርዎን እግዚአብሔር ለከናፍረ ጕህሉት።

ወለልሳን እንተ ተዐቢ ነቢበ።

ጸላእትየሰ እኩየ ይቤሉ ላዕሌየ።

ማእዜ ይመውት ወይሠዐር ስሙ።

ልቡ አስተጋብአ ኅጢአተ ላዕሌሁ።

ይወፅእ አፍኣ ወይትናገር ወየኅብር ላዕሌየ።

ወይትቃጸቡኒ ኵሎሙ ጸላእትየ።

ወይመክሩ እኩየ ላዕሌየ።

ነገረ ጌጋይ አውፅኡ ላዕሌየ።

ምንተ ይሁቡከ ወምንተ ይቄስኩከ በእንተ ከናፍረ ጕኅሉት።

አሕጻሁ ለኀያል ስሑል።

ከዚህም በኋላ ወደ መግደያው ስፍራ ደረሱ። ቅናትና ምቀኝነትም ፍቅርን ደብድበው ጣሉቱ። ገደለነውም ብለው ወካዎ እያሉ ሔዱ። ለተንኰልም ብዙ ሽልማት። ደግሞ ተካፍለው የያዙት ርስት ጭካኔ የሚባል ነበረ። ያንን ለተንኰል ብቻ ለቀቁለት።

## ምዕራፍ ፲፩

# ስለ ፍቅር ሕይወት

ከዚህም በኋላ የፍቅር ወዳጆች ሬሳውን አንሥተው ሊቀብሩ መጡ።

በቀረቡም ጊዜ ጥቂት ጥቂት ሲተነፍስ አገኙት። ከዚያም ቶሎ አንሥተው ልቡና ወደሚባለው ቤታቸው ይዘውት ሔዱ። ብዙ ቀንም አስታመሙት።

እኔም ወደ ተኛበት ቤት ገብቼ እግዚአብሔር ይማርህ እንደምን አልሁት።

ፍቅርም መለሰ፤ ዛሬ በጐ ነኝ፤ በእግዚአብሔር ቸርነት ከሞት የተረፍሁ ይመስለኛል። ቁስሉም ሊጠግ ጀምሯል አለ።

እንኪያ ምነው ወደ ደጅ ብቅ አለማለትህ አልሁት። እስካሁን ድረስ ግርሻውን ፈርቼ ነው፤ እንግዲህ ወዲህ ግን ብቅ እላለሁ። አለ።

አሁንም ምሕረቱን ይላክልህ፤ ደኅና ሰንብት አልሁት። ወንድሜ ሆይ፤ ማን ትባላለህ፤ የመጣህበትስ ከወዴት ነው። ከዚህ ቀድሞ የተዋወቅን አይመስለኝም አለ። እኔ ይህን ዓለም ለመዞር የመጣሁ እንግዳ ነኝ። በሽታህን ብሰማ ልጠይቅህ ብዬ መጣሁ አልሁት።

እግዚአብሔር ይጠይቅህ። አሁን ምን አደከመህ። ከዚህ ሀገር ያሉት ወዳጆቼማ፤ እግዚአብሔር ይማርህ ብለው እንኳ ሳይልኩብኝ አልቀሩም። ምን ይሆናል፤ ክፉ እንዳሆይኑ እንዲህ አንዳንድ ሰው ይገኛል።

ደግ እንዳይሆኑ ደግሞ ሰው እንዲህ ያስቀይማል። የእግዚአብሔርን ቸርነት ተመልክቶ ሁሉንም እንዲያው መተው ይሻላል።

በል አሁንም መሸብህ በቶሎ ሒድ ምናልባት ሰው ለመሆን ቢያበቃኝ ለወደ ፊቱ እንጠያየቅ አለኝ። መሆኑንማ ባባትህ አሽከር በዮሐንስ ቤት አይችሃለሁ።

ንግግርና ጨዋታ ግን የለንም አልሁት። ፩ ዮሐ. ፫፥ ፲፱።

ይሆናል፤ ይሆናል እርሱ እግጅ ወዳጄ ነው። አሁን ስንኳ ሦስት ጊዜ ያህል እየመጣ ጠየቀኝ አለኝ። እኔም በዚሁ ሀገር የምሰነብት ከሆነ እየመጣሁ አጫውትህ ነበረ። ነገር ግን አቶ እንደ ጊዚው አስጠርተውኝ ወደ እርሳቸው መሔዴ ነው። ከዚያም በቶሎ እመለሳለሁ።

አሁን ዝም ብዬ እንዳልቀር የኵራት ይመስልብኛል ብዬ ፈራሁ።

ያንተ ታናሽ ወንድም ትሕትና ወንበር ዘርግቶ ያስተምራል። እኔንም አስተምርሃለሁ ብሎኛል ከርሱ ጋራ ሁለት ዓመት ያህል ሳልቀመጥ አልቀርም። አንተስ ከሞት ከተረፍህ ወደ ወንድምህ ቤት ሳትመጣ ትቀራለህን፤ ያን ጊዜ በውል እንተዋወቃለን። ወይም ወዳገሬ ስመለስ መጥቼ እሰናበትሃለሁ ብዬው መንገዴን ሔድሁ።

# ምዕራፍ ፲፪

# ስለ አቶ እንደ ጊዜው

ከዚህም በኋላ ወደ አቶ እንደ ጊዜው ቤት ሔድሁ። አቶ እንደ ጊዜውም በታላቅ ወንበር ተቀምጠው ነበረ። በርሳቸውም ቤት የሚኖሩ ሰዎች በቁጥር የበዙ ነበሩ። ሁሉም አቶ እንደ ጊዜውን ከበው ተቀምጠዋል።

አቶ እንደ ጊዜው ሲስቁ ሁሉም ይስቃሉ።

ዝም ሲሉም ዝም ይላሉ። ሲዋሹም እነርሱ እውነት እውነት ይላሉ። ከእርሳቸው ተለይተው ምንም የሚሠሩት ሥራ የለም።

እኔም ወደ እርሳቸው ገብቼ ጌታ አቶ እንደ ጊዜው ሆይ፤ እኔን ስለምን አስጠሩኝ አልኋቸው።

እርሳቸውም በመልካም ቃል መለሱልኝ። አንተም ታውቃለህ ቤተ ሰዎቼ እንደ በዙ ገንዘቤም ሥፍር ቁጥር እንደሌለው።

አሁንም የገንዘቤን ዘገብአና ዘወጽአ እየጻፍህ ለቤተ ሰዎቼ በየጊዜው ምግባቸውን እየሰጠህልኝ ከእኔ ጋራ እንድትኖር ነዋ አሉኝ።

ነገሩስ መልካም ነው። ምግቤንና ደመወዜን እንደምን ነው የሚሰጡኝ አልኋቸው።

ምግብህን ከበለስ ፍሬ እንደ ፈቀደህ ትበላለህ። ደመወዝህንም ባመት የዘላለም ሞትን እሰጥሃለሁ አሉኝ። እኔም ቶሎ ብዬ ጌታው አቶ እንደ ጊዜው ሆይ፤ ይህስ ከቶ አይሆንልኝም። እኔ እምቢ ብዬ ነው እንጂ ታላቁ ንጉሥ ልጅ ከእኔ ጋራ ሁን፤ ምግብን ከሰማይ የወረደ እንጀራ ደሞዝህንም የዘላለም ሕይወትን እሰጥሃለሁ እያለ ያባብለኛል። ዮሐ. ፮፥ ፶፩።

ዳግመኛ ይህን ዓለም ዞሬ ሳልጨርስ ደብዳቤ እሐፊ አልሆንዎም።

ደግም ሁሉንም ነገር ከወዳጄ ልቤ ጋር መክሬ እነግርዎታለሁ። አሁንም ጤና ይስጥልኝ ብያቸው መንገዴን ሔድሁ።

ከዚህም በኋላ፤ ላቶ እንደ ጊዜው ጸሐፊ መሆን ጥቅም ይገኝበት እንደ ሆነ ብዬ ለወዳጄ ልቤ ባማከረው ወንድሜ ሆይ፤ ምነው ሁሉን ታስባለህ፤ ላቶ እንደ ጊዜው ጸሐፊ ከመሆን ለምኖ መብላት አይሻልምን አለኝ።

እኔም እውነትህ ነው ብዬ ያቶ እንደ ጊዜውን ነገር ቸል አልሁት።

# ምዕራፍ ፲፫

# ስለ ትምሕርት ቤት

ከዚህም በኋላ ወደ ትሕትና ቤት ሔድሁ

እርሱም በወንበር ተቀምጦ ያስተምር ነበረ። ከርሱ የሚማሩ ሰዎች ስንት ይመስላችኋል። እነ ንጽሕና፣ እነ እውቀትም፣ እነ እውነት፣ እነ ዝምታ፣ እነ ትዕግሥት፣ እነ ድኅነት፣ እነ የዋህነት፣ እነ ሰላም የጥበብ መጀመሪያ ፈሪሃ እግዚአብሔር እንኳ ከርሱ ይማር ነበረ። መዝ. ፻፲፩፥ ፲።

በዚህም ሁሉ ላይ ድኅነት አለቅነት ተሾሞ ነበረ። እኔም ወደ አለቃው ሔጄ፤ ትምህርት ለመማር መጥቻለሁና ንገርልኝ አልሁት።

እርሱም ሔዶ በነገረው ጊዜ ከተማሪዎቹ አንዱን ጠርቶ ይህን ሰው ቶሎ አስተምረው ብሎ አጋጠመኝ።

ከዚህም በኋላ ዳዊት ለመማር ጀመርሁ። ነገር ግን አሌፍ ብፁዓን እለ ንጹሓን በፍኖቶሙ የሚለውን ለማጥናት አልቻልሁም። መዝ. ፻፲፰፥ ፩።

ይህንም ትቼ የዜማ ትምህርት ጀመርሁ። ነገር ግን የዜማ ትምህርት እጅግ አድካሚ ስለ ሆነ ጥቂቶችን ብቻ በቃሌ አጠናሁ። እነርሱም ከዚህ ቀጥለው ያሉት ናቸው።

## አርያም

ኵሉ ኀላፊ ወፈላሲ ሃሌ ሉያ ለአብ። ወኵሉ ከመ ልብስ ይበሊ ሃሌ ሉያ ለወልድ። ሃሌ ሉያ ወለመንፈስ ቅዱስ። አንተሰ እግዚኦ ለዓለም ትነብር።

## እስመ ለዓለም ዘመፃጒዕ

ድልዋኒከሙ ንበሩ እስመ ኢተአምሩ ጊዜ ይመጽእ ሐዳስ በዓለ ቤት እመሂ ሠርከ ወእመሂ መንፈቀ ሌሊት ወእመሂ ጐሀ ጽባሕ ድልዋኒከሙ ንበሩ።

## አቡን ዘምኵራብ

## ሰብእኬ ንሕነ አኮኑ መሬት

ከመ ሐሠር ዘቅድመ ገጸ እሳት ወከመ ጢስ ዘያኃልፍ በነፍስ ሶበ ይመጽእ ሐዳስ በዓለ ቤት።

ወሶበ ይብልዋ ለነፍስ ንኢ ፃኢ ነፍስ ምን ትኬ ሰብእ ዘይጸንሖ እሳት።

## አቡን ዘምኵራብ

ሃሌ ሉያ አኀውየ ኀድግዎ ወመንንዎ ለዝ ዓለም። ኀድግዎ ወመንንዎ ለዝ ዓለም።

ዘይበሊ ወይስማን ወዒይከውን ቤዛ ለነፍስ። ኀድግዎ ወመንንዎ ለዝ ዓለም።

ኢታፍቅሩ ወርቀ ወኢብሩረ። ኀድግዎ ወመንንዎ ለዝ ዓለም።

ኢወርቅ ሤጡ ወኢብሩር ተውላጡ። ኀግድዎ ወመንንዎ ለዝ ዓለም።

## ንብረቱኒ ወፍትወቱኒ ኀላፊ ውእቱ

## ዕዝል ዘደብረ ዘይት

ሃሌ ሉያ አመ ዕለት ፍዳ ወአመ ዕለት ደይን አመ ዕለተ እግዚአብሔር ምንተ ንብላ ለነፍስ።

አመ ኢታድኅን እም ውሉዳ ወምድርኒኢ አመ ታገብዕ ማኅፀንታ። ምንተ ንብላ ለነፍስ።

አመ ይለብስ አብ ልብሰ ፍዳ ወያሞጥሕ ምጣሕተ በቀል ምንተ ንብላ ለነፍስ።

አመ ይወቅሰነ በግርምት ዓውድ አሜሃ ይትከሥት ወይሰጣህ ምግባራቲነ ወይትነበብ ኩሉ ዘገበርነ። ምንተ ንብላ ለነፍስ።

እንዘ ይነብር እግዚእነ ውስተ ደብረ ዘይት ቀርቡ ኀቤሁ ኩሎሙ አርዳኢሁ በዕለተ ሰንበት። ምንተ ንብላ ለነፍስ።

እምሔሶ ለሰብእ ሶበ ይምሕር ነዳየ ወይገብር ሠናየ።

## መዋሥዕት ዘፈላስያን

ትቤላ ነፍስ ለሥጋ ምድራዊት። አንቲ ለምንት ተሐንፂ አብያተ ኅበ ኢትነብሪ ለዓለም።

## ዝማሬ ዘመስቀል

መዓልተ በፅሙና ወሌሊተ በህሉና አንሰ ስእንኩ ለዛቲ ዓለም መጠና።

ንብረታኒ ሙስና ወብዙኅ ሐዘና። አንሰ ስእንኩ ለዛቲ ዓለም መጠና።

ዕፀ መስቀሉ ለወልድ ለነፍስየ ፀወና። አንሰ ስእንኩ ለዛቲ ዓለም ም እጠና።

ብፁዕ ውእቱ ዘመነና ይበልዕ ኅብስተ መና ወታስትዮ ቤተ ክርስቲያን እምወይና።

ከዜማ ወገን በቃሌ ያጠናኋቸው እነዚህ ናቸው።

ከዚህም በኋላ፤ የቅኔ ትምህርት ተማርሁ። ነገር ግን እኔ የተቀኘሁትን ቅኔ የምጽፍበት ጊዜ አላገኘሁምና የደጃዝማች ወልደ ገብርኤልን ቅኔ ጽፌላችኋለሁ።

## ሥላሴ

ዓለም እስከ ጊዜሃ፤ በሐብለ ዝንጋዔ ትስሐበነ፤

ወታወርደነ ካዕበ ኀበ ዘቀዳሚ መርገም፤
ለዘተወልድነ በሥጋ ወደም፤
ዘአእመራስ ማእምር ለባዊ ለኅልፈተ ዛቲ ዓለም፤
ፍዳ ወይን ይሰተይ ማየ ዝናም፤
ወህየንተ ልብስ ይትከደን ቈጽለ አዕዋም፤
እስመ ዛቲ ጽላሎት ወሕልም።

**መወድስ**

አወይ አወይ፤ ወይ እኔ ወይ እኔ።
የበደልሁህ በደል ጌታዬ ከሰማይ ኮከብ ይበዛ፤
ከምድር አሸዋም ቢቆጠር አያንስምና እምብዛ።
ወይ እኔኢ ሞኝ ሆይ ደንቆሮ ፈዛዛ፤
ሕያው አምላክ ሎዛ።
ስለ አዳም ብለህ በሸንጎ ከለሜዳ ለብሰህ ደምህ የተነዛ።
ዓለም ቆንጆ እያለችኝ
«ሕፃን እንጂ ነህ ወሬዛ።
ዛሬ ተጫውተን ነገር እንጽደቅ» መሰንቆ ሸንገላ በጣቷ ይዛ፣
ያንን ሸንገላ ሳደምጥ ዕድሜየኢ አለቀ በዋዛ፤
የመሔዴን ነገር ቁርጡን ሳውቀው ዳቦ ንስሐ ስንቄን ሳልገዛ።

ከዚህም በኋላ ይህን ቅኔ እያንጐራጐርሁ መንገዴን ሔድሁ።

## ምዕራፍ ፲

# ስለ ወይዘሮ ዓለሚቱ

በምሥራቅና በምዕራብ፤ በሰሜንና በደቡብ እየዞርሁ ይህን ዓለም (መጻሕፍትን) ስመለከት ድንገት መንገዴ አጠገብ ትልቅ አዳራሽ አገኘሁ።

ይህ አዳራሽ የማነው? ብዬ ብጠይቅ የወይዘሮ ዓለሚቱ ነው አሉኝ።

ከወይዘሮ ዓለሚቱ ጋራ በቃል እንተዋወቅ ነበረና በርሷ ቤት ለማደር ገባሁ።

እርስዋም የበክር ልጅዋን ምኞትን የምትድርበት ቀን ኖሮ እንዳጋጣሚ ሁሉ በድግስ ላይ ደረስሁ፤ እጅግም ደስ አለኝ።

አሳቤማ ወይዘሮ ዓለሚቱ በቃል ካወቀችኝ፤ መጣ ሲሏት ግባ በሉት ትልና ስበላ ስጠጣ አድራለሁ ብዬ ነበር።

ነገር ግን ቤተዘመዶቿ እነ ቅናት፣ እነ ምቀኝነት፣ እነ ተንኰል፣ እነ ሐሰት፣ እነ አቶ እንደ ጊዜው የነዚህም የልጅ ልጅ ሁሉ ያልታደመ ሰው እንዳይገባ ብለው በሩን የውጥር ይዘውታል።

ቢሆንም የድግስ ቀን ስለ ሆነ ሁሉም ሰክረው ግርግር ሲሉ ሹልክ ብዬ ገባሁ፤ ወደ ገበታው ቀርቦ ለመብላት ግን አልሆነልኝም። እንዲሁም ማለቴ ለወጉ ለማረጉ ነው እንጂ ለሆዴ ያህል ግን እንጀራውን ሲያነሡ ሲጥሉ የወደቀውን ፍርፋሪ እየለቀምሁ እጅግ ጠገብሁ።

ያ ወዳጄ ልቤም ከእኔ ጋራ ነበረና ወጥተን እንሒድ እንጂ ለማኝ ይመስል ፍርፋሪ ስንለቅም ልናድር ነውን አለኝ።

ምነዋ ወዳጄ ልቤ፤ ሞኝ ነህን ማየትም እንጂ አንድ ቁም ነገር ነው። ደግሞስ ያ ጳውሎስ የሚባል ሰው እንዳልበሉ ይሆናሉ ብሎ ያጫወተንን ነገር ዘነጋኸውን? ፩ ቆሮ. ፳፱ - ፴፩።

ይልቅስ መሰንቆህን እየከራከርህ ሠርገኞቹን አጫውታቸው አልሁት።

አሁን ሁሉም ሰክረዋል፤ ማን ሊሰማኝ ብዬ መሰንቆዬን አወጣለሁ አለ። ቢሰሙህ መልካም ነው ባይሰሙህ በነርሱ ይፈረዳል እንጂ ባንተ ይፈረዳልን አልሁት። ሕዝ. ፫፥ ፲፰ - ፲፱።

እነርሱ እንዳይሰሙኝ የታወቀ ነገር ነው። ነገር ግን ካዘዝኸኝ እሺ አለ።

# ምዕራፍ ፲፫

# ስለ አዝማሪው

ከዚህ በኋላ ወዳጄ ልቤ ልብሱን ታጥቆ መሰንቆውን አንግቶ ያጫውት ጀመረ።

አባቶች ሁሉ በልደቱ፣

ምን አጣላቸው በከንቱ።

የኔንስ ልቤን ያስጭነቀው፣

የኋላው ምጽአቱ ነው። ማቴ. ፳፭፥ ፴፩ - ፵፮።

የአዳም ልጆች ማደሪያቸው፣

መፍረሱ እንጂ ነው በላያቸው።

እንዲህ ወደ ዱር ገብተው፣

ቆርጠው ቢሠሩ ምነው። ማቴ. ፳፬፥ ፴፫።

አባቶቻችን በቅሎ ገዝተው፣

ኮርቻ ነበር አሳባቸው፣

የዛሬስ ልጆች እጅግ ኮሩ፣

ለመርገፉ ነው የሚጥሩ። የሐዋ. ፭፥ ፴፮ - ፴፯።

ሰናፍጭና ድንብላል፣

ምድራችን ሁሉ ያበቅላል።

በውስጡ ቆሜ ብመለከት፣

ጤናዳም አጣሁበት። ፩ ጴጥ. ፩፥ ፳፫ - ፳፬።

የቀድሞ ሰዎች ውኃ ዋና፣

ላይ ላዩን ነበር በጤና።

የዛሬ ልጆች ይበልጣሉ፣

ውስጥ ለውስጥም ይሔዳሉ። ኤርም. ፬፥ ፳፪።

አባቶቻችን እየሞቱ፣

ሳይቆረብ ነው የተፈቱ።

የኋላ ልጆች ጉድ አፈሉ፣

ከቁርባን ውጭም ይፈታሉ። ዕብ. ፲፥ ፳፱።

የዛሬ ዘመን ሙግት፣

ተጠየቅ ብሎ ሥራት።

አላውቅበትም በዚህ ነገር፣

ስለኔ ቆመህ ተነጋገር። ማቴ. ፲፥ ፲፱ - ፳።

ነገሩ እንኳ ለማሳየት፣

አውቅ ነበረ ጥቂት ጥቂት።

የምፈራውስ የማዝነው፣

በል ተቀጣ ሲሉኝ ነው። ዕብ. ፪፥ ፫።

ለወተትና ለወይን ጠጅ፣

መቼ እሑድ ነበር ከሰው ደጅ።

አሁን ግን ላንተ ነገርሁህ።

ማር እባክህን አልኩህ። መዝ. ፹፩፥ ፩፣ ፲፱።

ብዙ ቀን  ደከምሁ ባታክልት፣

የበሰለ ፍሬ ለመብላት።

አሁን ግን ሁሉም ደረቀብኝ፣

ወይኔ ብቻ ጸደቀልኝ። መዝ. ፻፬፥ ፲፭።

ዳዊት ገዝቼ ለመማር፣

ተስማምቻለሁ ባሥር ብር።

አሁን ግን እንጃ መማሬን፣
ወደ አምላኬ እንኳ መድረሴን። ፩ ቆሮ. ፬፥ ፫ - ፬።
    አለመንኩህም ላራዊት፣
ደግሞም ለእንስሳት።
የሰውን ነገር ምነው እኮ፣
ቦኑ ለከንቱ ፈጠርኮ። መዝ. ፹፰፥ ፵፯።
    የድኃ ድካም በያመቱ፣
ጥንት የቆየ ነው ካባቱ።
ሀብታሙ ስንኳ እንዳያርፍ፣
ከመ ጽላሎት የኀልፍ። መዝ. ፻፵፬፥ ፫ - ፬።
    ባልጋ መኝታ በጠፍር፣
መልካም ይመስለኝ ነበር።
አባቶቼ ግን ባያቸው፣
ሁሉም በመሬት ናቸው። ዘፍጥ. ፫፥ ፲፱።
    የተወለደ ካዳም፣
መሬት ያልገዛ የለም።
ግብሩን መገበር አቅቷቸው፣
ገና ብዙ ዕዳ አለባቸው። ዕብ. ፲፥ ፳፯።
ያባቶቼ ርስት ቀርቶብኝ፣
ጥቂት ስንኳ ባልቆጨኝ።
የስሞን መሬት ገዝቻለሁ፣
እየቆረብሁ እበላለሁ። ማር. ፲፬፥ ፳፪።
    ካልጠፉ ሁሉ ምድር፣

እንዴት ይገዟል የገባር።

በሔዋንማ በናታችሁ፣

ግንደ በል ነበራችሁ። ዘፍጥ. ፫፥ ፯።

ያባቶቻችን ፍቅር፣

በልባቸው ውስጥ ነበር።

የዛሬ ልጆች አጕሉት፣

በከናፍረ ጕህሉት። መዝ. ፲፱፥ ፱።

በእግዚአብሔር እድናለሁ፣

በእግዚአብሔር እሞታለሁ።

እርሱ ላያድን ላይገድል፣

ለምንት ይዜሐር ኃያል። መዝ. ፶፩፥ ፩።

ዕድሜ ስትሸጥ በስውር፣

ለተማመኑህ ነበር።

አሁን ግን እኔ ፈራሁኝ፣

በሰማኒያ ይሁንልኝ። መዝ. ፺፥ ፲ - ፲፩።

ለጠላቶቼ ጣፈጥኋቸው፣

ሥጋዬ ሆነ ምግባቸው።

ሰንጢውን ስለህ ስጥልኝ፣

እንዴት በጥርስ ይንጬኝ። መዝ. ፶፮፥ ፬።

ያባቶቻችን ቁርባን፣

ሥጋ መለኮት መድኀን።

ጠላቶቼ ግን ጉድ አመጡ፣

ሥጋዬን በልተው ደሜን ጠጡ። መዝ. ፷፰፥ ፳፩ - ፳፫።

ይህም ሁሉ ሲሆን ነገሩን የሚያዳምጠው አንድ ሰው ስንኳ አልነበረም። ወዳጄ ልቤም በዚህ ነገር ተቆጣና ያንተን ፈቃድ ልፈጽም ብዬ ነው እንጂ፣ ነገሬን የሚያዳምጥልኝ የለም ብዬህ አልነበረምን አለኝ። በዚህ ጊዜ ከቆሙት ሰዎች አንዱ ወደ ወዳጄ ልቤ ቀረበና፤ አሁን አንተ የምትመታውን ምት የሚያውቅልህ ሰው የለም። በዚህ የተቀመጡት ሰዎች ሁሉም ሰልፈኞችና ጀግኖች ናቸው። ስለዚህ ምቱን ለውጠህ ሰንጐ መገን፣ ተው ሰንጐ መንገ፤ ብትል እጅግ ደስ ይላቸው ነበር አለው።

የፈረስ ስማቸውን አላውቅ እንጂ ለዚህማ ምን ቸገረኝ ነበር አለው።

አቶ ቅናት የበለው ጌታ ይባላል። አቶ ተንኰልም የፍጀው ጌታ ይባላል። እነዚህን ሁሉ ሁለቱን ብቻ አሞግሳቸው እንጂ የቀሩት ከቁም ነገርም አይገቡ አለው። ይህንም ሲነጋገሩ ቅናት ሰምቶ ኖሮ ከሥርጉ ቤት ሹልክ ብሎ ወጣ። እኔም መቆታቱ ይሆንን ብዬ ፈራሁ። እርሱ ግን ሰንጐ መገን ሲባል መቼም መፎከር አይቀርም ብሎ የጦርነት ልብሱን ለብሶ መጣ። ከዚህ በኋላ፤ ወዳጄ ልቤ ደስ አለውና መሰንቆውን አንግቶ ከወዲህ ወዲህ እየተመላለሰ ተው ሰንጐ መገን፤ ተው ሰንጐ መገን፣ ቼ፤ ቼ፤ ቼ፤ ይል ጀመር።

ነቢያት ትንቢት ሲተነቡለት፣

አምላክም ደግሞ ሰው ሲሆን ቅጽበት፣

ሰብአ ሰገል ሲገብሩለት፣

የበለው ጌታ እንዴት ነህ ቅናት።

ድውያንንም የፈወሰ ለት፣

አልዓዛርም የተነሣ ለት፣

አምስት ሺ ሰው ያጸገበ ለት፣

የበለው ጌታ እንዴት ነህ ቅናት።

ዓርብ ተሰቅሎ ሲያወጣ ነፍሳት፣

እሑድ ማለዳም ሲነሣ ከሞት፣

ለሐዋርያት የታያቸው ለት፣

የበለው ጌታ እንዴት ነህ ቅናት።

በዚያ ጊዜ አቶ ቅናት ተነሣና ፈንዜውን በእጁ ፈንገጥ አድርጎ ይዞ ፉከራ ጀመረ።

ሀካኪ ዘራፍ፤ ሀካኪ ዘራፍ! እኔ የበለው ጌታ እኔ የበለው ጌታ፤ እኔ ያልተዋጋሁበት ዘመቻ ወዴት አለ! አዳምን ከገነት ያስወጣው ማነው! አቤልንስ ያስገደለው ማነው! እኔ የበለው ጌታ አይደለሁምን። ዘፍጥ. ፬፥ ፫ - ፲።

እንዲያውስ ከሙሴ እስከ ክርስቶስ የነበሩትን ነቢያትን የገደላቸው ማነው! ማቴ. ፳፫፥ ፴፫።

ሌላውስ ይቅርና ታላቁን ጀግና ክርስቶስን ሐሙስ ማታ ከዱር ውስጥ አውጥቼ ዓርብ በቀትር በንጨት ላይ አሰቅዬ ያስገደልሁት እኔ የበለው ጌታ ቅናት አይደለሁምን። ዮሐ. ፲፰፥ ፩ - ፴።

ደግሞ ለርሱ አሥራ ሁለት አሽከሮች ነበሩትና እነዚያን ሁሉ ወደ ሔዱበት ስፍራ እየተከተልሁ በሞት ያጠፋኋቸው እኔ አይደለሁምን፤ ይህም ሁሉ ሐሰቴ እንደ ሆነ እናንተ ሁላችሁም መስክሩብኝ።

እንዲያውስ እኔ ባልኖር የሲኦል መንግሥት ትጸና ኖሯልን።

አሁንም ወንድሞቼ ሆይ፤ ካይናችሁ ያውጣኝ ብሎ ተቀመጠ። ወዳጇ ልቤም አቶ ቅናት ሲፎክር ግድግዳውን ተጠግቶ ቆሞ ነበረና እርሱ ሲቀመጥ አይቶ መሰንቆውን አንግቶ እንደ ገና ተው ሰንጎ መገን ይል ጀመረ። ተው ሰንጎ መገን፤ እው ሰንጎ መገን፤ ቼ፤ ቼ፤ ቼ።

ታላቁ ጌታ ሲወለድ ባገር፣

ንጉሡ ሄሮድስ ድነግጦ ነበር፣

ኢየሩሳሌም እርዳ ነበር፣

ያገር ሕፃናት መች ያልቁ ነበር፣

የፍጇው ጌታ ተንኰል ባልነበር።

በዚያ ጊዜ አቶ ተንኰል ሰይፉን ውልቅ አድርጎ ይፎክር ጀመረ።

ሀካኪ ዘራፍ፤ ሀካኪ ዘራፍ። በቤተ ልሔምና በአውራጃዋ ያሉትን (ሕፃናት) ያስፈጃቸው ማነው። እኔ የፍጇው ጌታ አይደለሁምን። ማቴ. ፪፥ ፲፯ -፲፰።

እንዲያውስ ካቶ ቅናት በቀር በጦርነት ጊዜ የሚቀድመኝ ማነው። ዘወትርም በጦርነት ድል ማድረጌ ፊት ለፊት ተዋግቼ አይደለም። መሣሪያዬን ሰውሬ ይዤ ዱር ለዱር ስሔድ አድሬ ጧት በድንገት አደጋ እየጣልሁ ነው። አሁንም ካይናችሁ ያውጣኝ ብሎ ተቀመጠ።

ይህም ሁሉ ሲሆን ለአዝማሪው እስኪ አንድ ዋንጫ ጠጅ ስጡት ብሎ የሚናገር አልነበረም።

በዚያ ጊዜ ወዳጄ ልቤ ቆጬውና ወደኔ ቀርቦ አቶ ተንኰልን ላዋርደው አለኝ።

ቢመታህሳ አልሁት።

አስቄበት የሆነው ይሁን አለ።

አንተ እንደ ወደድህ አድርግ፤ እኔ ግን ውርድ ከራሴ ነው አልሁት።

ከዚህ በኋላ ቃሉን ከፍ አደረገና አቶ ተንኰል ያንተም ግዳይ ከግዳይ ተቆረጠና ትፎክራለህን አለው። በዚያም ጊዜ ሁሉም ዝም ብለው ይሰሙ ጀመረ። ተንኰልም በኀፍረት ቃል እንዴት አንተ አለው። በቤተ ልሔም ገደልሁ በልህ የፎከርከው ገና ጡት የሚጠቡትን ሕፃናት ከናቶቻቸው እጅ እየቀማህ አይደለምን አለው።

ለካ ሁሉም በዚህ ነገር ሆድ ለሆድ ሲተማሙ ቆይተው ኖረው ዳር እስከ ዳር ከት በለው ሳቁበት።

አቶ ተንኰልም እጅግ አፈረ። ወዳጄ ልቤ ግን አቶ ተንኰልን ፈራና እስኪነጋ ድረስ ድምጡ ሳይሰማ አደረ።

## ምዕራፍ ፲፯

# ስለ ንጉሥ መልእክት

ከዚህም በኋላ እነጋጋለሁ ሲል ከበር ውጭ ጩኸትና ፍጅት ሆነ። ሠርገኞችም እድመኞችም ከወዲያ ወዲህ ይራወጡ ጀመር።

እኔም ባለሁበት ሥፍራ ቆሚኤ እየተንቀጠቀጥሁ ወደ ወይዘሮ ዓለሚቱ ቤትም የገባሁበትን ቀን ረገምሁ። ከሙሽሮቹም አንዱ ወደ ወይዘሮ ዓለሚቱ ሲሮጥ ሔደና እመቤቴ ሆይ፤ ጉድ ፈላብን አላት።

እንዴት አለችው።

አንቺን ያሳደገሽ እግዚአብሔር የሚባለው ታላቁ ንጉሥ ተቆጥቶብሻል መሰለኝ አላት። ዘፍጥ. ፩፥ ፩።

ምንስ ቢሆን ያሳደግኋት ጌታዋ እኔ አይደለሁምን። የመጀመሪያ ባሏ አዳም እንኳ አታክልት ሲሰርቅ ተይዞ በታላቁ ወህኒ በሲኦል ቢታሠር፤ የእኔ ልጅ ዕዳውን ከፍሎ አስፈታው። ፩ ጴጥ. ፩፥ ፲፰።

እርሷንም እንዲህ እንዳላየ ማየቴ ምን አልባት ብትመከር ዘመዶችዋንም ብትመከር ብዬ ነበረ እንጂ፤ እንግዲያውማ ባንድ አፍታ ድራሽዋን ለማጥፋት እችል አልነበረምን። ሉቃ. ፩፥ ፴፯።

ምንስ ልጅዋ ቢሆን ጠላቴን ምኞትን በከተማዬ እንደ ምን ትረዳው። ወዳጆቼን ሁሉ የገደለ የርሷ ልጅ ምኞት አይደለምን።

አሁንም ወደ ዓለሚቱ ቤት የገቡትን እድመኞችንና ሠርገኞችን ሙሽሮቹንም ይዛችሁ አምጡ ብሎናል ብለው ሞትና መቃብር መጥተዋል አላት።

ብቻቸውን ናቸውን አለችው።

ደግሞ ብቻቸውን። ኧረ እልፍ አእላፋት ወታደሮች አስከትለው ነው አላት።

ስማቸውን ታውቀዋለህን አለችው።

ዋና ዋናቹን አውቃቸዋለሁ አላት።

እነማን ናቸው አለችው።

እነ ቁርጠጥ፣ ቁርጥማት፣ ፍልጠት፣ም ምች፣ ውጋት፣ ተስቦ፣ መጋኛ ንዳድ፣ ፈንጣጣ፣ ኩፍኝ፣ ቂጥኝ፣ ጨብጥ፣ ቁምጥና፣ ሳል፣ ያይን ሕመም፣ የልብ ሕማም ሌሎችም ብዙ አሉ አላት።

እርስዋም እያጉረመረመች ወደ ቤትዋ ገባች። እነዚያ ወታደሮች ግን ወደ ሠርጉ ቤት ገብተው ከሠርገኞች ወገን አንዱንም ሌላውንም እየያዙ ለሞት ይሰጡ ጀመሩ።

ሞትም ለመቃብር እያሳለፈ ይሰጥ ጀመረ።

መቃብርም ከያዘ የማይለቅ ጽኑ ጀግና ነበረ።

ይህም ሁሉ ሲሆን ሠርገኞች በር ዘለን ቅጥር ጥሰን እንሸሽ ብለው አያስቡም ነበር።

አንዳንዱስ እንዲያውም ይስቁ ነበሩ።

እንዲህምስ ሲስቁ እያንጠለጠሉ ይወስዱዋቸው ጀመር። መዝ. ፸፫፥ ፴ - ፴፭።

ነገር ግን የወይዘሮ ዓለሚቱ ቅጥር ግቢዋ ሰፊ ነበረና ታዘው የመጡት ወታደሮች ሠርገኞቹንና አድመኞቹን ሁሉ ባንድ ጊዜ ጨርሶ ለመያዝ አልሆነላቸውም።

አንዳንድ ከተያዙ በኋላ፤ እየተለማመጡ ተለቀቁ። ነገር ግን የኋላ ኋላ ወደ ዓለሚቱ ሠርግ የታደመ ሰው ሁሉ ተይዞ መታሰሩ አይቀርም። ወደ ሠርጉም የመጡትን ሰዎች ሁሉ ንጉሡ በሺወርኒ አስቆጥሯቸዋል ይባላል።

እኔና ወዳጄ ልቤም ለጊዜው ሳያንዝ ከወታደሮቹ አመለጥን።

## ምዕራፍ ፲፯

# ስለ ማቴዎስና ስለ ሉቃስ፤ ስለ ሙሴም ጨዋታ

ከዚህ በኋላ ወደ ምሥራቅ ዞርሁ። በዚያም ማቴዎስ የሚባል ሰው ቤቱን በሀገር መዳረሻ ሠርቶ አገኘሁ። እኔም ወደ ቤቱ ሔጄ ጌታዬ ሆይ፤ እባክህ አሳድረኝ አልሁት።

እደር አለኝ። ማቴ. ፳፭፥ ፴፭።

ጥቂትም እንደ ቆየን ሉቃስ የሚባለው ባልንጀራው መጣና ጨዋታ ጀመሩ።

ሁለቱ ሲጫወቱ ቃላቸው አንድ ነው። ግን የሉቃስ ቃል ትንሽ ረዘም ይላል። ሉቃስም ንግግሩን ጀመረ። ወንድሜ ማቴዎስ ሆይ፤ ያ ባለ ጠጋ እንዲያ ሲቀማጠል ኖሮ ሞተ፤ ግን በሞተበት ቀን ሰው ሁሉ ደስ አለው እንጂ አንድ ሰው እንኳ አላለቀሰለትም አለ። ሉቃ. ፲፮፥ ፲፱ - ፳፬።

ማቴዎስ መለሰ፤ ወንድሜ ሉቃስ ሆይ፤ ድኃ መሆን ምንኛ መልካም ነው ይመስልሃል አለ። ማቴ. ፭፥ ፫።

ይህንስ እኔም ብዬ ነበረ አለ። ሉቃ. ፮፥ ፳፬።

ከዚህም አያይዘው ያለሚቱን ነገር አነሡ።

ማቴዎስ ጀመረ። ንጉሡ ተቆጥቶ ወደ ዓለሚቱ ቤት የገቡትን ሠርገኞቹን ሁሉ አሲዞ ወሰዳቸው ሲሉ ሰማሁ። እንዲያውም እስከ እርስዋ ድረስ ተይዛ ልትጋዝ ነው ብሎ የንጉሡ ልጅ ነገረኝ አለው። ማቴ. ፳፬፥ ፴፫።

ሉቃስ መለሰ፤ እርስዋ ተይዛ ብትጋዝ እጅግ መልካም ነገር ነው። ሉቃ. ፲፮፥ ፲፯።

ስንት ሰዎች ያበላሸች ይመስልሃል። የጳውሎስ አሽከር ዴማስ የሚባለው አንድ ቀን ወይዘሮ ዓለሚቱን ቢያይ ጌታውን ትቶ ወደ እርስዋ ነጐደ። ፪ ጢሞ. ፬፥ ፲።

የወይዘሮ ዓለሚቱን ነገር ስንቱን ልንገርህ የርሷንስ ነገር ወንድማችን ዮሐንስ ይንገርህ። እርሱ ጥቂትስ ስንኳ አይፈራትም ነበረ። ሳትታሰሪ የቀረሽ እንደ ሆነ ምን አለ በዪኝ ይላት ነበረ። ዳግመኛ ሰው ሁሉ እንዳይወዳት የመከርባት ነበረ። ፩ ዮሐ. ፪፥ ፲፭ - ፲፯።

ማቴዎስ መለሰ፤ የርሷስ ነገር መቼም አንድ ጊዜ የታወቀ ነው ኧረ ደግሞ ይህ የርስዋ ዲቃላ ምኞት እንዲህ አድርጐ የጠገበበት ምክንያት ምንድር ነው። የሰው ሚስት ያየ እንደ ሆነ በላይዋ ልሙት ይላል። መልካም ፈረስ መልካም በቅሎ ያየ እንደ ሆነ የኔ በሆኑ ይላል።

እገሌ ተሾመ ሲሉ የሰማ እንደ ሆነ ምነው እኔ በሆንሁ ይላል። ከቶ የርሱ ነገር ብልሃቱ ጠፋኝ አለ። ማቴ. ፭፥ ፳፰።

ሉቃስ መለሰ፤ ይህ ይደንቅሃልን ወደ ድግስ ቤት የጠሩት እንደ ሆነ ከርሱ የሚበልጡ ብዙ ሽማግሎች ሳሉ ወደ ላይ ወጥቶ በመጀመሪያው ወንበር ይቀመጣል። ኋላ ግን ያ የጠራው ሰው መጥቶ እየጐተተ አውርዶ በታችኛው ወንበር ያስቀምጠዋል አለ። ሉቃ. ፲፬፥ ፰ - ፲።

ይህንንም ሲጫወቱ የምዕራብ ሀገር ባላባት ሙሴ መጣ፡ ምን ትጫወታላችሁ አላቸው።

አንድ ጥጋበኛ ሀገር አዋኪ ምኞት የሚባል ሰው አለና የርሱን ነገር እንጫወታለን አሉት።

ሙሴ መለሰ፤ ኸኸ፤ እርሱ ነውን፤ ኧረ ገና እርሱንማ አውቀው የለሞይ። ነገሩን ሁሉ በደንጊያ ጽፌ አኑሬዋለሁ። ይህንኑም ለእስራኤል ዕለት ዕለት አነበላቸው ነበረ። ዘጸ. ፳፥ ፲፯።

ዳግመኛ እርሱ ብቻ አይምሰላችሁ። ሌሎችም ዘጠኝ ባልንጀሮች አሉት። ዘጸ. ፳፥ ፩ - ፲፯።

ስማቸውም ከዚህ እንደሚከተለው ነው።

ጣዖት ማምለክ፣ ለጣዖት መስገድ፣ የእግዚአብሔርን ስም ከንቱ ማድረግ፣ ሰንበትን መሻር፣ አባትና እናትን ማዋረድ፣ መግደል፣ መስረቅ፣ መሴሰን፣ ባሰት መመስከር፣ እነዚህንም ሁሉ የሚመክርና የሚያበረታ ምኞት ነው አለ።

እኔም ከሙሴ ጋራ እጅግም አልተዋወቅም ነበረና ስፈራ ስቸር ጌታው አቶ ሙሴ ምኞት ከዚህ ሀገር የሚሔድበትን ጊዜ የለምን አልሁት።

ሞኝ ነህን እናቱ ወይዘሮ ዓለሚቱ ካልሞተች እሱ ወዴት ይሔዳል አለኝ።

እንኪያስ እርሱ ወደ ሌለበት ሀገር መሔድ ይሻላል አልሁት።

ሙሴ መለሰ፤ ዛሬ ገና ያልሰማው መጣ፤ ሌላውስ ይቅርና ወደ ገነት ገብቶ እናታችን ሔዋንን ከእግዚአብሔር ጋራ ያጣላት ማን መሰለህ። ምኞት አይደለምን። ዘፍ. ፫፥ ፮።

እባብ መጥታ ያንን ቅጠል ብዩ እያለች ለሔዋን ስትመክር ምኞት በዚያ ባልነበረ ትበላው ኖሯልን። ምን ይሆናል ቀረና የርሱንስ ነገር አለማንሣቱ ይሻላል።

ማቴዎስ መለሰ፤ ምኞትን ጉድ ያደረገው የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ብቻ ነው እንጂ አለ።

እንደምን አልሁት።

በገዳም ተቀምጦ አርባ ቀን አርባ ሌሊት በጾም ጊዜ ሰይጣን የወይዘሮ ዓለሚቱን ገንዘብ ሁሉ ይዞ መጣ። ምኞትም ከርሱ ጋራ ነበረ።

ምኞት ከሰይጣን ጋራ መምጣቱ ክርስቶስ ይህን ገንዘብ አልቀበልም ያለ እንደ ሆነ ይህን ሁሉ ገንዘብ እንዴት ትመልሳለህ። ኧረ ተቀበል ብሎ ለመምከር ነበረ። ማቴ. ፬፥ ፰።

ክርስቶስ ግን የሁለቱንም አሳብ ያውቅ ነበረና ገና ሲመጡ በሩቅ ባያቸው ጊዜ ከሙሴ እጅ አንድ በትር ነጠቀና አበረራቸው፡

በዚያ ጊዜ የሰይታንን ሩጫ ያየ ሰው ከመቅጽበት ዓይን እልም ብሎ ጠፋ። ምኞትም ከዚያ የበረረ ዓለሚቱ ቅጥር ደረሰ አለኝ። ማቴ. ፬፥ ፩ - ፲፩።

ለምኞት የደረሱ ልጆች አሉትን አልሁት።

እንዴታ። ነገር ግን ዲቃሎች ናቸው እንጂ ከሚስቱ አይደሉም አለኝ።

ስማቸውን ታውቀዋለህን አልሁት።

እኔ አላውቅም ግን ከሀገራቸው የመጣ ሰው ጳውሎስ የሚባለው ያንደኛውን ስም ሆስ አምላኩ ሲል ስምቻለሁ። ፊሊጵ. ፫፥ ፲፱።

ደግሞ የሁለተኛውን ስም ወንድሜ ሉቃስ ያውቀው ይሆናል። እውን ወንድሜ ሉቃስ ሆይ፤ የምኞት ልጅ የሆድ አምላኩ ታንሽ ወንድም ማን ይባላል አለው።

ሉቃስ መለሰ፤ እንዲህ የምትጨነቁት የርሱ ስም ጠፍቷችሁ ነውን። ልጅ ሰብስቤ የሚባለው አይደለምን አለ። ሉቃ. ፲፪፥ ፲፯ - ፳፩።

ሴት ልጅሳ የለችውምን አልኋቸው።

ማቴዎስ መለሰ፤ እርስዋንስ ዱሮ ቀራጭነት ተሾሜ ሳለሁ ወደ ገበያ እየመጣች አውቃታለሁ አለ።

ማን ትባላለች አልሁት።

አለማፈር ትባለለች፤ አክስቷ ግን ድፍረት ትላታለች አለኝ። ኸኸ፤ እርስዋ ናትና እርስዋማ ያቶ እንደ ልቡ ሚስት አይደለችምን። ያቶ እንደ ጊዜው ሚስት ወይዘሮ ሽውሽው ታላቅ እኅቷ ነበሩና ወደ እርሳቸው ስትሔድ አንድ ቀን በመንገድ አግኝቻታለሁ። በርስዋ ልክ ሰነፍ አይገኝም።

ባሏ አቶ መከለፍለፍ እንጀራ ሳያልፍለት ይኖራል። እንዳይፈታትም የሕግ ሚስቱ ስለ ሆነች አልቻለም አልሁት።

ማቴዎስ መለሰ፤ ኧረ ወዲያ፤ የሕግ ሚስቱ ብትሆን ከራሱ ትብሰበታለችን። እኔስ የሚጐዳኝ ከሆነ ቀኝ እጅጄም፣ ቀኝ እግሬም ቀኝ ዓይኔስ ቢሆን ምን ያደርግልኛል። ሞኝ ነህን፤ ይልቅስ የመከርኩህን አትርሳ።

ጌታዬ ማቴዎስ ሆይ፤ ካንተ ጋራ ብዙ ቀን ተቀምጦ መጫወት እጅግ መልካም ነበረ። ነገር ግን ወዳጄ ልቤ ዘመዶቹን ናፍቋልና ስለዚህ ወደ ሀገሬ ለመሔድ እቸኩላለሁ ጤና ይስጥልኝ፤ ወደ ፊት በደኅና ለመገናኘት ያብቃን ብዬው መንገዴን ሔድሁ።

# ምዕራፍ ፲፰

# ስለ ወዳጇ ልቤ ቁጣ

ከዚያም ጥቂት እንደ ሔድን ወዳጇ ልቤ ተቆጣና ቆም ብሎ አንድ ጊዜ ስማኝ ልንገርህ አለኝ።

እኔም እስቲ ተናገር አልሁት።

እንግዴህ አንተ ካገኘኸው ሰው ሁሉ ጋራ ስትቆምና ስትጫወት ጊዜው በከንቱ ሊያልቅ አይደለምን።

ብትወድ የመጣህበትን ነገር በቶሎ ጨርሰህ ወደ ሀገራችን እንመለስ።

አንተ በስም የንጉሡ ልጅ አሽከር ትባላለህ፤ ነገር ግን አንድ ቀን ስንኳ እርሱን ተከትለህ አገልግለኸው አታውቅም። በድንገት አስጠርቶ አገልግሎትህን ቢጠይቅህ ምን ልትመልስለት ይሆን። ሀገር ላገር እየዞርህ ይህን አየሁ ይህን ሰማሁ ብትል ከቁም ነገር የሚቆጥርልህ ይመስልሃልን። ሮሜ. ፪፥ ፲፫።

ይልቅስ ጋሻ ጦርህን ይዘህ ጌታህን ብትከተል መልካም ነበረ።

ነቢያትና ሐዋርያት፤ ጻድቃንና ሰማዕታት ሰፊ ሀገር እየተሾሙ መኖራቸው ጌታቸው ቢያገለግሉ አይደለምን፤ አሁም አንተ ጌታህን አገልግለው።

ዛሬ አሽከር ቸግሮታልና ደስ ያሰኘው እንደ ሆነ አንድ ርስት ሳይተክልህ አይቀርም።

ሲኦል ወርዶ ጢሰኛ ሁኖ ከመቀመጥ ደጅ ጠርቶ ርስት መተከል አይሻልህምን። ወይስ በሲኦል የሚኖሩ ጢሰኞች ባመት ባመት የሚገብሩትን ግብር አታውቅምን።

ያንዱ ሰው ግብር እሳት፣ ጨለማ፣ የማይሞት ትል፣ ጥርስ ማፋጨት፣ ልቅሶ ነው። እስኪ አስትውለው አንድ ሰው ሰው ባመት ይህን ያህል እየገበረ መኖር እንደ ምን ይችላል። ማቴ. ፲፫፥ ፵፪።

እኔ ይህን ያህል ዘመን ካንተ ጋራ መንከራተቴ ስንቅህን የሚሸከምልህ ሰው አታገኝም ብዬ ነው እንጇ ትቸህ እሔድ አልነበረምን። አንዳንድ ቀን እንኳ የተለየሁህ እንደ ሆነ ችጋር ይዞህ ይውላል። ድካሜ ሁሉ ላንተ ብዬ ነው እንጇ ለራሴ ምንም አላስብም። እንግዲያውማ ላቶ እንደ ልቡ አሽከር ብሆን አንድ ትልቅ ጥቅም ሳላገኝ የምቀር ኑሯልን። ከዋልሁ ካደርሁም ዘንድ ልጇቸውን ወይዘሮ ክፋትን ይድሩልኝ ነበር።

አሁንም ቁርጡን ንገረ፤ ከዚያ ወዲያ የማደርገውን አደርጋለሁ አለኝ።

እኔም በትህትና ቃል ወዳጄ ልቤ ሆይ፤ ያላንተ ምን ዘመድ አለኝ፤ ከቤቴም ስነሣ አንተን ተማምኜ እንጂ አንተ አይዞህ ባትለኝ ጥንቱንም አላስበው ነበረ።

አሳቤም ይህን ዓለም (መጻሕፍትን) በምሥራቅና በምዕራብ፣ በሰሜንና በደቡብ፣ ለማዞር እንደ ሆነ ታውቃለህ። አሁን ግን ከተቆጣህ ይቅርብኝ። እኔም ባስበው ይህን ዓለም እስከ ሞቴ ቀን እንኳ ብዞር የምጨርሰው አይመስለኝም። በውነትም አንተ እንደ ነገርከኝ አንዳንድ ቀንም ቢሆን ጌታዬን ማገልገል ይሻለኛል።

ነገር ግን በምሥራቅ ሀገር ያየናቸውን ሀገሮች ስማቸውን እየጻፍን ወዲያውም ዛፉን፣ ተራራውን እያየን ወዳጆቻችንንም ሁሉ እየተሰናበትን ወዳገራችን እንመለሳለን።

ደግሞ አንድ ነገር ልንገርህ። እኔ ለኑሮ የምሥራቅን ሀገር መርጫለሁ። ለምቾትማ የምዕራብ ሀገር ይመቻል። ግን ሰዎቹ ወሬ ያበዛሉ።

በሰሜን ሀገር መኖር መልካም ነበረ። ግን ሰዎቹ ሁልጊዜ ይጣላሉ። ዘወትርም እንደ ተካሰሱ ይኖራሉ።

በደቡብም ሀገር መኖር መልካም ነበረ። ግን የደቡብ ሀገር ሰዎች ከእውነተኞቹ ሐሰተኞቹ ይበዛሉ።

በምሥራቅም ሀገር መኖር ግን ምንም ሀገሩ አስቸጋሪና አድካሚ ቢሆን ሰዎቹ እጅግ መልካሞች ናቸው። ነገራቸውም አጭርና እውነት ነው።

ዳግመኛ ብዙ ወዳጆች አለኝና ሀገሩ ባይመቸኝ ስንኳ ስለ ወዳጆቼ ብዬ በምሥራቅ ሀገር ለመኖር አስቤአለሁ አልሁት።

ወዳጄ ልቤኢ መለሰ፤ ይሁን መልካም ነው፤ አንተንማ አንድ ስፍራ ከያዝህልኝ፤ እኔስ ለምን እለይሃለሁ። የሚያስቆጣኝና የሚያበሳጨኝ ይህ ሀገር ላገር መዞርህ ነው እንጂ አንድ ሥፍራ መያዝህን መቼ እጠላለሁ። አሁንም ያሰብኸውን አድርግ አለኝ። ወዳጄ ልቤ ሆይ፤ ሁልጊዜ እኔ አስቀይምሃለሁ እንጂ አንተ አስቀይመኸኝ አታውቅም። እግዚአብሔር ይባርክህ፤ የቀናውን መንገድ ይምራህ አልሁትና መንገዳችንን ሔድን።

## ምዕራፍ ፲፱

# ስለ ትልቅ አዳራሽ

በምሥራቅ ሀገር ጥግ ጥጉን ስሔድ አንድ ታላቅ አዳራሽ አየሁና ቶሎ ብዬ ወደዚያ ሔድሁ። በስተውጭም እጅግ ያማረ ነበረና ገብቼ ለማየት ቸኰልኩ።

ነገር ግን ወደ በር በደረስሁ ጊዜ ምናልባት በረኛ ይኖራል ብዬ፤ ደጅ ሰላሙን ለመግባት ስለ ፈራሁ አንድ ሰዓት ያህል ተቀመጥሁ። ቢሆንም ግባ የሚል ወይም ተመለስ የሚል አንድ ሰው ስንኳ አልነበረምና ወደ አዳራሹ ቀረብሁ። አዳራሹም ተቆልፎ ነበረ። በዚህ ነገር ተጨንቄ ሳለሁ ከወደ ጓሮ አንድ ብላቴና መጣ።

ማን ትባላለህ አልሁት፤

መልካም አሳብ እባላለሁ አለኝ።

ይህ አዳራሽ የማነው አልሁት፤

የንጉሡ ልጅ የክርስቶስ ነው አለኝ።

ለምን ጉዳይ ብሎ ሠራው አልሁት፤

ለልብስ ማጠቢያና ለመሣሪያ መስቀያ ብሎ ነው። በስተ ውስጡ ሁለት ክፍል አለው። ባንድ ወገኑ ከሰይጣንና ከአይሁድ ጋራ የተዋጋበት የጦር መሣሪያ ተሰቅሎበታል። በሁለተኛውም ወገን አሽከሮቹ ልብሳቸውን ያጥቡበታል አለኝ። ራእ. ፯፥ ፲፫ - ፲፬።

የጦር መሣሪያው ጥሩ ጥሩ ነውን አልሁት። እንዴታ፤ ግን ከባድ ከባድ ነው፤ ክርስቶስ ኃይለኛ ነበርና ሁሉንም ይዞ ተሰልፎ ነበረ እንግ ሌላ ሰውስ ቢሆን አንዱን መሣሪያ ስንኳ ይይዞ ሊሰለፍ አይችልም ነበር አለኝ።

የጦር መሣሪያው ስንት ነው አልሁት። እኔ የማውቀው አሥራ ሰባት ይሆናል። ቁጥሩም ከዚህ እንደሚከተለው ነው፡

እሥራት፣ ስድብ፣ ጥፊ፣ ግርፋት፣ የሾህ አክሊል መስቀል፣ ችንካር፣ ምራቅ፣ በትር፣ ልግጫ ሐሞት፣ መራራ፣ ራቁትነት፣ ውኃ ጥም፣ ሞት፣ በጦር መወጋት፣ መቃብር፣ ስሙን የማላውቀው ሌላም ብዙ መሣሪያ አለ አለኝ። ማቴ. ፳፯፥ ፩ - ፳፰።

ክርስቶስ ከአይሁድና ከሰይጣን ጋራ ሲዋጋ፤ ይህን ሁሉ የጦር መሣሪያ ይዞ ነውን አልሁት።

እንዴታ። ያውስ አንድ ሰዓት ብቻ ነውን፤ ከአሙስ ማታ ጀምሮ እስከ አርብ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ ነው እንጂ አለኝ።

ይህንም ከነገረኝ በኋላ ወደ መጣበት ዘወር አለ።

እኔም ወደ አዳራሹ ውስጥ ገብቼ መሣሪያውን ሁሉ ለማየት አሰብሁ፤ እንገር ግን በሩ ተቆልፎ ነበርና ደጅ ብመታ የሚከፍትልኝ አላገኘሁም።

ከዚህም በኋላ በራሴኢ እውቀት የሚባል መክፈቻ ነበረኝና ተኪሴ አውጥቼ ወደ ቁልፉ ውስጥ አግብቼ በል ና ተከፈት እያልሁ እታገል ጀመርሁ። ነገር ግን ብደክም ማን ፍንከች ይበል።

ያ መልካም አሳብ የሚባል ብላቴና በሩቅ ቆሞ ይመለከተኝ ኑሮ ሲሮጥ ወደኔ መጥጦ ምነው ምን ያለህ ደፋር ነህ፤ በሌላ መክፈቻ እከፍታልሁ ብለህ እንዴህ ስትታገል ይህ ቁልፍ ቢሰበር እንዴት ልትሆን ኖሯል? ዘበኞች አግኝተውህ ቢሆን እጅህን አጠልጥለው ወደ ግዞት ይሰዱህ ነበረ። አሁን አንተ ቁልፍህን ሌላ ሰው ቢከፍተው ወይም ቢሰብረው ታንቄ ልሙት ትላለህን፤ አሁንም የቁልፉን መክፈቻ የያዘው መንፈስ ቅዱስ ነውና እርሱ መጥጦ ካልከፈተልህ እገባለሁ ብለህ አታስብ፤ ከቶ ብታስብም አይሆልህም አለኝ። ዮሐ. ፲፬፥ ፳፯።

ይህንም ስንነጋገር የእኔን መክፈቻ ወደ ቁልፉ ውስጥ እንዳገባሁት ነበረና ሳላወጣው ያ መንፈስ ቅዱስ ከተፍ ማለት ነዋ።

በዚያ ጊዜ ምን ይዋጠኝ። እጄን እያርገበገብሁ፤ አይቴኑ አሐውር እመንፈስከ። ወአይቴ እጐይይ እምቅድመ ገጽከ። እመኒ ዓረጉ ውስተ ቀላይ ህየኒኢ ሀሎከ። ወእመኒ ነሣእኩ ክንፈ ከመ ርግብ። ወሰረርኩ እስከማኅለቅተ ባሕር። ህየኒ እዴከ ትመርሐኒ ወታነብረኒ የማንከ። መንክር ግብርከ ወነፍስየ ጥቀ ትጤይቆ። ወታነብረኒ እምኔከ አዕፅምትየ ዘገበርኮ በኅቡዕ። ወኢአካልየ በመትሕተ ምድር። ወዘሂ ገበርኩ ርእያ አዕይንትየ እያልሁ መቀባእር ሆነ። መዝ. ፻፴፱፥ ፯ - ፲፯።

እኔ ፈርቼኢ እንዲህ ተጨነቅሁ እንጂ እርሱ ግን ጥቂስትስ እንኳ ክፉ ነገር አልተናገረኝም።

በመክፈቻዬም አውጥቶ ጥሎ በርሱ መክፈቻ ከፍቶ አስገባኝ።

በገባሁም ጊዜ አንድ ነጭ በግ ታርዶ፤ በሳንቃ እንቸት ላይ ወድቆ አየሁ። ብዙ ሰዎችም ልብሳቸውን እያወለቁ በደሙ ያጥባሉ ደሙም ሳያቋርጥ ይወርዳል። ልብሳችወን ሲነከሩት ለጊዜው ደም ይመስላል። ጠምዝዘው ሲያወጡት ግን ከበረዶ አሥር ጊዜ ይነጣል። ያነንም ይለብሱና ከተሰቀለው የጦርነት መሣሪያ አንዳንድ እየያዙ ይወጣሉ። አንዱ አጥቦ ሲወጣ ሌላው ይገባል።

እጅግም ተደነቅሁ፤ ለመንገዴ ባልቸኰልሁ እነርሱን ስመለከት በኖርሁ ነበረ።

ባዳራሹም በስተቀኝ በኩል በመዘወር ገብቶ የሚፈስ ውኃ አየኹ። የጥሩነቱ ነገር እጅግ ያስደንቃል። በስተላይም ወገን ከዚህ ውኃ የሚጠጣ ለዘላለም አይጠማም የሚል ጽፈት ተሰቅሎ ይታያል። ዮሐ. ፬፥ ፲፬።

እኔ ግን መቅጃ አልነበረኝምና በእፍኜ እየዘገንሁ ፉት ፉት አድርጌ ወጣሁ።

## ምዕራፍ ፳

# ስለ ትልቅ ኃዘን

በዚያም ወራት አንድ ቀን ከቀትር በኋላ ባንድ ስፍራ ተቀምጬ አንገቴን ከጉልበቴ ጋራ እያስታገልሁ አዝን ጀመርሁ።

ወዳጄ ልቤም ወደኔ ቀርቦ ምነው ዛሬ እንዲህ አድርገህ አዝነሃል አለኝ።

ወደ አዳራሹ ውስጥ በገባሁ ጊዜ የውኃ መቅጃ ባለመያዜ እየተናደድሁ ነው አልሁት።

ተጠምተሃልን አለኝ።

መጠማትስ አልተጠማሁም። ነገር ግን ውኃ መቅጃ በነበረኝ እኔም በብዙ እጠጣ ነበር። ደግሞ በመቅጃው ይዤበት እወጣ ነበር አልሁት።

አንተን ካልጠማህ ለማን ብለህ ይህን አሰብህ አለኝ። ሞኝ ነህን፤ አሁን ባልጠማ ሌላ ቀን መጠማቴ ይቀራልን፤ ደግሞስ ስንቱ ጐረቤቶቼ በውኃ ጥም ይተላለቁ ይመስልሃል። ከዚያ ውኃ ቀድቼ በነጋኸውን ያ ባለጠጋ ዘመዳችን ንጉሡ አስጠርቶት በሔደ ጊዜ ስለ በረሃው ጽናት ውኃ ጥም ይዞት አንድ ጠብታ ውኃ የሚያቀምሰኝ ሰው ባገኘሁ እያለ ሲያለቅስ ወድቆ አልቀረምን። ሉቃስ. ፲፮፥ ፳፬።

የዚህ ነገር ትዝ እያለኝ ብዙኀ አዘንሁ አልሁት።

ወዳጄ ልቤም ይህን ስነግረው ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። እንባውም በጉንጩ ይወርድ ጀመር።

ወዳጄ ልቤ ሆይ፤ ስለ ምን ታለቅሳለህ፤ አሁን በነገርሁህ ነገር ነውን፤ ወይስ ሌላ ትዝ ነገር ትዝ ብሎህ ነው አልሁት።

ሌላ ነገር ትዝ ብሎኝ አይደለም። ነገር ግን የባለጠጋውን ነገር ብታነሣ የወደቀበት ሥፍራ ትዝ አለኝና ነው።

እንዴት ያለ ነው አልሁት።

ስፍራውም እጅግ በረሃና ጒድጓዳ ስለ ሆነ መሬቱ እንድ እሳት ይግላል። የፀሐይ ሙቀት ሲፋጅ ፀሐይ ቦታዋን ለቃ (ትታ) የወረደች ይመስላል።

ዳግመኛ የምድር አራዊት ሁሉ እባብም፣ ዘንዶም፣ ጊንጥም፣ በየመንገዱ ዳር ተጋድመው የሰን እግር ይጠብቃሉ።

በዚያ መንገድ የሚሔዱ ሰዎች ሁሉ ምላሳቸው በውኃ ጥም ይታሠራል። ጥርሳችውንም ያፋጫሉ። ወዲያም ወዲህም ቢመለከቱ አይዟችሁ የሚል አንድ ሰው ስንኳ አያገኙም። መዝ. ፺፱፥ ፯ - ፰።

በስተላይ ወገን ጥቂቶች መንደሮች ይታያሉ። ነገር ግን በዙሪያይቸው እልም ያለ ገደል ነው። ሰውስ ይቅርና አሞራ ስንኳ አያልፍበትም። ኢዮብ ፳፰፥ ፯።

እግር ክፉ ነውና ምናልባት የኛም መንገድ ባለጠጋው በሔደበት የሆነ እንደ ሆነ እንዴት እንሆናለን ብዬ ያዘንሁበት ምክንያት ይህ ነው አለኝ።

በእውነትም ይህ ነገር እጅግ የሚያሳዝን ነው።

ነገር ግን ንጉሡ ባስጠራን ጊዜ የክርስቶስ ሞት የሚባለውን ካርታ ያገኘን እንደ ሆነ ያንን እያየን ደጋ ደጋውን እንሔዳለን።

ትልቁስ ጭንቀት የክርስቶስ ሞት የሚባለውን ካርታ ያላገኘን እንደ ሆነ ነው። ካርታውንም ካላገኘን ወደ አንፉ ፈረፈር ወድቀን እንቀራለን እንጂ ያ ባለጠጋ የሔደበትን በረሃ እንዘልቃለን ብለን አናስብም አልሁት።

እውነት ነው፤ ግን ለሁሉም ነገር የተቀደሰ ፈቃዱ ይሁንልን አሜን አለኝ።

ይህንም ተነጋግረን መንገዳችንን ለመሔድ ጀመርን።

# ምዕራፍ ፳፩

ስለ ዕድሜ ተራራ

ከዚህም በኋላ የሚባለውን ዕድሜ ተራራ ለማየት ሔድሁ። በጥጉ ቆሜ ብመለከት ሄኖክና ኤልያስ ወደ ጫፉ ወጥተው ፊጥ ብለው ተቀምጠው ይታያሉ። ዘፍጥ. ፭፥ ፳፬፤ ፪ነገ. ፪፥ ፲፩።

መቼም አሳብ አይቀርምና፤ ምናልባት እኔም ብወጣ እንደርሳቸው ወደ ጫፉ እደርስ ይሆንን ብዬ ወደ ተራራው እግር ቀረብሁ።

ነገር ግን በዕድሜ ተራራ እግር የስንት ፍጥረቶች ሬሳ አየሁ ብላሁ ታምኑኛላችሁን። ሰማይና ምድር ወረቀት፤ መላእክት ጸሐፊዎች፤ ባሕር ቀለም ሆኖ ተጽፎና ተቆጥሮ ያልቅ እንደ ሆነ ነው እንጂ አንድ ሰው ሊጽፈውና ሊቆጥረው አይችል።

የሰው ወገን ሬሳ ባንድ ወገን፤ የእንስሳ ወገን ሬሳ ባንድ ወገን፤ የአራዊት ወገን ሬሳ ባንድ ወገን፤ የአዕዋፍ ወገን ሬሳ፤ ባንድ ወገን የተንቀሳቃሽ ወገን ሬሳ ባንድ ወገን፤ እነሺህ ሁሉ እንደ ቅጠል ረግፈው ይታያሉ።

ሬሳውንም ሁሉ በየወገኑ ካየሁ በኋላ ቀና ብዬ ወደ ዕድሜ ተራራ ብመለከት፤ እንስሳውም አራዊቱም፣ አዕዋፉም፣ ተንቀሳቃሹም፣ የሰው ወገን ሁሉ ወደ ዕድሜ ተራራ ለመውጣት ይፍጨረጨራሉ፤ ነገር ግን ያንን ዕድሜ ተራራ እስከ ጫፉ የወጣ ፍጥረት የለም።

እኩሌ ከተራራው መካከል ሲደርሱ ይወድቃሉ። እኩሉም ገና ጥቂት ከፍ እንዳሉ ይወድቃሉ። እኩሉም ገና አንድ ጊዜ እንደ ተራመዱ ይወድቃሉ። እኩሉም ገና እንወጣለን ብለው ሲያስቡ ይወድቃሉ።

ይህንም አይቼ ብዙ አለቀስሁ።

ያ ወዳጄ ልቤ ግን እጅግ ቸኩሎ ነበረና እንሒድ እንጂ በዚህ ቆመን እንኖራለን።

ይህ አሁን የምታየው ሁሉ ላንተ እንግዳ ቢሆንብህ አታድንቅ፤ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እንዲሁ ነው አለኝ።

ምንስ ቢሆን ክርስቲያን አይደለሁምን? ስለዚህ ይህን ሁሉ የሰው ሬሳ አይቼ ዝም ብዬ ብሔድ መልካም አይሆንምና ወደ ዛፉ እግር አርፈን ከዳዊት መዝሙር ጥቂት ልዘምር አልሁት።

ከዚህም በኋላ ዳዊቴን በጉልበቴ ላይ ዘርግቼ ልዘምር ጀመርሁ።

እንዲህ እያልሁ

«ምንትኑ ውእቱ ሰብእ ከመ ትዝክሮ?

ወምንትኑ ዕጓለ እመሕያው ከመ ተሐውጾ?

ሕቀ አሕጸጽ እመላክቲከ። መዝ. ፫÷ ፬ - ፯።

እስመ ኅልቀ በሕማም ሕይወትየ።

ወዓመትየኒ በገዓር።

ወደከመ በተጽናስ ኃይልየ።

ወአንቀልቀለ ኵሉ አዕጽምትየ። መዝ. ፴፩÷ ፩።

ወእቤ በልሳንየ ንግረኒ እግዚኦ ደኃሪትየ።

ምንት እማንቱ ኊልቆን ለመዋዕለየ።

ከመ አእምር ለምንት እዴኅር አነ።

ናሁ ብሉያተ ረሰይኮን ለመዋዕልየ።

ወአካልየኒ ወኢከመ ምንት በቅድሜከ።

ወባሕቱ ከንቱ ኵሉ ደቂቀ ዕጓለ እመሕያው።

ወከመ ጽላሎት ያንሶሱ ኵሉ ስብእ።»

ወባሕቱ ከንቶ ይትሀወኩ።

ይዘግቡ ወኢየአምሩ ለዘያስተጋብእ።

በተግሣጽከ በእንተ ኀጢአቱ ተዛልፍኮ ለሰብእ።

ወመሰውካ ከመ ሣሬት ለነፍሱ።

ወባሕቱ ከንቱ ይትሀወኩ ኵሉ ስብእ። መዝ. ፴፱÷ ፫ - ፲፩።

ተዘከር ምንት ውእቱ ኃይልየ።

ቦኑ ለከንቱ ፈጠርኮ ለዕጓለ እመሕያው።

መኑ ሰብእ ዘየሐዩ ወዒይሬእያ ለሞት።

ወመኑ ዘያድኅና ለነፍሱ እምእደ ሲኢአል። መዝ. ፹፱÷ ፵፪ - ፵፫።

እስመ ኅልቀ ከመ ጢስ መዋዕልየ።

ወነቅጸ ከመ ሣዕር አዕጽምትየ።

ወመዋዕልየኒ ከመ ጽላሎት ኅለፈ።

ወአነሂ ከመ ሣዕር የበስኩ።

ንግረኒ ውኅዶን ለመዋዕልየ።

ወኢትሰደኒ በመንፈቀ ዓመትየ።

ወኵሉ ከመ ልብስ ይበሊ።

ወከመ ሞጣሕት ትዌልጦሙ ወይትዌለጡ። መዝ. ፻፪÷ ፫ - ፳፯።

ተዘከር እግዚአ ከመ መሬት ንሕነ።

ወሰብእሰ ከመ ሣዕር መዋዕሊሁ።

ወከመ ጽጌ ገዳም ከማሁ ይፈሪ።

እስመ መንፈስ ይወፅእ እምኔሁ ወኢይሄሉ እንከ።

ወኢየአምር እንከ መካኖ። መዝ. ፻፫÷ ፲፬ - ፲፮።

ምንትኑ ውእቱ ሰብእ ከመ ታስተርኢ ሎቱ።

ዕጓለ እመሕያውሰ ዘተሐሰቦ።

ሰብእሰ ከንቶ ይመስል።

ወመዋዕሊሁኒ ከመ ጽላሎት የኅልፍ። መዝ. ፻፵፬÷ ፫።

ይህንም ከጨረሰ በኋላ ቆሜ የሬሳውን ብዛት እያየሁ አንድቅ ጀመርሁ።

ወዳጄ ልቤም ወደ እኔ ቀርቦ እንዲህ የሚያስደንቅህ የሞቱት ስዎች ነገር ነውን? አለኝ።

አዎን፤ አንተሳ፤ አልሁት።

እኔስ የሚያይስደንቀኝ የሄኖክና የኤልያስ ነገር ነው አለኝ።

እንደምን? አልሁት።

የዕድሜ ተራራን ወጥተው ወደ ጫፉ ከደረሱ በኋላ ተደላድለው አይቀመጡምን? እንዲህ አጉል አቀማመት ተቀምጠው ቍልቍል፥ ቍልቍል ሲመለከቱ ቢወድቁ እንደምን ሊሆኑ ነው። እነዚህ ሰዎች ያልወደቁ እንደ ሆነ ምን ተናገር በለኝ አለኝ።

እውነትህ ነው፤ አጉል አቀማመጥ ተቀምጠዋል። ነገር ግን ቢወድቁስ ባይወድቁስ እኛ ምን ቸገረን? ከወደቁማ ሥጋቸውስ ለመቃብር ይገኛልን? ደግሞም እነዚህ ሰዎች ይህን የዕድሜ ተራራ በገዛ ኃይላቸው ሊወጡ ባልቻሉ ነበር። ስለዚህ ያወጣቸው ጌታ ያውቅላቸዋል። ራእ. ፱፥ ፩።

ግን ሁሉንም በዓይን ለማየት ያብቃን፤ በጆሮም ለመስማት ያብቃን። አሁንስ መንገዳችንን እንሒድ። ምንም ቢሆን የደቡብን ሀገር ሳናይ ወዳገራችን አንመለስም አልሁት።

## ምዕራፍ ፳፪

# ስለ ደቡብ መንገድ

ከዚህም በኋላ ወደ ደቡብ ሀገር ሔድሁ።

የደቡብ ሀገር ሰፊ ሜዳ ነበርና በእግሬ ሔጄጄ ወደ አስብሁበት እንዳልደርስ አወቅሁ።

ስለዚህ አንዲኢት ሰጋር በቅሎ ገዛሁና ስሟን ማንበብ ብቻ ብዬ አወጣሁላት።

በሁለት ዓይን ልጓም ለጉሜ ወዳጄ ልቤን አፈናጥጬ አንድ ጊዜ ሾጥ ባደርጋት የሚበልጠውን ሜዳ አሳለፍሁት።

በዚያም ምርማሪ የሚባል ሣር የበቀለበት መስክ አገኘሁ። ይህ መስክ የማነው ብዬ ብጠይቅ የባሻ ማስተዋል ነው አሉኝ። እርሳቸወስ ድግ ሰው ናቸው። አንድ አፍታ ባግጣት የሚቆጡኝ አይመስለኝም ብዬ ልጓሟን አውልቄ ለቀቅኋት። ጥቂትም እንደ ነጩች እንድ ገና ለጉሚኤ አሰግር ጀመርሁ።

ነገር ግን የደቡብ ሀገር እጅግ ሰፊ ስለ ሆነ ፊት ለፊት አልዘልቀውም ብዬ ባንድ ወገን አቋርጬ ወደ ምሥራቅ ተመለስሁ። ወዳጄ ልቤም ምነው ባቋራጭ መንገድ ተመለስህ፤ ይህን ጊዜ እኔ ብዬህ በሆን እልክህ ይመጣ ነበረ አለኝ።

እንኳን እንኳን አንተ እንደ ሰለቸኸኝ አውቄ ወደ ምሥራቅ ሀገር ሔደን ወዳጆቻችንን ሁሉ ተሰነባብተን ወዳገራችን እንድንመለስ ብዬ ነው እንጂ ሌላ ነገር ብዬ አይደለም አልሁት።

ይህስ ከሆነ መልካም ነው አለኝ።

# ምዕራፍ ፳፫

# ስለ መሰነባበት

ይህንም ከተነጋገርንም በኋላ ወደ ምሥራቅ ሀገር ደረስሁ። የምሥራቅ ሀገር ግን ለበቅሎ የማይመች ወታ ገባ መሬት ነበረና በቅሎዬን ማንበብ ብቻን ለሊቀ ካህናት መራቀቅ ሸጥሁላቸው። በእግሬም ለመሔድ ጀመርሁ። ነገር ግን ዱሮ ዱሮ በቅሎ ተለመደና እግሬ ይደካከም ጀመረ።

ከዚህም በኋላ እያዘገምሁ ወደ ድኅነት ቤት ደረስሁ። ባየኝ ጊዜ እጅግ ደስ አለው። ከሰላምታው በኋላ ስለ ልጆቼና ስለ ሚስቴ ጤና ጠየቀኝ።

ደኅና ናቸው፤ እግዚአብሔር የዕለት ምግብና ያመት ልብስ አልነሣቸውም አልሁት። ፩ ጢሞ. ፮፥ ፰።

ከዚህም በኋላ ወደ ቤት ገባን። እርሱም ቶሎ ብሎ እንጀራውን በሌማት፤ ጕመኑን በድስት አድርጐ አቀረበልኝ።

እኔም ባርከህ ቀድሰህ ስጠኝ ብዬ ፈጣሪዬን ለምኜ እስከጠግብ በላሁ።

ከበላሁም በኋላ ይህን የበላሁትን ለጤና አድርግልኝ፤ በመንግሥተ ሰማያትም መንፈሳዊ ምግብ እንድትመግበኝ እለምንሃለሁ ብዬ ፈጣሪዬን አመስግኜ ወደ መኝታ ቤቴ ሔድሁ።

በነጋም ጊዜ ለመሔድ ተነሣሁ። ድኅነትም ብዙ መንገድ ሸኘኝ።

ምክርም መከረኝ፤ ምክሩም እንዲህ ነበር።

ብልጥግና የሚባል ወምበዴ ተነሥቶ ሰውን ሁሉ ሊፈጅ ነው። አሁንም አንተ ተጠንቅቀህ ሒድ አለኝ። ፩ ጢሞ. ፮፥ ፱ - ፲።

እንደምን አድርጌ እጠነቀቃለሁ። እነሆ አንተ እንደምታየኝ ባዶ እጄን ነኝ። ቢመጣብኝጽ በምን እመልሰዋለሁ አልሁት።

እርሱም ወደ ቤቱ እየሮተ ተመልሶ ይበቃኛል የሚባል አፎቄውን ይዞልኝ መጣ። ያንንም በጫንቃዬ ላይ አድርጌ እየተጐማለልሁ ሔድሁ።

ትሕትናንም ለመሰናበት ሔድሁ። ተሰነባበተንም ስሔድ ስለ መንገዴ መከረኝ።

ምክሩም እንዲህ ነበር።

በዚህ ወራት ትዕቢት የሚባል አንበሳ ከበረሃ መጥቶ መንገደኞችን ሁሉ እየሰበረ ሊጥል ጀምሯል። አሁን ስትሔድ ስንኳ ብዙ ሬሳ ወድቆ ታገኛለህ። አንተ ግን ተጠንቅቀህ ሒድ አለኝ።

እንሆ አንተ እንደምታየኝ በእጄ መሣሪያ የለኝም። እንደምን ልጠንቀቅ አልሁት።

በዚያ ጊዜ አላዋቂ ነኝ የምትባል ሽጉቱን ከወገቡ አውልቆ ሰጠኝ። ያንንም ታጥቄ ያላሳብ መንገዴን ሔድሁ።

ብላታ ቸርነትም ለመሰናበት ሔድሁ። እርሳቸውም ሸኝተውኝ ሲመለሱ ስለ መንገዴ መከሩኝ። ምክሩም እንዲህ ነበር።

ንፍገት የሚባል አቦ ሸማኔ እጅግ ከፍቷልና ተጠንቅቀህ ሒድ አሉኝ።

ያለ መሣሪያ እንዴት አድርጌ ለመጠንቀቅ እችላለሁ አልኋቸው።

ያለውን ለመስጠት የሚባል ጋሻቸውን ከክንዳቸው አውልቀው ሰጡኝ። እኔም ያንን አንግቤ ያለ ፍርሃት ሔድሁ።

## ምዕራፍ ፳፬

# ስለ ወንጌል መሰነባበት

ከዚህም በኋላ የምእመን ሚስት የነበረችውን ወንጌልን ለመሰናበት ያለችበትንስ ስፍራ አስጠይቄ ሔድሁ። ባየችኝም ጊዜ እያለቀሰች ወደ እኔ መጣች። ከሰላምታም በኋላ ወደ ቤት እንግባ አለችኝ።

እኔ ግን ቸኩየ ነበረና እዚሁ ተሰነባብተን ልሒድ አልኋት።

ምነው ወዳጄ፤ ይህን የሚያህል ዘመን ተለያይተን ኖረን መቼ ተጨዋወትንና ልሒድ ትላለህ። ስንኳን አንተ ማንም ወደ እኔ ቢመጣ ሳያድር አይሔድም አለችኝ። ዮሐ. ፮፥ ፴፯።

እኔም እሺ ብዬ ወደ ቤት ገባሁ። ጨዋታም ጀመርን። እቴ ወንጌል ሆይ፤ እንደምን ነሽ፤ ተጽናንሽን አልኋት።

የሞተ ተጐዳ እንጂ፤ የቆመ ምን አለበት። ባሌንም ከሀገር አስወጥተው የሰደዱት ሰዎች ዋና ዋናዎቹ ሲቀሩ፤ ሁሉም እየመጡ እግሬ ሥር እየወደቁ «ማሪን» አሉኝና ማርኋቸው አለች። ማቴ. ፩፥ ፺።

ካሣ እየተቀበልሽ ነውን አልኋት።

አልተቀበልሁም አለች።

እንግዲያማ ስለ ምን ማርሻቸው አልኋት።

አለቃ መመለስንና ቄስ ገበዝ ማመንን አማላጅ ልከው ቢያስጨንቁኝ ማርኋቸው አለችኝ።

እነዚያማ ከመጡ ምን ይደረጋል። መቼም የሞተ ሰው ከኋለኛው ቀን በቀር አይነሣም። ደግ አድርገሻል። ከዚያ ወዲህሳ ፍቅር ናችሁ፤ ልብሽ ጥቂትም ቂም አልያዘምን አልኋት።

ኧረ ወዲያ በስመ አብ በል ወንድሜ። አንድ ጊዜ ከታረቅሁ በኋላ ቂም የሚሉ ነገር ወዴት አውቃለሁ። አባቴ እግዚአብሔርም እንዴሁ ነው። ኢሳ. ፩፥ ፲፰።

ከምዕራብ ሀገር የመጣ ጳውሎስ የሚባል ሰው በደማስቆ ከተማ ሸፍቶ ያባቴን አሽከሮች ሁሉ እያሰረ ወደ ኢየሩሳሌም ይሰዳቸው ነበረ።

አባቴም ይህ ነገር ቆጪውና በከተማው አጠገብ ሙብረቅ የሚባለውን መድፍ ጠምዶ ቆየው።

ነገር ግን አባቴ እጅግ ርኅራኄ ያበዛ ነበርና እንዳይሞት ብሎ እርሳሱን አውጥቶ ባሩድ ብቻ ነበረ።

ጳውሎስም አሳቡን ጥሎ ሲሔድ ያንን ሙብረቅ የሚባለውን መድፍ ተኰሰበት።

በዚያ ጊዜ በድንጋጤ እስከ ሦስት ቀን ድረስ ወድቆ አደረ። አሽከሮቹም አንዱ ባንዱ ላይ እየተነባበሩ ወደቁ።

አባቴም በቶሎ ከምድር አንሥቶ ይዞ ብዙ ወቀሳ ከወቀሰው በኋላ ምሕረት አደረገለት። ከዚያ ወዲህ የሁለቱ ፍቅር ርጥብ ያቃጥላል።

ከፍቅራቸውም ጽናት የተነሣ የውጭ ሀገር ሚኒሲትር አድርጎ ሾመው። የሐዋ. ፱፥ ፩ - ፲፩።

ወዳጄ ሆይ፤ ከታረቅን በኋላ ቂም አናውቅም፤ የዘር ነው አለችኝ።

ወንጌል ሆይ፤ ይህስ ትልቅ ነገር ነው። ይኅን ያህል ነገር ስምቼ ደስታውንም አልችለው። አሁንም ማደሬ ካልቀረ ስለ ደስታዬ በዘፈን ሳሞግስሽ ልደር አልኋት።

ከበረታህማ መልካም ነው። ግን መንገደኛ ነህና ይደክምሃል ብዬ አስባለሁ አለች።

## ምዕራፍ ፳፫

# ወንጌል በዘፈን ስለ ማሞገስ

ከዚም በኋላ የወንጌል ቤተ ሰዎች ሁሉ ተጠርተው መጡ። እኔም ልዘፍን ጀመርሁ።

በዚህ ያላችሁ ልጁም ዐዋቂውም አንድ ጊዜ እጃችሁን አውጡና አጨብጭቡ። ከበሮውንም ድልቅ ድልቅ ድልቅ አደረጉት። እንግዴህ ያለ ዛሬ አንገናኝም አልኋቸው።

እነሱም እጃችወን ቸብ ቸብ ሲያደርጉ እኔ በመካከል ቆሜ እንደዚህ እያልሁ አወርድላቸው ጀመርሁ።

ይገቨሽ ወደ ሰማይ፣

ይገቨሽ ወደ ሰማይ።

አንች አጋዳይ፣

አንች አጋዳይ፣

ይገቨሽ ወደ ሰማይ።

ሰዎች በቤታቸው ሲተማሙ ዋሉ፣

ደጅ ለመታ ሁሉ ከፈተች እያሉ። ማቴ. ፯፥ ፯።

ከጌታው ተጣልቶ አስታርቂኝ ሲልሽ፣

ዶሮ ሲጮህ መጥቶ ገባ ከቤትሽ። ማር. ፲፬፥ ፷፪።

ይህን ወሬ ሰምቶ ከገዛ አሽከርሽ፣

በንጨት ታንቆ ሞተ የፈታሽ ባልሽ። ማቴ. ፳፯፥ ፭።

ቀምበርሽ ቀላል ነው እያሉ ሲያሙሽ፣

ከሌሎቹ ይልቅ በዛ መከርሽ። ማቴ. ፲፩፥ ፳፬ - ፴።

መከሩስ ብዙ ነው አሁን እንዳልሁት፣

እንክርዳዱን ነቅለሽ ብትጥይለት። ማቴ. ፲፫፥ ፳፯።

ለመከሩ ሥራ እኒዔ እንዳልመጣልሽ፣

አዲስ ሚስት አግብቼ እንዲህ ቀረሁብሽ። ሉቃ. ፲፬፥ ፳።

ሌላ ስንኳ አይደለች ዓለሚቱ ናት፣

አንችን የማትወድሽ ጠላትሽ ከጥንት። ዮሐ. ፲፩፥ ፲፰።

እናንተ ሁለታችሁ ብትታረቁልኝ፣

መጥቼ አይሽ ነበር ጊዜ ሲመሽልኝ።

ለጨዋ ላማላጅ ዕርቅ እንቢ ብላችሁ፣

ለልጆቻችሁም ቂም አተረፋችሁ። ፩ ዮሐ. ፫፥ ፲።

ለኔስ ትዝ የሚኢለኝ የናፈቀው ልቤን፥

ልጅሽን ጳውሎስን የዳርሽበት ዘመን። ዮሐ. ፳፲፥ ፩።

ወደ ሮሜ ሰዎች ተልኮ ነበረ፣

ወደ ቆሮንቶስም ተልኮ ነበረ፣

ወደ ገላትያም ተልኮ ነበረ፣

ወደ ኤፌሶንም ተልኮ ነበረ፣

ወደ ፊልጵስዩስ ተልኮ ነበረ፣

ወደ ቆላስይስ ተልኮ ነበረ፣

ወደ ተሰሎንቄም ተልኮ ነበረ፣

ለጢሞቴዎስም ተልኮ ነበረ፣

ደግሞ ለነቲቶ ተልኮ ነበእ፣

ለነፊልሞናም ተልኮ ነበረ፣

ለዕብራውያንም ተልኮ ነበአ፣

በሐምሌ አምስት ቀን ሮም ላይ ተዳረ። ገድለ ሐዋርያትን ይመልከቱ።

ንጉሥ ሰጡት አሉ የምሥራቹን፣

ነጫጭ ልብስና የወርቅ ዘውዱን። ፪ ጢሞ. ፬፥ ፰።

እንግዲህ ጳውሎስ ቀረ መታየቱ፣

ብቅም አይል አሉ ከሙሽራ ቤቱ። የሐዋ. ፳፥ ፳፭።

እጅግ አድጋ ነበር የሚያገባት አጥታ፣

እርሱ ጳደቀባት እንዳትኖር ገልሙታ።

እርሱ ከሚስቱ ጋራ ሁልጊዜ ደስታ፣

እናቱ ስታለቅስ የምጠራት አጥታ።

ጴጥሮስ ይመስለኛል ከሰው ሁሉ አጭር፣

ጳውሎስ ሲያገባ መዝሙር ሲዘምር።

ባንገቱ ሲዘፍን የሮም ወታደር፣

በንጨት ላይ ተሰቅሎ ቁልቁል ያይ ነበር።

ገድለ ሐዋርያትን ይመልከቱ።

ታናሽ ታላቅ ሥጋ ሞልቶሽ በቤትሽ፣

ምላስ ሥጋ ምነው ማስቆረጥሽ። ስንክሣር ይመልከቱ።

የቤትሽን ሥራት ኖሯል ባላውቀው

ሰምበት ሥጋ ለካ በስተኋላ ነው። ስንክሣርን ይመልከቱ።

ለዚያ ለወታደር ማን ነገረው ብላት፣

ምላስ አምጡ ይላል ታንሽ ሲያቀርቡለት። ንክሣር ይመልከቱ።

ከጀርመኖች ጋራ ቆይታ አደረግሽ፣

ከንግሊዞች ጋራ ቆይታ አደረግሽ፣

ከፈረንሳይ ሰዎች ቆይታ አደረግሽ፣

ከሮሞች አር ቆይታ አደረግሽ፣

ከግሪኮች ጋር ቆይታ አደረግሽ፣

ከመስኮቦች ጋራም ቆይታ አደረግሽ፣

ከስዊድኖችም ቆይታ አደረግሽ፣

ከአሜሪካኖችም ጋር ቆይታ አደረግሽ፣

ባሕሩም ሁሉ በመርከብ ዞረሽ።

ካገኘሽው ጋራ ቆይታ አደረግሽ፣

ከምስሮችም ጋራ ቆይታ አደረግሽ፣

ከኢትዮጵያም ጋር ቆይታ አደረግሽ፣

ከአፍሪቃም ክፍሎች ቆይታ አደረግሽ፣

ወዳጅሽ የቱ ነው ደግሞስ ጠላትሽ፣

የልብሽን ምሥጢር ከመረመሩሽ። ማቴ. ፳፫፥ ፲፱።

ለነገሩ አልሁ እንጂ አንቺማ ምን ዕዳሽ፣

ለሁሉ የሚሆን ብዙ ስፍራ ሳለሽ። ዮሐ. ፲፬፥ ፩ - ፪።

አንችን ተማምኜ ተጣላሁ ከሰይጣን፣

ጠበቃ እንድትሆኝ ኋላ በፍርድ ቀን። ዮሐ. ፫፥ ፶፬።

ዕዳ እንኳ ብገባ ጌታሽ ይክፈልልኝ፣

ወዳጅሽን እኔን አሥሮ እንዳያኖረኝ። ማቴ. ፭፥ ፳፭ - ፳፮።

ከዚህ ቀድሞ አባቴን ከነገር አግብቶት፣

ብዙ ዕዳ፤ ብዙ ዕዳ ጌታሽ ከፈለለት። ኤፌ. ፪፥ ፲፮።

ብትረሽው ነው እንጂ የጌታሽ ባሪያ ነኝ፣

በጲላጦስ ሹመት ዓርብ ቀን የገዛኝ። ገላ. ፫፥ ፲፫።

እፈራለሁ እንጂ ሚስቴን ዓለሚቱን፣

አገባሽ ነበረ አንችን በቃል ኪዳን።

ዘመድ ወዳጆቼ ጥትኑን ግን ሲመክሩኝ፣

እርሷን ብታገባ ዕድሜህ ያጥራል አሉኝ። ማቴ. ፲፥ ፳፩።

አግባት ባሉኝ እንጂ የዚያ መች ቸገረኝ፣

ካንች ተጋብቼ ብሞትም ግድ የለኝ። ማቴ. ፲፥ ፳፰።

ከባሪያ መጋባት ነውር መስሎኝ ነወይ፣

እኔ ባንች ገንዘብ ጌታ እሆን የለሞይ። ዮሐ. ፰፥ ፴፪።

የጌታሽም መንግሥት በምትወጅው፣

እኩል ናቸው አሉ ባሪያና ጌታው። ቆላ. ፫፥ ፲፩።

ካመት ዓመት ድረስ ግብር እየበሉ፣

የጌታሽ ቤት ሥጋ አያልቅም ይላሉ። ፩ ቆሮ. ፲፩፥ ፳፯።

ሥጋ ከነደሙ አትብሉ ይላሉ፥

ባንሽ ጌታ ቤት ግን አይለኝም አሉ። ዮሐ. ፮፥ ፶፬።

ሥጋ አትብሉ ያለው ማናቸው ሀኪም ነው፣

ሥጋማ ካልበላ ምን ጤና አለው ለሰው። ዮሐ. ፮፥ ፶፫።

እኔ ልንገራችሁ ብትሰሙ ምነው፣

ሥጋ አትብሉ ምላት ያጣ ወሬ እንጂ ነው። ዮሐ. ፮፥ ፶፪።

እኔስ ከሐኪሞች ያገኘሁት ጥበብ፣

የእጅን እድፍ ሁሉ ቶሎ ቶሎ ማጠብ።

እጅግ ያስጠይፋል ያሰኛል በሞትሁት፣

እጅን ሳያጠሩ ሥጋ ቆርጦ መብላት። ፩ ቆሮ. ፲፩፥ ፳፱።

የከሳ የነጣ አትወጅሞይ ከቶ፣

መልኩን ካላየሽው ተኩሎ ተቀብቶ። ማቴ. ፮፥ ፲፯።

እመቤት ናት ብሎ ሲያወራ ሰው ሁሉ፣

ተሰውረሽ ውለሽ ተመጸወትሽ አሉ። ማቴ. ፮፥ ፫ - ፬።

የብርሽን ሣጥን ብል እንዳይበላው፣

ከምድሩ ወደ ላይ ከፍ ከፍ አድርጊው። ማቴ. ፮፥ ፳።

ተበልቶ የማያልቅ ድግስ ደግሰሽ፣

ያገሩ ሰው ሁሉ ግቡልኝ ብለሽ፣

ያደባባዩን በር እንዲህ አጥብበሽ፣

ልግባ ልግባ ሲሉ ሁሉም ሞቱልሽ። ማቴ. ፯፥ ፲፬ - ፳፪፤ ፩፥ ፲፬።

የነዚያ ሰዎች ደም ፍዳው ደረሰብሽ፣

እዩው ዛሬ አንድ ሰው አይገባ በበርሽ። ፩ ጢሞ. ፬፥ ፩ - ፫።

አንድ ዓይን ነሽ አሉ መልክሽ አያምር፣

ይዘሻል መሰለኝ የመስተፋቅር። ማቴ. ፭፥ ፳፱።

ባላገሮች ሁሉ ተማማሉብሽ፣

ወደ አረመኔ ሀገር ወስደው ሊጥሉሽ። የሐዋ. ፲፫፥ ፵፮።

እኒያስ ባያውቁ ነው ባይጠረጥሩሽ፣

ካረመኔ ወገን ትውልድ እንዳለሽ። ማቴ. ፳፰፥ ፲፱።

ወዴት ባገኘሁት እንድጠይቀው፣

ጳውሎስ ነው አሉ ዘርሽን የሚያውቀው። ሮሜ. ፲፩፥ ፲፫።

ትውልድሽ ቢጠፋኝ ምንም ባላወቀው፣

መጀመሪያ ግንዱ ቆርነሌዎስ ነው። የሐዋ. ፲፥ ፩ - ፵፰።

ይገሸሽ ወደ ሰማይ፣

ይገሸሽ ወደ ሰማይ፣

አንቺ አጋዳይ፣

ይገሸሽ ወደ ሰማይ።

እንግዲህም ስንዘፍን ሌሊቱ ወለል አለ። በነጋም ጊዜ ለመሔድ ተነሣሁ። ከወንጌልም ጋራ ለመሰነባበት ስንነጋገር ወዳጄ ሆይ፤ ስንቅ ይዘሃልን አለችኝ። ምንም የለኝም አልኋት።

እንዴት ያለህ ክፉ ሰው ነህ። ብዙ ምሥጢር ተጫውተን ሳለን እንደ ሌላ ሰው ሁሉ ዝም ብለህ ትሔዳለህን፤ እንግዲህ ወዲህ እንደዚህ ያለ የልግም ሥራ አትሥራ።

አሁንም አንድ አፍታ ቆየኝ አለችኝና ወደ ቤቷ እየሮጠች ሔዳ የስንዴ እንጀራና ጥቂት የወይን ጠጅ ይዛልኝ መጣች። በዚህ ሀገር የስንዴ እንጀራ ውድ ነው ባደርህበትም ስፍራ በሥጋ ብትለውጠው ይለወጣል። እያለች በልብሴ አስቋጥራ ሰደደችኝ።

## ምዕራፍ ፳፯

# ስለ ፍቅር መሰነባበት

ከዚህም በኋላ ፍቅር ታሞ ወደ ነበረበት ሀገር ሒድሁ። እርሱም ትንሽ የሸማ ቁራጭ በራሱ ላይ አስሮ ባደባባይ ኩርምት ብሎ ተቀምጦ ነበር።

እኔንም ባየ ጊዜ ባንድ እጁ ምርኩዙን ባንድ እጁ ምድሩን ይዞ በግድ ተነሣና ሊቀበለኝ መጣ። መልኩም ሁሉ ተለዋውጦአል።

እኔም ፍቅር መሆኑን አጣሁት፤ እንዲያውም ከብቶች የሚመለከት ሽማግሌ መስሎኝ ነበረ።

እርሱ ግን ወደኔ ቀርቦ አንገቴን አቅፎ ይስመኝ ጀመረ።

ኧረ ማን ትባላለህ አልሁት።

ምነው ዘነጋኸኝን፤ እኔ ፍቅር አይደለሁምን። አንተ እንዴህ የዘነጋኸኝ ሌላውማ ያለሁም የሌለሁም አያስበኝም አለኝ።

በዚያ ጊዜ ራሴን ይዤ እጮህ ጀመርሁ።

ዋ ወንድሜ ሆይ፤ እኔኢን መከራ በቁም ተነጋግረው አያልቅምና ይልቅ ጥቂት አረፍ ብለህ እንጫወት አለኝ።

ከዚህም በኋላ ወዳንድ ስፍራ ሔደን ተቀመጥንና ወዳጄ ፍቅር ሆይ፤ ዛሬ እንደምን ነህ አልሁት። እግዚአብሔር ይመስገን ዛሬ ደኅና ነኝ።

ነገር ግን ያን ጊዜ ራሴን ሲመቱኝ ሹመት የሚባለው አጥንት በራሴ ውስጥ ተሰብሮ ቀርቶ ነበርና ጤና የሚያሳጣኝ እርሱ ብቻ ነው። በተረፈ ደኅና ነኝ አለኝ።

ታነክሳለህና አልሁት።

አዎን፤ ሐሜት በሚባል ሾተል ቋንጃዬን መትተውኝ ነበረና እርሱ እንደ ገና እያመረቀዘ የስነከሰኛል። ደግሞ ጉቦ በሚባል ክርናቸው ልቤን አሽተውኝ ነበረና እርሱ ሳል ተክሎብኝ ሔደ አለኝ።

ምነው፤ መተው የሚባለውን ቅቤ እየጠጣህ አትሞክረውምን አልሁት።

ወንድሜ ሆይ፤ መቼ ሳልሞክረው ቀረሁ።

ነገር ግን ይኸ መተው የሚባል ቅቤ ብዙ ቀን የኖረ ሆነና ገና ሲሸተኝ ያንገፈግፈኛል አለኝ።

እንኪያውማ እንደምን ትሆናለህ አልሁት።

ቅጣት የሚባል ሰው መድኀኒቱ ያውቀዋል ሲሉ ስምቻለሁ። ስለዚህ ወደርሱ ሔጄ አንድ ዓመት ያህል ወህኒ በሚባል እልፍኙ አግብቶ እስራት የሚባለውን መድኀኔት እያጠጣ ነቅሎ ቢጥልልኝ ይሻለኝ ይሆናል ብዬ አስባለሁ፤ አለኝ። መልካም ነው። ይህ ካልሆነ አትድንም አልሁት።

ፍቅር መለሰ፤ ወንድሜ ሆይ፤ ከሁሉም ይልቅ እጅግ የሚያመኝ በራሴ ውስጥ ተሰብሮ የቀረ ሹመት የሚባለው አጥንት ነው አለኝ።

እየሥሩ መብላት ለሚባለው ሀኪም አታሳየውምን አልሁት።

ወደ ሀኪም ከመሔድማ አንድነት በሚባለው ወረንጦ ይዞ ሳብ ቢያደርጉት በገዛ እጁ ወጥቶ ይወድቅ አልነበረምን አለኝ።

እስከዚያ እንደምን ትሆናለህ አልሁት።

እየተበሳበሰ በገዛ እጁ ቢወጣልኝ በማለት ነዋ አለኝ።

አሁን እኔ በዚህ አንድነት በሚባለው ወረንጦ ይገፍ ብስበው ይወጣ እንደ ሆነ ልሞክርልህ አልሁት። ተው ተው፤ ብቻህን አይሆንልህም።

እንዲያውም ይናጋና እንደ ገና ያመኛል። እግዚአብሔር በፈቀደ ጊዜ ቢወጣልኝ ይሻለኛል አለኝ።

ከዚህም በኋላ ተሰነባብተን መንገዴን ሔድሁ።

## ምዕራፍ ፳፲

# ስለ ፍቅር ምክር

ከፍቅርም ተሰነባብቼኢ ጥቂት መንገድ ከሔድኩ በኋላ ፍቅር እንደ ገና ሲጣራ ሰማሁና ዘወር ብል ምርኩዙን ይዞ እንክል እንክል ሲል አየሁት።

እኔም ድምጤን ከፍ አድርጌ ኧረ ምን ሆነሃል ብለው ጥቂት ጉዳይ ረስቻለሁና አንድ ጊዜ መለስ በል አለኝ።

እኔም በቶሎ ተመልሼ አሁን ባሁን ምን ጉዳይ አገኘሁ አልሁት።

ትንሽ ምክር ልምከርህ ብዬ ነው አለኝ።

ወዳጄ ሆይ፤ እግዚአብሔር ያስብልህ።

እንደምን ያለ ምክር ትመክረኛለህ አልሁት።

ከሰው ጋራ አትጣላ፤ ሰውን ስለ ሃይማኖቱና ስለ ምግባሩ አትንቀፈው። እርሱም ያንተን ሃይማኖትና ያንተን ምግባር ይነቅፈዋልና። ሮሜ. ፫፥ ፳።

ክፉ ለተናገረ ክፉ አትመልስ። ፩ ጴጥ. ፫፥ ፱።

ጥበብን እሻት፤ ታገኛታለህም። ምሳ. ፪፥ ፩ - ፲።

ከቅዱስ መጽሐፍ ባልተገኘ በማይረባ ነገር አትከራከር። ፪ ጢሞ. ፪፥ ፳፫።

ከሁሉ ጋራ ተፋቀር። ፩ ጴጥ. ፬፥ ፰።

እውነቱን በሐሰት አትለውጥ። ዕብ. ፲፥ ፳፮።

ከሚያለቅስ ጋራ አልቅስ፤ ደስ ከሚለው ጋር ደስ ይበልህ። ሮሜ. ፲፪፥ ፲፭።

ከሁሉ የሚበልጥ እግዚአብሔርን፣ ሞትንና መቃብርን፣ መንግሥተ ሰማያትንና ኩነኔን ሁልጊዜ አስባቸው አለኝ።

ሁሉም ይሆናል፤ ነገር ግን ከሁሉ ጋራ ተፋቀር ስላልኸው ነገር በሃይማኖት የማይመስሉኝ በምግባር የማይተባበሩኝ ብዙ ሰዎች አሉ። እነዚያን ሁሉ መውደድ እንደምን ይሆንልኛል አልሁት።

ይህንስ የሚያስረዳ ነገር ከቅዱስ መጽሐፍ ክፍል ላንብብልህ ብሎ ሊያነብ ጀመረ። መንግሥተ ሰማያት በርሻው መልካም ዘር የዘራ ሰውን ትመስላለች፤ ሰዎቹም በተኙ ጊዜ ጸላቱ መጣ።

እንክርዳድም በስንዴው መካከል ዘርቶ ሔደ።

ስንዴውም በበቀለና ባፈራ ጊዜ በዚያ እንክርዳድ ደግሞ ታየ።

የባለቤቱም አገልጋዮች መጥተው ጌታችን ሆይ፤ በርሻህ መካከል መልካም ዘር ዘርተህ አልነበረም፤ እንክርዳዱ ከወዴት መጣ አሉት።

እርሱ ግን ጸላት ሰው ይህን አደረገ አላቸው። ሔደን ብንለቅመው ትወዳለህን አሉት።

እርሱ ግን እንክርዳዱን ስትለቅሙ ስንዴውን ትነቅሉብኛላችሁ፤ አይሆንም ተዋቸው እስከ መከር ድረስ ባንድ ይደጉ። በመከርም ወራት አጫጆች እንክርዳዱን ቀድማችሁ ሰብስቡ። እንዲቃጠልም በየነዶ እሥሩት ስንዴዬን ግን በጎተራዬ አከማቹ እላቸዋለሁ አላቸው። ማቴ. ፲፫፥ ፳፬ - ፴።

ደግሞም ይህን የመሰለ ቃል ከቅዱስ መጽሐፍ በብዙ ክፍል ይገኛል አለኝ። ፩ ቆሮ ፱፥ ፳፤ ማቴ. ፭፥ ፵፬ - ፵፰።

ወዳጄ ፍቅር ሆይ፤ መልካም ምክር መከረኸኛል፤ ግን ይህን ሁሉ ለማድረግ የእኔ ፈቃድ ብቻ አይበቃኝምና የጌታዬ የተቀደሰ ፈቃዱ ይሁንልኝ አልሁት።

ይህስ እውነት ነገር ነው፤ አሁንም በደህና ሰንብት።

ድንገት ወደ እኔ የሚመጣ ሰው ያገኘህ እንደ ሆነ ሰላምታ እንድትልክብኝ አለኝ።

ካገኘሁማ ምን ከፋኝ፤ ነገር ግን መጣላት የሚባል አውሬ ተነሥቶ መንገድ አላፊውን ሁሉ ሊፈጀው ነው። ስለዚህ ወዳንተ የሚመጣ ሰው መገኘቱን እንጃ ብዬው መንገዴን ሔድሁ። ፍቅርም እያዘገመ ወደ ጐጆው ተመለሰ።

ወዳጇ ልቢሌም ወደ እኔ ቀርቦ በምሥራቅ ሀገር ካየናቸው ሰዎች ሁሉ እንደ ፍቅር ያለ መልካም ሰው የለም አለኝ።

ኧረ መቼ አየኸውና ከርሱ ጋራ አንድ ወር ብትቀመጥ ዓለምን ከነከብሩ አታስበውም ነበር አልሁት።

# ምዕራፍ ፳፰

# ስለ መንግሥተ ሰማያት ወሬ

ከዚህም በኋላ ወደ ሀገራችን ለመመለስ ቁርጥ ምክር መከረን ጨረስን። ወዳጇ ልቤም እጅግ ደስ አለው። ነገር ግን እኔን ጥቂት ቅርታ ገብቶብኝ ነበርና ወዳጇ ልቤ ቅርታ እንዳገባብኝ አይቶ ምነው አዝነሃል አለኝ።

ወደ ሀገራችን ለመመለስ መከረን ጨረስን። ነገር ግን ባለፈው ወራት አንተ ለጌታ ማደሬን አሳስበኸኝ ነበር። እርሱ የንጉሥ ልጅ መሆኑን አይቼ ባድርለት የሚገዛው ሀገር ለምም ጠፍም እንደ ሆነ አላውቀውምና ያን ሀገር የሚያውቁት የምሥራቅ ሰዎች ስለ ሆኑ ወደ መንደር ገብተን ወሬ ጠይቀን ብንሔድ መልካም ነው ብዬ ነዋ አልሁት።

ይህስ መልካም ነገር ነው አለኝ።

ከዚህ በኋላ ወደ መንደር ገባሁ። ብዙ ሰዎችም ተሰብስበው አገኘሁ።

ጌቶች ሆይ፤ መንግሥተ ሰማያት የሚባለውን ሀገር ታውቁታላችሁን አልኋቸው።

እንዴታ፤ ነገር ግን በወሬና በጋዜጣ ነው እንጂ ባይናችን አላየነውም አሉ። ዕብ. ፲፩፥ ፴፱ - ፵።

ያወራላችሁ ሰው እውነተኛ ነውን፤ ጋዜጣውንስ ጨርሳችሁ አንብባችሁታልን አልኋቸው።

ወሬውን ያወሩልን የንጉሡ ልጅ አሽከሮች ናቸው። ጋዜጣውም በየእለቱ የሚጻፈው የዚያው ሀገር ነገር ነው አሉኝ። እንዴት እንዴት ብለው አወሩላችሁ

አልኋቸው። መንግሥተ ሰማያት ወደ ሚባለው ሀገር የሚወስድ የባቡር መንገድ ተሠርቷል። በባቡሩ የሚሔዱ ሰዎች ሁሉ ደስ እያላቸው ወደ ከተማው ይገባሉ።

ወደ ከተማው በገቡበት ቀን ከንጉሡ ጋራ ይገናኛሉ። በከተማውም ውስጥ ዘወትር ተድላ ደስታ ነው። በሩም በቀንና በሌሊት አይዘጋም። ራእ. ፳፩፥ ፳፭።

በዚያ የሚራብ፣ የሚጠማ የሚያዝን፣ የሚያለቅስ፣ የሚታመም፣ የሚሞት የለም። በዚያ ንፍገትን፣ ቅናትን፣ ምቀኝነት፣ ድፍረትን ተንኰልን፣ ፀብን፣ መሠሪነት፣ መክሰስን፣ መውቀስን የሚያስብ የለም።

በዚያ ጨለማና የሞት ጽላ የሉም።

በዚያ መብራትና የፀሐይ ብርሃን አይፈለግም። የሀገሩ ብርሃን እርሱ እግዚአብሔር ነውና። ራእ. ፳፩፥ ፳፫።

ባዳራሹም ውስጥ ልዩ ልዩ የሆነ የሙዚቃ ዜማ ይሰማል። ራእ. ፲፬፥ ፫።

ወደዚያ ሀገር የደረሱ ሁሉ ነጫጭ ልብስ እየለበሱ ከጽሩ ወርቅ የተሠራ ዘውድ በራሳቸው እየደፉ ባደባባዩ ይመላለሳሉ።

ወደዚያ ሀገር የደረሱ ሁሉ ቀድሞ ወደ ነበሩበት ስፍራ ለመመለስ አይመኙም።

ደግሞ በዚህ ዓለም ስለ ጽድቅ የተበደሉ ሰዎች የተሰደቡም፤ ገንዘባቸውንም የተወረሱ፤ የታሠሩም፤ የተገረፉም፤ የተሰደዱም፤ በአራዊትም የወደቁ፤ በእሳትም የተቃጠሉ፤ በሰይፍም የታረዱ፤ ሌላም ብዙ መከራ የተቀበሉ ሁሉ ወደ ንጉሡ እየገቡ በደላቸውን ይናገራሉ። ንጉሡም በእውነት ይፈርድላቸዋል። ጠላቶቻቸውንም ያጠፋላቸዋል።

የንጉሡን ደግነት፤ የሀገሩን ውበት ማን ተናግሮ ይጨርሰዋላል አሉኝ።

ከዚህም በኋላ ጌቶች ሆይ፤ ቸር ወሬ ያሰማችሁ በዚያ ሀገር ለመገናኘት ያብቃን ብያቸው መንገዴን ሔድሁ።

## ምዕራፍ ፳፱

# ስለ ጸሎት መጸለይ

በዚያ ጊዜ ወዳጄ ልቤ ወደ እኔ ቀርቦ ያሰብኸውን ሁሉ ጨረስህ፤ እንግዴህ ወዲህ ወደ ሀገራችን አንመለስምን አለኝ።

ወዳጄ ሆይ፤ እሺ እንመለሳለን። ነገር ግን ወደ ቤተ ክርስቲኢያን ሔጄ ጸሎት አድርጌ ልመለስ አልሁትና ከዚያ ቶሎ ብዬ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሔድሁ፤ ጸሎትም ጀመርሁ።

አቤቱ እጅግ የተፈራና ሁሉን ማድረግ የምትችል እኔን ኃጢአተኛውን ሰው ስለ ታገሥኸኝ እጅግ አመሰግንሃለሁ።

እንደ ኃጢአቴና እንደ ክፋቴ መጠን ሞትና የዘላለም ኵነኔ ይገባኝ ነበረ።

አንተ ግን ኃጢአተኛውን መመለሱን እንጂ ጥፋቱንና ሞቱን አትወድምና እስካሁን አቆየኸው። ከማርና ከወተት የሚጣፍጥ ክቡር የወንጌል ቃልህን አቀመስኸኝ። እስካሁን ድረስ ጣዕሙ በጕረሮዬ አለ። ባለፈው ዘመንኔ ሁሉ አንድ ቀን ስንኳ ፈቃድህን ፈጽሜ አላውቅም ኃጢአት የሚሠራ ሁሉ የኃጢአት ሎሌ መሆኑን እያወቅሁ ከሕግህ አርነት ወጥቼ ነበርሁ።

አንተ ግን ይህን ሁሉ እያየህ ስለ ታገሥኸኝ፤ ፈጽሜኢ አመሰግንሃለሁ። ዳግመኛም እለምንሃለሁ።

የቀደሙ አባቶች የሔዱበትን ቅኑን መንገድ መርተህ የሰማያዊ ከነዓን ወራሽ ታደርገኝ ዘንድ።

በሕጻንነቴም የበደልሁህን በደል አታብብኝ። አቤቱ አትጣላኝ፤ ብትጣላኝ ስንኳ እንደተጣላኸኝ አትቅር። ይቅርታህን አብዛልኝ፤ ሰላምህን ስጠኝ።

ከኃጢአት ባርነት አርነት አውጣኝ።

ዓለምንና ሰይጣንን፤ ኃጢአትንም የማሸፍንበት ዕቃ ጦር አልብሰኝ። አቤቱ ለዚህም ሁሉ የተቀደሰ ፈቃድህ ይሁን፤ አሜን።

## ምዕራፍ ፴

# ስለ ሁለተኛው ዘፈን

ጸሎቴንም ከጨረስሁ በኋላ ከቤተ ክርስቲያን ስወጣ በደጃ ሰላሙ የቆሙት ዘበኞች ያዙኝ።

ጌቶች ሆይ፣ ምን ጥፋት አገኛችሁብኝ አልኋቸው።

ጥፋትስ አልተገኘብህም። ነገር ግን ወደዚህ የሚገቡ ሰዎች ሁሉ የንጉሡን ልጅ በዘፈን ሳያሞግሱ እንዳይወጡ ክልክል ነውና አንተም እንደ ደንቡ አሞግስና ውጣ አሉኝ። ከበሮ የሚኢሙቱና ዘፈኑን የሚቀበሉ ሰዎች አሉን አልኋቸው።

ለዚህስ አታስብ ብለው ብዙ ሕዝብ ወደ ተሰበሰቡበት ስፍራ ወሰዱኝ።

እነዚያም ባዩኝ ጊዜ ለዘፈን መሆኑን አውቀው ኖረው ከበሮውን እየመጡ ያጨበጭቡ ጀመሩ።

ልዘፍንም ጀመርሁ።

የሰቀለህ ማነው፤ የሰቀለህ ማነው፣

ዘመድ ምቀኛ ነው።

እስኪ ሰላም ብዬ ምስጋና ላቅርብ፣

አንተ አይደለህሞይ የርሁባን ምግብ። ማቴ. ፮፥ ፴ - ፴፩።

እስኪ ሰላም ብዬ አንተን ላሞግስ፣

አንተ አይደልህሞይ የዕሩቃን ልብስ።

እስኪ ሰላም ብዬ ስምህን ልጀምር፣

አንተ አይደለህሞይ ያንካሳ በትር።

እስኪ ሰላም ብዬ ልጀምር ውዳሴ፣

አንተ አይደለህሞይ ቤዛዋ የነፍሴ። ፩ ጴጥ. ፬፥ ፩።

እንደምን ብሩቱ ነህ እንደምን ለመድኸው፣

የአዳምን መከር አንድ ቀን ጨረስከው። ዮሐ. ፲፱፥ ፴።

ከማጨዱ ይልቅ የጐዳህ አንተን፣

መቃረሙ እንጂ ነው የረገፈውን። ዮሐ. ፲፩፥ ፶፪።

ያንተ ማጭድ ሥልጣን ጠንካራ ነው ብርቱ፣

ስንዴውን ከንክርዳድ ቶሎ መለየቱ። ማቴ. ፲፫፥ ፴።

ጥንቱን ግን ሲዘራ ነጭ ስንዴ ነበረ፣

ይህ እንክርዳድ ደግሞ መቼ ተጨመረ። ዘፍጥ. ፩፥ ፳፺።

እኔንስ አቃተኝ መቆም መነሣት፣

የተሰቀለ ዕቃም አውርድ ማየት። ገላ. ፫፥ ፩።

በርትቼ ብነሣ አውርጀም ባየው፣

ለካ ምግብ ኖሯል የተሰቀለው። ሉቃ. ፳፪፥ ፲፱።

ያባቴ ጠላቶች ቢከሱኝ ድንገት፣

ወምበሮችም ላይ እንዳልሟገት፣

ይግባኝ ብዬ መጣሁ ካንተ ዳኝነት። መዝ. ፹፥ ፪ - ፫።

ነገሩም እንዲህ ነው ልንገርህ ከሥሩ፣

ቦታ ላይሆናቸው በውስጡም ላይኖሩ፣

አባቴን አታለው ነቀሉት ከምድሩ። ዘፍጥ. ፫፥ ፳፫ - ፳፬።

ዝም ብሎ ከኖረ ፭ ዓመት ሙሉ፣

ርስቱን ይነቀል ወንበሮች ይላሉ። ፍትሐ ነገሥት ይመልከቱ።

አሁን የት ይገኛል እንዳንት ያለ ቃል፣

በአምስት ሺህ ዘመን ይመለስ የሚል። ፩ ጴጥ. ፫፥ ፲፱ - ፳።

ምንድነው አመልህ ምንድነው ግብርህ፣

ዓቃቢ ይመስል ልብ መውደድህ። ፩ ሳሙ. ፲፮፥ ፲፺።

ዓቃቢስ ለመሆን የተገባህ ነህ፣

ሁሉን አጠጣኸው ያርብ ውኃ ቀድተህ። ዮሐ. ፲፱፥ ፴፬።

ታላቅ ታናሽ ሥጋ አትቀምስም አሉኝ፣

እገዛልሃለሁ ልብ ሥጋ ባገኝ። ማቴ. ፲፪፥ ፴፫።

ውሻው እንኳን ወስዶ በልቶም አልበላው፣

ላንተም እንዳልሰጥህ ባፉ አረከሰው። ማቴ. ፯፥ ፮።

ትሰማኝ እንደሆን ምክር ልምከር፣

ባርከህ ብትበላው ምንም አይጎዳህ። ኢሳ. ፩፥ ፲፮ -፲፱።

ምነው ከጠቢቦች ዝምድና በኖረኝ፣

ሥጋው ሞቶ ሳለ መቁረጫው ቸገረኝ። ፩ ቆሮ. ፲፩፥ ፲፰።

እንደምን ኮርተዋል ጠቢቦቹ ሁሉ፣

ሥሩልኝ ብላቸው ይሰድቡና አሉ። ዮሐ. ፯፥ ፶፪።

ምነው በተሾምሁት በሆንሁ ሚኒስትር፣

እንዳይሳደቡ አድርጋቸው ነበር። ፩ ቆሮ. ፲፩፥ ፳፩፥ ፳፬።

ጠቢቦች አባት አንተ መሰልከኝ፣

መልካም ዓይነት ጥበብ እንድትሠራልኝ። ፩ ቆሮ. ፩፥ ፳።

ጃኖማ ሁልጊዜ አለብስ የለሞይ፣

ብርቅ ይሆንብኛል ጥበብ ለብሰው ሳይ። መክ. ፱፥ ፲፫።

ወዳንተ ስመጣ መንገዱ ጠፍቶኝ፣

መልሶ መልሶ እንቅፋት መታኝ። ምሳ. ፳፬፥ ፲፮።

አዝግሜ መጥቼ ካንተ እንዳልገናኝ፣

ውስጥ እግሬን ሆነና አላስኬድህ አለኝ። ዘፍ. ፮፥ ፭።

ያለመንገድህ ስሔድ ድንገት ቢያገኘኝ፣

ለዚያ ለዱር አውሬ ያፉ ጉርሻ ነኝ። ፩ ጴጥ. ፭፥ ፰።

ለመምሬ ዓለሙ ባማከራቸው፣

ሀብት የለህም አሉኝ እርሱን ካልተውከው። ዕብ. ፲፩፥ ፳፯፣ ፵።

ጥንቱን ሳድርልህ ብንግራቸው ምሥጢር፣

መምሬ ዓለማየሁ ገዝተውኝ ነበር። ሮሜ. ፯፥ ፲፫ - ፳፫።

በመምሬ ዓለሙ የተገዘተ ሰው፣

እንኳን በምድርና በሰማይ እሥር ነው። ያዕ. ፩፥ ፩።

አንተ እስካሽከሮችህ እንዲህ ብትንቃቸው፣

መምሬ ዓለማየሁ ጉዳይም የላቸው። ማቴ. ፲፱፥ ፳፪።

በኢጣልያ ሀገር የከበሩ ናቸው፣

በመስኮብም ሀገር የከበሩ ናቸው፣

በጀርመንም ሀገር የከበሩ ናቸው፣

በእንግሊዝም ሀገር የከበሩ ናቸው፣

በፈረንሳይ ሀገር የከበሩ ናቸው፣

በምስሮችም ሀገር የከበሩ ናቸው፣

በቱርኮችም ሀገር እንደ ጳጳስ ናቸው፣

እስከ ጊዜው ድረስ ምንም አትጉዷቸው። መዝ. ፴፱፥ ፯።

ወዳንተ ስመጣ ጊዜ መሽቶብኝ፣

መምሬ ዓለማየሁ ቆየኝ ብለውኝ።

ብጠብቅ ብጠብቅ ወዲያው ቀሩብኝ። ያዕ. ፩፥ ፪ - ፫።

እንዲኢህ ቀጠሮ አፍራሽ ከሆኑ እርሳቸው፣

ቢሻሩ መልካም ነው ከቅስናቸው። ሉቃ. ፲፮፥ ፲፯።

መምሬ ዓለማየሁ ቅስና ሳላቸው፣

ምነው የነፍስ አባት አለመሆናቸው። ማቴ. ፲፮፥ ፳፮።

እኔስ አንድ ነገር ሰማሁባቸው፣

ጥንቱንም ሲመጡ ቆበጣል ናቸው። ዘፍ. ፫፥ ፳፫።

አልተሰማም ብለው እንዲህ ሲቀድሱ፣

የት ይደርሱ ይሆን ሲመጣ ንጉሡ። ማቴ. ፳፱፥ ፴፫።

ዳፈን እከፍላለሁ ቅዳሴም አልቀድስ፣

መምሬ ዓለማየሁ ካልወጡ ከመቅደስ። ፩ ቆሮ. ፲፩፥ ፳፤ ፳፫።

መምሬ ዓለማየሁ ምነው ኩራታቸው፣

ድኃ ባዩ ጊዜ ሰውም አይመስላቸው። ያዕ. ፪፥ ፪ - ፫።

መምሬ ዓለማየሁ ታላቅ ሀብታም ናቸው፣

ከልጅ እስካዋቂ ጠላትም የላቸው።

መምሬ ዓለማየሁ ተጣሉኝ አጥብቀው፣

ወይዘሮ ደስታን አላገባህ ብለው። ዮሐ. ፲፯፥ ፲፱።

ምናቸው ናት ብዬ ብጠይቅ ሰዎች፣

የንጀራ ልጃቸው ሆና ተገኘች።

ወይዘሮ ደስታን አግብቶ ከመኖር፣

ይሻል ይመስለኛል ሞትና መቃብር። ምሳ. ፯፥ ፩ - ፳።

ገንዘብም ቢኖራት ብታበላም ሥጋ፣

ሴሰኛ ናት አሉ ባንድ የማትረጋ። ፩ ነገ. ፩፥ ፶፫።

እርስዋን አላገባም አልደክምም ዝም ብሎ፣

ዮሐንስ ነግሮኛል ትሞታለች ብሎ። ፩ ዮሐ. ፪፥ ፲፯።

የሰቀለህ ማነው የሰቀለህ ማነው፣

ዘመድ ምቀኛ ነ።

ከዚህ በኋላ ከሰዎቹ ተሰነባብቼ መንገዴን ሔድሁ። ወደ ሀገራችንም የመመለሳችን ነገር እርግጥ ስለ ሆነ ወዳጄ ልቤን ደስ አለው።

## ምዕራፍ ፴፩

# ስለ ሀገራችን መንገድ

ከብዙ ቀን በኋላ ንብረት ወደሚባል ሀገራችን ደረስን። ዘመዶቻችን እነ አሳብ፣ እነ ውዝዋዜ፣ እነ አድር ብዬ፣ የነዚህ የልጅ ልጅ ሁሉ እየመጡ ሰላምታ ሰጡን። እህል የምንቀምስበት ጊዜ አላገኘንም። ሌሊት ስንኳ ወደ ተኛንበት ስፍራ እየመጡ እንኳን ደኅና ገባችሁ ይሉን ነበር። ያ ወዳጄ ልቤም ስልችት አለው። ከዚያው ሀገር በኖርነ ይሻለን ኑሯልን አለኝ።

አላስቆም አላስቀምጥ ብለህ ከዚህ ያደረስከኝ አንተ አይደለህምን፤ ይኸውም ሲያንስህ ነው አልሁት።

ወንድሜ ሆይ፤ እኔ አንተን እጎዳለሁ ብዬ የሠራሁት ሥራ የለም። ሲሆን ቢውል በራሴ ክፉ እመከራለሁ፣ ያንተ መከራ የእኔ ሳይሆን ቀርቶ ነውን። ይልቅስ እንግዲህ ወዲህ በሆነ ባልሆነው እየተበሳጩ ከመቀመጥ የመጣውን ነገር ሁሉ በምሥጋና መቀበል ይሻላል አለኝ።

ለሁሉም ነገር የጌታዬ የተቀደሰ ፈቃዱ ይሁን አልሁት።

ከዚህም በኋላ ወዳጄ ልቤ እንደ መከረኝ ለክፉውም፣ ለመልካሙም ነገር ለእግዚአብሔር ምስጋና እየሰጠሁ ንብረት በሚባለው ሀገሬ ተቀመጥሁ።

ከዚህ ላደረሰን ለእግዚአብሔር ምስጋናና ክብር ይሁን። ዛሬም፣ ዘወትርም ለዘላለም።

# ክፍል ፪ ለልጅ ምክር

## ለአባት መታሰቢያ

## መቅድም

የተወደድህ ልጄ ወዳጄ ፈቃደ ሥላሴ ሆይ፤ እግዚአብሔር ብዙ ተባዙ ብሎ በተናገረው ቃል ኪዳን አባቴ እኔን ከወለዱኝ በኋላ እንዳይርበኝ አብልተው፤ እንዳይጠማኝ አጠጥተው፤ እንዳይበርደኝ አልብሰው፤ ሌላውንም በሕፃንነቴ ወራት የሚያስፈልገኝን ሁሉ ሰጥተው ይልቁንም ካደግሁ በኋላ ሰውነቴን የምረዳበት፤ ንብረት የምይዝበትን፤ የንባብ የጽሕፈት ትምህርት እያስተማሩ ስለ አሳደጉኝ እኔም

በእርጅናቸው ወራት በሚቻለኝ ነገር ሁሉ እየረዳሁና እየጦርሁ ብድራቸውን መመለስ ይገባኝ ነበረ።

ነገር ግን እኔ ከሕፃንነት ወደ ጎልማሳነት ሳልደርስ እርሳቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው ስለ ሔዱ ብድራቸውን ሳልመልስ ቀረሁ።

የተወደድህ ልጄ ሆይ፤ አባቴ እስካሁን በሕይወተ ሥጋ ቆይተው እኔ ልጃቸው ሚስት ሳገባ፤ ንብረት ስይዝ፤ ልጆችም ስወልድ አይተውኝ ቢሆን ያ በዕድሜ ያረጀው ሰውነታቸው በደስታ ይታይስ ነበረ።

እኔም ጧት ስወጣ ማታ ስገባ በረከታቸውን እየተቀበልሁ ልቤ እንደ መልካም አምባ ይታመንባቸው ነበረ።

ነገር ግን የእግዚአብሔር አሳብና የሰው አሳብ እንደ ሰማይና እንደ ምድር የተራራቀ ነውና እርሱ የተቀደሰውን አሳቡን አድርጎ በኋለኛው ቀን እስከናገኝ ድረስ በዚህ ዓለም ተለያይተን ቀረን።

የተወደድህ ልጄ ሆይ፤ አባቴ በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ስለ እኔ በደከሙት ድካም ሁሉ እኔ አሁን በሰማይ ወሮታቸውን ለመመለስ የማይቻለኝ ነገር ሆነ።

ስለዚህ ቀድሞ በእርሳቸው ብርታትና ድካም ተምሬ ባገኘሁት እውቀት ላንተ ለልጄ የጻፍሁልህን ይህን መጽሐፍ በዚህ ዓለም ለስማቸው መታሰቢያ እንዲሆንልኝ ብዬ ጽፌዋለሁ።

ስለ አንተም ይህን መጽሐፍ መጻፌ እግዚአብሔር ያስበልህ ዘመን ባጭሩም እንደ ሆነ በረጅሙም እንደ ሆነ አውቄው አይደለም።

ነገር ግን እኔ ያሰብኩልህን ላደርግልህና እግዚአብሔር ደግሞ ያሰበውን ያድርግልህ ብዬ ነው።

ይህም አሳቤ ስለ ወንድሞችህና ስለ እኅቶችህም ሁሉ ነው እንጂ ስለ አንተ ብቻ አይደለም።

የተወደድህ ልጄ ሆይ፤ ሰው ሁሉ በዚህ ዓለም የሚኖርበት ዘመኑ እጅግ አጭር ነው። ከዚያውም የሚበዛው በመከራና በኃዘን ይፈጸማል።

ይህንንም መከራና ኀዘን አንዳንድ ሰዎች በገዛ እጃቸው ፈልገው ያመጡታል። አንዳንድ ሰዎች ግን ሳያስቡት በድንገት ይመጣባቸዋል። መከራና ኀዘን በገዛ እጃቸው ፈልገው የሚያመጡ እንዴት ያሉ ሰዎች ናቸው ትለኝ እንደ ሆነ ስማኝ ልንገርህ።

አንዳንድ ሰዎች የሰው ገንዘብ ሊሠርቁ ሔደው እዚያው ይሞታሉ ወይም ተይዘው ይቀጣሉ።

አንዳንድ ሰዎች የሰው ሚስት ለመቀማት ሔደው እዚያው ላይ ይሞታሉ ወይም ይቆስላሉ።

አንዳንድ ሰዎች ሰድውን ለማጥፋት የሐሰት ነገር ይዘው ይነሡና ባወጡት ዳኛ በቁጥሩ ምስክር ተረተው ይቀጣሉ። አንዳንድ ሰዎች የሰው ማኅተም አስመስለው ቀርጸው አትመው በውስጡም የሐሰት ቃል ጽፈው ይገኙና ይቀጣሉ።

አንዳንድ ሰዎች አይታወቅብንም አይሰማብንም ብለው ንጉሥ ለመግደል መንግሥት ለማጥፋት ሲመከሩ ይገኙና ብርቱ ቅጣት ይቀጣሉ።

አንዳንድ ሰዎች ለኩራትና ለትዕቢት ብለው አንበሳና ዝሆን ለመግደል በረሃ ይወርዱና በበረሃ በሽታ ይሞታሉ ወይም ያው ለመግደል የፈልጉትን አውሬ ይገድላቸዋል።

እነዚህን የመሰሉ በገዛ እጃቸው መከራንና ኀዘንን በራሳቸው የሚያመጡ ብዙ ሰዎች አሉ።

ደግሞ ሳያስቡት በድንገት መከራና ኃዘን የሚመጣባቸው እንዴት ያሉ ሰዎች ናቸው ትለኝ እንደ ሆነ ስማኝ ልንገርህ።

አንዳንድ ሰዎች መሬታቸውን ሲያርሱ ሲዘሩ ከርመው አዝመራቸውን በረዶ የሚመታባቸው፤ አንበጣ የሚበላቸው ናቸው።

አንዳንድ ሰዎች ሲነግዱ ከርመው ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ በበረሃ ወምበዴ የሚነሣባቸው፤ በባሕር መርከብ የሚሰርበርባቸው ናቸው።

አንዳንድ ሰዎች በንግድም በእርሻም ቢሆን ወይም በማናቸውም ሥራ ቢሆን የሰበሰቡትን ገንዘብ እሳት የሚያቃጥልባቸው፤ ሌባ የሚሰርቅባቸው፤ ዘራፊ የሚዘርፍባቸው ናቸው።

አንዳንድ ሰዎች ባልሠሩት ሥራ ይከሰሱና ቆሞ የሚሚገት ጠበቃ ተቀምጦ የሚፈርድ ዳኛ ያጡና የሚታሰሩ ወይም ገንዘብ የሚከፍሉ ናቸው።

አንዳንድ ሰዎች የወለዱት የማያድግ፤ የዘሩት የማይበቅል፤ ያረቡት የማይባረክ የሆነባቸው ናቸው። እነዚህን የመሰሉ ሳያስቡ በድንገት መከራና ኀዘን የሚመጣባቸው ብዙ ሰዎች አሉ።

ላንተ ግን ይህን መጽሐፍ የጻፍሁልህ በፊት እንደ ተናገርኋቸው ሰዎች በገዛ እጅህ መከራንና ኅዘንን ፈልገህ እንዳታመጣ፤ ደግሞ ጥቅም ለማታገኝበትና ለማታገኘው ነገር ሰውነትህን እንዳታደክም ብዬ ነው። ሳያስቡት በድንገት ከሚመጣው መከራና ኅዘን ግን እግዚአብሔር ይጠብቅህ እንጂ ሌላ የምጽፍልህና የምመክርህ ነገር የለኝም።

ደግሞ በገዛ እጃቸው መከራንና ኅዘንን ፈልገው የሚያመጡ ሁለት ወገን ሰዎች አሉ።

አንደኛው ወገን ሃይማኖታችሁን ካዱ፤ ለጣዖት ስገዱ፤ የሚል ጠላት የመጣባቸው እንደ ሆነ ስለ ሰማያዊ መንግሥት ብለው በትዕግሥት ሆነው አንገታቸውን ለስለት፤ ጀርባቸውን ለግርፋት የሚሰጡ ሰዎች ናቸው።

ሁለተኛው ወገን ሀገራችሁን ልቀቁ የሚል ጠላት የመጣ እንደ ሆነ ሀገራችንን ለባዕድ አሳልፈን አንሰጥም ብለው ሰይፋቸውን መዘው፤ ጋሻቸውን መክተው፤ ጠመንጃቸውን አንግተው በሰልፍ መካከል ገብተው የሚዋጉ ሰዎች ናችው። የነዚህ የሁለቱ ወገኖች መንገድ ፍሬ ያለበትና የሚያመሰግን ነው።

ነገር ግን በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ይህንኑ አጭሩን ዘመናቸውን ያለ መከራና ያለ ኅዘን በደስታ የሚጨርሱ አንዳንድ የታደሉ ሰዎች አሉና እግዚአብሔር ቁጥርርህን ከነዚያ ጋር ያድርግልህ።

የተወደድህ ልጄ ሆይ፤ ይህን አሁን ወደ ፊት የምጽፍልህን መጽሐፍ ልብ ወለድ የጻፍሁልህ መስሎህ እንዳትነቅፈው እለምንሃለሁ፤ ነገር ግን ከመጻሕፍት ያነበብሁትንና ከሽማግሎችም፣ ከዐዋቆችም ሰዎች በየጊዜው የሰማሁትን ነገር ሁሉ ጽፌልሃለሁና አክብረህ ተቀበለው። በልብህም አስበው። ለወንድሞችህና ለእኅቶችህም ይህንኑ ነገር ንገራቸው።

ምናልባት እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ መጻሕፍትን ለማንበብና ከሽማግሎች ነገርን ለመጠየቅ ያበቃህ እንደ ሆነ የጻፍኩልህን ነገር ሁሉ ልብ ወለድ አለመሆኑን ታገኘውና ያን ጊዜ ታመሰግነኛለህ።

ደግሞም ከዚሁ ከምጽፍልህ ነገር አንዳንዱ ባንተ በራስህ ላይ ወይም በወዳጆችህ ላይ ሳይደርስ አይቀርምና ያን ጊዜ ለካ አባቴ የነገረኝ ነገር እውነት ኑርዋል ብለህ እኔን ሳታስበኝ አትቀርም። ነገር ግን ይህ ሳይሆንብህ አስቀድመህ የኔን ምክር ብትቀበል ይሻልሃልና ልዑል እግዚአብሔር አስተዋይ ልብና ሰሚ ጆሮ ይስጥህ።

አሜን።

በአብና በወንድ በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ አሜ።

# መጀመሪያ ክፍል

ልጄ ሆይ ፈቃድህ ሥላሴ፤ አሳብ አታብዛ፤ ወደ ፊትም ምን ነገር ይመጣ ይሆን ብለህ አትጨነቅ፤ ምንም አሳብና ጭንቀት ብታበዛ የሚሆን ነገር ሳይሆን አይቀርም።

ወደ ፊትም እሾማለሁ፤ እሸለማለሁ፤ ብለህ በአሳብህ ደስ አይበልህ። ለሰውም አትናገር፤ ምናልባት ከተናገርህ በኋላ ስታገኘው የቀረህ እንደ ሆነ ታላቅ ኀፍረት ይሆንብሃልና።

ወደ ፊት የሚያናድድ ሥራ አትሥራ። በገዛ እጅህም በሠራኸውና ባለፈው ሥራ አትናደድ።

ልጄ ሆይ፤ ጌታ ለመሆን ትፈልግ እንደ ሆነ ጌትነት ማለት ያለ አሳብና ያለ ጭንቀት መኖር ነው።

አሳብህም ሁሉ ከሞትህ በኋላ ወዲያኛው ዓለም ስለሚሆነው ስለ ነፍስህ ነገር ይሁን እንጂ በዚህ ዓለም በሥጋህ ስለሚሆነው ነገር እጅግ አትጨነቅ።

በዚህ ዓለም ኑሮህ ሁሉ እንደ እንስሳ ወይም እንደ ዛፍ ነው እንጂ ከእን እዚህ የበለጠ ኑሮ የለህም። እንደ ምን ትለኝ እንደ ሆነ፤ እነሆ እንስሳ ተወልዶ ሣር እየበላ ውኃ እየጠጣ ያድጋል። ኋላም ያረጅና ይሞታል። ወይም ገና ሳያረጅ ሰው ይገድለዋል። ዛፍም ከመሬት ይበቅላል፤ ያድጋል፤ ኋላም ይፈራል። ከብዙ ዘመን በኋላ ግን ያረጅና በገዛ እጁ ነግሎ ይወድቃል ወይም ገና ሳያረጅ ለቤት ሥራ ወይም ለማገደድ አንድ ሰው ይቆርጠዋል።

ሰውም እንደዚሁ ከአባት ከእናቱ ተወልዶ ያድጋል፤ ልጆችም ይወልዳል። ካደገ በኋላ ግን ያረጅና ይሞታል ወይም ገና ሳያረጅ ባንድ በሽታ ወይም በጠላቱ እጅ ይሞታል።

ደግሞ ከእንስሳና ከዛፍ ወገን ለክብር የሚሆን ለጎሣርም የሚሆን አለ። ከእንስሳ ወገን ለክብር የሚሆነው በነገሥታትና በመኳንንት ቤት ገብቶ በወርቅና በብር ዕቃ እየተጫነ፤ ግምጃ እየለበሰ፤ ጨው እየላሰ፣ ድንገሎ እየዋጠ ይኖራል። ለጎሣር የሚሆነው ግን በነጋዴ እጅ ገብቶ ጀርባው እሲመለጥ እየተጫነ፤ በደጅ እየቆመ፤ መሬት ሲግጥ እያደረ፤ ገለባ እየቃመ ይኖራል።

ከዛፍም ወገን ለክብር የሚሆነው የቤተ መንግሥት ሠረገላና ዐምድ ሁኖ ቀለም እየተቀባ፤ በግምጃ እየተሸፈነ ይኖራል።

ለኀሣር የሚሆነው ግን ላር ወይም ለማገዶ ተቆርጦ በእሳት እየተቃጠለ ዐመድና ከሠል እየሆነ ይቀራል።

ከሰውም ወገን እንዲሁ ለክብር የሚሆን ለኀሣርም የሚሆን አለ። ለክብር የሚሆን ነግጄ አተረፍሁ፤ አርሼ አመረትሁ፤ ዘምቼ ማረክሁ ሳይል ሥራ ሳይሠራ ሳይደክም እንዲያውም በድንገት ጌታ ሆኖ በተድላና በደስታ ይኖራል። ለኀሣር የሚሆነው ሰው ግን ቢነግድ ትርፍ ያጣል፤ ቢያርስ አንበጣ ይበላበታል፤ በረዶ ይመታበታል፤ ከብት ቢያረባ ይሞትበታል፤ ቢዝምት ይቆስላል፤ በመጨረሻውም ሁሉም ከመሬት የተገኙ ናቸውና ሁሉም ወደ መሬት ይመለሳሉ። ስለዚህ በዚህ ዓለም በሚሆነው ነገር ሁሉ አትመካ።

ልጄ ሆይ፤ የሆነውን ነገር ተናገር እንጂ ገና የሚሆነውን ነገር አትናገር። ሌሎችም ሰዎች ገና የሚሆነውን ነገር ቢነግሩህ አትመናቸው። ክፉ የሚሠራ እንዲጐዳ ደግ የሚሠራ ግን እንዲጠቀም የታወቀ ነውና፤ ደግ ሥራ እየሠራህ ብቻ ወደ ፊት የሚሆነውን ነገር ጠብቅ። ነገር ሁሉ ጊዜው ሲደርስ በግድ ይፈጸማል እንጂ ጊዜው ሳይደርስ አይፈጸምምና ለማናቸውም ነገር ቢሆን አትቸኩል።

ልጄ ሆይ፤ ወደ ፊት እንደዚህ ያለ መከራ ያገኘኛል ብልህ አትጨነቅ፤ ነገር ሁሉ የሚሆነው በእግዚአብሔር ፈቃድ ነውና እርሱ በፈቃዱ ያመጣው አይቀርልህም፤ ያለ እርሱ ፈቃድ የሚመጣው አያገኝህም፤ እነሆ ይህንንም በምሳሌ አስረዳሃለሁ። ከገደል አፋፍ በሚወጣ ምንጭ ላይ አፈር ወይም ጉድፍ ቢጨምሩበት ምንጩ በውስጥ እየገፋ ውኃው እየጠራ ይወርዳል እንጂ አይደፈርስም። እንደዚሁ ሁሉ የውስጥህን የሚያውቅ እግዚአብሔር ካልፈረደብህ ንብረትህ እየሰፋ ጠላትህ እየጠፋ ይሔዳል እንጂ፤ ምንም ክፉ ነገር አይመጣብህምና አትጨነቅ።

ደግሞ በኩሬ ውኃ ወይም በጉድጓድ ውኃ ውስጥ አፈር ወይም ጉድፍ ቢጨምሩበት የውኃው ሽታ እየተለወጠ ውኃው እየደረቀ ይሔዳል እንጂ ውኃው ጥሩ አይሆንም።

እንደዚሁ ሁሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ የመጣውን መከራ በጉልበቴ ወይም በእውቀቴ አስቀረዋለሁ ብሎ መጣጣር በመከራ ላይ መከራ ለመጨመር ነው እንጂ፤ ሌላ ትርፍ ነገር አይገኝበትም።

# ሁለተኛ ክፍል

ልጆ ሆይ፤ ይህ ዓለም ቀድሞ ከወዴት መጣ ኋላስ ወዴት ይሔድ ይሆን ብለህ ለመመርመር አትጨነቅ። እንኳን የዓለምን ነገር የራስሕንም ነገር መርምረህ ለማወቅ አትችልም። አሳብህም ሁሉ ለዛሬ ብቻ ይሁን እንጂ ላለፈው ቀን ለትናንቱ፤ ወይም ለሚመጣው ቀን ለነገ አታስብ።

ልጆ ሆይ፤ ወዳጅ ማለት ሰው አይምሰልህ። ነገር ግን ወዳጅ ማለት ጊዜ ነውና በጊዜው ሁሉ ይወድሃል፤ አለጊዜህ ግን ወዳጅህ እንኳ ይጠላሃል። ጊዜ ማለትም ቀንና ሌሊት አይምሰልህ። ነገር ግን ጊዜ ማለት የእግዚአብሔር አሳብ የሚፈጸምበት ነው። ስለዚህ በሆነውም በሚሆነውም ነገር ሁሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን እያልህ ተቀመጥ።

ልጆ ሆይ፤ ብዙ ተድላና ደስታ ለማድረግ አትጨነቅ፤ ይህንን ለማድረግ የፈለግህ እንደ ሆነ ግን ለሰው መራራትና ደግነትን አታገኛቸውም። ስለዚህ ተድላና ደስታህ በልክ ይሁን፤ ዕድሜህም ያለ ኀዘንና ያለ መከራ በደስታ ብቻ ለመጨረስ አይሆንልህም። ነገር ግን ኀዘንና ደስታ ከባሕርይህ ጋር ባንድነት ተዋሕደው የሚኖሩ ናቸውና በዕድሜህ ሙሉ ሁለቱም በየተራ ታገኛቸዋለህ፤ ካልሞትህም በቀር ከኀዘንና ኃጢአት ከመሥራት አትድንም።

ልጆ ሆይ፤ መቅሠፍት ይመጣብኛል ብለህ አትጨነቅ። ትልቅ መቅሠፍት ማለት አሳብ ማብዛት ነው።

ልጆ ሆይ፤ የሰውን ነገር ችሎ ለማይኖርና አሳብ ለሚያበዛ ከኀጢአቱም ለማይመለስ ሰው ቶሎ መሞት ይሻለዋል።

ልጆ ሆይ፤ ደጉን ሰው ለማጥፋት አታስብ፤ ደጉን ሰው ለማጥፋት ብታስብ ግን ራስህን ጨምረህ ታጠፋለህ። ለሌላ ሰውም የክፋትን መንገድ አታስተምር። ፈጣሪህም እግዚአብሔር እንደ ሆነ እመን። ነገር ግን የርሱን መጀመሪያና መጨረሻ መርምሬ አገኘዋለሁ ብለህ አትጨነቅ።

ልጆ ሆይ፤ ሰው ባጭሩም ቢሆን በረጅሙም ቢሆን፤ በዚያው በዘመኑ ለራሱ ደስ ብሎት ካልኖረ፤ ከእርሱ በኋላ ለሚነሡት ለልጆቹ ወይም ለዘመዶቹ ገንዘብ ቢሰበስብ ምንም ትርፍ የለውም።

ሰው ሁሉ እርሱ ከሞተ በኋላ በሰማይ በሚያገኘው ነገር ደስ ይለዋል እንጂ ደክሞ ሰብስቦ በዚህ ዓለም በተወው ገንዘብ ደስታ የለውም።

ልጄ ሆይ፤ ለንስሓ ዕድሜ ስጠኝ ብሎ ወደ እግዚአብሔር መለመን ደግነት ወይም ክርስቲያንነት አይምሰልህ። ነገር ግን ለንስሓ ዕድሜ ስጠኝ ብሎ መለመን በሕፃንነቴ ወራት እንደ ልቤ ኃጢአትን ሁሉ ስሠራ ኖሮ ስሸመግልና ኃጢአትን ለመሥራት ጉልበቴ ሲደክም ያንጊዜ ንስሐ እገባለሁ ማለት ነው።

ትርጓሜውንም ገልጬ ብነግርህ ለንስሐ ዕድሜ ስጠኝ ብሎ መለመን የዚህን ዓለም ተድላና ደስታ፤ ፍትወትንም ሁሉ ሳልጠግበው አትግደለኝ ማለት ነው።

ልጄ ሆይ፤ አንተ ግን ከሚስትህና ከልጆችህ፤ ከዘመዶችህና ከወዳጆችህ ጋራ በዚህ ዓለም ደስ ብሎህ እንድትኖር ዕድሜ ስጠኝ ብለህ ለምን እንጂ፤ ለንስሐ ዕድሜ ስጠኝ ብለህ አትለምን። ሲሸመግሉና ሲደክሙም ኃጢአት መሥራትን መተው የሚያጸድቅ አይምሰልህ።

ሰውም ተወልዶ እስኪሞት ድረስ ምንም ቢሆን ኃጢአት ንጹሕ ሆኖ አይገኝምና በየጊዜው ንስሐ ግባ እንጂ፤ ለንስሐ የሽምግልና ጊዜ ብቻ አትጠብቅ።

ልጄ ሆይ ለባሕርይህ የሚያስፈልግህን ሁሉ አድርግ፤ ለሌላውም ሰው ለባሕርዩ የሚያስፈልገውን አትከልክል። ለሰው ባሕርይ ከሚያስፈልገው ነገር ሁሉ ዋኖቹ ሦስት ናቸው። መጀመሪያው ምግብና መጠጥ ነው፤ ሁለተኛው ልብስ ነው፤ ሦስተኛ ሚስት ናቸው። ሰው እነዚህን ሦስቱን ካላገኘ ኑሮው ሁሉ ጐድሎ ይሆናል።

ደግሞ ሰው ምንም ክፉ አድራጊ ቢሆን ምግብና መጠጥ ከልክሎ መቅጣት አይገባም።

ልጄ ሆይ፤ ጠላትህ ሲሞት ወይም ሌላ መከራና ጭንቀት ሲያገኘው ደስ አይበልህ። እርሱ ሞቶ አንተ በዚህ ዓለም አትቀርምና አንተ ደግሞ በሠራኸው ሥራ እንደ እርሱ መከራና ጭንቀት ሳይገኝህ አይቀርም፤ በመከራና በሞትም የሰው ሁሉ ድርሻው ትክክል እንደ ሆነ እወቅ።

ልጄ ሆይ፤ ነውርህን ለብቻህ የሚነግርህ ሰውን አትጥላው፤ አንተም በወዳጅህ ላይ ነውር የሚሆን ነገር ያየህበት እንደ ሆነ ለብቻህ አድርገህ ንገረው። ለሌላ ሰው ግን አትንገርበት።

ልጄ ሆይ፤ በየጊዜው በሰውነትህ ውስጥ የሚነሣውን አሳብ ደግና ክፉ መሆኑን ሳትመረምር ያሰብኸውን ሁሉ ለመፈጸም አትቸኩል። በዚህ ዓለም እግዚአብሔር የሚሰጠን በረከት ሁሉ እጅግ መልካም ነው። ነገር ግን ከስጦታው ሁሉ ሚስትና ልጆች መስጠቱ እንዲበልጥ እወቅ።

ልጄ ሆይ፤ አንተ ራስህ የምትጠቀምበት ወይም ወዳጅህ የሚጠቀምበት ነገር ካልሆነ በቀር ሰው እንዲያመሰግነኝ ብለህ ሰውነትህን አታድክም። ሰውም በከንቱ ቢያመሰግንህ ደስ አይበልህ። አመስጋኙም ተመስጋኙም ሁለቱም ይሞታሉና ደስ አይበልህ።

ልጄ ሆይ፤ በነገርህ ሁሉ የታመንህ ሁን። ባነጋገርህም ደማም ሁን ሰውን የሚያስፈራና ሰውን የሚያሳዝን ነገር ለመናገር አትድፈር። በልዝብ ምላስ ሰውን አታታል። ሰውንም ከሚያሙ ሰዎች ጋር አትደባለቅ።

ልጄ ሆይ፤ ንብረትህ በልክ ይሁን። ቤተ ሰዎችም አታብዛ የቀንድ ከብትና የጋማ ከብትም በብዙ አታርባ። ላንተ የማይገባህን ነገር ከማንም ቢሆን አትቀበል።

አንተም ለማንም ቢሆን የማይገባውን ነገር አትስጥ።

የማታገኘውንም ነገር አትመኝ። ባይንህ ካላየህና እርግጥ መሆኑን ካልተረዳኸው በቀር በማንም ሰው ላይ የሚወራውን ወሬ እውነት ነው ብለህ አትቀበል።

ለሰውነትህ የሚያስፈልገውን ነገር ለማግኘት አስብ እንጂ ሰው የሚጠፋበትን፤ ሰው የሚጨነቅበትን ነገር አታስብ።

ልጄ ሆይ፤ ሮጠህ ለማታመልጠው ነውገር አትሸሽ። እርሱም ሞት ነው። ደጋ ብትወጣ፤ ቆላ ብትወርድ፤ ወንዝ ተሻግረህ ብትሔድ፤ በዋሻ ብትደበቅ፤ ጠመንጃና መድፍ ይዘህ ብትሰለፍ ምንም ቢሆን ከሞት ለማምለጥ አትችልም።

እግዚአብሔርንም ፍራ፤ በሥጋና በነፍስህ ላይ ሥልጣን አለውና።

ንጉሥንም አክብር፤ እግዚአብሔር ሰይፍን አስታጥቆታልና።

ባንተም ላይ የሹመት ሥልጣን ያላቸውን ሀገረ ገዢዎችን ሁሉ አክብራቸው፤ ታዘዝላቸው። አባትና እናትህን፤ የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስተምሩ መምህሮችህን፤ ያገር ሽማግሎችና ባልቴቶችን ሁሉ በሚቻልህ ነገር እርዳቸው።

ልጄ ሆይ፤ ካረጀህ በኋላ እንደ ገና ተመልሼ ምነው ልጄ በሆንሁ ብለህ አትመኝ። ምንም ቢሆን አታገኘውምና።

ወደ ፊትም ምነው በሞትሁ ብለህ አትመኝ፤ ምንም ቢሆን አይቀርልህምና።

ልጄ ሆይ፤ እገሌ ቸር ነው ይበሉኝ ብለህ ገንዘብህን ለማንም አትስጥ። ለወዳጅ ከመስጠት ለዘመድ መስጠት ይሻላል ለጠላትም ከመስጠት ለወዳጅ መስጠት ይሻላል።

ከሁሉ ይልቅ ለተቸገሩ ድኆች መስጠት ይበልጣል። ለድኆች የሰጠው ሰው ብድሩን በሰማይ ያገኛል። ልጄ ሆይ፤ ማናቸውንም ነገር ቢሆን ለመስማት እንጂ ለማውራት አትቸኩል። ከወዳጅህም ጋር በተጣላህ ጊዜ ቀድሞ በወዳጅነታችሁ ጊዜ የንገረህን ምስጢር አታውጣበት።

ከወዳጅህም ጋራ አንድ ጊዜ ጠብ ከጀመርሁ በኋላ፤ ምንም ብትታረቅ ሁለተኛ ምሥጢር ለእርሱ ለመናገር አትድፈር። ቂምህንም አትርሳ። ቂምህን አትርሳ ማለቴ ከታረቅህ በኋላ ክፉ አድርግበት ማለቴ አይደለም። ነገር ግን እርሱ ሞትንና ኩነኔን የማያስብ ክፉ ሰው የሆነ እንደ ሆነ ዕርቅ አፍርሶ እንዲያጠፋ ሳትዘነጋ ተጠንቅቀህ ተቀመጥ ማለቴ ነው።

ልጄ ሆይ፤ ከሚያሸንፍህ ሰው ጋራ አትጣላ። ሐሰት ነገርም ይዘህ በዳኛ ፊት አትቅረብ።

ልጄ ሆይ፤ ሰው አንድ ጊዜ ከሞተ በኋላ፤ ሁለተኛ አይገኝምና ምንም ቢሆን ሰውን ለማጥፋት አታስብ።

አካሉም ከተቆረጠ በኋላ ሁለተኛ እንደ ዛፍ አያቆጠቁጥምና የሰውን አካላ ለማበላሸት አታስብ። በማንም ሰው ላይ አትቆጣ።

ስለ ሃይማኖቱና ስለ ምግባሩም ቢሆን፤ ስለ ምግቡና ስለ ልብሱ ልዩነትም ቢሆን በማናቸውም ምክንያት ቢሆን አትቆጣ።

እግዚአብሔር ለሁሉም ፀሐይን አውጥቶ፤ ዝናሙን አዝንሞ፣ ሁሉም እንደ ጠባያቸው ያኖራቸዋልና አንተም የእግዚአብሔር ልጅ እንድትባል ሁሉንም እንደ ጠባዩ ውደደው እንጂ አትጥላው።

ልጄ ሆይ፤ ለልጆቼና ለዘመዶቼ ላሽከሮቼና ለገረዶቼ ደስ ይበላቸው ብለህ፤ ድኃ እያስለቀስህ የግፍ ገንዘብ እየሰበሰብህ አትስጣቸው። እነዚህ ሁሉ አንተ ደክመህ የሰበሰብኸውን የግፍ ገንዘብ ይበላሉ እንጂ በወዲያኛው ዓለም በነፍስህ ላይ ከሚመጣው መከራ አያግዙህምና የግፍ ገንዘብ እየሰበሰብህ አትስጣቸው።

ልጄ ሆይ፤ ማንም ሰው ቢሆን ባንተ ላይ የሐሰት ወሬ ሲያወራብህ የሰማህ እንደ ሆነ ታገሠው። መታገሥ ባትችሎ ግን ጠብህን በግልጥ አድርገውና ሰው ሁሉ ይወቀው። ጠብህን ካስታወቅህ በኋላ፤ ምንም ክፉ ወሬ ቢያወራብህ እውነት ነው ብሎ የሚቀበለው ሰው አይገኝም።

ማንንም ሰው ቢሆን በአግቦና በሽሙት አትናገረው አንተንም በአግቦና በሽሙጥ ቢናገርህ ወደ ዳኛ ሔደህ አትከሰስ። ርስትና ጉልትህን የሚነቅል፤ ገንዘብህን የሚቀማ፤ ሰውነትን የሚያጠፋ ነገር ካልመጣብህ በቀር በማናቸውም ባሉባልታ ነገር ወደ ዳኛ አትሒድ።

በወዳጅህም ላይ በቶሎ አትቆጣ። ነገር ግን ብዙ ጊዜ እያሳለፍህ መጨረሻውን ተመልከተው።

ልጄ ሆይ፤ ነገርህ እረጅም አይሁን። ለማድረግም የማትችለውን ነገር አደርጋለሁ አትበል። ከጐረቤቶችህ ጋራ ተስማምተህ ኑር።

ልጄ ሆይ፤ ሰልፍ ለኃይለኞች፤ ሩጫም ለፈጣኖች፤ ባለጠግነትም ለሠራተኞች አይደለም። ነገር ግን ሁሉንም ጊዜ ያጋጥማቸዋል። ስለዚህ ሰውን ከመመልከትና ሰውን ከመጠበቅ ጊዜን መመልከትና ጊዜን መጠበቅ ይሻላል።

ልጄ ሆይ፤ የአንበሳና የነብር የሌሎቹንም አራዊት ግርማ ከመፍራት ይልቅ፤ እግዚአብሔርን የማይፈሩ የክፉ ሰዎችን ፊት ፍራ። የዱር አራዊት ለመግደል ካልፈለጓቸው እነርሱ ፈልገው አይመጡም። ክፉ ሰዎች ግን ሰውን ፈልገው ካላጠፉ እንቅልፍ አይወስዳቸውም። ከተሳለ ጦር ይልቅ የክፉ ሰዎች ምላስ ጠልቆ ይወጋል።

# ሦስተኛ ክፍል

ልጄ ሆይ፤ ለባዕድ አትበለጥ። ምንም ቢከፋ ዘመድ፤ ምንም ቢጠም መንገድ የተባለውን ምሳሌ አትርሳ። የባዕድ ፍቅር እስከ ጊዜው ነው፤ የዘመድ ፍቅር ግን እስከ ጊዜ ሞት ድረስ ነው።

ልጄ ሆይ፤ ለሁሉ ጊዜ አለው ብሎ ሰሎሞን የተናገረው አትርሳ። ይህንም ነገር ለማስረዳት ሌላውን ነገር ሁሉ ትቼ የጌታችንን ነገር እጽፍልሃለሁ።

አይሁድ በጌታችን ላይ በቅናት የተነሡበት ገና ሲጸነስ ጀምሮ ነው። ከዚያ ጀምሮ እስከ ሠላሳ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ድረስ ጌታችንን ለመግደል ያስቡና ይመከሩ ነበረ።

ጌታችንም በየምኵራባቸውና በቤተ መቅደሳቸው በግልጥ ሲያስተምር ነበረ። ግን ግዜው እስቲደርስ በርሱ ላይ እጁን ያነሣበት ሰው አልነበረም።

ጊዜው በደረሰ ጊዜ ግን እውነቱን ሐሰት፤ ጽድቁን ኀጢአት፤ ብርሃኑን ጨለማ አድርገው ቢነሡ ነገሩ በቶሎ ተፈጸመላቸው። ይህም ጊዜው ስለ ደረሰ ነው።

ጌታችንም አይሁድ ሊይዙት በመጡ ጊዜ እንደዚህ ብሎ መለሰላቸው፤ ሁል ጊዜ በመቅደስ ከናንተ ጋራ ነበርሁ። እጃችሁንም አልዘረጋችሁብኝም። ነገር ግን ይህች ጊዜያችሁ ናት፤ የጨለማውም ሥልጣን። ሉቃስ ፳፪፥ ፶፫።

ጌታችን እንዲህ ማለቱ ማናቸውም ነገር ቢሆን በጊዜው ይፈጸማል እንጂ ከጊዜው አያልፍም ሲል ነው። ስለዚህ ጊዜን አልፋለሁ በለህ አታስብ፤ ግን በኃጢአት የመጣውን ክፉ ጊዜ በንስሐ ለማሳለፍ ይቻላል። ልጄ ሆይ፤ እኔ ድግ ሰው ነኝና ጠላት የለብኝም በለህ አትናገር። ጠላቶችም የሚነሡ በክፉ ሰው ላይ ብቻ አይምሰልህ። ግን አንተ ደግ ሰው ሆነህ ጠላቶች ቢነሡብህ እግዚአብሔር ይረዳሃልና ምንም አትፍራ። ለጊዜው እንኳ ባይረዳህ ሊፈትንህ ነውና እግዚአብሔርን አትጠራጠር።

እግዚአብሔርን ከማይፈሩ ሰዎች ጋራ ባልንጀርነት አታድርግ። በክፉ ምክራችውም አትደባለቅ። ምንም ብትጨነቅ ሀገርህ የሚጠፋበትን ምክር አትምከር። ልጄ ሆይ፤ በሠራሁት ሥራ ትርፍ ነገር አላገኘሁም ብለህ ሥራህን አትተው።

ነገር ግን ባንዱ ወገን እንቢ ቢልህ በሌላው ወገን ፈትን።

ለሥራው ሁሉ ዕድል አለውና፤ እግዚአብሔር ድካምህን አይቶ ባንዱ ወገን ሳይረዳህ አይቀርም።

ልጄ ሆይ፤ ጦርነት የመጣብኛል ብለህ አትፍራ። ጦርነት በሰው ሁሉ ላይ ይመጣል እንጂ ባንተ ብቻ አይመጣብህም።

ነገር ግን ዋናው ጦርነት ማለት እግዚአብሔርን በማይፈሩ ንጉሥን በማያከብሩ፤ የራሳቸውን ጥቅም ብቻ በሚፈልጉ ሰዎች መካከል መኖር ነውና እንደዚያ ያለውን ጦርነት ፍራ።

ልጄ ሆይ፤ ክፉ ሕልም አለምሁ ብለህ አትደንግጥ። ደግ ሕልምም አየሁ ብለህ ደስ አይበልህ።

ሕልም ማለት የሰው አሳብ እንደ ሆነ እውቅ። እንኳን ሌሊት በሕልም ቀንም ባይን የታየ ነገር ሳይደረግ ይቀራል።

ደግሞ ሌሊት በሕልም፤ ቀንም ባይን ያልታየ ነገር እንዲያው በድንገት ይደረጋል። እግዚአብሔር ይሁን ያለው ነገር ጊዜውን ይጠብቃል እንጂ ምንም ቢሆን ሳይሆን አይቀርም።

ልጄ ሆይ፤ አካልህና ልብስህን ዘወትር ንጹሕ ይሁን። እጅህን ለሥራ፤ ዓይነህ ለማየት፤ ጆሮህን ለመስማት፤ ፈጣኖች አድርግ። አፍን ግን በጠንካራ ልጓም ለጉመህ ያዝ። አረጋገጥህ በዝግታ፤ አነጋገርህ በለዘብታ ይሁን። ያልነገሩህን አትስማ፤ ያልሰጡህን አትቀበል። ያልጠየቁህን አትመለስ። ሽቅርቅር አትሁን፤ ንብረትህ ጠቅላላ ይሁን፤ ምግብህና መጠጥህ በልክ ሆኖ ያው የጠዳና የጣፈጠ ይሁን። ምግብህና መጠጥህም የሚቀርብበት ዕቃ ሁሉ ንጹሕ ይሁን። የምትተኛበት አልጋና የምትቀመጥበት ስፍራ ከእድፍና ከጉድፍ ንጹሕ ይሁን። በእውነትና በሚገባ ነገር ሁሉ ይሉኝታ አትፍራ። የምትሠራው ሥራ ሁሉ የመንግሥት ሥራ ካልሆነ በቀር ፖለቲከኛ አትሁን። ልጄ ሆይ፤ በዚህ ዓለም ነግሥ በሥጋትና በአሳብ ከሚኖር ንጉሥ ይልቅ እግዚአብሔር የሰጠውን ዘመን ያለ ሥጋትና ያለ አሳብ የሚጨርስ ድኃ ይበልጣል።

ልጄ ሆይ፤ እግዚአብሔር የሚቀየምበት፤ ንጉሥ የሚቆጣበት፤ ሰው የሚጠፋበት ነገር ካልሆነ በቀር ያሰብኸውን ከማድረግ አትመለስ። ነገር ግን በዚህ ዓለም ለሥጋህ ጥቅም፤ በወዲያኛው ዓለም ለነፍስህ ጥቅም የሚሆን ነገር ካልሆነ በቀር ለስሜ መጠሪያ ይሆናል ብለህ ሰውነትህን እጅግ አታድክም።

ልጄ ሆይ፤ ወደቅሁ ብለህ እጅግ አትዘን፤ ደግ ሰው የሆንህ እንደ ሆነ ከወደቅህ በኋላ ትነሣለህና።

ደግሞ ተነሣሁ ብለህ በጣም ደስ አይበልህ። ክፉ ሰው የሆንህ እንደ ሆነ ከተነሣህ በኋላ፤ ትወድቃለህ።

ልጄ ሆይ፤ በሚስትህና በልጆችህ፤ በቤተ ሰዎችህም ላይ ጨካኝና ቁጡ አትሁን። ያለ ሥርዓት ሲኖሩ ዝም አትበላቸው። ግን አንተም ሰነፍ ትባላለህ። እነዚያም ላይ ቅጣትን ታመጣባቸዋለህ። ወረተኛም አትሁን፤ የሠራተኛም ደመወዝ አታስቀር፤ የንጉሥን ትእዛዝ ጠብቅ፤ በቆላ ሀገር አትኑር። ብዙ ሥራም አትጀምር፤ ነገር ግን ልብህ የወደደውን አንዱን ብቻ አጠንክረህ ሥራ።

ልጄ ሆይ፤ ጨቅጫቃና እልከኛ ሚስት፤ ትዕቢተኛና ልግመኛ አሽከር በቤትህ አታኑር። የዕለት ምግብና ልብስ ካልቸገረህ በቀር ሥጋና ቅቤ ለመብላት፤ ጠጅና ጠላ ለመጠጣት ጌት ለማጌጥ፤ ገንዘብ አትበደር። በኋለኛውም ወዳጅህ ፊት የቀድሞውን ወዳጅህን አትማ። በእኔም ጊዜ ይኸው ነው ብሎ ይታዘብኛል።

ልጄ ሆይ፤ የዚህን ዓለም ብልጥግና ወይም ንብረት ለማግኘት እጅግ አትድከም። ይህንንም ለማግኘት እጅግ አትሩጥ። እንኳን የዚህ ዓለም ክብር የወዲያኛውም ቢሆን እግዚአብሔር ለመረጠውና ለታደለ ነው እንጂ ለሮጠ አይሆንምና።

ልጄ ሆይ፤ ክፉ ሰው ሳለ ደግ ሰው በመሞቱ፤ ሥራ የሚሠራ ሳለ ሰነፍ ሰው በመከበሩ፤ እግዚአብሔር አድሎአዊ ነው ብለህ አትናገር።

በዚኢህም ነገር የጠለቀውን የእግዚአብሔርን ፍርድ ለመመርመር አታስብ። ነገር ግን በማናቸውም ምክንያት ብሆን የተሰወረውን ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር ብቻ ተውለት።

ልጄ ሆይ፤ ከጌታህ ጋራ ሳለህ በፍጹም ልብህ አገልግለው። ትእዛዙንም ጠብቅ። በፍጹም ልብህ ለማገልገልና ትእዛዙን ለመጠበቅ የማትችል የሆንህ እንደ ሆነ ግን ተሰናብተህ ሒድ እንጂ ጌታህን አታስቀይመው። ያለዚያ ግን ይቆጣና ይቀጣሃል። ወይም ደመወዝህን ቆርጦ ያስቀርብሃል።

ልጄ ሆይ፤ በቤተ ክህነት ለመኖር የወደድህ እንደ ሆነ መልካም ወደድህ፤ ነገር ግን ቄስ ወይም ዲያቆን ለመሆን አስብ እንጂ፤ ደብተራ ለመሆን አታስብ። ጠንቋይና አስማተኛም አትሁን። ምንም ጥንቆላ ብታበዛ፤ እግዚአብሔር ይሁን ብሎ የፈቀደውን ነገር ለማስቀረት ወይም አይሁን ብሎ የተናገረውን ነገር ለማድረግ አትችልም።

ወደ ጠንቋይ ቤት አስማተኛም አትሒድ። እግዚአብሔር መልካምም ያደርግልህ እንደ ሆነ ክፉም ያደርግ እንደ ሆነ ጊዜው ሲደርስ ሁሉም አይቀርም።

# አራተኛ ክፍል

ልጄ ሆይ፤ እግዚአብሔር በምድር ላይ የፈጠረውን ፍጥረት በሙሉ ባይሆን እንደ ተቻለህ መጠን በጥቂቱ መርምር። ፍጥረትንም በመመርመር ብዙ እውቀት ታገኛለህ። እነሆ መልካምና መጥፎ መሬት አለ፤ ከመልካም መሬት ወርቅ፣ ዕንቁ፣ ብር፣ ናስ፣ ብረት፣ ሌላም ይህን የመሰለ ሁሉ ይገኝበታል። ደግሞ ልብስና ለቤት ጌጥ የሚሆን ቀይና ጥቁር፣ አረንጓዴና ብጫ፣ ነጭና ሰማያዊ፣ ቀለም ሁሉ ይገኝበታል። ቢዘሩበት ያበቅላል፤ ቢተክሉበትም ያለመልማል።

መጥፎ መሬት ግን ቢዘሩበት አያበቅልም፤ ቢተክሉበትም አያለመልምም። በላይም ከእሾህና ከመጥፎ ደንጊያ በቀር አይገኝበትም። ከደንጊያም ወገን ለጌጥ የሚሆን ክቡር ደንጊያ ይገኛል። ደግሞ ልግንብ ወይም ለቅጥር የሚሆን ደንጊያ አለ። ደግሞ ለማናቸውም ጉዳይ የማይሆን ደንጊያ አለ። ከሣርም ወገን ለሽቱ፣ ለጉዝጓዝም፣ ለከብትም ምግብም፣ ለቤት ክዳንም የሚሆን መልካም ሣር አለ። ደግሞ ቢያሸቱት የሚገማ፣ ቢጐዘጉዙት የሚዋጋ፣ ለከብት ምግብ ቢያቀርቡት የሚረክስ፣ ለቤት ክዳንም ቢያደርጉት የሚያፈስ መጥፎ ሣር አለ።

ከወፎችም ወገን ድምጣቸው ያማረ ጠጉራቸው የለሰለሰ ይገኛሉ። ደግሞ ሲጮሁ እለቁ እለቁ ያሉ የሚመስሉ ጠጉራቸውም ለማየት የሚያስጠይፍ ወፎች አሉ።

ከእንስሳም ወገን የኋላ እግሩን እንኳ ቢይዙት የማይራገጥ ወይም የማይዋጋ ገራም እንስሳ አለ። ደግሞ ባጠገቡ ሰው የማያስቀርብ ተራጋጭና ተዋጊ እንስሳ አለ።

ከአራዊትም ወገን እንዲሁ ደግና ክፉ አይታጣም።

ከመላእክትም ወገን ደግና ክፉ አለ። ደጉ እንደ ሚካኤል እንደ ገብርኤል፤ ክፉው እንደ ዲያብሎስና እንደ ጭፍሮቹ።

ከሰውም ወገን ደግና ክፉ አለ። ደጉ እንደ ኖኅ፣ እንደ ኤርምያስ፣ እንደ ዮሐንስ መጥምቅ፣ እንደ ድንግል ማርያም፣ ክፉው እንደ ቃየል፣ እንደ ኤሳው፣ እንደ ይሁዳ አስቆሮታዊ።

ከመሬትና ከደንጊያ፣ ከወፍም፣ ከእንስሳም፣ ከአራዊትም፣ ከመላእክትና ከሰውም ወገን ደግና ክፉ መኖሩ እግዚአብሔር ደግና ክፉ እያደረገ ፈጥሮት ነው፤ ወይስ ከተፈጠረ በኋላ ካንዱ ይልቅ ላንዱ እያደላ ነውን፤ ወይስ ፍጥረት ሁሉ በገዛ ራሱ ደግና ክፉ ለመሆን ይችላልን ትለኝ እንደ ሆነ፤ ይህ እጅግ የጠለቀ ጉድጓድና የረቀቀ ምስጢር ነውና እኔ መርምሬ ላውቀው አልችልም። አንተም ይህን መርምሬ አውቃለሁ ብለህ አትድከም።

ልጄ ሆይ፤ ዘመዶችህና ወዳጆችህ ጐረቤቶችህና አሽከሮችህ በጠላትነት በተነሡብህ ጊዜ በራስህና በጊዜው እዘን እንጂ በነዚያ አትዘን። ኃጢአት ካልበዛ ጊዜው ካልደረሰ እንኳን ወዳጆችህ ጠላቶችህም ቢነሡ አይጐዱህም።

ልጄ ሆይ፤ ሰው ምንም ብልህና ዐዋቂ ቢሆን በራሱ ሥራ ብቻ ራሱን ችሎ እንዳይኖር እወቅ። ነገር ግን ሁሉም በየሥራው ጸንቶ እርስ በርሱ በሥራ ይፈላለጋል። ስለዚህ ሰውን ሁሉ አክብረህ ኑር እንጂ ሰውን አትናቅ። ሥራውንም አትንቀፍ።

ገበሬውን አትንቀፍ፤ ከነቀፍኸውም እህሉንና አታክልቱን ከእርሱ አትፈልግ።

ነጋዴውን አትንቀፍ፤ ከነቀፍኸውም ሐሩን፣ ምንጣፉን ሌላውንም የንግድ ዕቃ ከእርሱ አትፈልግ።

ወታደሩን አትንቀፍ፤ ከነቀፍኸውም ሀገርህን የሚያጠፋ፣ ነፍስህን የሚገድል ጠላትህ ሲመጣ ተዋጋልኝ አትበለው።

ካህኑን አትንቀፍ፤ ከነቀፍኸውም አስተምረው፤ አጥምቀኝ፤ አቁርበኝ አትበለው።

እረኛውን አትንቀፍ፤ ከነቀፍኸውም በቁርበቱ አትተኛ።

ፋቂውን አትንቀፍ፤ ከነቀፍኸውም በቁበቱ አትተኛ።

ሸክላ ሰሪውን አትንቀፍ፤ ከነቀፍኸውም የሸክላውን ዕቃ ሁሉ ከርሱ አትፈልግ።

ሸማኔውን አትንቀፍ፤ ከነቀፍኸውም ልብስ ሥራልኝ አትብለው።

ሌላውንም ይህንን የመሰለውን ሠራተኛ ሁሉ አትንቀፍ። ሁሉ እንደ ዕድሉ በየሥራው ጸንቶ ንብረቱን ጠብቆ እግዚአብሔርን አመስግኖ ይኖራል እንጂ አንተን የሚጐዳ ነገር የለበትም።

ልጄ ሆይ፤ ዋዘኛና ቀልደኛ አትሁን። በመከራ ለሚኖሩ ሰዎች ሁሉ የምታዝንና የምትራራ ሁን፤ በድኃ ላይ አትጨክን፤ ርስቱንና ቤቱንም በምክንያት አትውሰድበት፤ ለመጨረስም የማትችለውም ነገር አትጀምር። እሳትና የሞላ ውኃ አትድፈር። በማናቸው ነገር ከሚበልጥህ ሰው ጋራ ባልንጀርነት አትያዝ። ከዳኛ ጋራ ወዳጅ ሁን። በፊቱ በቆምህ ጊዜ እውነቱን እንዲፈርድልህ።

ከሀኪምም ጋራ ወዳጅ ሁን። በታመምህ ጊዜ ፈጥኖ እንዲመጣልህ።

ልጄ ሆይ፤ በልተህ ስትጠግብ ረኃብን፤ ስትበለጥግ ድኅነትን፤ ስትሾም ሽረትን፤ ሌላውንም ይህን የመሰለውን ሁሉ አትርሳ።

ልጄ ሆይ፤ ለሞተው ወዳጅህ ከማልቀስ ይልቅ በሕይወቱ ሳለ የክፋት ሥራ ለሚሠራ ወዳጅህ አልቅስለት።

ልጄ ሆይ፤ ባለጠጋ ሲወድቅ ሰው ሁሉ ይደግፈዋል፤ ድኃ ሲወድቅ ግን ሰው ሁሉ ወዲያው ይገፋዋል።

ባለጠጋ ቢከሰስ ሸንጐ የተቀመጠው ሁሉ ይሚገትለታል፤ ድኃ ሲከሰስ ግን በሸንጐ የተቀመጠው ሁሉ ይፈርድበታል።

መልካም ዳኛ በመካከላቸው የተቀመጠ እንደ ሆነ ግን ፍርዱን እንደ ፀሐይ ያበራለታል። ስለዚህ በምኖርበት ሀገር መልካም ዳኛ አያጥፉብህ።

ልጄ ሆይ፤ በማናቸውም ነገር ቢሆን ሞት አይቀርም። ነገር ግን በሰው ልጅ ከመውደቅ በእግዚአብሔር እጅ መውደቅ ይሻላል።

ለአፍህ መሐላ አታልምደው፤ እግዚአብሔር ስሙን ከንቱ ያደረገውን ሳይቀሥፈው አይቀርምና ስሙን በከንቱ አትጥራው።

ልጄ ሆይ፤ በዚህ ዓለም ኃይለኞች ገንዘብና ዕውቀት ሁለቱ ብቻ ናቸው። ገንዘብና ዕውቀት ያለው ሰው እስከ ጊዜው ደስ ብሎት ይኖራል። ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች ገንዘባቸውን በማይረባ ጉዳይና ሰውን በማጥፋትና ራሳቸውን ብቻ ለመጥቀም አድርገው ኃይላቸው ይደክማል። ገንዘባቸን ለንግድና ለድኃ፤ ዕውቀታቸውንም ለሥራና ለሰው ጥቅም የሚያደርጉ ሰዎች ግን በኃይል ላይ ኃይል እየጨመሩ ይኖራሉ። እነሆ ለዚህ አንድ ምስሌ እነግርሃለሁ፤ ነጭ ስንዴ በባለሚያ እጅ ሲሆን እጅግ ያማረና የጣፈጠ እንጀራ ይሆናል። በባለሚያ እጅ ያልሆነ እንደ ሆነ ግን እንደ ዘንጋዳ እንጀራ ይሆናል። ገንዘብና እውቀትም በደግ ሰው እጅ ሲገቡ ለመልካም ነገር ይሆናል። በክፉ ሰው እጅ ሲገቡ ግን ለጥፋት ነገር ብቻ ይሆናል።

ልጄ ሆይ፤ የምትሠራውን ሥራ ሁሉ ሰው ቢያየው ቢሰማውም አይጐዳኝም ብለህ ትሠራው እንደ ሆነ እንጂ አይታብኝም፤ አይሰማብኝም ብለህ አትሥራው። አንተ ምንም ተሰውረህ ብትሠራው ከተሠራ በኋላ መታየቱና መስማቱ አይቀርም።

ልጄ ሆይ፤ አንተ አስቀድመህ በሰው ላይ ላይ አትነሣ፤ ሰው ባንተ ላይ ቢነሣብህ ግን እንዳትሸነፍ ጠንክረህ መክት። እምነትህንም በእግዚአብሔር ላይ አድርግ።

ልጄ ሆይ፤ ሚስትህ ሰነፍ የሆነች እንደ ሆነ የቤትህን ሥርዐት አንተው ጠብቀህ ኑር እንጂ ለርሷ ፈቃድ አትስጣት።

ልባም የሆነች እንደ ሆነ ግን፤ የቤትህን ሥርዐት ሁሉ ለርሷ ልቀቅና አንተ በውጭ ሥራህን አሳምር፤ አንተ የውጭውን እርሷ የውስጡን ሥራ ብትሠሩ ትበለጥጋላችሁ።

ልጄ ሆይ፤ ሰው ሳይኖር ብቻህን ከሴት ጋር አትነጋገር። ባልዋም አለመኖሩን በደጅ ጠይቀህ ከደጅ ተመለስ እንጂ ወደ ቤት አትግባ። ሰው ሳይኖር ብቻህን ከሴት ጋር ንግግር የተነጋገርህ እንደ ሆነ ግን፤ ምንም ሌላ ምስጢር ባይኖራችሁ በመነጋገራችሁ ብቻ መጠርጠር አይቀርም።

ልጄ ሆይ፤ ለልጆችህ የምታወርሳቸው ብዙ ገንዘብ በሣጥን ውስጥ ከማስቀመጥ፤ አንተ በሕይወት ሥጋ ሳለህ ወደ ትምሕርት ቤት እየሔዱ እውቀትን እንዲማሩ ገንዘብህን ብትሰጣቸው ይሻላል። ባልዋም ለሞተባት ሴት አባታቸውም ለሞተባቸው ልጆች እጅህ አጭር አይሁን።

ልጄ ሆይ፤ ሚስትህ ያስቀናችህ እንደ ህ ኦነ ከቤትህ አስወጥተህ ስደዳት እንጂ የርሷን ነፍስ ወይም የሌላ ሰው ነፍስ ለማጥፋት አታስብ። እርሷን ወይም ሌላውን ሰው ገድለህ ኋላ ከመጠጠት እርሷን አስወጥተህ ሌላይቱን አግብተህ ብትኖር ይሻልሃል።

ልጄ ሆይ፤ በጌታህም ቤት ቢሆን በሌላም ሥፍራ ቢሆን ገንዘብ ወይም ሌላ ዕቃ ወድቆ ብታገኝ አታንሣ። ብታነሣውም መልሰህ ለጌታህ ወይም ለዳኛ ስጥ እንጂ ሰውረህ አታስቀር።

ልጄ ሆይ፤ በፍጹም ልብህ ለማትወደው ሰው ቤትህንና የቤትህን ዕቃ አታሳይ።

ልጄ ሆይ፤ ገንዘብን ለጠጅና ለጠላ ከማውጣት ለወተትና ለማር አውጣ። ለአረቄና ለስቢርቶ ከማውጣት ለጠጅና ለጠላ አውጣ። በጣም ካልቸገርህ በቀር ውኃ ብቻ አትጠጣ። ምሳህን እስክትጠግብ ብላ። ማታ ግን ምግብህም መጠጥህም በልክ ይሁን። ሥጋ ዘወትር አትብላ። የአታክልት ምግብ አዘውትር። በ፲፭ በ፲፭ ቀን የሚያስቀምጥ መድኃኒት ጠጣ። ሀኪሞች ያልመረመሩትን ዐዋቆች ነን የሚሉ ሰዎች የማሱትን ሥር፤ የበጠሱትን ቅጠል መድኃኒት ነው ብለህ ለመቅመስ እጅግ አትድፈር። ልክና ሚዛን ስለ ሌለው ሰውነት ይጐዳልና፤ ተጠንቀቅ።

ልጄ ሆይ፤ ከብዙ ሰዎች ጋራ ተቀምጠህ በምትበላበት ጊዜ፤ ቶሎ ቶሎ አትጉረስ። ቶሎ ቶሎም አትጠጣ፤ በቤትህ ውስጥና በሚስትህ ፊት ግን እስክትጠግብ ብላ። እስክትረካም ጠጣ። ነገር ግን እስክትጠግብ በልተህ፤ እስክትረካም ጠጥተህ ጥቂት የእንቅልፍ እረፍት ሳታደርግ ሥራ አትጀምር። ከቤትህም ወጥተህ አትሒድ። የእንቅልፍ እረፍት ለማድረግ ጊዜ የማታገኝ እንደ ሆነ ግን እስክትጠግብ አትብላ። እስክትረካም አትጠጣ።

ልጄ ሆይ፤ በዕድሜ ያረጀ ሽማግሌና ልጅ የሌለው ሰው ካልሆነ በቀር፤ ርስቱን ወይም ቦታውንና ቤቱን ቢያወርስህ አትቀበለው። ካልተቸገረና ካልተጨነቀ በቀር ርስቱን ለሌላ ሰው አያወርስምና በተቻለህ ነገር ርዳው እንጂ፤ ርስቱን አትውሰድበት።

ደግሞ በሙግትም ቢሆን በጉልበትም ቢሆን ድኃውን ከርስቱና ከቤቱ አታስወጣው። ዕዳም ቢኖርበት የሚከፍልበት ቀን ስጠው እንጂ በግድ ይዘህ ርስቱንና ቤቱን አታሽጠው።

ልጄ ሆይ፤ ንጹሕ አለመሆንህን እግዚአብሔር ያውቃልና በእርሱ ፊት ንጹሕ ነኝ አትበል። በንጉሥ ፊትም ብልህ ነኝ አትበል፤ የብልሃት ሥራ ሠርተህ አሳየኝ ያለህ እንደ ሆነ ታፍራለህና።

# አምስተኛ ክፍል

ልጄ ሆይ፤ ምንም የሹመት ፍቅር ቢኖርብህ፤ የፈረድህበት ሰው ጠላትህ ይሆናልና የዳኝነት ሹመት አትፈልግ። አንተ ሳትፈልግ ለዳኝነት ሹመት የተመረጥህ እንደ ሆነ ግን እውነተኛ ፍርድ የእግዚአብሔር የባሕርይ ገንዘቡ ነውና በዳኝነት ነገር ጠላትህን ለመጉዳትና ወዳጅህን ለመጥቀም እንዳታስብ ተጠንቀቅ። እውነትን በሐሰት ለውጠህ የፈረድህ እንደ ሆነ ግን የእግዚአብሔርን ገንዘብ ማጥፋት ነው። ይህንም በማድረግህ ባንተ ላይ ከሁሉ የበለጠ ፍርድ ይፈረድብሃል።

ልጄ ሆይ፤ ከኃይለኛና ከነገረኛ ሰው ጋራ አትጣላ። ከነገረኛና ከኃይለኛ ሰው ጋራ መጣላት በሚነድ እሳት ላይ ገለባ እንደ መጨመር ነውና ተጠንቀቅ።

ልጄ ሆይ፤ ለጌታህ ገንዘብ አታበድር። ከፈለኝ ባልኸው ጊዜ አንተ የምትጠፋበትን ምክንያት ይፈልጋልና።

ለተሚጋችም አታበድር። ከፈለኝ ባልኸው ጊዜ ነገር ፈልጎ ወደ ዳኛ ይወስድሃልና።

ልጄ ሆይ፤ ጠላት በዛብኝ፤ ምቀኛ አሴረብኝ ብለህ እጅግ አትጨነቅ። በዓለም የሚኖር ፍጥረት ሁሉ ጠላትና ምቀኛ አለበት እንጂ ባንተ ብቻ አይደለም። ከዚሁም በጥቂቱ እጽፍልሃለሁ።

በፍየል ነብር፤ በበግ ተኩላ፤ ባህያ ጅብ፤ በላም አንበሳ፤ በዓይጥ ድመት፤ በዶሮ ጭልፊት አለባቸው። ይህንንም የመሰለ ብዙ አለ። ሰውም እርስ በርሱ እንዲሁ ነው።

ስለዚህ የሚመታብህን ነገር ሁሉ በትዕግሥት ሆነህ ተቀበለው። በመጨረሻው ግን ሁሉ አላፊ ነውና ጠላቶችህ ሁሉ ያልፋሉ። ወይም አንተ አስቀድመህ ታልፍና ከዚህ ዓለም መከራና ጭንቀት ታርፋለህ።

ልጄ ሆይ፤ እስቲ ያለፉትን ሰዎች ሁሉ አስባቸው። እነዚያ ሁሉ ጀግኖች ሁሉም መሬት ሆነዋል።

እነዚኢያ ሁሉ ዓለመኞች፤ እነዚያ ሁሉ ቀልደኞችና ፌዘኞች፤ እነዚያ ሁሉ ግፈኞች፤ እነዚያ ሁሉ በድኃ ላይ የሚሥቁና የሚሣለቁ ሁሉም መሬት ሆነዋል።

እነዚያ ሁሉ ድኆች ሲበድሉ፣ ሲያዝኑ፣ ሲያለቅሱ ካንዱ ሀገር ወደ ሌላው ሀገር ሲሰደዱ፣ ሲራቡ፣ ሲጠሙ፣ ሲታረዙ የነበሩ መሬት ሆነዋል።

ስንት ሰዎች የነበሩ ይመስልሃል።

የድኃ እንባ ሲፈስ የወንዝ ውኃ የሚፈስ የሚመስላቸው ስንት ሰዎች ነበሩ።

ድኃ ሲጮህ ውሻ የሚመስላቸው ስንት ሰዎች ነበሩ።

ድኃ ታስሮ ወይም በሌላ ጭንቅ ነገር ተይዞ ሲሞት የወፍ ግልገል የሚሞት የሚመስላቸው ስንት ሰዎች ነበሩ።

ጉልበት ካለን ብለው በደካሞች ላይ ያሰቡትን ሁሉ የሚሰሩ ስንት ሰዎች ነበሩ።

ሰውን ለማጥፋት እጅግ የሚጥሩ ሰውን ካላጠፉ እንቅፍል የማይመጣላቸው ስንት ሰዎች ነበሩ።

ነገር ግን ከዚህ ቀድሞ የነበሩት ሁሉም መሬት ሆነዋል። ከመሬት የተገኘ ሁሉ መሬት ስለ ሆነ ወደ መሬትም የማይመለስ ስለሌለ እኛም ነገ እንደዚያው እንሆናለን።

ስለዚህ በማናቸውም ምክንያይት ቢሆን፤ የሰው ደስታውና አዘኑ እጅግ አጭር መሆኑን በጣም እወቀው።

ልጄ ሆይ፤ ማንም ሰው ቢሆን በኃጢአቱ ተይዞ ሲፈረድበት ባየህ ጊዜ እዘን እንጂ ደስ አይበልህ። ሰው ሆኖ ኃጢአት የሌለበት አይገኝምና በሰው የፈረድህ እንደ ሆነ ባንተም ይፈረድብሃል። ደግሞ ኃጢአቱ በሰው ፊት የማይገለጥበት ሰው ምስጉን ነውና ኃጢአትህ በሰው ፊት እንዳይገለጥብህ ወደ ልዑል እግዚአብሔር ለምን።

ልጄ ሆይ፤ ለእኔ ለአባትህ እንደ መሰለኝ ከሃይማኖት ሁሉ የሚበልጠው ክርስቲያንነት ነው።

ከመጻሕፍትም ሁሉ ወንጌል ትበልታለች። ይህንም ማለቴ አንተ በወንጌል ተምረህ ክርስቲያን ሆነህ እንድትኖር ብዬ ነው እንጂ የእኔ ሃይማኖት ይበልጣል፤ የእኔ መጽሐፍ ወንጌል ትበልጣለች እያልህ ክርክርን ከሚወዱ ሰዎች እንድትከራከር ብዬ አይደለም።

ልጄ ሆይ፤ ምሳህን ወይም ራትህን ለመብላት ወደ ሰደቃህ በቀረብህ ጊዜ በቃልህም ቢሆን በልብህም ቢሆን የእግዚአብሔርን ቅዱስ ስሙን ሳትጠራ እንጀራህን አትቁረስ። በልተህም ከጠገብህ በኋላ እግዚአብሔርን ሳታመሰግን ሰደቃህን አታንሣ።

ልጄ ሆይ፤ ሁልጊዜ በኪስህ ውስጥ አንድ መናኛ መሐረም፤ አንድ ማለፊያ መሐርም ያዝ። መናኛው መሐርም ከአፍንጫና ከአፍም ለሚወጣው እድፍ፤ ማለፊያው መሐርም ደግሞ ለዓይንህና ለጥርስህ እድፍ ይሆንልሃል።

ልጄ ሆይ፤ ጧትና ማታ ከምግብህ በኋላ ጥርስህን በብሩሽና በውኃ ዕጠብ (ተጉመጥመጥ)።

ነገር ግን ሰው ሲያይህ ባፍህ ውስጥ መፋቂያ አታድርግ፤ በሰውም ፊት ምራቅህን ጢቅ አትበል።

ልጄ ሆይ፤ ቀን በሥራህ ላይ፤ ሌሊት ባልጋህ ላይ፤ የሚጠብቅህ እግዚአብሔር ነውና ማታ ስትተኛ፤ ጧት ስትነሣ እግዚአብሔርን አምላክህን መለመንና ማመስገን አትተው።

ልጄ ሆይ፤ በምትተኛበት አልጋ አጠገብ ክብሪትና መብታ፤ ውኃና ብርጭቆ አታጥፋ። መንገድም በምትሔድበት ጊዜ በኪስህ ገንዘብ ሳትይዝ ከቤትህ አትነሣ።

ልጄ ሆይ፤ እኔ በተቻለኝ አሳብ ይህን ጻፍሁልህ፤ ነገር ግን ማናቸውም ነገር ቢሆን ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ አይሆንምና የተቀደሰ ፈቃድ ይሁንልህ።

አሜን።

# ክፍል ፫ ሱካርና ወተት

## የልጆች ማሳደጊያ

ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ተተረጐመ።

# ልጆቼ ሆይ፤

በዚህ መጽሐፍ የተጻፈው ቃል የተወሰነው እንደ ታሪክ የተወሰነውም እንደ ምሳሌ፤ ሌላው ደግሞ እንደ ተረት ነው።

ነገር ግን የዚህ መጽሐፍ ዋና ጥቅምነቱ ለናንተ ለሕጻናቱ ብቻ ስለ ሆነ ስሙን ሱካርና ወተት ብየዋለሁ። እናንተም በየጊዜው ሁሉ ሱካርና ወተት ለማግኘት ፈቃዳቸው እንደ ሆነ ሁሉ ይህም የጻፍሁላችሁን መጽሐፍ በየጊዜው ለማንበብ ፈቃዳችሁ ይሆን ዘንድ እለምናችኋለሁ።

## መጀመሪያ

# ስለ አንድ ከበርቴ ሰው

በእንግሊዝ ሀገር የሚኖር አንድ ከበርቴ ሰው ነበረ። እርሱም ሦስት ልጆች ነበሩት። ነገር ግን ሰው ምንም ባለ ብዙ ገንዘብ ቢሆን ገንዘቡ ከሞት አያድነውምና ሰውነቱ እንደ ሸመገለ የሞቱም ጊዜ እንደ ቀረበ አውቆ ሦስቱን ልጆቹን ጠርቶ ገንዘቡን ሁሉ አካፈላቸው። ርስቱንና ቤቱንም እንደሚገባቸው እያየ ሰጣቸው።

ነገር ግን አንድ ትልቅ አልማዝ ነበረውና ያንን ለብቻው በእጁ አንሥቶ ይዞ ልጆቼ ሆይ፤ ከእናንተ ከሦስታችሁ እጅግ ደስ የሚያሰኝ መልካም ሥራ ለሠራው ልጅ ይህን አልማዝ እሰጠዋለሁና የሠራችሁትን ሥራ ንገሩኝ አላቸው።

ታላቁ ልጁ ቀረበ። አባቴ ሆይ፤ አስቀድሞ የማያውቀኝ አንድ ሰው መጥቶ ብዙ ገንዘብ አደራ አስቀመጠብኝ። እርሱ መስጠቱን እኔ መቀበሌን አንድ ሰው እንኳን አላየም ነበረ። እኔም አደራ አስቀምቻለሁ የሚል ወረቀት አልሰጠሁትም ነበረ። ከብዙ ቀን በኋላ ተመልሶ መጥቶ የሰጠኸኝ ይኸ ብቻ ነው ብለው ወይም ጭራሽ አላየሁም ብለው ይቻለኝ ነበረ። ዳሩ ግን ይህን ማድረግ አይገባም ብዬ አንድ እንኳ ሳላስቀር ገንዘቡን ሁሉ ሰጠሁት። ይህ መልካም ሥራ አይደለምን አለው።

አባቱም መለሰ፤ ልጄ ሆይ፤ ይህ እውነተኛ ሰው ያሰኝሃል እንጂ ሥራ አይባልም አለው።

መካከለኛው ልጁ ደግሞ ቀረበ። አባቴ ሆይ፤ አንዲት ሴት በባሕር ዳር ልጅዋን ታቅፋ ቆማ ጀልባ ወዲያና ወዲህ ሲመላለስ ስትመለከት ልጅዋ ከክንድዋ አምልጦ ወደ ባሕር ወደቀባት። እኔም የእርስዋን መጨነቅ አይቼ ለራሴ ሳላዝን ወደ ባሕሩ ውስጥ ገብቼ ልጅዋ ሳይሞት አወጣሁላት፤ ይህ መልካም ሥራ አይደለምን አለው።

አባቱ መለሰ፤ ልጄ ሆይ፤ ይህ ርኅሩኅ ያሰኝሃል እንጂ ሥራ አይባልም አለው።

ሦስተኛው ልጁ ቀረበ። አባቴ ሆይ፤ በደረቅ ውድቅት ብቻዬን ስሔድ ጠላቴ በገደል አፋፍ እንደተቀመጠ ወዲያው እንቅልፍ ይዞት ሲያጉላጅ አገኘሁት። በዚያ ጊዜ ጥቂት ብነካው በገደሉ ተንከባሎ ይወርድ ነበረ። ወይም በታጠቅሁት ሰይፍ አንገቱን ብመታው ቆርጬ እጥለው ነበረ። ግን ይህን ማድረግ አይገባም ብዬ ወደ እርሱ ቀርቤ እጥለው ነበረ። ግን ይህን ማድረግ አይገባም ብዬ ወደ እርሱ ቀርቤ እንዲነሣ ቀሰቀስሁት፤ የሚተኛበትም መልካም ሥፍራ አሳየሁት። ይህ መልካም ሥራ አይደለምን አለው።

አባቱም ይህን በሰማ ጊዜ የልጁን አንገት አቅፎ ይዞ ልጄ ሆይ፤ ልጄ ሆይ፤ ከዚህ የሚበልጥ መልካም ሥራ የለምና ይህ አልማዝ የሚገባው ላንተ ነው ብሎ አልማዙን ሰጠው።

ልጆቼ ሆይ፤ እናንተም ጠላቶቻችሁን ውደዱ ለሚጠልዋችሁም መልካም አድርጉ፤ ጊዜ ተመችቶናል ብላችሁ ጠላቶቻችሁን ለመጉዳት አታስቡ።

### ሁለተኛ

## ስለ ሁለት ባልንጀሮች

ሁለት ባልንጀሮች ባንድነት ሲሔዱ በድንገት ዳልጋ አንበሳ መጣባቸው። በዚያ ጊዜ አንዱ ባልንጀራውን ትቶ እየሮጠ ሔዶ ወደ ዛፍ ላይ ወጣና የዛፉን ቅጠል ከለላ ሰጥቶ ተቀመጠ።

ያ ሌላው ግን የሚያደርገው ነገር ቢቸግረው ዳልጋ አንበሳ የሞተ ሰው አይበላም ሲባል ይሰማ ነበርና እንደ ሞተ ሰው ሆኖ በመንገዱ ላይ ተኛ።

ዳልጋ አንበሳውም በላዩ ቆሞ እያገላበጠ አፍንጫውንም፣ አፉንም፣ ጆሮውንም፣ ልቡንም ያሸተው ጀመረ። እርሱ ግን ፈጽሞ እንደ ሞተ ሰው ዝም አለ። በዚያ ጊዜ በውነት የሞተ ሰው መስሎት ትቶት ሔደ። ባልንጀራውም በዛፉ ላይ ሆኖ ቁልቁል ያይ ነበረና ዳልጋ አንበሳው ትቶ እንደ ሔደ አይቶ ከዛፉ ወርዶ ወደ ባልንጀራው ቀርቦ ወንድሜ ሆይ፤ ዳልጋ አንበሳው አፉን በጆሮህ ላይ ተክሎ ባየሁት ጊዜ የበላህ መስሎኝ እጅግ ደንግጬ ነበረ አለው። ባልንጀራው መለሰ፤ አይደለም ያንጊዜስ አንድ ትልቅ ነገር በጆሮዬ ነገረኝ አለው። እንዴት ያለ ነገር ነገረህ አለው።

በመከራና በጪንቅ ቀን ጥሎ የሚሸሽ ሰው ባልንጀራ አትሁን አለኝ አለው።

እርሱም ያደረገውን ያውቃልና ሰምቶ ዝም አለ።

ልጆቼ ሆይ፤ በመከራና በጪንቅ ቀን ባልንጀራችሁን አትጣሉት። ባልንጀራችሁም የሚጠቀምበትን ሥራ ሥሩ እንጅ እናንተ ብቻ የምትጠቀሙበትን ሥራ አትሥሩ። ካልታመነም ሰው ጋር ባልንጀርነት አታድርጉ።

### ሦስተኛ

# ስለ የብራማ ካህን

ብራማ ወይም ብራህማ ህንዶች እንደ አምላክ የሚያመልኩት ነው። የብራማ ካህናት ደግሞ እንደዚያው እንደ ሕጋቸው ከኃጢአት ሁሉ የራቁ ንጹሐን ናቸው ይባላሉ።

ከብራማ ካህናቶች አንዱ ወደ ገበያ ወጥቶ የፍየል ወጠጤ ገዝቶ በጫንቃው ተሸክሞ ወደ ቤቱ ሲመለስ ሦስት አታላዮች አዩት። እነርሱም ይህን ካህን እናታለው ብለው ተማከሩና ቀደም ቀደም እያሉ እያሉ ሒደው በሦስት ስፍራ ላይ የተቀመጡት ቆዩት።

በመጀመሪያ አንደኛው አታላይ አገኘው። ካህን ሆይ፤ እርስዎ ቅዱስ ንጹሕ ሆነው ሳሉ ስለምን ርኩስ ውሻ በጫንቃዎ ተሸክመዋል አለው። ካህኑ መለሰ፤ ወዳጄ ሆይ፤ ፍየል ነው እንጂ ውሻ አይደለም አለው።

ጥቂትም እንዳልፈ ሁለተኛው አታላይ አገኘው። የብራማ ካህን ሆይ፤ እርስዎ ቅዱስ ንጹሕ ሆነው ሳሉ ስለምን ርኩስ ውሻ በጫንቃዎ ተሸክመዋል አለው።

ካህኑም ያንን ፍየል ከጫንቃው ላይ አውርዶ እንደ ገና እያገላበጠ ያይ ጀመረ። ካየም በኋላ ወዳጄ ሆይ፤ ፍየል ነው እንጂ ውሻ አይደለም ብሎ ተሸክሞ ሔደ።

ከዚያ ደግሞ ጥቂት እንዳለፈ ሦስተኛው አታላይ አገኘው። የብራማ ካህን ሆይ፤ እርስዎ ቅዱስ ንጹሕ ሆነው ሳሉ ስለምን ርኩስ ውሻ በጫንቃዎ ተሸክመዋል አለው።

ከዚያ በኋላ ያ የብራማ ካህን ሦስተኛ ይህን ነገር በሰማ ጊዜ ያየው ሰው ሁሉ ውሻ ነው እያለ ሲመሰክር እኔ ብቻዬን ፍየል ነው እላለሁን ብሎ ከጫንቃው አውርዶ ወርውሮ ጥሎት ሔደ። እነዚያም አታላዮች ያንን ፍየል ይዘው ወደ ቤታቸው ወስደው አርደው በሉት።

ልጆቼ ሆይ፤ በምንም በምን ቢሆን ሰውን አታታሉ። እናንተም በምንም በምን ቢሆን አትታለሉ። አውቆ የሠሩት ሥራ ነው እንጂ ተታሎ የሠሩት ሥራ እንዳይጠቅም እወቁ።

## አራተኛ

# ስለ የእስጳንያ ሰውና የህንድ ሰው

የእስጳንያ ሰውና የህንድ ሰው በመንገድ ላይ ተገናኝተው ባንድነት ሲጓዝ የእስጳንያው ሰው ፈረሱ ደከመበት። ወዲያው ወደ ህንዱ ዞወር ብሎ እባክህ ፈረስ ለፈረስ እንላወጥ አለው። ህንዱ ግን እምቢ አለ። በዚያ ዘመን ህንዶች የተናቁ ሰዎች ነበሩና ያ የእስጳንያ ሰው ከፈረስ ወርዶ ህንዱን ከፈረሱ ላይ ጐትቶ አውርዶ ፈረሱን ነጥቆ ይዞበት ሔደ። ህንዱም በኋላ በኋላው እየተከተለ ሲሔድ ወደ መንደር ደረሱ። በዚያ ጊዜ እየጮኸ ሔዶ፤ ለመንደሩ ዳኛ ነገረ። ዳኛውም ያንን የእስጳንያ ሰው አስጠርቶ ፈረሱን ለምን ቀማኸው ብሎ ጠየቀው። እስጳንያው መለሰ፤ ጌታዬ ሆይ፤ ይህ ፈረስ የኔ ጥሩ ገንዘቤ ነው። ህንዱ ግን አሁን ለእርስዎ መንገሩ ሲቀጥፍ ነው። የህንድ ሰው አባይና ቀጣፊ መሆኑ የታወቀ ነው እያለ ይምል ይገዘት ጀመረ።

በዚያ ጊዜ ዳኛው ቶሎ ብሎ ተነሥቶ መሐርሙን ከኪሱ አውጥቶ የፈረሱን ሁለተንም ዓይኖች ሸፍኖ ይዞ በል እስቲ ፈረሱ ያንተ ጥሩ ገንዘብህ ከሆነ፤ የትኛው ዓይኑ ዕውር ነው የቀኙ ነውን ወይስ የግራው አለው። ያ የእስጳንያ ሰው ግን ፈረሱን መቀማቱን እንጅ ዕውር ይሁን ደህና ይሁን ልብ አድርጐ አላስተዋለውም ነበረና እንዲያው ምናልባት ብሎ የፈረሴ ቀኝ ዓይኑ ዕውር ነው አለ። ደግሞ ወደ ህንዱ ዞወር ብሎ አንተሳ አለው። ፈረሴ ቀኝ ዓይኑም ግራ ዓይኑም ደህና ነው። ዕውርነት የለበትም አለው። በዚያ ጊዜ ዳኛው መሐረሙን አንሥቶ፤ ፈረሱን ቢያየው እንደ ህንዱ ቃል ሁለቱም ዓይኖቹ ደህና ሆነው ተገኙ። ከዚህ በኋላ ፈረሱን ለህንዱ ሰጥቶ እስጳንያውን ለቅጣት አሳልፎ ሰጠው።

ልጆቼ ሆይ፤ በምትኖሩበት ሀገር እንደዚህ ያለ ዳኛ እንዳይሰጣችሁ ወደ እግዚአብሔር ለምኑ። መልካም ዳኛ ከሌለ ገንዘባችሁ ይቅርና አካላችሁም የናንተ አይደለም።

## አምስተኛ

# ስለ አንድ አንበሳና አንድ ቡችላ

በእንግሊዝ ሀገር በሎንዶን ከተማ የአራዊት ለማዶች አሉ። ከሁሉም ይልቅ አንበሶቹ እጅግ የሚያምሩና ለማየት የሚያጓጉ ናቸው። እነዚያንም ለማየት የሚሔድ ሰው ሁሉ ገንዘብ ካልሰጠ ወደ ውስጥ እንዳይገባ ክልክል ነው።

ገንዘብ የሌለው ሰው ግን በቤቱ የውሻ ቡችላ ወይም የድመት ግልገል ያለው እንደ ሆነ ለአንበሳው ይዞለት ይሔዳል።

እንደዚሁ ሁሉ አንድ ሰው አንድ ቡችላ ይዞ ሔደ። ውስጥም በገባ ጊዜ ለአንበሳው ጣለለት። ቡችላውም የአንበሳውን መዳፍ እየላሰ ማረኝ እንደ ማለት በኃዘን ቃል ይጮኽ ጀመረ። አንበሳውም ለቡችላው አዘነና ወደ መኝታው አስጠግቶ ተወው። ምግቡም በመጣለት ጊዜ የሚበላውን እየበላ የተረፈውን እየወሰደ ለቡችላው ይጥልለት ጀመረ። እንደዚህ ባንድነት እየተጫወቱ ባንድ ሥፍራ እየተኙ ብዙ ዘመን ተቀመጡ። ከብዙ ዘመን በኋላ ያ ቡችላ ታመመና ሞተ። አንበሳው ግን የተኛ መስሎት ዝም አለው።

ካንድ ቀን በኋላ አንበሳው ወደ ቡችላው ቀርቦ ከወደ ራሱ ቀና አድርጐ ቢያየው እንደ ሞተ አወቀ። በዚያ ጊዜ በታላቅ ድምጥ ያገሣ ጀመረ። የአንበሳውም ጠባቂ ይህ አንበሳ ምን ሆኖ ይሆን ብሎ ቢመጣ ያ ቡችላ ሞቶ ተገኘ። ጥንቡን አንሥቶ ለመጣል ቢቀርብ አንበሳው ከለከለው። አንበሳው አራት ቀን ሙሉ ምግቡን ሳይመገብ በቡችላው ሬሳ አጠገብ ተቀመጠ። ባራተኛው ቀን ግን የአንበሳው ጠባቂ መጥቶ ቢያየው ቡችላውን በመዳፉ ታቅፎ ራሱን በላዩ አስደግፎ ሞቶ ተገኘ። ጠባቂውም የሁለቱንም ሬሳ አንሥቶ ባንድ ጉድጓድ ቀበራቸው።

ልጆቼ ሆይ፤ ደግነትና ፍቅርን ከያዛችሁ ኃይለኛው ደካማ፤ ንፉጉ ቸር፤ ክፉው ደግ፣ ይሆንላችኋልና የትዕቢት ሥራ አትሥሩ።

## ስድስተኛ

# ተረት ስለ ሚወድ ንጉሥ

በቀድሞ ዘመን አንድ ንጉሥ ነበረ። እርሱም እግዚአብሔር የሰጠውን የመንግሥቱን ሥራ ትቶ ተረት የሚያውቅ ሰው እያስፈለገ ተረት ሲሰማ ይውል ነበረ። ተረት የሚያውቁ ብዙ ሰዎች እየመጡ ተረታቸው እያለቀባቸው ሔዱ። ንጉሡ ግን እያደረ የተረት ፍቅር እየጸናበት ይሔድ ጀመረ።

ከእለታት አንድ ቀን ወረቀቱንና ቀለሙን አቅርቦ እኔ በቃኝ እስክል ድረስ አዲኢስ አዲስ ተረት የሚነግረኝ ሰው የተገኘ እንደ ሆነ፤ ልጄን አጋብቼ መንግሥቴን አወርሰዋለሁ ብሎ ጽፎ ማኅተሙን አተመ። እንዲህ ማለቱ ግን መቸም ብዙ ተረት የሚያውቅ ሰው አይገኝም ብሎ ነበረ።

ከዚህም በኋላ ሰው ወሬ በያገሩ ደረሰና አንድ ብልህ ሰው መጥቶ እኔ ለንጉሡ በቃኝ እስኪል ድረስ ተረት እነግራቸዋለሁና ንገሩልኝ አለ። ንጉሡም በሰማ ጊዜ እጅግ ደስ አለው። የውሉንም ወረቀት ሰጠው። ከዚህ በኋላ ተረቱን ሊነግር ጀመረ።

ንጉሥ ሆይ፤ አንድ ባለ ጠጋ ሰው አዝመራውና መከሩ አማረለት፤ እንድ አማረለትም ካየ በኋላ፤ ስንዴውን የሚያኖርበት ታላቅና ሰፊ ጐተራ ሠራ። የጐተራው ርዝመቱ ሠላሳ ክንድ፤ ወርዱ ሀያ ክንድ፤ ቁመቱ አሥር ክንድ ነበረ።

በመከርም ወራት ስንዴውን ወቅቶ በጐተራው ሞልቶ አስቀመጠ። ነገር ግን በሙቀት ምክንያት እንዳይነቅዝ ብሎ ለነፋስ መግቢያ ትንሽ መስኮት አውጥቶለት ነበረና አንዲት ገብረ ጉንዳን በዚያ ገብታ አንድ ቅንጣት ስንዴ ይዛ ወጣች ብሎ ነገረው። ንጉሡም እኽ አለው።

ድግሞ ሌላይቱ ገብረ ጉንዳን ገባችና አንድ ቅንጣት ስንዴ ይዛ ወጣች አለው። ከዚያ ወዲያሳ አለው። ደግሞ ሌላዪቱ ገብረ ጉንዳን ገባችና አንድ ቅንጣት ስንዴ ይዛ ወጣች አለው። ከዚህ በኋላ ንጉሡ ተነሥቶ ዛሬ ይበቃናል ነገ ደግሞ እንጫወታለን አለው።

በማግሥቱም በማለዳ ንጉሡ መጥቶ ወደ መጫወቻው ቤት ገብቶ ተቀመጠ። ሰውዬውም ቀረበ ንጉሡም እኽ አለው። ደግሞ ሌላዪቱ ገብረ ጉንዳን ገባችና አንድ ቅንጣት ስንዴ ይዛ ወጣች አለው።

ይህንማ ትናንት ነግረኸኝ የለምን አለው። ሰውዬው መለሰ፤ ንጉሥ ሆይ፤ ጐተራው እንጂ ሰፊ ነው። ስንዴውም እኮ አላለቀም አለው። ንጉሡም ተቆጣና ተነስቶ ወደ ቤቱ ገባ። በማግሥቱም በማለዳ መጥቶ ወደ መጫወቻው ቤት ገባ። ሰውዪኤውም ቀረበ፤ ንጉሥ እኽ አለው። ደግሞ ሌላዪቱ ገብረ ጉንዳን ገባችና አንድ ቅንጣት ስንዴ ይዛ ወጣች አለው።

ንጉሡም ይህን በሰማ ጊዜ ይህንስ ትናንት ነግረኸኛል። ሌላ ተረት የለህምን አለው። ተረትስ ሞልቶኛል፤ ነገር ግን ስንዴው መች አለቀ። ጐተራው እንጂ ሰፊ ነው አለው። እንዲህ እያለ አስራ አምስት ቀን ሙሉ አስለቸው። በመጨረሻው ንጉሡ እንደ ልማዱ በመጫወቻው ቤት ገብቶ ተቀመጠ። ሰውዬውም ቀረበ። ንጉሡም እኽ አለው። ደግሞ ሌላዪቱ ገብረ ጉንዳን ገባችና አንድ ቅንጣት ስንዴ ይዛ ወጣች አለው። ንጉሡም ተቆጣና ይህንማ ስትነግረኝ ሰንብተህ የለምን፤ ሌላ ተረት እንዳለህ አምጣ አለው።

ንጉሥ ሆይ ተረስት ሞልቶኛል ነገር ግን የተጀመረውን ሳልጨርስ ሌላ መጀመር አይገባኝም። ጐተራው እጅግ ታላቅ ነው፤ ስንዴውም ብዙ ነው አለው።

በዚያ ላይ ንጉሡ እጅግ ተናደደና ሁለተኛ ይህን ተረት አትንገረኝ፤ እጅግ ሰለቸኝ። ልጄንም ሰጥቼሃለሁ መንግሥቴንም አውርሼሃለሁ አለው።

ሰውዬም የንጉሡን ልጅ አግብቶ መንግሥቱን ወርሶ በዙፋኑ ተቀመጠ።

ልጆቼ ሆይ፤ የሚረባውን ነገር ትታችሁ የማይረባውን ነገር አትፈልጉ። ቀልድና ቸዋታም አትውደዱ። ወደ ጨዋታ ቤት ከመሔድ ወደ ልቅሶ ቤት መሔድ ይሻላል የተባለውን ነገር አስቡ።

## ሰባተኛ

# ስለ አንድ ጫማ ሰፊ

አንድ ጫማ ሰፊ ከጧት እስከ ማታ በእጁ ጫማ ሲሰፋ፤ ባፉ ሲዘፍን ይውል ነበረ። በጐረቤቱም አንድ ባለጠጋ ነበረና አንድ ቀን ወደ እርሱ መጥቶ፤ ወዳጄ ሆይ፤ እንዲህ ሌት ቀን ስትደክም ባመት ምን ያህል ታተርፋለህ አለው።

ጫማ ሰፊውም እየሳቀ መለሰ፤ ጌታ ሆይ፤ እኔ ያመት ትርፍን አላስብም። ነገር ግን አሳቤ ሁሉ እጄ ወደ አፌ የሚያቀርበው የዕለት ምግብ እንዳልቸገር ብቻ ነው አለው።

ባንድ ቀን ምን ያህል ታተርፋለህ አለው።

ጌታዬ ሆይ፤ አንድ ቀን ብዙ አንድ ቀን ጥቂት እሠራለሁ። ትርፉ በምን ይታወቃል አለው።

ባለጠጋውም እንግዲህ ወዲ እኔ ያለችግር አኖርሃለሁና ከኒኤ ዘንድ መቶ ምዝምዝ ወርቅ ውሰድና በጥንቃቄ ጠብቀህ አኑር። በቸገረህም ጊዜ የሚበቃህን ያህል እንጂ በከንቱ አታባክን ብሎ ሰጠው።

እርሱም ይህን ያህል ገንዘብ ባይኑ ስንኳ አይቶ አያውቅም ነበረና ደስ እያለው ተቀብሎ ወደ ቤት ሔደ። ነገር ግን ይጠፋብኛል ብሎ ሲጨነቅ ሌሊቱን ሁሉ ካይኑ እንቅልፍ ሸሸ። በሌሊትም የሰው ድምፅ ቤቱ ባነቃነቀው ጊዜ ገንዘቡን የሚሰርቅ ሌባ የመጣ እየመሰለው ይጨነቅ ጀመረ።

እንዲህም እየሆነ ብዙ ቀን ተቀመጠ። ነገር ግን ልቡ የዚህን አሳብ የማይችለው ሆነ።

ከእለታት አንድ ቀን እንዲህ ሲጨነቅ አደረና በማግሥቱ በማለዳ ተነሥቶ ወደዚያ ባለጠጋ ቤት እየሮጠ ሔዶ፤ ለኔስ የቀድሞ ኑሮዬ እጅግ ይሻለኛል። አሁንም ይህን

የሰጠኸኝን መቶ ምዝምዝ ወርቅ ተቀበለኝ። ቀን ስሥራ እየዋልሁ ሌሊት እንቅልፍ ቢወስደኝ ለኔ እጅግ መልካም ነው ብሎ በትኖለት ሔደ።

ልጆቼ ሆይ፤ ለምግባችሁና ለልብሳችሁ የሚበቃችሁን ገንዘብ ካገኛችሁ ለብዙ ገንዘብ አትጨነቁ። ለባለጠጋ ከማየት በቀር ሌላ ትርፍ የለውም።

## ስምንተኛ

# ስለ አንድ ሰውና ስለ አንድ ውሻ

በስዌድን ሀገር በመናገሻው ከተማ በስቶኮልም አንድ ውሻ ያለው ሰው ነበረ። ፍቅር ማለት ከልማድ የተነሳ ነውና ውሻው ጌታውን በጣም ይወደው ነበረ። ጌታውም ለውሻአው እንደ ልጁ ያስብለት ነበረ። ነገር ግን እንኳን የውሻ ፍቅር የሰውም ፍቅር ቢሆን ከሞት አያድንምና ጌትዮው ታመመና ሞተ። ውሻውም ጌታው ከታመመ ጀምሮ እስኪሞት ድረስ ካልጋው ሥር አልተለየም። ከሞተም በኋላ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲወስዱት ሬሳውን ተከትሎ ሔደ። በዚያም መቃብር ቆፍረው ሲቀብሩት አየ። ከተቀበረም በኋላ ግን ሰዎቹ ሁሉ በየቤታቸው ሲገቡ እርሱ እዚያው በመቃብሩ አጠገብ ቆሞ ቢጠሩትም ቢሙቱትም ዝም ብሎ ቀረ። ማታ ማታም በመቃብሩ ላይ እየተኛ ያድር ጀመረ።

አንዲት ሴት ወይዘሮ ወሬውን ሰምታ ራትና ምሳውን ትሰጠው ጀመረ። እንዲሁ የቀን ሀሩር፤ የሌሊት ቁር ሳይፈራ ብዙ ቀን በመቃብሩ ላይ ኖረ። ሴቲቱም እንደ ገና አስባ የብርድ ልብስ ሰደደችለት።

ከብዙ ቀን በኋላ ራትና ምሳውን የምትሰድለት ወይዘሮ በድንገት ታመመችና ውሻውን የሚጠይቅ ሰው ሌላ ሰው ጠፋ። ውሻው ግን ይህን ሁሉ መከራና ችጋር ታግሶ እዚያው በጌታው መቃብር ላይ ሞተ።

ሴቲቱም ከበሽታዋ ስትድን ትዝ አላትና ሰው ልካ ብታሳየው ሞቶ ተገኘ። ከዚያ በኋላ እርሷ ራሷ ሔዳ በብዙ ሐዘን በዚያው በጌታ መቃብር አጠገብ አስቀበረችው።

ልጆቼ ሆይ፤ እንኳን ሰው እንስሳም ቢሆን ከወደዱት መውደዱ አይቀርምና ሁሉን ውደዱ። ወዳጃችሁንም በፍጹም ልባችሁ ከወደዳችሁት በመከራችሁ ቀን አይለያችሁም።

## ዘጠነኛ

# ስለ አንበሳና ስለ አይጥ

አንበሳ በዱር ውስጥ ወዲያና ወዲህ እየሮጠ ምግቡን ሲፈልግ ውሎ ደከመውና ባንድ ዛፍ ሥር ተኛ። በዛፉም ሥር አንዲት አይት ከጉድጓድዋ ውስጥ ወጥታ በአንበሳው ላይ እየዘለለች ትጫወት ጀመረች። አንበሳው ግን ከድካሙ ብዛት የተነሳ አልሰማትም። ከዚህ በኋላ ባፍንጫውና ባይኑ ላይ ትዘል ጀመረች። በዚያ ጊዜ አንበሳው ከእንቅልፉ ነቃና አፈፍ አድርጎ ያዛት። ሊውጣትም ያንን የሚያስፍራ አፉን ከፈተ። አይጢቱም ያራዊት ንጉሥ ሆይ፤ ማረኝ፤ በድዬሃለሁ፤ የዛሬን ብቻ ማረኝ፤ ከእንግዲህ ወዲህ ቸርነትህን ለዘላለሙ አልዘነጋም። ደግሞም ምንም ትንሽ ፍጥረት ብሆን አንድ ቀን በተቻለኝ ነገር እረዳሃለሁ እያለች ትቀባጥር ጀመረች።

አንበሳውም አይጢቱ እረዳሃለሁ ባለችው ነገር ሳቀና ለቀቃት።

አይጢቱም እግዚአብሔር ይስጥልኝ ብላ ወደ ጉድጓድዋ ጥልቅ አለች።

ከጥቂት ቀን በኋላ አንበሳው በጨረቃ ብርሃን ላደን ወጥቶ ሳለ አዳኞች ያንን የሚተኛበትን ዛፍ አይተው ኑሮ ወጥመድ አጥምደውበት ሔዱ። አንበሳውም ከስፍራው ሀያ ኪሎ ሜትር እርቆ ሔዶ ነበረና ሲመለስ በድንገት ወጥመዱ ያዘው።

ከዚያም በኋላ ወጥመዱን ለመበጠስ ቢዘል፤ ቢያገሣ፤ የማይሆንለት ሆነ። አዳኖቹም ባንድ ሥፍራ ተቀምጠው ይመለከቱ ኑረው ወጥመዳቸው እንደ ያዘላቸው አይተው አንበሳውን ወስደው ለንጉሥ ለመስጠት የብረት አጥር ያለው ሠረገላ ለማምጣት ወደ ከተማ ሔዱ።

በዚያን ጊዜ ያች አይጥ አንበሳው ሲያገሣ ስምታ ኑራ ከጉድጓድዋ ብቅ አለችና ያራዊት ንጉሥ ሆይ፤ አንድ ቀን ረዳሃለሁ ብዬህ አልነበረም አለችው። አሁንም አንበሳው በብርቱ ጭንቀት ተይዞ ዛለ ባይጢቱ ንግግር ሳቀ። አይጢቱ ግን አትሳቅ እመነኝ። አሁን ባሁን ከዚህ ጭንቀትህ አወጣሃለሁ አለችው። ይህንም ከተናገረች በኋላ አንበሳው የታሰረበትን የወጥመዱን ገመድ ባንድ አፍታ ቀረጣጥፋ ጨረሰችው። አንበሳውም ከወጥመዱ አምልጦ በወጣ ጊዜ አይጢቱ ቀርባ ያራዊት ንጉሥ ሆይ፤ እኽ፤ እኔ እውነተኛ አይድለሁምን አለችውና ወደ ጉድጓድዋ ጥልቅ አለች።

ልጆቼ ሆይ፤ ሰውን ድኃ ነው ወይም ትንሽ ነው ብላችሁ አትናቁ። ለሁሉ ጊዜ አለውና ምንም ድኃ ቢሆን ባንድ ምክንያት ሳይረዳችሁ አይቀርም።

## *አሥረኛ*

## ስለ የህንድ ንጉሥና ስለ የሚናገር ወፍ

አንድ ሰው መናገር የሚችል አንድ ወፍ ያዘና ንግግር ያስተምረው ጀመረ። ሲያስተምረውም ሌላውን ንግግር ሁሉ ትቶ አይጠረጠርም፤ በል እያለ አስተማረው። ይህንም ብዙ ዘመን አስተማረው። ና ሲለው አይጠረጠርም ይል ጀመረ። ሒድም ሲለው አይጠረጠርም ይል ጀመረ።

ከዚህ በኋላ ለመሸጥ ወደ ገበያ ይዞት ወጣ። ወፍም የሚገዙ ሰዎች እየመጡ ዋጋ ንገር አሉት። መቶ ብር አላቸው። እነዚያ ግን የሚናገር ወፍ መሆኑን አያውቁምና ዋጋ በዛ እያሉ ጥለውት ሔዱ። ከዚህ በኋላ ንጉሡ መጥቶ ባለ ወፍ ዋጋ ንገር አለው። መቶ ብር አለው። ንጉሡም ተቆጣ፤ አብደኃልን፤ አንድ ወፍ እንደምን አድርጐ መቶ ብር ያወጣል አለው።

ባለ ወፉ መለሰ፤ ንጉሥ ሆይ፤ እኔን ለምን ይቆጡኛል። ዋጋህ ምን ያህል ነው ብለው ወፉን አይጠይቁትምን አለው።

ንጉሡም ወፍ እንዴት አድርጎ ይናገራል ብሎ አሰበ። ወዲያው ወደ ወፉ ዘወር ብሎ አንተ ወፍ፤ እውን መቶ ብር ታወጣለህን አለው። አይጠረጠርም አለው።

በዚያ ጊዜ ንጉሡ ደስ አለውና በቶሎ መቶውን ብር ቆጥሮ ሰጥቶ ወፉን ይዞ ሔደ።

ወፉም ብዙ ንግግር የሚያውቅ መስሎት ነበርና ንጉሡ ቀርቦ ያነጋግረው ጀመረ። ወፉ ግን ንጉሡ በተናገረ ቁጥር ምላሹ አይጠረጠርም ማለት ነው። አሁንም አሁንም ይህን መስማቱ ስልችት አለው። በመጨረሻው ተናደደና ወደ ወፉ ቀርቦ ላንተ ዋጋ መቶ ብር ሰጥቼ እንዴት ያለሁ እብድና ድነቆሮ ነኝ አለው። ወፉም አይጠረጠርም አለው። አሁን ጊዜ አጋጠመውና መልካም ምላሽ ሆነለት።

ልጆቼ ሆይ፤ ከገበያ የምትገዙትን ሁሉ በጣም ሳትመረምሩ አትግዙ። ከገዛችሁት በኋላ ግን ብትጠጡት ምንም ጥቅም አታገኙም።

## አሥራ አንደኛ

# ስለ የሌት ወፍ

የሌት ወፍ እንደ ዓይጥ ጥርስ አላት፤ እንደ ወፍም ክንፍ አላት። አንድ ጊዜ የሰማይ ወፎችና የዱር አራዊቶች ተጣልተው አራት ቀን ሙሉ ጦርነት አደረጉ። የሌት ወፍ ግን በዳር ሁና ስትመለከትና የዱር አራዊቶች ሲበረቱ ያየች እንደ ሆነ ወደነዚያ ትሔድና

እኔ እኮ ቁጥሬ ወደናንተ ነው፤ እዩት ጥርሲኤን፤ እዩት ጡቴን፣ እስቲ ከሰማይ ወፎች እንደኔ ጥርስና ጡት ያለው ማነው ትላቸዋለች።

ደግሞ የሰማይ ወፎች ሲበረቱ ያየች እንደ ሆነ ወደነዚያ ትሔድና እኔ እኮ ቁጥሬ ወደናንተ ነው፤ እዩት ክንፌን፣ እስቲ ከዱር አራዊት ወገን እንደኔ በክንፍ እየበረረ በአየር ላይ የሚሔድ ማነው ትላቸዋለች። ወደ ጦርነቱ ግን ምንም ቢሆን አትገባም።

ከጥቂት ቀን በኋላ ዕርቅ ተደረገና ጦርነቱ ቆመ። ስለዚሁም የሰማይ ወፎችና አራዊቶች ትልቅ በዓል አደረጉ። የሌት ወፍም ወደ ወፎች ድግስ ብትሔድ እኛ እንደ አውሬ ጥርስ የለን ወደኛ ለምን መጣሽ ብለው አባረርዋት። ወደ ዱር አራዊትም ብትሔድ እኛ እንደ ወፍ ክንፍ የለን ወደኛ ለምን መጣሽ ብለው አባረርዋት።

ከዚህ በኋላ አፈረችና ወፎችም አራዊትም እንዳያይዋት ቀን ቀን እየተደበቀች እየዋለች፤ ማታ ማታ ምግብዋን ለመፈልግ ጀመረች። ቀን ወፎችም ቢያገኙዋት፤ አራዊትም ቢያገኝዋት ይገልዋታል እንጂ አይተዋትም። የሌት ወፍ የተባለችውም ከዚያ ወዲህ ነው ይባላል።

ልጆቼ ሆይ፤ በምትሠሩበት ሥራ ሁሉ ልብ አትሁኑ። ሁለት ልብ የሆነ ሰው አንዱን ሳይዘው በመካከል ወድቆ ይቀራል።

## *አሥራ ሁለተኛ*

# ስለ ቀበሮና ስለ ፍየል

ቀበሮና ፍየል ባልንጀርነት ገጥመው ባንድነት ሲውሉ፤ አንድ ቀን የፀሐይ ሙቀት እጅግ ጸንቶ ነበረና ሁለቱም ውኃ ጥም ያዛቸው። እንዲሁ ውኃ እየፈለጉ ካንዱ ሥፍራ ወደ አንዱ ሥፍራ ሲሮጡ የጉድጓድ ውኃ አገኙ። ሁለቱም እጅግ ተጠምተዋልና የኋላ መውጫቸውን ሳያስቡ ባንድ ጊዜ ዘለው ገቡ። ውኃውንም ጠጥተው ከረኩ በኋላ የመውጫቸው ነገር ትዝ አላቸውና፤ ያስቡ ጀመሩ። ብዙም ልዩ ልዩ አሳብ አሰቡ። ግን አልሆነላቸውም። ከዚህ በኋላ፤ መቸም ቀበሮ ተንኰለኛ ነውና ወዳጄ ፍየል ሆይ፤ እኔ አንድ መልካም አሳብ አገኘሁ አለው። እንግዲህ አንተ በጣም ጠንክረህ በኋላ እግርህ ቁም፤ እግርህም ግራና ቀኝ አንፈራጠህ በቀንድህና በግምባርህ የጉድጓዱን መሬት ተደግፈህ ቁም። እኔ በጀርባህ ላይ ተንጠላጥዬ ከወጣሁ በኋላ፤ ቀንድህን ይዤ ሽቅብ እየጐተትሁ አወጣሃለሁ አለው። ሞኝ ፍየል ሆይ፤ እውነት መሰለውና ቀበሮ እንደ ነገረው አደረገ። ቀበሮም በፍየል ጀርባ ላይ ተንጠላጥሎ ወጣ። ከዚህ በኋላ ፍየል ራሱን ቀና አደረገና በል እንግዲህ ሽቅብ ጐትተህ አውጣኝ አለው። ቀበሮ መለሰ፤ ፍየል ሆይ፤

አንተ ሽማግሌ ነህ፤ ጢምም አውጥተሃል፤ በእውቀት ግን ገና ሕፃን ነህ፤ እኔስ አንድ ጊዜ ከወጣሁ በኋላ አንተን ጐትቼ አወጣለሁ ብዬ ሁለተኛ ሰውነቴን አላጠፋም። የሆነ ሆኖ፤ ባልጀራዬ ነህና አንድ ምክር ልምከርህ፤ ከእንግዲህ ወዲህ መውጫህን ስታስብ ወደ ጉድጓድ ዘለህ አትግባ ብሎ ጥሎት ሔደ።

ልጆቼ ሆይ፤ ቃሉን አፍርሶ በተንኰል ከዳነው ቀበሮ ይልቅ፤ በቃሉ ጸንቶ በጉድጓድ ውስጥ የሞተው ፍየል ይሻላል። ስለዚህ ባልንጀራችሁም የሚጠቀምበትን ሥራ ሥሩ እንጅ እናንተ ብቻ የምትጠቀሙበትን ሥራ አትሥሩ።

## *አሥራ ሦስተኛ*

# ስለ የጦጣ ፍርድ

ሁለት ድመቶች ባንድነት ይኖሩ ነበረ። አይጥ ለማደንም ቢሆን ምናምንም ለመስረቅ ቢሆን አይለያዩም ነበረ። አንድ ቀን ከአንዱ ቤት ወደ አንዱ ቤት ሽርሽር ሲሉ መስኮቱ የተከፈተ ቤት አገኙ። በዚያ ጊዜ ድምጣቸውን አጥፍተው ቀስ እያሉ በመኮቱ ዘለው ገቡ። በዚያም በእንቁላልና በሱካር በሌላም በሚጣፍጥ ነገር የተሰናዳ ምግብ በጠረጴዛ ላይ አዩ። በጓዳውም አንድ ሰው እንኳ አለመኖሩን አይተዋልና ባንድነት ዘለ ያንን የጣፈጠ ምግብ አፋቸው እንደ ቻለላቸው ይዘው በመስኮት እየሾለኩ ወጡ። ከወጡም በኋላ በአታክልት ውስጥ ተደብቀው ለመብላት ሁለቱም የያዙትን ቀላቅለው አስቀምጠው ሰው እንዳያያቸው ግራና ቀኝ ይመለከቱ ጀመር። ለመብልም በቀረቡ ጊዜ አንዱ ክፍል ምግብ ካንዱ በልጦ አዩት። በዚህም ምክንያት ትልቁ የኔ ነው፤ የኔ ነው፤ በማለት ሁለቱ ድመቶች ተጣሉ። ምግቡንም ትተው እርስ በርሳቸው ይሞጫጨሩ ጀመሩ።

አንድ ጦጣም ብ አታክልት ውስጥ ሁኖ ይመለከታቸው ኑሮ፤ በቶሎ እየሮጠ መጥቶ እርስ በርሳችሁ ምን ያጣላችኋል። አሁን በአመጣችሁት ምግብ ተጣልታችሁ እንደ ሆነ፤ የአታክልቱ ውስጥ ዳኛ እኔ ነኝና ወደ ሸንጎ ቀርባችሁ በዳኛ ፊት ነገራችሁን መጨረስ ነው አላቸው።

ድመቶቹም ይሁን ደግ ነው አሉ። እንግዲያው ኑ አለና ወደ ዛፉ ሥር ሔዶ በጥላው ውስጥ አስቻለ። ከዚህም በኋላ ፍርዱን ጀመረ ይህን ምግብ ሁለታችሁም ባንድነት አይታችሁ አንስታችሁ የለምን አላቸው። አዎን፤ ስንገባም ባንድነት፤ ስናየውም ባንድነት፤ ስናነሣውም ባንድነት ነው አሉ። እንግዲያው ትክክል ተካፈሉ፤ ነገር ግን

ትክክል ለመካፈል ሚዛን ያስፈልጋልና ሚዛን አምጥታችሁ ላካፍላችሁ አላቸው። ይሁን ብለው ሚዛን አመጡ።

ቢመዝነው በውነትም አንዱ ክፍል ትልቅ ኑሮ ሚዛኑ ደፋ። ዳኛውም አንዱ መብለጡን አይቶ ልክ ላግባቸው ብሎ ከሚዛኑ ላይ አነሳና አንድ ጊዜ ገመጠለት። መልሶ ቢመዝነው ደግሞ ያ ትንሽ የነበረው በዛና ሚዛኑ ደፋ፤ ደግሞ ያንን አንድ ጊዚ ገመጠና መልሶ ቢመዝነው የፊተኛው ሚዛኑ ደፋ፤ ሦስተኛ አንሥቶ እገምጣለሁ ሲል ድመቶቹ ነገሩን አዩና ዳኛ ሆይ፤ ተወው፤ እኛዋ እስማምተን እንካፈለዋለንና ስጠን አሉ።

ዳኛው ጦጣ መለሰ፤ እመቤቶቼ ሆይ፤ እናንተ እንዲህ ብትሉ መቸ ይሆናል፤ ያጤ ስር አይደለምን፤ ሳላስተካክል ብሰጣችሁ ፍርድ መጉደሉ አይደለምን አለና ደግሞ አንድ ጊዜ ገመጠለት። እንደዚሁ ከዚያም ከዚያም እየገመጠ ጨረሰና፤ ጥቂት ሲቀረው ቢመዝነው ትክክል ሆነ። እነሆ አሁን ትክክል ሆነላችሁ አላቸው። እንግዲያውስ ስጠን አሉ።

ጦጣ መለሰ፤ ቆዩ አትቸኩሉ፤ እናንተ ነገሩ ሁሉ በመቸኰል የሚሆን ይመስላችኋል። እኔ ሥራዬን ሁሉ ትቼ እስካሁን ድረስ በናንተ ነገር ደክሜ እንዲያው ልቀር ነውን፤ ይህስ የዳኝነቴ ነው አለና ያንኑ የተረፈውን ወደ አፉ አድርጐ ችሎት ተመለሰ።

ድመቶቹም እያዘኑ ወደ ስፍራቸው ሔዱ።

ልጆቼ ሆይ፤ ከባልጀራችሁ ጋር በተጣላችሁ ጊዜ ቢቻላችሁ ነገሩን ትታችሁ ተቀመጡ። ባይቻላችሁ ግን በዘመድና በወዳጅ ተዋቅሳችሁ ታረቁ እንጅ ወደ ዳኛ ለመሔድ አትቸኩሉ።

## *አሥራ አራተኛ*

# ስለ አንበሳና ስለ ነብር፤ ስለ ጅብና አህያ ባልንጀርነት

አንበሳና ነብር፤ ጅብና አህያ፤ ባልንጀርነት ይዘው ባንድነት ሲኖሩ ምግብ ተቸገሩ። አንድ ቀን ባንድነት ተሰብስበው ስለ ምግባቸው ምክር ጀመሩ። ከቶ እግዚአብሔር ምግብ የነሳን በምን ምክንያት ይሆን፤ ምናልባት ከመካከላችን ትልቅ ኃጢአት የሠራ እንዳለ ሁላችንም እንናዘዝ፤ ትልቅም ኃጢአት ሠርቶ የተገኘውን ከመካከላችን እናጥፋው ተባባሉ።

መጀመሪያ አንበሳን ተናዘዝ አሉት። አንበሳም ሊናዘዝ ቀረበ። እኔ አንድ ቀን እጅግ ተርቤ ወዬ ነበርሁ። ዘላኖች ብዙ ከብት ይዘው በዱር ውስጥ በረት ሠርተው ተቀምጠው ነበረና ቀኑ ሲመሽ አይቼ በበረቱ ውጭ ቆሜ አንድ ጊዜ ባገሣ ሰንጋው ሁሉ በበረቱ እየዘለለ ወጣ፤ እኔም አንዱን ሠንጋ ሰብሬ ደሙን ጠጥቼ ሥጋውን በላሁት፤ ይህ ኃጢአት እንደ ሆነ ፍረዱብኝ አለ።

ባልንጀሮቹ መለሱ፤ ወዲህ ተርበህ ወዲህ ደግሞ በዱር ውስጥ የሚኖሩ ከብቶች አግኝተህ እንኳን አንድ ሰንጋ ብዙውንስ ብትበላ ምን ኃጢአት አለብህ ብለው ፈረዱለት።

ነብር ቀረበ፤ እኔም አንድ ቀን እጅግ ተርቤ በዱር ውስጥ ወዲያና ወዲህ እያልሁ ምግብ ስፈልግ፤ አንዲት ፍየል ከእረኛዋ ጠፍታ ብቻዋን ቅጠላ ቅጠሉን ስትለቃቅም አገኘኋት። ወዲያው አንቄ ይዤ ደምዋን ጠጥቼ ሥጋዋን በላሁት። ይህ ኃጢአት እንደ ሆነ ፍረዱብኝ አለ።

ባልንጀሮቹ መለሱ፤ ወዲህ ተርበህ ወዲህ ደግሞ ከእረኛዋ የጠፋች ፍየል አግኝተህ፤ እንኳን አንዲት ፍየል ብዙስ ብትበላ ምን ኃጢአት አለብህ አሉት።

ጅብ ቀረበ፤ እኔም አንድ ቀን እጅግ ተርቤ ውዬ ነበረ። ማታ ከጉድጓዴ ወጥቼ ምግቤን ስፈልግ ነጋዶች ቢደክምባቸው ጥለውት የሔዱ አንድ ፈረስ አጋሥሥ፤ ከመንገድ ዳር ወድቆ መነሣት አቅቶት ሲገለባበጥ አግኝቼ እርሱን በልቻለሁ፤ ይህ ኃጢአት እንደ ሆነ ፍረዱብኝ አለ።

ባልንጀሮቹ መለሱ፤ ወዲህ ተርበህ ወዲህ ደግሞ ነጋዶች ጥለውት የሔዱ አጋሥሥ አግኝተህ፤ እንኳን አንድ አጋሥሥ ብዙስ ብትበላ ምን ኃጢአት አለብህ አሉት።

ከዚህ በኋላ አህያን ነይ ተናዘዢ አሏት። አህያም ቀረበች፤ አንድ ቀን ጌታዬ ብዙ ጭነት ጭኖብኝ ስሔድ፤ ጌታዬ በመንደር ላይ አንድ ሰው አገኘና ከዚያ እየተነጋገረ ቆመ። እኔም እጅግ ተርቤ ነበረና እነዚያ እስቲነጋገሩ ድረስ በመንገዱ ዳር ሠርዶ መሳይ አግኝቼ ያንን እየነጫጨሁ ቆየሁ፤ ወዲያው ጌታዬ መጣና መጫኛውን አጠባበቀልኝ መንገዳችንን ተጓዝን። ይህ ኃጢአት እንደ ሆነ ፍረዱብኝ አለች።

ባልንጀሮችዋም መለሱ፤ ከዚህ የበለጠ ምን ኃጢአት አለ፤ ጌታሽ ከሰው ጋር እስቲነጋገር ከመንገድ ወጥተሽ ሠርዶ እየነጨሽ የቆየሺው ትልቅ ኃጢአት አይደለም፤ እግዚአብሔር ምግባችንን የነሣን ለካ ባንች ኃጢአት ኖርዋል።

አንችን ከመካከላችን ካላጠፋን እግዚአብሔር አይታረቀንም በለው ወዲያው ገነጣጥለው በሏት።

ልጆቼ ሆይ፤ ከኃይለኞችና ከክፉ ሰዎች ጋር ባልንጀርነት አትግጠሙ፤ በክፋታቸው መክረው በኃይላቸው ያጠፏችኋልና።

## አሥራ አምስተኛ

# ስለ አንድ ቅምጥል የበግ ግልገል

ብዙ በጐች ያሉት አንድ ሰው ነበረ። እርሱም በጐቹን ሲጠብቅ በብዙ ጥንቃቄ ነው። የለመለመ ሣር ይመግባቸዋል፤ የጠራ ውኃ ያጠጣቸዋል፤ ወደ ተራራ ላይ ቢወጡ በጥንቃቄ ያወርዳቸዋል፤ የደከሙትንም ይሸከማቸዋል፤ ወደ ማሳ ውስጥ እየገቡ ሲለቃቅሙ ባጠገባቸው ተቀምጦ ዋሽንት ይነፋላቸዋል፤ በጐቹም ዋሽንቱን እየሰሙ እጅግ ደስ ይላቸዋል።

ሲመሽም እንዳይርባቸው ወደ መልካሙ ጉረኖዋቸው አግብቶ ያጉራቸዋል። አውሬም እንዳያስደነግጣጨው ውሾች በስተ ውጭ ሆነው ይጮሁላቸዋል። ካንዱ ግልገል በቀር ሁሉም ጠባያቸውን ይወዳሉ። ያ አንዱ ግልገል ግን ጠባቂውን አይወድም ነበረና ማታ ማታም ወደ ጉረኖው መግባት አይወድም ነበረ። አንድ ቀን እናቱን ቀርቦ እናቴ ሆይ፤ እኛ ማታ ለምን ይዘጋብናል፤ እንሆ ውሾቹ ሳይዘጋባቸው በደኅና ያድራሉ፤ አሁንም ማታ እናንተ ስትገቡ እኔ ተደብቄ ቀርቼ በጨረቃ ብርሃን ከወዲያ ወዲህ እየሮጥሁ ደስ ሲለኝ ልደር አላት።

እናቲቱ መለሰች፤ ልጄ ሆይ፤ አርፈህ ተቀመጥ ጠባቂያችን እጅግ መልካም ሰው ነው። እርሱ እንዳዘዘን ውለን ብንገባ ይሻለናል። እምቢ ያልህ እንደ ሆነ በራስህ ላይ ጥፋትን ታመጣለህ አለችው።

ግልገሉም ይህን በሰማ ጊዜ፤ እናቴ ሆይ፤ መልካም ምክር አልመከርሽኝም። እኔስ ያሰብሁትን ሳላደርገው አልቀርም አላት።

ከዚህ በኋላ ጠባቂያቸው ማታ በጐቹን ሁሉ ነድቶ ወደ ቤቱ ሲመለስ ያ ግልገል ወደ ጉረኖው የገባ መስሎ ባጥር ውስጥ ምናምኑን ከለላ ሰጥቶ ቀረ። ጠባቂውም ግልገሉ ቀደም ብሎ የገባ መስሎት አጉሮባቸው ወደ በቱ ገባ።

ጊዜው ሲጨልምና በጐቹ ሁሉ ለጥ ብለው ሲተኙ እርሱ ከተደበቀበት ስፍራ ተነሥቶ እየሮጠ ወደ ዱር ተመለሰ። በዚያም ወዲያና ወዲህ እየሮጠ ሲጫወት አንድ

ተኩላ አይቶት ኑሮ በድንገት ደረሰበት። ወደ ጉረኖውም ለመሮጥ ቢያስብ ሩቅ ነበረና የማይሆንለት ሆነ። ከዚህ በኋላ ተኩላው ታቅፎ ወስዶ ወደ ጉድጓዱ ውስጥ አግብቶ አነጣጥጥሎ በላው።

ልጆቼ ሆይ፤ ያባትና የናታቸውን ምክር የማይሰሙ ልጆች እንደዚህ ይሆናሉና፤ የሽማግሎችን ምክር እንዳትንቁ ተጠንቀቁ።

## አሥራ ስድስተኛ

# አንድ ዳውላ እህል ስለ ተሰረቀበት ሰው

አንድ ባለ ጠጋ ዳውላ እህል ከቤቱ ተሰረቀበት። እርሱም ወደ ዳኛ ሔዶ ነገሩን ሁሉ ነገረ።

ዳኛውም የቤትህን ሰዎች ሁሉንም ሰብስበህ አምጣልኝ አለው። እርሱም ሰብስቦ አቀረበ። ዳኛውም ብዙ በትር አስመጥቶ ሁሉንም በትክክል አስቆረጠው። ከዚያም በኋላ፤ ለዚያ ሰው ቤተ ሰዎች ለሁሉም አንዳንድ በትር ሰጣቸው። ሲሰጣቸውም ነገ በዚህ ጊዜ ተመልሳችሁ ኑ፤ እያለ ሰጣቸው። ያ የጌታውን እህል የሠረቀ ሰው ይህን በሰማ ጊዜ ማታ ከበትሩ አንድ ጋት ቆረጠለት። በማግሥቱም በዚያው በታዘዙት ሰዓት ሁሉ ተሰብስበው ወደ ዳኛው ቤት ሔዱ። ዳኛውም ሁላችሁም የሰጧችሁን በትር አምጡ ብሎ ባንድነት ቢያቆመው የሌባው በትር አጥሮ ተገኘ። ከዚያ በኋላ እጁ ተይዞ ቢመረመር መስረቁን አምኖ ቅጣት ተፈረደበት።

ልጆቼ ሆይ፤ አይታወቅብንም ብላችሁ ኃጢአት አትሥሩ። የተደረገ ነገር ምንም በስውር ቢደረግ ሳይገለጥ አይቀርምና።

## አሥራ ሰባተኛ

# ስለ እንግሊዝ ንጉሥ ጆርጅ ፫ኛ

የእንግሊዝ ንጉሥ ፫ኛ ጆርጅ ለሽርሽር ወደ ባላገር ሔደው ሳሉ ድርቆሽ የሚያጭዱና የሚሰበስቡ ሰዎች ሁሉ ሥራቸውን እየተዉ ንጉሡን ለማየት ወደ መንደር እየሮጡ ሔዱ። ንጉሡ ግን አንደኛ ወታደር መስለው ድርቆሽ ወደ ሚታጨድበት ቢሔዱ፤ ካንዲት ሴት በቀር አንድ ሰው እንኳ ሳያገኙ ቀሩ። ባልንጀሮችሽ ሁሉ ወዴት ሔዱ ብለው ሴቲቱን ጠየቋት። ሴቲቱም መሰለች። ንጉሥ ወደ ባላገር መጥተዋል ተብሎ ተወርቶ ነበረና ርሳቸውን ለማየት ሔዱ አለቻቸው።

አንቺ ምነው ሳትሔጂ ቀረሽ አሏት። ንጉሡ ወዳሉበት ሥፍራ ሲገቡ ገንዘብ እየተከፈለው ነው። እኔ ግን ድኃ ነኝና ለዚያ የምከፍለው ገንዘብ የለኝም፤ ደግሞ አስምት ልጆች አሉኝና ለነዚያ ምግብ ስል ሥራ መፍታት አልወድም። ሥራም ካልሰራሁ፤ ገንዘብ አይገኝም ብላ መለሰች። ይህንም ሁሉ ስትናገር ንጉሥ ጆርጅ መሆናቸውን አላወቀችም ነበረ። ንጉሡ ግን የሦስት መቶ ብር ወርቅ ከኪሳቸው አውጥተው ሰጧት። ወዲያውም ባልንጀሮችሽ ሲመጡ ንጉሡ መጥቶ ሳለ ሦስት ሦስት መቶ ብር ታገኙ ነበራችሁ ብለሽ ንገሪያቸው ብለዋት እየጋለቡ ተመልሰው ሔዱ። እነዚያም ሠራተኞች ሥራቸውንም ሳይሠሩ፤ ንጉሡንም ሳያዩ፤ ገንዘብም ሳያገኙ እንዲያው በከንቱ ደክመው ቀሩ።

ልጆቼ ሆይ፤ በታዘዛችሁበት ሥራ ጸንታችሁ ብትኖሩ፤ እግዚአብሔር ድካማችሁን ሁሉ አይቶ የምትጠቀሙበትን ነገር ያዝላችኋል።

## አሥራ ስምንተኛ

# ስለ የጀርመን ንጉሱስ

የጀርመን ንጉሥ ታላቁ ፍሬድሪክ የሚባሉት ወደ ጦርነት ሲሔዱ፤ የሰፈሩበትን ቦታ ጠላቶቻቸው እንዳያይዩት ብለው አንድ ሰውስንኳ በድንኳኑ ውስጥ መብራት እያበራ፤ የኔን ትእዛዝ አፍርሶ መብራት አብርቶ የተገኘውን የሞት ፍርድ እፈርድበታለሁ፤ ብለው አዋጅ ነገሩ።

አንድ ቀን ማታ በሰፈር መካከል ብቻቸውን ሲመላለሱ አንዱ የወታደር አለቃ አልታይም ብሎ በድንኳኑ ውስጥ መብራት አብርቶ ደብዳቤ ጽፎ ለማተም ሲዘጋጅ በድንገት ደረሱበት።

አንተ ትእዛዜን ማፍረስህ ስለምን ነው አሉት። ጃንሆይ አይቆጡኝ፤ ለሚስቴ ደብዳቤ እጽፋለሁ ብዬ ነው አላቸው። እንግዲያውስ ሳታትመው አንዲት ቃል ጨምረህ ጻፍ አሉት። እንዴት ብዬ አላቸው።

ይህ ደብዳቤ ሲደርስሽ እኔ የንጉሡን ትእዛዝ በማፍረሴ ተፈርዶብኝ መሞቴን እወቂው ብለህ ጻፍ አሉት። እርሱም ይህን ጽፎ አትሞ ላከ። ንጉሡም በማግሥቱ አስፈረደው ገደሉት።

ልጆቼ ሆይ፤ ንጉሥ እምቢተኞችን ሁሉ ለመቅጣት ከእግዚአብሔር ሰይፍ ተቀብሏልና የንጉሥን ትእዛዝ ጠብቁ።

## አሥራ ዘጠኝ

# ስለ አንድ ሽማግሌ ሰውና ስለ አንዲት ሴት ልጅ

በመስኮብ ሀገር ሦስት ሴቶች ልጆች ያሉት አንድ ሽማግሌ ነበረ። ከሦስቱ አንዲቱ በመልኳና በጥበብዋ እጅግ ስመ ጥሩ ናት። አንድ ቀን ወደ ገበያ ሲወጣ ልጆቼ ሆይ፤ ከገበያ ምን ገዝቼላችሁ ልምጣ አላቸው። ሁለቱ ልጆቹ ጌጥ ገዝተህልን ና አሉት። አንዲቱ ግን እኔ ምንም አልፈልግም፤ ነገር ግን የምመክርህ ምክር ስማኝ አለቻው። ለጊዜው ነገሩ ከበደው፤ ነገር ግን ልጁ እጅግ ብልህ መሆኗን ያውቃልና ይሁን ንገሪኝ አላት። ወይንማውን በሬ ወደ ገበያ አውጥተህ ስትሸጥ፤ ዋጋ ንገር ያሉህ እንደ ሆነ የንጉሡን ግራ ዓይኑን አምጡና በሬውን ውሰዱ በላቸው አለችው። እርሱም በገበያ ተቀመጠና የበሬውን ዋጋ ንገር ሲሉት ልጁ እንደ መከረችው የንጉሡን ግራ ዓይኑን አምጡና ውሰዱት ይል ጀመረ።

ይህ ወሬ ንጉሡ ሰምቶ እጁን ይዛችሁ አምጡልኝ ብሎ አዘዘ። ሽማግሌውም በቀረበ ጊዜ ንጉሥ ሆይ፤ እንደዚህ ያደረገችኝ ልጄ ናትና ማረኝ እያለ ይለምን ጀመረ። ንጉሡም ይህን በሰማ ጊዜ ሔደህ ልጅን አምጣትና እምርሃለሁ አለው። ሽማግሌውም እያዘነና እየተንቀጠቀጠ ሔዶ ልጁን ይዞ ወደ ንጉሡ ቀረበ። ንጉሡም ልጅቱን ባያት ጊዜ ለበሬው ዋግጋ የንጉሡን ግራ ዓይኑን አምጡና ውሰዱ በላቸው ብለሽ ለአባትሽ የመከርሽው ስለምን ነው አላት።

ንጉሥ ሆይ፤ አልቀጣሽም ብለህ ማልልኝና እነግርሃለሁ አለችው። አልቀጣሽም ብሎ ማለላት።

ንጉሥ ሆይ፤ ድኃና ጌታ ተጣልተው ወዳንተ የመጡ እንደ ሆነ በቀኝ የቆመውን ጌታውን ብቻ ታያለህ እንጂ፤ በግራ የቆመውን ድኃውን አታይም፤ ስለዚህ መቸም ግራ ዓይንህ ሥራ ካልያዘልህ ብዬ ነው አለችው።

ንጉሡም የልጅቱን ንግግር ሰምቶ እጅግ አደነቀ። ወዲያውም ወንድ ልጁን ጠርቶ ልጄ ሆይ፤ በመልክና በእውቀት ከርሷ የምትሻል ሴት የለችምና እርሷን አግብተህ መንግሥቴን ይዘህ ኑር አለው። ልጁም እርሷን አግብቶ እርሱ ንጉሥ እርሷ ንግሥት ተብለው ኖሩ።

ልጆቼ ሆይ፤ መልካም ንግግርና ጥበብ ሰውን ታስከብራለችና ንግግራችሁ ሁሉ፤ በመልካምነትና በጥበብ ይሁን። የጥበብም መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው።

ተጨረሰ፤ አሜን።

# ክፍል ፬ የልብ አሳብ

## የብርሃኔና የጽዮን ሞገሳ ጋብቻ

### መቅድም

ጠጅ በብርሌ፤ ነገር በምሳሌ፤ እንደተባለ ነገር ሁሉ በምሳሌ ሲሆን ለሰሚው በቶሎ ያስረዳዋል።

ለገበሬው በእርሾና በእንጀራ፤ በወጥና በጠላ መስለው ከሚነግሩት እርሱ በሚያውቀው በርሾና በዘር፤ በመከርና በበልግ በስለው ቢነግሩት ያስረዳዋል።

ለነጋዴም በጠመንጃና በሸጉጥ፤ በጋሻና በጦር መስለው ከሚነግሩት፤ እርሱ በሚያውቀው በንግድ ዕቃ በልብስና በምንጣፍ፤ በግምጃና በሐር፤ በብርሌና በብርጭቆ መስለው ቢነግሩት ያስረዳዋል።

ለወታደርም በጽሕፈት፣ በድጉሰት፣ በማንበብና በመተርጐም መስለው ከሚነግሩት እርሱ በሚያውቀው በጠመጃና በሸጉጥ፣ በጋሻና በጦር መስለው ቢነግሩት ያስረዳዋል።

ለካህንም በእርሻና በዘር፣ በመከርና በበልግ፣ መስለው ከሚነግሩት እርሱ በሚያውቀው በከበሮና በጸናጽል፣ በመስቀልና በጥና መስለው ቢነግሩት ያስረዳዋል።

ለሴትም በከበሮና በጸናጽልን፤ በመስቀልና በጥና መስለው ከሚነግሩዋት እርስዋ በምታውቀው በርሾና በእንጀራ፤ በወጥና በጠላ መስለው ቢነግሩዋት ያስረዳታል።

ይህም የልብ አሳብ የተባለ ጽሑፍ ዋና ምሳሌነቱ ሚስት ስለ ማግባትና ልጅ ስለ መውለድ፤ ልጅንም በጥንቃቄና በትምሕርት ስለ ማሳደግ ነውና ሚስት ለማግባት የሚፈልግ ወንድና ባል ለማግባት የምትፈልግ ሴት ሁለቱም አስቀድመው ይህን መጽሐፍ በቅንነትና በማስተዋል ቢያነቡት ወደ መልካም ፍጻሜ የሚያደርስ ምክር ያገኙበታል። የእግዚአብሔር የተቀደሰ ፈቃዱ ይሁንላችሁ፤ አሜን።

### ምዕራፍ ፩

# አቶ ክብረትና ገነሆይ ንጋቷ ጽዮን ሞገሳን ስለ መውለዳቸው

በቡልጋ አውራጃ እቲሳ በሚባል ሀገር የሚኖር አቶ ክብረት የሚባል ሰው እመየት አጥናፊ ወርቅን አግብቶ ሲኖር መካን ነበረችና ልጅ የማትወልድለት ሆነች። በዚህም ላይ አመንዝራና አመለ መጥፎ ስለ ሆነችበት በፍትሐ እንገሥት አስፈርዶ እርስዋን ፈታና ገነሆይ ንጋቷን አገባ። ገነሆይ ንጋቷ እግዚአብሔርን የምትፈራ፤ ባሏን የምታከብርና የምታፍር ስለ ሆነች ኑሮው ሁሉ ኑሮ ሆነለት።

ባገባትም በሁለተኛው ዓመት አንዲት ሴት ልጅ ወለደችለት። ልጅቱም የተፀነሰችው በሙቀት ወራት በሚያዝያ ስለ ሆነ፤ ወዲያውም እናትዋ ያለ ኅዘን በደስታ ነዋሪ ስለ ሆነች አካልዋ ትልቅ ሆኖ ተወልዳ ነበር።

አቶ ክብረትም ልጅቱ ትልቅ ሆና መወለዷን ባየ ጊዜ ገና ስትወለድ እንደዚህ ትልቅ የሆነች ከጥቂት ዓመት በኋላም ምን ታህል ይሆን፤ ዛሬውኑ አንድ አቅ ሽማ የምትፈጅ ትመስላለች። ስታድግማ ልብስዋ ብቻ እጅግ የሚያከስረኝ ነውና ከወዴት እያመጣሁ ላለብሳት ነው እያለ ያጉረመርም ጀመር።

እናትየዋም የባልዋን ማጉረምረም በሰማች ጊዜ ጌታዬ ሆይ፤ ክርስቲያን ሆነህ ይህን ይህን የመሰለ የማይገባ ንግግር መናገርህ ስለምን ነው። በማሕፀን ውስጥ በክርታስ ጠቅልሎ በእትብት መግቦ ዘጠኝ ወር ሙሉ ያሳደጋትና የጠበቃት ፈጣሪዋ የዕለት ምግብና ልብስ የሚነሣት ይመስልሃልን አለችው።

ከዚህም በኋላ በተወለደች በ፹ ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን ወስደው ክርስትና አነሱዋት። የክርስትና እናትዋም እመየት አቅሌሳ ነበሩ። የክርስትና ስምዋም ጽዮን ሞገሳ ተባለ።

ጽዮን ሞገሳ አንድ ጊዜ ብቻ ፈንጣጣ ተከትባ በብዙ ስለ ወጣባት ሁለት ወር ያህል ታማ ነበር እንጂ ከሕፃንነትዋ ጀምራ ባለ ጤና ነበረች።

እድሜዋም ሰባት ዓመት በሆነ ጊዜ አባትና እናትዋ ትምሕርት እንድትማር ስለ ፈቀዱ ስለ ትምሕርትዋ ክርክር አነሡ።

አባትዋ መጽሐፍ ማንበብና ጽሕፈት መጻፍ፤ የእጅ ሥራ ስፌት መስፋት፤ ልብስ መጥለፍ፤ ይህን የመሰለውን ሁሉ ትማር አለ። እናትዋ ግን ፈትል መፍተል፤ እንጀራ መጋገር፤ ወጥ መሥራ፤ ጠጅ መጣል፤ መጥመቅ ትማር አለች።

በዚህም ነገር አባትና እናትዋ ሳይሰማው በመቅረታቸው ክርክር ስለ አበዙ የነፍስ አባታቸው መምሬ ተስፋ ተጠርተው መጡ። ያልተስማሙበትንም ነገር ሳያነሱ እንዲያው በድፍን አድርገው አባታችን ሆይ፤ ልጃችን ጽዮን ሞገሳ በጣም አደገች እንግዴህ ትምህርት ብትማር ይሻላል ብለን አስበናልና ምን ዓይነት ትምሕርት ብትማር ይሻል ይመስልዎታል ብለው ጠየቋቸው።

መምሬ ተስፋ ግን እጅግ ብልህ ነበሩና የዛሬ ዘመን ልጆች እንደ ቀድሞ ዘመን ልጆች አይደሉም፤ ስለዚህ ለጽዮን ሞገሳ የሚሻላትን ትምሕርት ለይቼ ለመናገር አልችልም። ዳሩ ግን ለልጅ ይታየዋልና እርስዋን ራስዋን የትኛው ትምሕርት ይሻልሻል ብለን ብንጠይቃት ሳትነግረን አትቀርም በልው መለሱ።

በዚህም ነገር አባትና እናትዋ ተስማምተው ጽዮን ሞገሳ ተጠርታ መጣችና በፊታቸው ቆመች። መምሬ ተስፋም እንግዴህ ወዲህ ትምሕርት ብትማሪ ይሻልሻል፤ ቁመትሽም አደገ፤ እድሜሽም ከሰባት ዓመት ሊያልፍ ነው። ስለዚህ ደስ የሚያሰኝሽንና የምፈቅጅውን ትምሕርት ንገሪኢን አልዋት።

ጽዮን ሞገሳም ይህን በሰማች ጊዜ እኔ ልጅ ስለሆንሁ የትምሕርቱን ዓይነት ሁሉ ለይቼ ለማወቅ አልችልምና የትምሕርቱን ዓይነት አንዳንዱን እየለያችሁ በተራ ብትነግሩኝ ለመምረጥ እችላለሁ ብላ መለሰች።

መምሬ ተስፋም ይህን በሰሙ ጊዜ የዛሬ ዘመን ልጆች ገና ሲወለዱ ብልጠታቸው ይበዛል። እርስዋን ብንጠይቃት ነገሩን መልሳ በእኛ ላይ ጣለችው። ቢሆንስ እኛ ምን ቸገረን። የትምሕርቱን ዓይነት በየተራ እየነገርን እንጠይቃትና የምትመርጠውን ትንገረን ብለው ጥያቄውን ሁሉ በየተራ አቀረቡላት።

ጥያቄ፤ እንጀራ መጋገር ብትማሪ ትወጃለሽ?

ምላሽ፤ ስፈጭ፣ ሳቦካ፣ ስጥድ፣ ስጋግር በዚህ ሁሉ መድከሜ ስለ ምን ነው፤ ቢያንስ ሁለት መሐልቅ ቢበዛ አራት መሐልቅ ለአንድ አሸከር ሰጥቼ እንጀራ ወይም ዳቦ ገዝቶ አያመጣልኝምን።

ጥያቄ፤ ፈትል መፍተል ብትማሪስ ትወጃለሽ?

ምላሽ፤ ጥጥ በመፈልቀቅና በመዳመጥ፤ በመንደፍና በመፍተል ጣቴ ሲነድ መኖሩ ስለ ምን ነው። ባንድ ብር ድር፤ በሁለት ብር ማግ ገዝቼ ኩታ ቢያምረኝ ኩታ፤ ጃኖ ቢያምረኝ ጃኖ፤ ቀሚስ ሚያምረኝ ቀሚስ አላሰራውምን።

ጥያቄ፤ ጠጅ መጣል፤ ጠላ መጥመቅ ብትማሪ ትወጃለሽ?

ምላሽ፤ ማርና ጌሾ በመግዛት፤ ገብስና ማሽላ በመሸመት፤ አሻሮ በመቁላትና በመፍጨት፤ እንኩሮ በማንኮር ብቅል በማብሰል፤ ጌሾ በመውቀጥ፤ ስደክም መኖሬ ስለ ምን ነው፤ ሶዳ ቢያምረኝ ሶዳ፣ የወይን ጠጅ ቢያምረኝ የወይን ጠጅ፤ እያስገዛሁ ይህ ቢጠፋ የተጣራ ውኃ አልጠጣውምን።

ጥያቄ፤ መጽሐፍ ማንበብ ብትማሪ ትወጃለሽ?

ምላሽ፤ ይህማ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነገር ነው። መጽሐፍ በማንበብ የቀድሞውን ዘመን ያባቶቻችንንና ታሪክ፤ የዛሬውን ዘመን በእውቀትና በጥበብ የተሠራውን ሥራ ሁሉ ለማወቅ እችላለሁ። በመንፈሳዊም ወገን ቢሆን የእግዚአብሔርን አንድነቱንና ሶስትነቱን ክርስቶስም ስለ እኛ ብሎ ሰው መሆኑንና በመስቀል ተሰቅሎ መሞቱን ትንሣኤውንና ዕርገቱን፤ ለቃሉ በመታዘዝ ጽድቅ መገኘቱን፤ ባለምታዘዝ ኵነኔ መፈረዱን ለማወቅ እችላለሁ።

ጥያቄ፤ ደግሞስ ጽሕፈት መጻፍ ብትማሪ ትወጃለሽ?

ምላሽ፤ ይህም ትልቅ ጥቅም የሚገኝበት አንድ ዋና ነገር ነው። ያሰብሁትን እንዳልረሳው፤ አስቤ የሠራሁትን እንዳልዘነጋው እየጻፍሁ አቀምጣለሁ። መኖሪያዬም ከአባቴና ከእናቴ፤ ከዘመዶቼና ከወዳጆቼ በራቀ ሀገር የሆነ እንደ ሆነ ሰላምታዬንና ጉዳዬን እየጻፍኩ ለመላክ ይጠቅመኛል። ይልቁንም በትምሕርት ትልቅ እውቀት ያገኘሁ እንደ ሆነ ድርሰት እየደረስሁ፤ ታሪክ እየጻፍሁ ለስሜ መታሰቢያና ለሀገሬ ልጆች ጥቅም የሚሆን መጽሐፍ ለመጻፍ እችላለሁ።

ጥያቄ፤ የእጅ ሥራ ብትማሪ ትወጃለሽ?

ምላሽ፤ ይህማ ለሰው ኑሮ የሚያስፈልግና የሚጠቅም ስለ ሆነ በግድ ለመማር ይገባኛል። ቀኑን ሙሉ ያለ ሥራ ተቀምጬ ብውል በሽተኛ መሆኔ አይቀርምና እጄን በማንቀሳቀስ ሥራ በመሥራት ሕዋሳቶቼ ሁሉ የተፈጥሮ ሥራቸውን እየሠሩ ጤናዬን አገኛለሁ።

ደግሞ ለእግርና ለእጅ፤ ለደረትና ላንገት የሚሆን ሹራብ እየሰራሁ እለብሳለሁ። ልጆችም ብወልድ የሚሞቅ ሹራብ እየሠራሁ አለብሳቸዋለሁ። ከዚህም የተረፈውን በመልካም ዋጋ እየሸጥሁ ለሕይወቴ የሚያስፈልገኝን ምግብና መጠጥ እገዛበታለሁ። ይህም ሁሉ ጥቅም የሚገኝበት ነውና መጽሐፍ ማንበብ፤ ጽሕፈት መጻፍ፤ የእጅ ሥራ መሥራት ለመማር ፈቃዴ ነው ብላ አሳብዋን ገልጣ ነገረቻቸው።

መምሬ ተስፋም ይህን የመሰለ ትልቅ ነገር ከጽዮን ሞገሳ አፍ በሰሙ ጊዜ እጅግ አደነቁና ልጄ ሆይ፤ አንቺ እንደ ማርታ እኅት እንደ ማርያም ነሽ። ማርታ ቀኑን ሁሉ ምግብ በማሰናዳት ትውል ነበረ፡ እኅቷ ማርያም ግን የመጽሐፍ ትምሕርት ብቻ ለመስማት ትወድ ነበርና ማርታ በዚህ ነገር ስለ ተናደደች በማርያም ላይ የቁጣ ቃል ብትናገር ጌታችን ማርታ ሆይ፤ ብዙ በማሰናዳት ለምን ብዙ ትደክሚያለሽ። ለዚህ ጥቂት ይበቃል። ማርያም ግን ማንም ቀምቶ ሊወስድባት የማይቻለውን ትምሕርት ወዳለች ብሎ መልሶላታልና አንችም እንደ ማርያም ነሽ ብለው ተናገሩ። ሉቃ. ፲፰ - ፵፪።

የጽዮን ሞገሳ አባት አቶ ክብረት ጥንቱንም አሳቡ ልጁ መጽሐፍ ማንበብና ጽሕፈት መጻፍ፤ የእጅ ሥራ እንድትማርለት ነበርና አሁን የርስዋም አሳብ እንደ እርሱ በመሆኑ እጅግ ደስ አለው።

መምሬ ተስፋም የሚሻላትን ትምሕርት እርስዋ ትጠየቅና ትመልስ ብለው ስለ ማመልከታቸው ትልቅ ምስጋና አገኙ።

በዚያም ዘመን እቲሳ ገዳም አባ ወልደ ሕይወት የተባሉ ሽማግሌ በቤተ ክርስቲያኑ አጠገብ በኢት አሥርተው የሰበካውን ልጆች ሁሉ ያስተምሩ ነበርና ጽዮን ሞገሳም በአባትና በእናትዋ ፈቃድ እየሔደች ትማር ጀመር። ትምሕርት በጀመረች በሁለት ዓመት ማንበብና መጻፍ ተምራ ጨርሳ ዳዊት ደገመች።

ከዚህ በኋላ የተማረችውን እንዳትገድፍ ሁለት ዓመት ያህል እየተመላለሰች ቆይታ ነበር። ደግሞ እንዳጋጣሚ እማኖይ ወለተ ኪዳን የተባሉ መነኵሲት ወደ ኢየሩሳሌም ሲኖሩ እየጅ ሥራ ሹራብ መሥራትና ልብስ መጥለፍ ተምረው በዚያው እቲሳ ገዳም በአባ ወልደ ሕይወት ቤት አጠገብ ይኖሩ ነበርና ጽዮን ሞገሳ እግረ መንገድዋን አንዳንድ ጊዜ እየሔደች የእጅ ሥራ ተማረች።

## ምዕራፍ ፪

# ስለ ጽዮን ሞገሳ እጮኛ - ስለ ብርሃኔ

በተጉለት አውራጃ ዘንዶ ጉር በሚባል ሀገር አጠገብ የሚኖር አቶ ዘሚካኤል የተባለሰው ነበር። እርሱም ከቡልጋ አውራጃ ከእቲሳ በለጥሻቸው የተባለች ሴት አግብቶ ሲኖር በተጋቡ በሦስተኛው ዓመት ወንድ ልጅ ወለደችለት።

ሕፃኑም ገና ከመወለዱ የጽጌ ረዳ አበባ ይመስል ነበር። አርባ ቀንም በሆነው ጊዜ ወደ ደብረ ብርሃን አውጥተው ክርስትና አስነሡት። የክርስትና አባቱም የደብረ ብርሃን

አለቃ መምሕር ፀሐይ ነበሩ። የክርስትና ስሙም ብርሃነ ሥላሴ ተባለ። ነገር ግን በከፊለ ስም ብርሃኔ እያሉ ይጠሩት ነበር።

ዕድሜውም ሰባት ዓመት በሆነ ጊዜ አባቱ አቶ ዘሚካኤል ወደ ደብረ ብርሃን አውጥቶ ተምሮ ዳዊት እስቲደግም ከእርስዎ ጋራ ይቀመጥልኝ ብሎ ለክርስትና አባቱ ለመምሕር ፀሐይ ሰጥቷቸው ተመለሰ።

ብርሃኔም ንባብና ጽሕፈት ተምሮ ከጨረሰ በኋላ ዳዊት ደገመና የምሥራች ለማለት ወደ አባቱ ቤት በወረደ ጊዜ ዘመድ አዝማዱ ሁሉ ተሰብስቦ ሲመርቀውና ሲሸልመው ዋለ።

ከዚህም በኋላ እንደ ገና ወደ ደብረ ብርሃን ተመልሶ ወጥቶ ሰዋሰው ተምሮ ቅኔ አወቀ። አንዳንድ ግዜም ወደ እናቱ ሀገር ወደ እቲሳ እየወረደ ከእናቱ ዘመዶች ጋር እየተዋወቀና እየተላመደ ይመለስ ነበር።

ዕድሜው ፲፰ ዓመት በሆነ ጊዜ በታሕሣሥ ፳፬ ቀን ስለ ሚሆነው ስለ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የልደት በዓል ከእናቱ ዘመዶች ጋር በዓሉን ለማክብር ለበዓሉ ሳምንት ቀን ሲቀረው እቲሳ ወርዶ ነበርና አንድ ቀን ጽዮን ሞገሳ ከባልጀሮችዋ ጋር ከቤተ ክርስቲያን ወደ ቤትዋ ስትመለስ እርሱ በመንገድ ዳር ቆሞ ካንዱ ዘመዱ ጋር ሲነጋገር አያትና ሰውነቱ ደንገጠበት።

ወዲያውም ይህች ልጅ የማን ልጅ ናት? ብሎ ቢጠይቅ ያቶ ክብረት ልጅ መሆንዋን ነገሩት።

ከዚህም በኋላ በሌላ ቀን ደግሞ እንደ ልማዷ ወደ ቤተ ክርስቲያን ስትሔዱ አገኛትና ብቻዋን ስለ ሆነች ሊያነጋግራት ቀረበ። ንግግርም በጀመረ ጊዜ የፊትዋን ደም ግባት የንግግርዋን ውበት አይቶ በፍቅርዋ ተነደፈና ለጋብቻ ያስብ ጀመር።

ወደ ዘመዶቹም ቤት በገባ ጊዜ በመንገድ ላይ እጅግ መልከ መልካም ቆንጆ ልጅ አይቶ ማነጋገሩን ነገራቸው። ዘመዶቹም ገና ተናግሮ ሳይጨርስ ጽዮን ሞገሳ መሆኗን አውቀው እርስዋማ የወዳጃችን ያቶ ክብረት ልጅ ናት። አንተ የምትናገርው የመልኳን ማማር ብቻ ነው። ነገር ግን የእውቀቷንና የደግነቷን፤ ያመሏንም ነገር አይተህ ብትሆን በጣም ያስደንቅ ነበር። አሁንም ነገ ወደ አባቷ ዘንድ ወስደን እናስተዋውቅሃለን ብለው ነገሩት።

በማግሥቱም ወደ አቶ ክብረት ቤት ወስደው ይህ ልጅ የእኅታችን የመየት በለጥሻቸው ልጅ ነው። ከአሥር ቀን በፊት ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት በዓልና ወዲያውም

እኛን ዘመዶቹን ለማየት መጥቶ እዚሁ ሰንብቷል። ከጽዮን ሞገሳም ጋራ ቢተዋወቁ መልካም ነው እያሉ ተናገሩ። ብርሃኔ ምንም ነገሩን ገልጦ ለዘመዶቹ ባይናገር ባነጋገሩ ጽዮን ሞገሳን ለማግባት ማሰቡን አውቀውበት ነበርና ቢተዋወቁ መልካም ነው ከማለት የደረሱበት ስለዚህ ነው።

የልደትንም በዓል እቲሳ ውሎ በማግሥቱ ወደ ተጉለት ተመለሰ። በፊት ወደ እቲሳ ለመውረድ ከአባትና ከእናቱ ለልደት እመለሳለሁ ብሎ ነበር። ነገር ግን በድንገት ጽዮን ሞገሳን በማግኘቱና አዲስ አሳብ ስለ ተነሳበት ጊዜውን አሣልፎ ወጣ።

ብርሃኔም ጽዮን ሞገሳን ከማየቱ አስቀድሞ ዘመዶቹን ለማየት ወደ እቲሳ የሚወርደው ባመት አንድ ጊዜ ብቻ ነበር። ከዚያ ወዲህ ግን ዘመዶቼ ናፍቀውኛል እያለ በሁለት ወር ይመላለስ ጀመር።

እቲሳም ደርሶ በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ወደ አቶ ክብረት ቤት ሳይሄድና ከጽዮን ሞገሳ ጋራ ሳይነጋገር አይመለስም ነበር።

ጽዮን ሞገሳ ግን በብርሃኔ ልብ የጋብቻ አሳብ መኖሩን ምንም አታውቅም ነበርና በገርነት ልብዋን ከፍታ ታነጋግረው ነበር እንጂ እንደ ልጅ አገረድ አንገቷን ደፍታ፤ ፊቷን አዞራ አታነጋግረውም ነበር።

## ምዕራፍ ፫

# ብርሃኔ ጽዮን ሞገሳን ለማግባት ቊርጥ አሳብ ስለ ማድረጉ

ብርሃኔም የጽዮን ሞገሳ እድሜዋ ፲፫ ዓመት መሆኑን ጠይቆ ባወቀ ጊዜ እናቱ ዘመዶቹ ሔዶ ጽዮን ሞገሳን ለማግባት ማሰቡን ገልጦ ነገራቸው። ዘመዶቹም ባንድ ወገን የእኅታቸው ልጅ ለዚህ ማዕረግ ስለ መድረሱ በሁለተኛውም ወገን ከሌላ ሀገር ሳይሆን ከዚያው ከእናቱ ሀገር ሚስት ለማግባት ስለ ማሰቡ እጅግ ደስ አላቸውና ነገ ጧት ወደ አቶ ክብረት ቤት ሔደን ልጅህን ጽዮን ሞገሳን ለእኅታችን ልጅ ለብርሃኔ ስጥልን ብለን እንለምንልሃለን አሉት።

ብርሃኔም የዘመኑን እውቀት የተማረ ብልህ ነበርና ይህስ ከቶ ምንም ቢሆን አይሆንም። ነገር ግን እኔው ራሴ ልጅቱን ለብቻዋ ጠርቼ እነግራታለሁና የምትመልሰውን ነገር ከሰማሁ በኋላ የሚያስፈልገውን ነገር ታደርጉልኛላችሁ አላቸው።

ከዚህም በኋላ የጽዮን ሞገሳ አባት አቶ ክብረት በእቲሳ ብዙ አታክልት ነበረውና ወደ ማታ በአታክልት ውስጥ ገብታ ሎሚና ትርንጎ ስትለቅም ብርሃኔ በድንገት ደረሰና እርስዋን ለማግባት ማሰቡን ገልጦ ነገራት።

እርስዋም ይህን ነገር በሰማች ጊዜ ደነገጠችና ኧረ በስመ አብ በል አሁን የእኔ እድሜ ገና ፲፫ ዓመት ነው፤ ዳሩ ግን ፲፭ ዓመት ሳይሆነኝና አካለ መጠን ሳላደርስ ምንም ቢሆን ባል አላገባም አለችው።

ብርሃኔ እስከ ፲፭ ዓመት ባል ሳታገቢ መቆየትሽ ስለ ምን ነው? ብሎ ጠየቃት።

ጽዮን ሞገሳ ፲፭ ዓመት ሳይሆነኝና አካለ መጠን ሳላደርስ፤ ሥጋዬ ሳይሞላና አጥንቴ ሳይጠነክር ባል አግብቼ የፀነስሁ እንደ ሆነ ሕፃኑ ብርቱ አይሆንም፤ እኔም በደህና ለመገላገል አልችልም። ምናልባት እስከ ሞት ያደርሰኝ ይሆናል አለችው።

ብርሃኔ ምነው ካንች የሚያንሱ ሴቶች በአሥር አመትቃቸው ባል እያገቡ በደህና እየተገላገሉ ይወልዱ የለምን። ባንቺኢ ብቻ ምን መጥቶብሻል አላት።

ጽዮን ሞገሳም ወዳጄ ሆይ፤ ይህስ እውነትና መልካም ነገር አይምሰልህ። ምናልባት አካለ መጠን ሳይደርሱ ባል የሚያገቡ ሴቶች ምናልባት ከመቶው ዘጠናው ሞተው አሥሩ በደህና ተገላግለው ይሆናል።

ይህንም ለመረዳት ብትፈልግ ለምሳሌ አስረዳሃለሁ። አንድ ዛፍ በግልገልነቱ የሆነ እንደ ሆነ ትንሽ ልጅ ነቅሎ ይጥለዋል። በጣም ያደገ እንደ ሆነ ለመቁረጥ ብዙ መጋዝና ብዙ ምሳር ያስፈልገዋል።

እንደዚህ አካለ መጠን ያልደረሰች ሴት ባል አግብታ የፀነሰች እንደ ሆነ ዘጠኝ ወር ሙሉ ሕፃኑን ለመሸከም አትችልምና ትጨነቃለች። በምትወልድበትም ጊዜ ለመውለድ ኃይል አታገኝምና በቶሎ ወደ ሞት ትደርሳለች።

አካለ መጠን አድርሳ ባል ያገባች እንደ ሆነ ግን ሥጋዋ ሙሉ፣ ጉልበትዋ ብርቱ ስለ ሆነ ሕፃኑን ዘጠኝ ወር በሆድዋ ለመሸከም ትችላለች። ለመውለድም ኃይል ታገኛለች። ስለዚህ አካለ መጠን ሳላደርስ ባል ባገባ በወሊድ እንድሞት አውቃለሁና ምንም ቢሆን ዛሬ ባል አላገባም አለችው።

ብርሃኔም ከጽዮን ሞገሳም ቃል ይህን በመስማቱ እየተደነቀ እኔ አንችን ለማግባት ማሰቤ በትምህርት ቤት ማደግሽን ስለ ሰማሁ ትዳሬን እንድታሳድሪልኝ፤ ቤተ ሰዎቼን እንትጠብቂኢልኝ ብዬ ነበር አንጂ የጌታ ልጅ ነሽ ወይም ባለገንዘብ ነሽ ብዬ አልነበረም።

አሁንም ፈቃድሽ ካልሆነ ምን አደርጋለሁ፤ ወደ ፊት እግዚአብሔር የሚያደርገውን እጠብቃለሁ። በደህና ሰንብቺ ብሎ ከአታክልቱ ውስጥ ወጥቶ ሔደ።

ነገር ግን የጽዮን ሞገሳን ጋብቻ የፈለገው በፍጹም ልቡ ስለ ሆነ ተቆጥቶ ለመሔድ አልቻለምና ጥቂት መንገድ ከሄደ በኋላ ተመልሶ መጣ።

ጽዮን ሞገሳም ከዓይንዋ እስቲርቅ ድረስ ቆማ ትመለከተው ነበርና ተመልሶ ሲመጣ ባየችው ጊዜ በፍጥነት ቀርባ ተመልሶ የመጣበትን ምክንያት ጠየቀችው። በርሃኔም ጋብቻው እንዳይቀርበት ስለ ተጨነቀ ምናልባት አንድ ሌላ ምክንያት ለመፈለግ መሆኑን ነገራት።

ጽዮን ሞገሳ እኔ አንተን ለማግባት ፈቃዴ መሆኑ እርግጥ ነው፤ ነገር ግን አካለ መጠን ሳላደርስ ምንም ቢሆን ባል አላገባምና እኔን ለማግባት ቁርጥ አሳብ አድርገህ እንደ ሆነ እስከ ሁለት ዓመት ታግሠህ ቆይ አለችው።

ብርሃኔም መታገሡንማ ከዚህስ የበለጠ ዘመን ብታገሥ ምን ጉዳት አለብኝ። ነገር ግን የሽመገሉ አባትና እናት ጠባቂ የሌላቸው ቤተ ሰዎች አሉኝና ጋብቻው በቶሎ እንዲሆን ማሰቤ ስለዚህ ነበር፤ ካልሆነም ምን አደርጋለሁ እኔኑ እግዚአብሔር ባያድለኝ ይሆናል። አሁንም በደህና ሰንብች ብሎ መንገዱን ጀመረ። ነገር ግን አንድ ምዕራፍ ያህል ከሔደ በኋላ እንደ ገና ተመልሶ መጣ።

ጽዮን ሞገሳም ሦስተኛ ተመልሶ ሲመጣ ባየችው ጊዜ የፊተኛው አሳቡን ለውጦ አካለ መጠን እስክትደርሺ እታገሣለሁ ለማለት የተመለሰ መስሏት በደስታ ልትቀበለው ሔደችና የተመለሰበትን ምክንያት ጠየቀችው።

እርሱም አንቺ አካለ መጠን ለመድረስ የቀረሽ ሁለት ዓመት ብቻ ነው ብለሽኛልና እንደዚህ ከሆነ እስከ ሁለት ዓመት በግብረ ሥጋ እንዳልገናኝሽ ልማል፤ ልገዘትና የጋብቻውን ሥርዓት እንድንፈጽም ፈቃድሽ እንዲሆን ልጠይቅሽ ተመልሼ መጣሁ አላት።

ጽዮን ሞገሳም ይህን የመሰለ የማይገባና እውነት ያልሆነ ነገር በመስማቷ እጅግ አዘነች፤ ወዲያውም ፊቷን ወደ እርሱ አቅንታ ወዳጄ ሆይ፤ እስከ ዛሬ ድረስ ባስተያየትህና በንግግርህም ሁሉ አዋቂና አስተዋይ ትመስለኝ ነበር፤ ለካ እንደዚህ ሞኝና ዝንጉ ኑረሃልን።

ወንድና ሴት ባንድ ቤት ተቀምጠውና ባንድ አልጋ ተኝተው በግብረ ሥጋ ሳይገናኙ ይኖራሉ በለህ ብትናገር አእምሮ ያለው ሰው ከሆነ እውነት ነው ብሎ እንደምን

ሊቀበልህ ይችላል። እሳትን በገለባ ውስጥ ቢሸጉጡት ገለባው ሳይቃጠልና ሳይነድ ይቀራልን። ስለዚህ ምንም ቢሆን በዚህ ነገር አልታለልም። አንተም በዚህ ነገር ለማታለል ማሰብህ በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ ኃጢአት ነውና ንስሐ ግባ። ደግሞም አሁን ይህን ሁሉ ነገር የሚያናግርህን ንግግርህ ላይ አግኝቸዋለሁ፤ ለእኔ እንደ መሰለኝ አሁን የጋብቻውን ሥርዓት ካልፈጸምሁ ምናልባት እስከ ሁለት ዓመት ከሌላ ሰው ጋር የጋብቻ ነገር ትነጋገርብኛለች በልህ ጠርጥረህ ነውና እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ከሌላ ሰው ጋር የጋብቻ እንዳልነጋር የእግዚአብሔርን ስም ጠርቼ እምልልሃለሁ። ሁለት ዓመት ካለፈ በኋላ ግን ከመሐላው ንጹሕ ነኝ። ያም ቢሆን ሁለቱ ዓመት እስቲጨረስ ወደ ደብረ ሊባኖስ ወርጄ በሴቶች ገዳም ተቀምጬ መንፈሳዊ ትምህርት ለመማር አስቤአለሁና በዚሁ በሁለት ዓመት ውስጥ ከሌላ ሰው ጋር የጋብቻ ነገር ትነጋገራለች በለህ አትጠራጠር አለችው።

ብርሃኔም ይህን የእምነት ንግግር ከቃልዋ በሰማ ጊዜ ደስ አለውና አሁን ገና የልቤን አገኘሽው። እስካሁን የተነጋገርነው ሁሉ በመተፋፈር በከንቱ ጊዜ ማሳለፊያ ነበር። ዋናው አሳቤ ግን አሁን እንደ ተናገርሽው ነውና ከእንግዲህ ወዲህ ልቢኤ ያርፍልኛል። ለልቤም ትልቅ ተስፋ ሆኖ የሚቆይ ይህን የእምነት ነገር ስለ ነገርሽኝ አመሰግንሻለሁ።

እንግዲህማ ከሆነልኝ ሁለቱ ዓመት ይቅርና አምስት ዓመትስ ታግሼ ብቆይ ምን ጉዳት አለብኝ፤ እስካሁንም የፈራሁት አሁን የተናገርሽው ነገር እንዳይደርስብኝ ነበርና ለዚሁ ቃልሽን ከሰጠሽኝ እምነቴን ባንቺ ላይ አደርጋለሁ። ነገር ግን ጥቂት የሚያሳዝነኝ ወደ ደብረ ሊባኖስ ወርደሽ በሴቶች ገዳም የተቀመጥሽ እንደ ሆነ ወደዚያ ስፍራ ወንድ አይገባምና እስከ ሁለት ዓመት ዓይን ላይን ሳንተያይ መቆየታችን ነው አላት።

ጽዮን ሞገሳም መለሰች፤ ወዳጄ ሆይ፤ ይህን የመሰለ አሳብ ማሰብህ እጅግ ያስደንቃል። እኔስ ሁለት ዓመት ሙሉ አባትና እናቴን ዘመዶቼንስ ሁሉ ሳላይ እንደምን የምቆይ መሰለህ፤ ጥንቱንም ይህን አሳብ ባሰብሁ ጊዜ ባመት ሦስት ጊዜ ለእንቁጣጣሽ፣ ለልደትና፣ ለፋሲካ፣ ወደ ሀገሬ እየመጣሁ አባትና እናቴን ለማየት ቁርጥ አድርጌ ነውና አንተ እነዚህን ሦስቱን ጊዜዎች እየጠበቅህ ወደ እቴሳ ብትመጣ ልታየኝ ትችላለህ አለችው።

ብርሃኔም ይህን በመስማቱ የበለጠ ደስታ አደረገና ባመት ሦስት ጊዜ ካየሁሽ ሌላ ምን እፈልጋለሁ፤ ነገር ግን ለሁሉም ነገር የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁንልን፤ እንግዲህ እኔም ወደ ሀገሪኤ መውጣቴ ነውና በደህና ያገናኘን ብሎ ተሰነባብተው ተለያዩ።

## ምዕራፍ ፬

# ጽዮን ሞገሳ ለትምሕርት ወደ ደብረ ሊባኖስ ስለ መውረድዋ

ጽዮን ሞገሳ ከብርሃኔ ጋራ ከተሰነባበተች በኋላ በአባትዋና በእናትዋ ፊት ቆማ እንደዚኢህ እያለች ተናገር ጀመረች።

እስካሁን ድረስ የተማርሁት ትምሕርት ሥጋዬን የምረዳበት፤ ባልም ሳገባ ባሌን ደስ የማሰኝበት ሥጋዊ ትምሕርት ነው እንጂ ነፍሴ የምትድንበትን፤ እግዚአብሔርን አገልኄ ደስ የማሰኝበትን፤ መንግሥተ ሰማያትን የምወርስበትን፤ መንፈሳዊ ትምሕርት አልተማርሁምና ወደ ደብረ ሊባኖስ ወርጄ በሴቶች ገዳም ተቀምጬ መንፈሳዊ ትምሕርት እንድማር ትፈቅዱልኝ ዘንድ እለምናለሁ አለቻቸው።

አባትና እናትዋም ይህን የመሰለ ትልቅ ነገር ስትናገር በሰሙ ጊዜ ደነገጡ። ይልቁንም ከእርስዋ በቀር ሌላ ልጅ አልነበራቸውምና በሴቶች ገዳም ገብታ መንፈሳዊ ትምሕርት ከተማረች በኋላ ምናልባት መንኩሳ ወዲያው የቀረች እንደ ሆነ ያለ ልጅና ያለ ዘር መቅረት ይሆንባል ብለው እጅግ አዘኑ።

ጽዮን ሞገሳም አሁን በተናገረችው ነገር አባትና እናትዋ መደንገጣቸውን አይታ በዚህ ዓለም የሚደረገው ማናቸውም ነገር ሁሉ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ሊደረግ አይቻልምና በደብረ ሊባኖስ ቢሆን በዚህም ቢሆን ለእግዚአብሔር ሁሉም አንድ ነው። ሕይወቴ ፈቃዱ ካልሆነ በፊታችሁም ቢሆን መሞቴ አይቀርም፤ ፈቃዱም ከሆነ ከዱር አራዊትም ጋር ብቀመጥ አልሞትም። ስለዚህ በልባችሁ ጥርጣሬ ሳታስገቡ ብትፈቅዱልኝ ይሻላል እያለች የሚያጽናና ቃል ትነግራቸው ጀመረች።

አባትና እናትዋም ቁርጥ አሳብ ማድረጓን በንግግርዋ ከተረዱት በኋላ እርስዋ ትንሽቱ ልጃችን እምነቷን በእግዚአብሔር ላይ አድርጋ ይህን የመሰለ ብርቱ ቃል ስትናገር እኛ ሽማግሌዎቹ ይልቅ እምነታችንን ለማጉደልና እግዚአብሔርን ለመጠራጠር እንደምን ይገባናል። ስለዚህም በፍጹም ልብዋ ያመነችው እግዚአብሔር ከክፉ ነገር ሁሉ ሳይጠብቃት አይቀርምና ያሰበችውን ታድርግ ብለው ወደ ደብረ ሊባኖስ ወርዳ በሴቶች ገዳም እንድትማር ፈቀዱላት።

ጽዮን ሞገሳም የእግዚአብሔርና የአባት የእናትዋ ፈቃድ ስለ ሆነላት እጅግ ደስ ካላት በኋላ በሰኔ ፩ ተነስታ ከአባትና ከእናትዋ፤ ከዘመዶችዋም ሁሉ ጋራ ተሰነባብታ ወደ ደብረ ሊባኖስ ወረደች። በደረሰችም ጊዜ ወደ ገዳሙ እመ ምንኔት ወደ እማሆይ

ወለተ ማርያም ሒኢዳ የመጣችበትን ጉዳይ ሁሉ ነገረቻቸው። እርሳቸውም በደስታ ተቀብለው ከአስተማሪዋ ከእማሆይ ወልተ ጻድቅ ጋር አጋጠሙዋት።

በዚያም ሁለት ወር ያህል እንደ ቆየች እንደ አጋጣሚ የተስቦ በሽታ በገዳሙ ገብቶ መበለቶቹ ሁሉ ታመሙ። ባንድ ሳምንትም ፲፫ ያህል መበለቶች ሞቱ። የሞቱትም እኩሉ ከእቲሳ እኩሉም ከተጉለት የወረዱ ነበሩና የበሽታው ወሬ በሁሉም ስፍራ ይወራ ጀመር።

ብርሃኔም በደብረ ሊባኖስ በሴቶች ገዳም የተስቦ በሽታ ገብቶ ብዙ መበለቶች መሞታቸውን በሰማ ጊዜ እጅግ አዘነ።

ይልቁን እርሱ ራሱ ወደ ደብረ ሊባኖስ ወርዶ የጽዮን ሞገሳን ደህንነት እንዳይጠይቅ በሴቶች ገዳም ወንድ እንዳይገባ ክልክል ነው። ለቅዳሴ እንኳ ወደ ሴቶች ገዳም የሚሔዱ ቀሳውስት በጣም የሸመገሉ መነኮሳት ከወንዶች ገዳም የተመረጡ ነው። ስለዚህ እርግጠኛውን ወሬ ለማግኘት እጅግ ተቸገረ። ብትሞትማ ወሬ አይደበቅምና ይሰማው ነበር። ነገር ግን ትልቅ ኃዘን የሆነበት ምናልባት ታማ እንደ ሆነ አስታማሚ በማጣት ትሞታለች ብሎ ነበረ።

ዳሩ ግን ለማናቸውም ቢሆን ወደ ደብረ ሊባኖስ ወርጄ ብጠያይቅ ይሻለኛል በማለት ለአባትና ለእናቱ የጽዮን ሞገሳን ነገር ሳያነሳ ለነሐሴ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ደርሼ ጠበል ጠጥቼ እመለሳለሁ ብሎ ተሰናብቶ በፍልሰታ ውስጥ ደብረ ሊባኖስ ደረሰ።

ለነሐሴ ኪዳነ ምሕረት ከወንዶች ገዳም ሽማግሎች መነኮሳት ለቅዳሴ ወደ ሴቶች ገዳም ሲመለሱ በመንገድ ዳር ቆሞ ጠብቆ አባቶቼ ሆይ፤ ከሴቶች ገዳም የምትመጡ መስላችሁኛልና ወሬ እንድጠይቃችሁ ፍቀዱልኝ አላቸው።

የሰማነውና ያወቅነው ከሆነ እንነግርሃለንና ጠይቀን አሉት።

በሴቶች ገዳም የተስቦ በሽታ ገብቷል የሚባለው እርግጥ ነው? አላቸው።

ከመካከላቸውም አባ ወልደ ማርያም የሚባሉት ራሳቸውን ይዘው ልጄ ሆይ፤ የበሽታውን ነገር ለምን ታነሳዋለህ እንዲያው አያድርስ፤ አያድርስ ማለት ይሻላል።

ባንዳንድ ቀን ሁለት ሁለት መበለቶች ሳይሞቱ አይውሉም። የታመሙትንማ ማን ይቆጥራቸዋል። ዛሬም ኪዳነ ምሕረት ስለ ሆነች ለቅዳሴ ሔደን ነበርና ሥጋ ወደሙ አቀብለናቸው ኑዛዜም አናዘናቸው ተመለስን አሉት።

ብርሃኔም የጽዮን ሞገሳ ስም ጠርቶ እንዳይጠይቅ ስለ ፈራ በዚህ ገዳም የሚኖሩ መበለቶች ብቻ ናቸውን ወይንስ ልጃገረዶችም እየገቡ ይኖራሉ? ብሎ ጠየቃቸው።

አካለ መጠን ያላደረሱ ልጆች ለትምህርት ቢገቡ አይከለከሉም። ብዙ ልጃገረዶች ገብተው የሚማሩ አሉ። አካለ መጠን ካደረሱ በኋላ ግን እየወጡ ይሄዳሉ። ወይም እንቻላለን ያሉ እየመነኮሱ ይቀራሉ ብለው መለሱለት።

አሁንሳ በዚህ በተስቦ በሻ የሚታመሙና የሚሞቱ መበለቶች ብቻ ናቸው ወይስ ለምትሕርት የገቡ ልጃገረዶችም ይታመማሉ? ብሎ ጠየቃቸው።

እስካሁን እንደ እድል ሆኖላቸው አካለ መጠን ካላደረሱት ልጃገረዶች ወገን እገሊት ታማለች፤ እገሊት ሞታለች፤ ሲሉ አልሰማንም አሉት።

ብርሃኔም በመኮሳቱ አነገገር ጽዮን መታመሚን አለመሞቷን ስለ ተረዳው ደስ ካለው በኋላ አባቶቼ ሆይ፤ እስካሁን በመንገድ ላይ ስለ አቆምኋችሁና ስለ አደከምኋችሁ ይቅር በሉኝ ብሎ ወደ ወንዶች ገዳም ተመለሰ።

የአቡነ ተክለ ሃይማኖት በዓል ካለፈ በኋላ ለእንቁጣጣሽ በዓል ወደ ሀገሩ ወደ ተጉለት ተመለሰ።

ጽዮን ሞገሳም ወደ ደብረ ሊባኖስ ሳትወርድ እቲሳ ላይ ከብርሃኔ ጋራ ስትነጋገር ባመት ሦስት ጊዜ እንተያያለን ብላ ስለ ነገረችው እጅግ ደስ ብሎት ነበር። ነገር ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ ካልተጨመረበት ሰው አሳቡን በትክክል ለመጨረስ አይችልምና እርስዋ ወደ እቲሳ በምትመጣበት ጊዜ አንዳንድ መሰናክል እያገኘውና እየቀረ ዓይን ላይን ሳይተያዩ ሁለት ዓመት አለፈ። በዚህም ላይ ደግሞ የጋብቻውን ነገር ሁለቱ ብቻ በቃል ተነጋግረው ነበር እንጂ በዳኛ ፊት ወይም በጽሕፈት አልጨረሱም ነበርና ብርሃኔ በዚህ ሁሉ ሕሊናው ስለ ተንቀሳቀሰበት ደብዳቤ ጽፎ ሊልክላት ቁርጥ አሳብ አደረገ። ነገር ግን በተጉለት ብርሃን አውራጃ ያንጊዜ ወረቀት ችግር ነበርና ብራና ለመፈለግ ወደ ደብረ ብርሃን ወጥቶ ባንድ ጨው አንድ ብራና ገዝቶ ተመለሰ። በማግሥቱም ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ጻፈላት።

ይድረስ እጅግ ከተወደደችና ከታመነች ወይዘሮ ጽዮን ሞገሳ፣

እጅጉን እንዴት ነሽ። እኔ አንቺን ከመናፈቅና ፊትሽን ለማየት ከመመኘት በቀር ደህና ነኝ። እግዚአብሔር ይመስገን።

ወዳጄ ሆይ፤ የመልክሽን ውበት፤ የምግባርሽን ትክክልነት፤ በትምሕርትም ያገኘሽውን እውቀት ተመልክቼ ካንቺ ጋራ በቃል ኪዳን ለመጋባት ካሰብሁና ከተነጋገርሁ ሁለት ዓመት ሆነ። ይህ ሁለት ዓመት እንደ ሃያ አመት ሆኖብኛል።

ወደ እግዚአብሔር ጧትና ማታ የምጸልየው ጸሎት አንችን በቃል ኪዳን አግብቼ ልጅ ሳልወልድ እንዳልሞት ነው።

ባለፈውም ዓመት በደብረ ሊባኖስ በሴቶች ገዳም የተስቦ በሽታ ገብቶ ነበር የሚል ወሬ ስምቼ በድንጋጤ ወደ ደብረ ሊባኖስ መጥቼ ዓይሽን ለማየት የማይቻለኝ ቢሆን በወንዶች ገዳም ሆኜ ተጠያይቄ ደህንነትሽን ስምቼ ተመለስሁ።

አሁንም እግዚአብሔር በቸርነቱ ሁለታችንንም ጠብቆ ከዚህ ካደረሰን ያሰብነው አሳብ እንዲፈጸም በቃል ኪዳን እንድንጋባ ፈቃድሽ መሆኑን በቶሎ በጽሕፈት አስታውቂኝ።

ከዚህም በኋላ አሽከሩን ጠርቶ ወደ ደብረ ሊባኖስ ወርደህ ለቅዳሴ ወደ ሴቶች ገዳም የሚሔዱትን መነኵሴዎች ተጠያይቀህ ይህን ደብዳቤ ጽዮን ሞገሳ ለምትባለው በሴቶች ገዳም ለምትማረው ልጃገረድ ስጡልኝ ብለህ አስረክበህ ተመለስ አለው።

አሽከሩም ደብዳቤውና ብራናውን ተቀብሎ ወደ ደብረ ሊባኖስ ወረደ።

ጌታውም እንደ ነገረው ለቅዳሴ የሚሔዱትን መነኮሳት አግኝቶ ለጽዮን ሞገሳ ስጡልኝ ብሎ ደብዳቤውን አስረከባቸው።

ጽዮን ሞገሳም ደብዳቤውን ተቀብላ ባነበበችው ጊዜ ስለ ሁለት ነገር እግዚአብሔርን አመሰገነች።

መጀመሪያ፤ ፲፫ ዓመት ሳይሆነኝና አካለ መጠን ሳላደርስ ባል አላገባም ብላ ቁርጥ አሳብ ማድረጓን እንደ ብፅዓት ለእግዚአብሔር አስታውቃ ነበርና ይህ አሳብዋ ስለ ተፈጸመላት ነው።

ሁለተኛ፤ በትምሕርቱና በእውቀቱ እጅግ የተመሰገነ፤ ምግባሩ፤ የቀና፤ ሃይማኖቱ የጸና ብርሃኔን የመሰለ ባል በማግኘቷ ስለ መታደልዋ ነው።

ደግሞ በደብረ ሊባኖስ ብራና ፈልጋ ለማግኘት አለመቻሏን አስቦ ብራና ጨምሮ መላኩ ምላሹን እንድትጽፍለት መሆኑን ስለ ተረዳች አመሰገነችው።

ከዚህም በኋላ የደብዳቤውን ምላሽ ልትጽፍ ጀመረች።

ይድረስ እጅግ ለተወደደና ለታመነ ጌታ አቶ ብርሃኔ፤ በእውነትም የልቤ ብርሃን።

እጅጉን እንዴት ነህ፤ እኔ በእግዚአብሔር ቸርነት ደህና ነኝ።

የዛሬ ሁለት ዓመት ገና በእቲሳ ሳለሁ የጋብቻ ነገር አንስተህ ብትጠይቀኝ አካለ መጠን ሳላደርስ ባል አላገባም። እስከዚያም ድረስ መንፈሳዊ ትምህርት ለመማርና የኑሮዬን አካሔድ ለማሻሻል ሰውነቴንም ከክፉ ሥራ ለመጠበቅ ወደ ደብረ ሊባኖስ ወርጄ በሴቶች ገዳም እቆያለሁ ብዬ ነግሬህ ነበር።

እንደዚያው እንደ ነገርሁህ ወደ ገዳሙ በገባሁ ጊዜ ከሁለት ወር በኋላ የተስቦ በሽታ ገብቶ ብዙ መበለቶች ነፍሳቸውን ለእግዚአብሔር አደራ እየሰጡ አረፉ። የእኔም ተራ አንድ ቀን ይደርስ ይሆናል እያልሁ ስጨነቅ ለጊዜው ከዚህ ተስቦ በሽታ አመለጥሁ።

እንዲያውም ለታመሙት መበለቶች ምግብና ውኃ በመስጠት፤ በማቅናትና በማስተኛት የተቻለኝን ያህል በመርዳቴ ጌታችን ብታመም ጠየቃችሁኝ ብሎ የተናገረውን ቃል የፈጸምሁ መስሎኝ ለልቤ ትልቅ ተስፋ አግኝቻለሁ። ማቴ. ፳፭፥ ፴፮።

ወዳጄ ሆይ፤ እኔማ ብሞትም ፋንታዬን መውጣቴ ነበር። ነገር ግን አንተ እምነትህን ሁሉ በእኔዒ ላይ አድርገህ እውነተኛውን የቃል ኪዳን ጋብቻ የምንፈጽምበት ቀን ስትጠብቅ የሞቴን ወረቀት ብትሰማ ራስ የሚያዞር ትልቅ ሐዘን እንዲያገኝህ እርግጥ ነበርና ለጊዜው እኔን ከሞት አንተንም ከኃዘን ስለ ጠበቀን ሁለታችንም ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብ ይገባናል።

ደግግሞ ያን ጊዜ የበሽታውን ወሬ ሰምቼ ለመጠየቅ ወደ ደብረ ሊባኖስ መጥቼ ነበር ብለህ ሰል ሳፍህልኝ እጅግ አመሰግንሃለሁ። ነገር ግን ያን ጊዜ ዓይን ላይን ተያይተን በነበረ እንዴት ደስ ባለን ነበር። አሁንም የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ከዚህ ጊዜ ካደረሰን የጋብቻው ነገር እንዲፈጸም ፈቃዴ ነውና ክረምቱ ሲያልፍ ወደ እቲሳ በተመለስሁ ጊዜ በቶሎ መጥተህ ለአባትና ለእናቴ አስታውቀህ ነገሩን እንጨርሳለን።

ጤና ይስጥህ፤ ደህና ሁን።

በደብረ ሊባኖስ በሴቶች ገዳም ተጻፈ።

ደብዳቤዋን ጽፋ ከጨረሰች በኋላ የተላከው አሽከር በወንዶች ገዳም መኖሩን ብታስጠይቅ ውኃ ይሞላብኛል ብሎ ተመልሶ ሔደ ብለው ነገርዋትና እጅግ አዘነች። በፖስታም እንዳትልክለት በዚያ ዘመን በደብረ ሊባኖስ ይቅርና በአዲስ አበባም ቢሆን ፖስታ አልነበረም። ለቅዳሴ የሚመላለሱትም መነኮሳት ወደ ተጉለት የሚወጣ ሰው ፈላልጋችሁ ለአቶ ብርሃንኒኤ ላኩልኝ ብላ እንዳትነግራቸው በሴቶች ገዳም ውስጥ ሆና

ከወንድ ጋራ ትላላካለች ብለው ስሟን እንዳያጠፉዋትና ከገዳሙ እንዳያስወጥዋት ፈራች። ስለዚህ ብርሃኔ የላከላትን ደብዳቤና እርስዋም የጻፈችለትን ደብዳቤ እያነሳችና እያነበበች ታለቅስ ጀመር።

ብርሃኔም አሽከሩ የደብዳቤውን ምላሽ ሳያመጣለት በመቅረቱ እጅግ አዝኖ ነበር። ሁለተኛም መልሶ እንዳይልከው ባንድ ወገን የጤፍ ዘር ደርሶበት ነበርና ባንድ ወገንም ውኃ ሞልቶ ነበርና አልተመቸውም።

ነገር ግን ከልብ ያዘኑበት ነገር ሳይፈጸም አይቀርምና በብርሃንኔ ቤት አጠገብ የሚኖሩ እማሆይ ወለቴ ለነሐሴ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወደ ደረበ ሊባኖስ ወርጄ፤ ጠበል ጠጥቼ፤ ወዲያውም በሴቶች ገዳም ያሉትን አክስቴን እማሆይ አፀደ ማርያምን አይቼ እመለሳለሁ ብለው አሳባቸውን ለብርሃኔ ገለጡለት። ብርሃኔም ይህን ነገር በሰማ ጊዜ እጅግ ደስ አለው። ነገር ግን ነገሩን ለማረጋገጥ ሲል ዘንድሮ ክረምቱ ስለ በረታና የጫጫና የበሬሳ ወንዝ ሳይሞላ አይቀርምና እንደምን አድርገው ሊወርዱ ይችላሉ አላቸው።

እማሆይም ዘንድሮ ለነሐሴ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከደብረ ሊባኖስ እንዳልቀር ስለት አለብኝና ወንዙም ቢሞላ እስቲጎድል በዳሩ እየቆየሁ እወርዳለሁ እንጂ ምንም ቢሆን አልቀርም። ወይም አባቴ አቡነ ተክሌ ዝናሙን ብራ ያደርጉልኛል ብለው መለሱለት።

ብርሃኔም እማሆይ ወለተ ጨክነው ቢወርዱና የጽዮን ሞገሳን ወሬ ቢያመጡለት ደስታው ስለ ሆነ በውኃ ሙላትና በጭቃ አይውረዱ ብሎ አጠንክሮ ለመናገር አልወደደምና እግዚአብሔር አሳብዎን ይፈጽምልዎ። እኔም ከእርስዎ ጋር ወርጄ ጠበል ጠጥቼ ብመለስ እወድ ነበር፤ ነገር ግን የጤፍ አረም ስለ ደረሰ እኔ ትቼው የሔድሁ እንደ ሆነ ጤፉን አረም ይውጠዋል። ስለዚህ ዛሬ ቀርቼ በታህሣሥ እወርዳለሁ። መቼም የነሐሴው በዓለ ዕረፍታቸው ቢሆን የታህሣሡም ልደታቸው ነውና ሁሉም አንድ ነው እያለ እማሆይ እንዳይቀሩ ያበረታታቸው ጀመር።

እማሆይም በበኩላቸው ብርሃኔ ከእርሳቸው ጋር ቢወርድ ውኃም ቢሞላ ጊዜውም ቢመሽ ያለ ሥጋት እንዲሔዱ ያውቁ ነበርና ልጄ ሆይ፤ ልብ ካልቆረጠ ማናቸውም ነገር አይሆንም፤ ታህሣሥ ቢሆንስ የመከር ጊዜ አይደለምን፤ ልብህ ካልቆረጠ ያንጊዜም ቢሆን ገብስ አጭዳለሁ ስንዴ እወቃለሁ ማለትህ አይቀርም። ይልቅስ በርታና ዛሬውኑ እንውረድ እያሉ ያደፋፍሩት ጀመሩ።

ብርሃኔ የጽዮን ሞገሳ ወሬ ለመስማት እንጅ ጠበል ለመጠጣት አሳብ አልነበረውምና እማሆይ የማይቀሩበትን እርሱ የሚቀርበትን ማስረጃ ነገር እየፈለገ ይናገር ነበርና በታሕሣሥ ዝናምና ጭቃ የለም፤ በሁለት ቀን ደብረ ሊባኖስ ደርሼ በበዓሉ ቀን ጠበል ጠጥቼ ቤተ ክርስቲያን ስሜ ታቦት ዞሮ ሲገባ የተነሣሁ እንደ ሆነ በማግሥቱ ተጉለት እገባለሁ። የምወርደውም በከብት እግር ነውና ድካም ሳያገኘኝ ለሥራዬ በቶሎ እደርሳለሁ። እርስዎ ግን ዛሬም ቢሆን በታሕሣሥም ቢሆን ሥራ የለብዎትምና ቀደም ብለው ተነሥተው ሲደክምዎ እያረፉ ውኃ ሲሞላ እያሳለፉ ቢወርዱ ምንም አይቸገሩም አላቸው።

እማሆይም ብርሃኔን የልቡን አሳብ ሳያውቁ የቃሉን ንግግር ብቻ ሰምተው አሁንማ የተናገርኸው ሁሉ እርግጥ ነው። እንግዴህ ነገር ማለዳ መነሣቴ ነውና ደህና ሰንብት አሉት።

ብርሃኔም የጽዮን ሞገሳን ነገር እንዳያነሳባቸው ለጊዜው ይጠረጥሩኛል ብሎ ፈርቶ ነገሩን ለማደናገር እማሆይ ሲመለሱ ጠበልና መሬት እንዲያመጡልኝ አደራ አላቸው።

እማሆይም ልጄ ሆይ፤ መሬቱኑን አመጣልሃለሁ፤ ስለ ጠበሉ ግን በዚህ በዝናምና በጭቃ ስመጣ የወደቅሁ እንደ ሆነ የጠበል ቅሉ ተሰብሮ ጠበሉ መፍሰሱ አይቀርም እንጅ መሆኑን እሞክረዋለሁ አሉት።

ከዚህም በኋላ በማግሥቱ በማለዳ ተነሥተው ወደ ደብረ ሊባኖስ ጉዞ ጀመሩ። ብርሃኔም ወደ ስዮን ሞገሳ የሚልከውን ቃል አሰናድቶ አድሮ ነበርና መልክቱን ለመንገር ወደ እማሆይ ቤት ቢሔድ በማለዳ ተነሥተው ሔዱ በለው ነገሩትና እየሮጠ ተከተላቸው።

እማሆይም አንድ ሰው እየሮጠ ሲከተላቸው በሩቅ ባዩት ጊዜ ቆመው ቆዩት። ወዲያውም እንደ ደረሰ ብርሃኔ መሆኑን ስለ አወቁ ምነው ልጄ፤ በደህና ነውን፤ አሁን ይህን ሁሉ መንገድ እየሮጥህ ከመምጣት ጉዳይህን ትናንትና ማታ አትነግረኝም ነበርን አሉት።

ብርሃኔም የምነግርዎን ጉዳይ ትናንትና ሳላስበው ዛሬ ሌሊት ትዝ ስላለኝ በማለዳ ብመጣ ሔደዋል ብለው ነገሩኝ፤ ነገሩም ትንሽ ነው።

የዛሬ ሁለት ዓመት ወደ እናቴ ሀገር ወደ እቲሳ ወርጄ በእናቴ ዘመዶች ቤት አጠገብ አቶ ክብረት የተባለው ሰው ጽዮን ሞገሳ የምትባል ሴት ልጁን አምጥቶ አስተዋውቆኝ ነበር፤ አሁን ወሬዋን ብጠይቅ ደብረ ሊባኖስ ወርዳ በሴቶች ገዳም ገብታ ትማራለች ሲሉ ሰማሁ፤ አሁን እርስዎ ወደዚያው መውረድዎ ከሆነ እግረ መንገድዎን ደርሰው

ቢያገኙኡዋት ቃል ለቃል ተነጋግረው፤ ባይገኙዋት ወሬዋን ተጠያይቀው የደህንነቷን ነገር እንዲያመጡልኝ አደራ ብዬዎታለሁ አላቸው።

ምነው ልጄ፤ እግረ መንዴን ለማደርገው ነገር ምን አደራ ያሰኝሃል፤ ምንም ቢሆን ሳላያትና ሳልጠይቃት አልቀርም፤ በደህና ሰንብት የቤቴንም ነገር አደራ ብየሃለሁ ብለው ተሰነባብተው ተመለሱ።

ከዚህም በኋላ ዝናሙም እየዘነመባቸው፤ ውኃም እየሞላባቸው ከተጉለት በተነሡ በሰባተኛው ቀን በብዙ ችግር ደብረ ሊባኖስ ደረሱ። የደረሱትም በዋዜውማው ነበርና ጠበል ጠጥተው በቤተ ክርስቲያን አደሩ። በማግሥቱም ዋናው በዓሉ ነበርና ወደ ሴቶች ገዳም ለመሔድ አልተመቻቸውም። በሦስተኛውም ቀን ስለ ድካማቸው አርፈው ዋሉ።

ባራተኛው ቀን ግን በማለዳ ተነሥተው ወደ ሴቶች ገዳም ተሻግረው ከአክስታቸው ከእማሆይ አፀደ ማርያም ጋራ ተገናኝተው ሲጫወቱ ብርሃኔ የላካቸው ጉዳይ ትዝ አላቸውና በዚህ ገዳም ለትምሕርት የመጣች ጽዮን ሞገሳ የምትባል ልጅ አለች ሲሉ ሰምቼ ነበር፤ ያውቋት ይሆንን ብለው ጠየቋቸው።

ምነው እኅቴ በዚህ ገዳም ጽዮን ሞገሳን የማያውቅ ማነው። ለሁላችንስ ዋና አገልጋያችን እርስዋ አይደለችምን። ባለፈው ዓመት እንኳ በገዳማችን ተስቦ በሽታ ገብቶ ሁላችን በታመምን ጊዜ እርስዋን ብቻ እግዚአብሔር ስለ ጠበቃት ምግብና ውኃ እየሰጠችን አስታመመችን። ጎጆዋም ከዚህ ከእኔ ጎጆ አልፎ ሦስተኛ ነው። ቢፈልጉም ልጥራልዎ አሏቸው።

እማሆይም እንደ ዘመኑ ሥልጡን ነበሩና ጉዳይ ያለበት ሰው ራሱ ሔዶ ይናገራል እንጂ ጉዳይ አለኝ ብሎ ጠርቶ አይናገርምን፤ ስለዚህ እኔው ራሴ ሔጄ እጠይቃታለሁ ብለው ተነሡ።

ጽዮን ሞገሳም በደጅዋ አጠገብ ባለው ዛፍ ሥር ቆማ የሠለስት ጸሎት ትጸልይ ነበርና እንግዳ መንኩሲት ወደ እርስዋ ሲመጡ ባየች ጊዜ ጸሎትዋን በቶሎ ጨርሳ ተቀበለቻቸው። ለጊዜው ከሀገርዋ ከእቲሳ የመጡ መስለዋት ነበር። በኋላ ግን ከተጉለት መምጣታቸው ቢነግርዋት እርስዋም የብርሃኔን ወሬ ለመስማት ስትመኝ ነበርና በቶሎ ወደ ጎጆዋ ይዛቸው ገባች።

ወዲያውም እርስዋን የሚፈልጉበትን ምክንያት ጠየቀቻቸው።

እማሆይም ብርሃኔ የነገራቸውን ሁሉ ከሥር እስከ ጫፉ አጫውተው ወዲያውም ጎረቤት መሆናቸውን በነገርዋት ጊዜ በቶሎ ተነሥታ አስቀድሞ ወደ ብርሃኔ ለመላክ

የጻፈችውን ደብዳቤ አምጥታ አሳየቻቸው። በሚመለሱበትም ጊዜ ደብዳቤውን ወስደው እንዲሰጡላት ለመነቻቸው።

ከዚህም በኋላ እማሆይ እስከ ጳጉሜ ድረስ ጠበል ሲጠጡ ሰንብተው ለቅዱስ ዮሐንስ (ለእንቁጣጣሽ) ሀገራቸው ለመግባት በጳጉሜ ፩ ቀን ከደብረ ሊባኖስ ተነሱ። ክረምቱም ማለፉ ነበርና ዝናሙ እያነሠ፤ ወንዙ እየጎደለ፤ ጭቃው እየደረቀ ስለ ሔደ ሲወርድ በሰባት ቀን የዘለቁትን መንገድ አሁን ባራት ቀን ዘልቀው ተጉለት ገቡ።

ብርሃኔም እማሆይ ወለቴ የሚገቡበትን ቀን ሲጠባበቅ ነበርና መግባታቸውን በሰማ ጊዜ በቶሎ ሔዶ አያቸው። እማሆይም ከጽዮን ሞገሳ ያመጡለትን ደብዳቤ አስረከበው ወዲያው ደህንነቷን ሁሉ በቃላቸው ነገሩትና ከደስታው ብዛት የተነሳ እራቱን ሳይበላ አደረ። ለእማሆይም ይህን የደስታ ወሬ ስለ አመጡለት አሥር እንጀራና አንድ ገንቦ ጠላ፤ አንድ ሲካካ ዶሮ ላከላቸው።

አባትና እናቱም፣ የብርሃኔ ፊቱ በደስታ መብራቱን አይተው እስከ ዛሬ ፊትህን አይጠዳውም ነበር፤ ዛሬ ፊትህ እንደ ፀሐይ ማብራቱ ምን ወሬ ሰምተህ ነው? ብለው ጠየቁት።

ብርሃኔኢ ግን ነገሩ ወደ ፍጻሜ ሳይደርስ አባትና እናቱ እንዲሰሙበት አልፈቀደም ነበርና የደስታውን ምክንያት ሰውሮ እማሆይ ወለቴ ያባቴን የአቡነ ተክሌን ጠበልና መሬት ስለ አመጡልኝ ደስ ብሎኛል፤ እናንተም ከነጋ እህል አልቀመሳችሁ እንደ ሆነ ላምጣላችሁና ከጠበሉ ጠጡ። ከመሬቱም ተቀቡ አላቸው።

አሁን ማለዳ ነው፤ ምን ጊዜ እህል ቀመስን። ገና አሁን ከቤተ ክርስቲያን መመለሳችንን ታይ የለምን። ይልቅስ በቶሎ አምጣልን ብለው ከጠበሉ ጠጥተው ከመሬቱም ተቀቡ።

## ምዕራፍ ፳

# ጽዮን ሞገሳ ትምሕርቷን ጨርሳ ወደ ሀገርዋ ስለ መመለስዋ

ጽዮን ሞገሳ ሁለት ዓመት ሙሉ በደብረ ሊባኖስ በሴቶች ገዳም መንፈሳዊ ትምሕርቷን እየተማረች ከቆየች በኋላ ወደ ሀገርዋ ለመመለስ ማሰብዋን ለመበለታቱ አስታወቀቻቸው። መበለቶችም ይህን በሰሙ ጊዜ የምትረዳው እርዳታና ደግነቷ ሁሉ

ትዝ እያላቸው ያዝኑ ጀመር። እንዲያውም በዚሁ ኖረሽ የኋላ ኋላ መንኩሰሽ የምትቀሪ መስሎን ነበር እያሉ ያለቅሱ ጀመር።

ጽዮን ሞገሳ ግን ከምንኩስና ኑሮ የሚበልጠውንና የሚሻለውን በቃል ኪዳን ባል ማግባትን መርጣ ነበርና መበለቶቹ የሚናገሩትን ወደ ልብዋ አላገባቸውም ነበር።

ከዚህም በኋላ ወደ እመ ምኔትዋ ሔዳ ተሰናበተች። እመ ምኔትዋም ስለ እውቀትዋና ስለ ምግባርዋ መልካምነት የምስክር ወረቀት ሰጡዋትና በማግሥቱ ማለዳ ለመንገድዋ ስትነሣ መበለቶቹ ሁሉ እስከ ወንዶች ገዳም ወሰን ሸኝተዋት ተመለሱ።

አባትዋ አቶ ክብረትም ልጁ የምትመለስበትን ጊዜ ልካበት ነበርና አንድ በቅሎና ሁለት አሽከሮች ልኮላት ነበር።

መላከተኞቹም በወንዶች ገዳም በመስቀል ማሳያው አጠገብ በቅሎዋን ሣር እያጋጡ ሲጠብቁ ነበርና በመጣችላቸው ጊዜ በመዞሪያ መንገድ ዙረው ጉረኔ ወጥተው አደሩ። በሦስተኛውም ቀን እቲሳ ደረሱ።

አባትና እናትዋም ቤተ ዘመዳቸውን ሁሉ ጠርተው ይጠብቁ ነበርና ጽዮን ሞገሳ በበቅሎ ተቀምጣ ብቅ ስትል ባዩ ጊዜ በውስጥም በውጭም እልልታ ብቻ ሆነ። አባትዋም እስከ በሩ እየሮጠ ሔዶ ከበቅሎው ላይ ታቅፎ አወረዳት።

ወዲያውም አንድ ማለፊያ የፍየል ሙክት ታረደና አንድ ጋን ጠላ ተዘነበለና እየበሉ፤ እየጠጡ በደስታ አመሹ።

በማግሥቱም በማለዳ ተነስታ ወደ እቲሳ ገዳም ወርዳ ያደገችበትን ቤተ ክርስቲያን ተሳልማ በሕፃንነትዋ ሲያስተምርዋት የነበሩትን ሽማግሌ መምህርዋን ጠይቃ ወደ ቤትዋ ተመለሰች።

ቀኑን ሙሉ ያገሩ ሰዎችና ባልንጀሮችዋ ሁሉ እየመጡ ሲያጫውቷት ይውሉ ነበር።

ብርሃኔም በተጉለት ወደ ቡሎ ወርቄ ገበያ ወጥቶ ሳለ ከእቲሳ የመጡ ገባያተኞች አግኝቶ አቶ ክብረት ደህና መሆኑን ታውቁ የለምን ብሎ ቢጠይቃቸው አሁን በቅርብ ቀን አይተነዋል ደህና ነው። ባለፈውም ሳምንት ልጁ ጽዮን ሞገሳ የምትባለው በደብረ ሊባኖስ ስትኖር ስለ ተመለሰች ያገሩ ሰው ሁሉ እየመጣ እንኳን ደስ አለህ ይለው ነበር ብለው ነገሩት። ወደ ቤቱም ከተመለሰ በኋላ የማስታወሻውን መጽሐፍ አውጥቶ ቢመለከት በገዳም የምቀመጠው ሁለት ዓመት ብቻ ነው ብላ አስቀድሞ በቃልዋ እንደ

ነገረችው ዘመኑ ልክ ሆኖ ስለ አገኘው በንግግርዋ የምትጸና ቃልዋንም የምታከብር መሆኗን ተረዳውና እጅግ ደስ አለው።

ነገር ግን የጋብቻውን ነገር ከጽዮን ሞገሳ በቀር አባትና እናትዋ ወይም ሌላ ዘመድ ባዕድ አያውቁም ነበርና ነገሩን ለአባትና ለእናትዋ ማስታወቅ የሚገባ ስለ ሆነበት ከተጉለት ወደ እቲሳ ወረደ።

የወረደበትም ወር መስከረም ነበርና እንደ አጋጣሚኢ ለመስቀል በዓል አንድ ቀን ሲቀረው ደረሰ። በማግሥቱም ደመራ ተደምሮ ከህናቱም፣ ባላገሩ፣ ሴቱ፣ ሕፃናቱም ተሰብስበው ካህናቱ በመስቀሉ አብርሃ ኢዮሐ፤ ኢዮሐ፤ ሲሉ ወንድ ወንዱም ኢዮሐ አበባዬ፤ አበባሽ ለአባበ፤ እልል ብዬ ልግባ፤ ሲሉ ልጅ አገረዶችም በራሳቸው ላይ የመስቀል አበባ እያሠሩ በደመራው ቀኝና ግራ ቆመው ነበርና ብርሃኔ ወዲያና ወዲህ እየተዘዋወረ የበዓሉን ማማር ሲመለከት በድንገት ጽዮን ሞገሳን አይቶ በቁመትዋ ማደግ፤ በመልኳ ውበት እጅግ ደስ አለው። እርስዋ ግን በዚህ ወር ብርሃኔ ወደ እቲሳ ይመጣል ብላ ምንም አልጠረጠረችም ነበር።

የደመራውም በዓል ተጨርሶ ወንዶችም ሴቶችም በየቤታቸው ሲመለሱ ብርሃኔ በመንገዱ ዳር ቆሞ ጽዮን ሞገሳ ስታልፍ ለማየት ሊጠብቅ ነበርና ባኳያው ስትደርስ በፍጥነት ቀርቦ ሰላምታ ሰጣት። እርስዋም ሁለት ዓመት ሙሉ ምንም መልኩን ባይንዋ ሳታየው ብትቆይ በልብዋ ውስጥ እንደ ሥዕል ተሥሎ ይኖር ነበርና ብርሃኔ መሆኑን በቶሎ አወቀችው።

ከዚህም በኋላ ባንድነት ወደ አባትዋ ቤት ሔደድው በደስታ ሲጫወቱ አመሹ። አቶ ክብረት ሁለት ዓመት ሙሉ ዓይንህን አላየነውም ነበር። ለካ ቀድሞ እየመጣህ የምትጠይቀን ለጽዮን ሞገሳ ስትል ኖሯልን እያለ ነገሩን ሳያዞር በገርነት ይናገር ጀመር። በጣም በመሸ ጊዜ ግን ለመኝታው ወደ ዘመዶቹ ቤት ሔደ።

በማግሥቱም የመንደሩ ሰው ሁሉ ወንዱም ሴቱም የደመራ አመድ ለመርገጥ የሸክት ሐረግ እየያዙ ይሔዳሉና ብርሃኔ ለዚሁ ብሎ በመንገድ ዳር ቆሞ አሸክት ሲነቃቀል ጽዮን ሞገሳ እንደ አጋጣሚ ብቻዋን ሆና መጣች።

ከዚያም ጀምሮ እስከ ደመራው ስፍራ ብቻቸውን ስለ ሆኑ የጋብቻ ምስጢራቸውን ገልጠው ለመነጋገር ተመቻቸውና እንግዲህ ወዲህ አባትና እናቴ ይስሙትና ነገር ቢጨረስ መልካም ነው ብላ እርሱ የፈራውን እርስዋ ደፍራ ነገረችው።

ከዚህም በኋላ ባንድነት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሔደው ቅዳሴ ሰምተው ሲመለሱ እንደ ገና ወደ አባትዋ ቤት ወስዳ ምሳውን ጋበዘችው።

በዚህም ቀን ወደ ማታ ወደ እቲሳ ገዳም መምሕር ወደ አባ ተስፋ ሥላሔ ሔዶ አባቴ ሆይ፤ ያቶ ክብረት ልጅ ጽዮን ሞገሳን በቃል ኪዳን ለማግባት አስቤ ከእርስዋ ጋር መነጋገርና መላላክ ከጀመርሁ ሁለት አመት ሆነ። አሁንም ከእርስዋ ጋራ ተነጋግሬ ጨርሻለሁና ለአባትና ለእናትዋ ነግረው እንዲያስፈቅዱልኝ እለምንዎታለሁ። ይህንም ማለቴ ለልማዱ ብዬ ነው እንጂ ባይፈቅዱ እንኳ በእኔና በእርስዋ መካከል ነገሩ የተቆረጠ ሆኗልና ለማሰናከልና ለማስቀረት የማይችሉ መሆናቸውን ገልጠው ይንገርዋቸው ብሎ ጉልበታቸውን እየሳመ ለመናቸው።

መምሕር ተስፋ ሥላሴም ጽዮን ሞገሳ በደብረ ሊባኖስ መንፈሳዊ ትምሕርት እየተማረች ሁለት ዓመት መኖርዋን ያውቁ ነበርና ልጄ ሆይ፤ እጅግ መልካም አሳብ አስበሃልና እግዚአብሔር ይፈጽምልህ። ነገር ግን ዛሬ ሔጄ እንዳልጠይቅልህ በማኅሌት ውዬ ደክሞኛልና ነገ በጧት ሔጄ እጠይቅልሃለሁ። እግዚአብሔር በነገሩ ከተጨመረበት ከዚህ የሚሻልና የሚበልጥ ነገር የለም። ከደብረ ሊባኖስ ወደ እቲኢሳ የሚመጡ መበለቶች ሁሉ የእውቀቷንና የምግባርዋን መልካምነት እየነገሩኝ እርስዋን የሚያገባ እጅግ የታደለ ሰው ነው እያልሁ ስናገር ነበር። አሁንም ከዚሁ አምሽተህ ራትህን ከእኔ ጋራ ተጋብዘህ ትሔዳለህና ቆይ ብለው ወደ እንግዳ ማረፊያ ቤት እንዲወስዱት አዘዙ።

ከራትም በኋላ የዚሁኑ ነገር እየመላለሱ ሲነጋገሩ አምሽተው ወደ ዘመዶቹ ቤት ተመልሶ ሔደ።

በማግሥቱም አባ ተስፋ ሥላሴ በማለዳ ወደ ቤተ ክርስቲያን ደርሰው ዳዊትና ወንጌለ ዮሐንስ ከደገሙ በኋላ ወደ አቶ ክብረት ቤት ሔዱ። ከዚህም ቀድሞ አቶ ክብረት ለቡራኬም ቢሆን ለሌላ ጉዳይም ቢሆን ወደ መምሕር ተስፋ ሥላሴ ይሔድ ነበር እንጂ መምሕር ወደ እርሱ ቤት መጥተው አያውቁም ነበርና መምህር መጥተዋል ብለው ቢነግሩት እጅግ ደነገጠ። መምህርም መደንገጡን አይተው አይዞህ ልጄ ደስ የሚያሰኝ ወሬ ይዤልህ መጥቻለሁ እያሉ ደስ በሚያሰኝ ንግግር እያነጋገሩት ወደ ቤት ገቡ።

በድንክ አልጋ ላይም ከተቀመጡ በኋላ ብርሃኔ የነገራቸውን የጋብቻውን ነገር ነገሩት። አቶ ክብረትም አስቀድሞ ብርሃኔ መልኩ የተዋበ፤ ምግባሩ የቀና መሆኑን እያየ ምንም ደፍሮ ልጄን አግባ ባይለው በልቡ ለአማችነት ሲመኘው ይኖር ነበርና ይህን ነገር ከመምሕር ተስፋ ሥላሴ ቃል በሰማ ጊዜ አባቴ ሆይ፤ ይህ ነገር ከእግዚአብሔር የሆነ ይመስለኛልና ይሁን ከማለት በቀር ሌላ ነገር ለመናገር አልችልም አላቸው።

መምሕርም ይህን የመሰለውን የደስታ ቃል ስለሰሙ የደስታውን ነገር ለብርሃኔ ለመንገር እየቸኮሉ ሔዱ። ብርሃኔም ለወሬ ቸኩሎ በበሩ ትይዩ በሩቅ ሆኖ መምጣታቸውን ሲጠብቅ ነበርና ገና ከበሩ ብቅ ሲሉ ባይያቸው ጊዜ እየሮጠ ሔዶ አባቴ ሆይ፤ እንደምን አድርገውልኝ ተመልሰው ይሆን አላቸው።

ልጄ ሆይ፤ እንደ አንተ የታደለ ሰው በዕድሜዬ ሙሉ አላገኘሁ፤ ጥንቱንም ስትጀምረው የእግዚአብሔር ፈቃዱ ኖርዋልና ነገሩ ሁሉ በቶሎ ቀናኝ እንግዲህ የሠርጉን ቀን ብቻ ተነጋግረህ መሔድ ነው እንጂ ሌላ ነገር የለም ብለው የምሥራቹን ነገሩት።

ብርሃኔም እስከ ቤታቸው ተከትሎ ሔዶ ጉልበታቸውን ስሞ ተሰናበተ።

በማግሥቱም ጽዮን ሞገሳን ፈልጎ የጋብቻቸውን ነገር አባትዋ በደስታ መፍቀዱን መምሕር ተስፋ ሥላሴ እንደ ነገሩት አድርጎ ነገራትና ሁለቱም ለእግዚአብሔር የደስታ ምሥጋና አቀረቡ።

አቶ ክብረትም የብርሃኔን ዘመዶች ጠርቶ ከእንግዲህ ወዲህ ሥጋችንና ደማችን ሊቀላቀል በመታሰቡ ደስ ብሎኛልና ደስ ይበላችሁ እያለ ደስታውን ሁሉ ገለጠላቸው። ወዲያውም የሠርጉ ቀን ከፋሲካ በኋላ በሚያዝያ ፳ ቀን እንዲሆን ተነጋግረው ተስማሙና ብርሃኔ በጥቅምት ፪ ቀን ከእቴሳ ተነስቶ ተጉለት ወጣ። ስለ ደስታውም ብዛት የመንገዱ ድካም አልተሰማውም ነበር።

## ምዕራፍ ፮

# ስለ ብርሃኔና ጽዮን ሞገሳ የቃል ኪዳን ጋብቻ

ብርሃኔ የጋብቻውን ነገር ለመጨረስ ወደ እቴሳ ወርዶ ነገሩን ጨርሶ ከተመለሰ በኋላ ዘመድ አዝማዱን ሰብስቦ ከጽዮን ሞገሳ ጋራ መነጋገሩን ሳይገልጥ ሚስት ለማግባት ቁርጥ አሳብ ማድረጉን ብቻ ነገራቸው። ነገሩን በሰሙ ጊዜ እንደዚህ ከሆነ የእገሌን ልጅ ቢያገባ ይሻላል እያሉ ሁሉም በልባቸው ማማረጥ ጀመሩ። ከመካከላቸው አንዱ አጎቱ ተነሥቶ አንኮበር ወጥቼ ሳለሁ ያቶ ገብረ ሥላሴን ልጅ እጅግ የተዋበች ቆንጆ አይቻለሁና እርስዋን ያግባ ብሎ ተናገረ።

ደግሞ አንዱ ዘመዱ ተነሥቶ ወደ ሰላ ድንጋይ በወጣው ጊዜ ባንድ ከበርቴ ቤት አድሬ ማለፊያ የደረሰች ልጃገረድ አይይቻለሁና እርስዋን ብናጋባው ይሻላል ብሎ ተናገረ።

ሦስተኛው ዘመዱ ግን ብርሃኔ የሚያገባትን ሴት አስቀድሞ ሳያስብና ሳይዘጋጅ የነገረን አይመስልምና ሚስት ለማግባት ፈቃድህ ከሆነ የማንን ልጅ እናጋባህ ብለን ብንጠይቀው ይሻላል ብሎ ተናገረ።

በዚህም ነገር ሁሉም ከተስማሙ በኋላ ብርሃኔን ጠርተው ሚስት ለማግባት ቁርጥ አሳብ ማድረግህን ብታስታውቀው እጅግ ደስ አለን። ነገር ግን አሳብህ እንደምን ነው እኛ ፈልገን ብናጋባህ ትወዳለህን ወይስ አንተው ራስህ ፈልገህ ትነግረናለህ ብለው ጠየቁት።

ብርሃኔም ይህም ጥያቄ በሰማ ጊዜ እኔ ዛሬ እናንተን ሰብስቤ ማስታወቄ ያለ ፈቃዳችን ሚስት አገባ ብላችሁ እንዳትቀየሙብኝ ነው እንጂ የማገባትንስ ሚስት ከሁለት ዓመት አስቀድሞ መርጩ ነገሩን ጨርሻለሁ። ባለቤቱ ያልወደደውን ምግብ በግድ ቢያበሉት ጤና እንዳይሆነው እንደዚሁ ራሱ ባለቤቱ ያልመረጣትን ሚስት ዘመዶቹ በግድ ቢያጋቡት ፍቅራቸው የጸና አይሆንም። ስለዚህ እኔን የምትስማማኝን ሚስት ራሴ መርጫለሁና እናንተም በዚህ ሀገር አላደከማችሁም አላቸው።

ወደ ቤትም በገቡ ጊዜ አባትና እናቱ ለብቻው አድርገው ለማግባት ያሰባት ሴት ሀገርዋ ወዴት፤ አባታዋም ማን፤ እንደ ሆነ ጠየቁት። እርሱም ሀገርዋ እቲሳ በሚባል በእናቱ ዘመዶች አባትዋም አቶ ክብረት መሆኑን በነገራቸው ጊዜ አባትና እናቱ ከደስታቸው ብዛት የተነሣ አንገቱን አቅፈው ይዘው ይስሙት ጀመረ። እኛ የተጨነቅነው አንዲት ያንኮበር ወይም የይፋት ቅሬ ማግባት ያሰብህ መስሎን ነው እንጂ እቲሳማ ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የተወለዱበት የእኛው ሀገር አይደለምን። ይህንም የመሰለ መልካም አሳብ ስለ ማሰብህ እግዚአብሔር ይባርክህ እያሉ ይመርቁት ጀመሩ።

የሠርጉም ቀን የተቆረጠው በዚያው ዓመት በሚያዝያ ፳ ቀን ነበርና ከፋሲካ ድግስ ጋራ የሠርጉ ድግስ ተጀመረ።

ቢሆንም የሠርጉ ድግስ ለታደሙትና ለሠርገኞቹ ብቻ የሚበቃ ሆኖ በልክ እንዲደገስ እንጂ ለዘፈንና ለጫዋታ ተብሎ ብዙ ድግስ እንዳይደገስ ብርሃኔ አስታውቆ ነበር።

የሠርጉም ቀን በደረሰ ጊዜ ከሚዜዎቹ በቀር አሥር ሠርገኞች ብቻ ከባልንጀሮቹ መርጦና አስከትሎ ወደ ቡልጋ ወረደ። በሚያዝያ ፲፱ ቀን እቲሳ ደረሰና ሠርገኞቹን በእናቱ ዘመዶች ቤት አቆይቶ እርሱ ብቻውን ወደ መምሕር ተስፋ ሥላሴ ሔዶ ጋብቻችን በተክሊል ነውና የተክሊሉ ሥርዓት እንዲሰናዳ ለቀሳውስቱና ለዲያቆናቱ ያስታውቁልኝ ብሎ ነገራቸው።

መምሕርም የብርሃኔ አሳብና ሥራ እንደ መጽሐፍ ቃል በመሆኑ ደስ ስላላቸው ከሌሊቱ ፺ ሰዓት ተነሥተው ወደ ቤተ ክርስቲያን ሔደው ጸሎተ ተክሊሉ እንዲጀመር አደረጉ።

ጸሎተ ተክሊሉና ሥርዓተ ተክሊሉም ከተጨረሰ በኋላ ሙሽራውና ሙሽራይቱ ባንድነት ቀርበው ከዚህ ቀጥሎ ባለው ንግግር ቃል ኪዳን ተጋቡ።

በኑሮ ችግርና በሕማም፤ በሌላውም ይህን በመሰለው ነገር ሁሉ እየተረዳዳንና እየተጽናናን እንኖራለን እንጂ ከሞት በቀር የሚለየን የለም። ለዚህም ሁሉ እግዚአብሔር ምስክራችን ነው እያሉ እጃቸውን በወንጌል ላይ እየጫኑ መሓላ አደረጉ። ቀሳውስቱም እግዚአብሔር ቃል ኪዳናችሁን ያጽናላችሁ፤ በአምልኮቱ ለመጽናት፤ ሕጉን ለመጠበቅ ያብቃችሁ ብለው አቡነ ዘበሰማያት አሳረጉላቸው።

ይህም ሁሉ ከተደረገ በኋላ ቀሳውስቱ ጸሎተ ቅዳሴ አድርሰው ሥጋ ወደሙ አቀበሏቸው። ከቅዳሴውም በኋላ ሙሽራውና ሙሽራዪቱ የተክሊሉን አክሊል እንደ አደረጉ ካህናቱም ልብሰ ተክህና እንደ ለበሱ ወጥተው ትዌድሶ መርዓት ወትብሎ ወልድ እሁየ ቃልከ አዳም እየተባለ በቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያ ዑደት ተደረገና የተክሊል ጋብቻቸው ሥርዓት ተፈጸመ።

ከዚህም በኋላ ብርሃኔ ወደ ዘመዶቹ ቤት፤ ጽዮን ሞገሳም ወደ አባትዋ ቤት ሔደው የደስታ ዕረፍት አድርገው ዋሉ።

በዚሁም ቀን ከማታው ባንድ ሰዓት ብርሃኔ ሚዜዎቹንና ሥርገኞቹን አስከትሎ ወደ ሙሽራዪቱ አባት ቤት ሔደ።

በዚያም ዘመን በቡልጋ የጋዝ ወይም የኤሌክትሪክ መብራት አልነበረምና በአጥሩ ግቢ የወይራና የግራር ፍልት አንዳንዱ ሸክም ባንድ ጊዜ እየተጨመረ ይንቀለቀል ነበርና ደጁ ሁሉ የጨረቃ ብርሃን ያህል ያበራ ነበር።

በዳሱም ውስጥ ባንድ ወገን የወይራና የግራር ፍልጥ እየነደደ ደግሞ ባንድ ወገን ጧፍና ሞራ ይበራ ነበር።

የሙሽራዪቱም አባት ዳሱን በሙሉ ቄጠማ አስጎዝጉዞ፤ በስተ ላይም ወገን ነትና ማስ አስነጥፎ ከእድመኞቹ ጋራ ተቀምጦ ይጠብቅ ነበርና ሥርገኞቹ መጡ በተባለ ጊዜ በቶሎ እንዲገቡ አዘዘ።

በገቡም ጊዜ እንደ ደንቡ «ለምን ቆማችኋል» ተብለው ተጠየቁና «ልጅ ታደርጉን ብለን» ብለው ከመለሱ በኋላ «እጃችሁ ከምን» ቢሏቸው «ከወርቅ» ብለው ለማጫ የተያዘውን ብር አቀረቡ። ወዲያውም የሙሽራዪቱን ልብስ በሙሉ፤ የቀረውንም የሴት ጌጥ በሙሉ፤ ያባትና የእናትም ልብስ በሙሉ አቀረቡ።

ስለ ማደሪያቸውም ተጉለት ዋሻ አንድ የገባር መሬት፤ ደብረ ብርሃን አንድ የዲቁና መሬት፤ አምሳ ዳውላ እህል፤ ጥንድ በሮች፤ ሁለት ላሞች፤ አሥር በጎች፤ አሥር ፍየሎች፤ ሁለት በቅሎች፤ ሁለት አጋሰሶች ብለው ቆጠሩና ወደ ፊትም በሀብታችን ከምናገኘው ሁሉ የግል አናደርግም ብለው አጼ ይሙቱ እያሉ ተፈጠሙ።

ከዚህም በኋላ ለሠርገኞቹ ወደ ተሰናዳው ስፍራ ወስደው አሳረፉዋቸው። አንድ ሰዓትም ያህል ከቆዩ በኋላ ራት አቀረቡላቸው። የተዘጋቸውንም ምግብና መጠጥ ሁሉ የሚጣፍጥ ለሰውነት የሚስማማ ነበር እንጂ እንደ ሌሎች ሰዎች ሠርግ ምግቡ የማይጣፍጥ፤ መጠጡ የሚያሰክር አልነበረም።

ሚዜዎቹና ሠርገኞቹም ተቀምጠው የደስታ ንግግር እየተነጋገሩ ከመጫወት በቀር የእተነሡና እየቆሙ የብልግና ዘፈን እንዳይዘፍኑ ብርሃኔ ከልክሎ ነበርና እስኪጠግቡ በልተው፤ እስኪረኩ ጠጥጠው የጤና ቅንቅልፍ ተኝተው አደሩ።

በማግሥቱም በማለዳ ሙሽራዪቱን ተቀብለው ምሳቸውን ባንድነት በልተው፤ በአባትና በእናትዋ ፊት ቀርበው ተመርቀው ተሰነባበቱና ከእቲሳ ወደ አፋፍ ወጥተው አደሩ። ከዚያም ጥቂት በጥቂት እየተጓዙ ተጉለት ደረሱ።

የብርሃኔም አባትና እናት ቤተ ዘመዶቻቸውንና ጎረቤቶቻቸውን ሰብስበው በደስታ ተቀበሏቸው። የሠርጉም ድግስ እጅግ ያማረ ነበረ። ሙሽሮቹም እንደ ሀገሩ ልማድ አሥር ቀን ያህል በጫጉላ ቤት ተቀምጠው የሠርጉ ወራት ተፈጸመ።

ብርሃኔም አማትና ምራት ምንም ቢፋቀሩ ባንድ ቤት ለመኖር የማይቻል መሆኑን አስቀድሞ ያውቅ ነበርና ይህንኑ ለአባትና ለእናቱ ገልጦ ነግሮ በቶሎ ቤት ሠርቶ ጎጆ ወጣ። ከዚህም በኋላ ብርሃኔ የውጭውን እያሰናዳ፤ ጽዮን ሞገሳም የውስጡን እያስተነተነች ትዳራቸውን አቃንተው በፍቅርና በደስታ ይኖሩ ጀመር።

## ምዕራፍ ፺

# ስለ ጽዮን ሞገሳ ልጅ መውለድ

ብርሃኔና ጽዮን ሞገሳ በፍቅርና በደስታ እግዚአብሔርን በመፍራት ሰውን በማክበር አንድ ዓመት ያህል ከኖሩ በኋላ ጽዮን ሞገሳ ፀነሰችና ትልቅ ደስታ አደረጉ። እርስዋም በትምሕርትና በእውቀት ያደገች ስለ ሆነች የቦካ ከመብላት፤ የኮመጠጠ ከመጠጣት ተከልክላ ጤናዋን እየጠበቀች ቆይታ ዘጠኝ ወር ከሆናት በኋላ ወንድ ልጅ ወለደች። ዕድሜዋ ፲፪ ዓመት ስለ ሆነ ሰውነቷ በምጥ ሳይጎዳ በደህና ተገላገለች።

ሕፃኑም ፵ ቀን ሲሞላው ወደ ደብረ ብርሃን ወስደው ክርስትና አስነሡት፤ የክርስትና አባቱ የድባሮ ማርያም አለቃ ወልደ አብ ነበሩ። የክርስትናም ስሙ እንደ እናቱ ወገኖች በኩረ ጽዮን ተባለ።

ጽዮን ሞገሳ የተማረች ስለ ሆነች ሰውነቷን በመጠበቋ በሽታ የሌለባት ጤናማ ነበረችና ሕፃኑ የእናቱን ጡት በመጥባት ብቻ በየቀኑ እያደገና እየፋፋ ያድር ነበር። ነገር ግን በተወለደ ባሥር ወሩ እናቱ ጽዮን ሞገሳ ዘመዶችዋን ለማየት ወደ ቡልጋ ስትወርድ ሞግዚቱ በአንቀልባ አዝላው ነበርና እቲሳ ሲደርሱ እያቃሰተ በጭንቅ ታመመ። ጽዮን ሞገሳም ከተጉለት የተነሣችበትን ቀን ትረግም ጀመረች። ይልቁንም የመከር ወራት ስለ ሆነ አባቱ ብርሃኔ አዝመራው እንዳይጠፋበት አስቦ ከሚስቱ ጋራ ወደ ቡልጋ አልወረደም ነበርና ብቻዋን ሳለች ልጅዋ በመታመሙ ኅዘንዋ ከልክ ያለፈ ሆነ። ዘመዶችዋም ጭንቀትዋንና ሐዘንዋን ባዩ ጊዜ እኩሉ ትከሻ ወርዶት ይሆናልና የሚያሽ ወጌሻ እንፈልግ ብለው ሔዱ።

እኩሉም የዛር ውላጅ ይዞት ይሆናልና ወደ ደብተራ ዱባለ ዘንድ ሔደን መጽሐፍ እናስገልጥለት ብለው ሔዱ።

ከስድት ሰዓትም በኋላ የፊተኞቹ ትከሻ የሚያሽ ወጌሻ ይዘው መጡ። ቀጥሎም ሌሎቹ ዘመዶቹዋ ደብተራ ዱባለ ጽፎ የሰጣቸውን አስማት በባሕር አረብ አሰፍተው ይዘው መጡ።

ጽዮን ሞገሳም የዘመዶችዋን አሳብና ሥራ አይታ ዘመዶቼ ሆይ፤ ስለ ልጄ በሽታ በማሰባችሁ በመጨነቃችሁ አመሰግናችኋለሁ። ነገር ግን ትከሻውን በወጌሻ ለመታሸት ሰውነቱ ያልጠነከረ ገና ሕፃን ስለ ሆነ ያጥንቶቹ መገናኛ ይለያይና የባሰ በሽታ ይሆንበታል።

ስለ ክታቡም የዛር ውላጅ የሚወጣው በጾምና በጸሎት፤ በሃይማኖትም ነው እንጂ ክታብ በመሸከም አይወጣም። ይህንም ለመረዳት ብትፈልጉ ጌታችን ከደብረ ታቦር በወረደ ጊዜ ለደቀ መዛሙርቱ የነገራቸውን ነገር መመልከት ነው። ማቴ. ፲፯፥ ፳፩።

ለሌላውም በሽታ ቢሆን የሚዋጥና የሚጠጣ መድኃኒት የተገኘ እንደ ሆነ ከሥጋና ከደም ጋራ ተዋህዶ ደሙን እያጠራ በሽታውን ያጠፋዋል እንጂ በባሕር አረብ የተሰፋ ክታብ ሰውን ለማዳን አይችልምና ምንም ቢሆን በልጄ አንገት አላስረውም። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ወስጄ የጌታችንን ሥጋና ደም ከተቀበለ በኋላ ቢሞትም የዘላለም ሕይወትን ይወርሳል። ጥቂትም በጎ የሆነልኝ እንደ ሆነ በአዲስ አበባ ከተማ የልጆች ሀኪም መኖሩን ሰምቻለሁና ወስጄ አሳክመዋለሁ ብላ መለሰችላቸው።

ዘመዶችዋም ወጌሻው ምንም ሕፃኑን ባያሽው መምጣቱ አልቀረምና የድካሙን ዋጋ አንድ አሞሌ ጨው ሰጥተው አሰናበቱት። ለደብተራ ዱባለም የክታቡን ዋጋ ሁለት ቁና ጤፍ ላኩለት።

ጽዮን ሞገሳም በማግሥቱ ሕፃኑን ወደ እቲሳ ገዳም ወስዳ ሥጋ ወደሙ ከተቀበለ በኋላ ማቃሰቱ ተወውና ትንፋሹ ተመለሰለት። ዓይኑም ፃዕረ ሞት የያዘው መስሎ ነበርና አሁን የእናቱን ፊት በደህና እያየ ፍግግ ፍግግ እያለ መጫወት ጀመረ።

ይህም ሁሉ ሲሆን ጽዮን ሞገሳ አባቱ እንዳይሰማና እንዳይጫነቅ ስለ አሰበች የልጁን መታመም አልላከችበትም ነበር። ነገር ግን ከተወለደች ጀምራ የአዲስ አበባን ከተማ አይታ አታውቅም ነበርና ከተማውን ለማየት ልጅዋንም ለማሳከም ስለ አሰበች የልጁን ሕማም ሳትገልጥ አዲስ አበባን አይቼ እንድመለስ ፍቀድልኝ ብላ ላከችበት።

ብርሃኔም ሚስቱ በትምሕርት ማደጓን እግዚአብሔርንም መፍራቷን ያውቃልና ሳይጠራጠር በቶሎ ሔደሽ ለቅበላ ወደ ተጉለት እንድትመለሽ ፈቅጃለሁ ብሎ ላከባት።

ከዚህ በኋላ ለመንገድዋና ለአዲስ አበባ የሚበእቃ ስንቋን አሰናድታ ተነሣች። ደግሞ ልጅዋ የታመመው ከተጉለት ወደ ቡልጋ ስትወርድ በአንቀልባ በመታዘሉ እንደ ሆነ አውቃ ነበርና አሁን ግን ቅርጫት አስመጥታ በውስጡ የገብስ ገለባ ሞልታ በላይ ሸማ ጎዝጉዛ በሸማው ላይ አንቀልባውን ዘርግታ ሕፃኑን አስተኛችው። በላይም ነፋስ የማይከለክል ዝንብና ትንኝ የሚከለክል ሻሽ አለበሰችው።

ከዚም በኋላ እየተፈራረቁ የሚሸከሙት ሁለት ወንድ አሽከሮች አስከትላ ወደ አዲስ አበባ ተጓዘች።

አዲስ አበባም በደረች ጊዜ ወዲያው በፍጥነት የልጆች ሀኪም ያለበትን ሥፍራ ጠይቃ ልጅዋን ይዛ ሔደች።

ሀኪሙም ሕፃንኑን በመመርመሪያው አልጋ ላይ አስተኝቶ መስሚያውን በደረቱና በትከሻው በልቡም ላይ እያደረገ ከሰማ በኋላ በሽታው የሆድ መድረቅ የተነሳበትም፣ በብርድ ምክንያት መሆኑንና አሁንም ፈጽሞ እንዳልተወው ስለ ተረዳው የሚያስቀምጥ መድኃኒት ቀምሞ ሰጥቶ ዛሬ ማታ ከዚህ መድኃኒት በሾርባ ማንካ አንድ አጠጭውና ይደር። ይህም ያላስቀመጠው እንደ ሆነ ነገ ጧት ደግሞ አንድ ማንካ ጨምሪለት። ከነገ ወዲያ መልሰሽ አምጭውና አየዋለሁ አላት።

ሕፃኑ ግን ወዲያው መድኃኒቱን እንደ ቀመሰ አንድ ሰዓት ያህል ቆይት ተቅማጥ ጀመረውና እስኪነጋ አራት ጊዜ አስቀመጠው።

በሦስተኛው ቀን እንደ ሀኪሙ ትእዛዝ መልሳ ወደ ሀኪሙ አመጣችው።

ሀኪሙም እንደ ገና እያገላበጠ በመስሚያው ከመረመረው በኋላ በሽታው ሁሉ በተቅማጥ ስለ ወጣለት ባለ ጤና ሆኖ አገኘው፤ ለእናቲቱም የምሥራቹን በነገራት ጊዜ ደስታዋ ከልክ ያለፈ ሆነ።

ከስምንት ቀንም በኋላ ሀገርዋ የምትመለስበት ጊዜ ስለ ደረሰ ወደ ሀኪሙ ሔዳ ልጅዋን ያከመበትን ዋጋውን ከፈለች። ሀኪሙም ጽዮን ሞገሳ የተማረች ደግ ሴት መሆኗን ልጅ መውደድዋን አይቶ ወደ ፊት ስለ ልጅ ማሳደግ የምታደርገውን ምክር ሊመክራት አሰበ። ወዲያውም ወንበር አቅርቦ ጥቂት አረፍ በይና ልምከርሽ አላት። በወንበም በተቀመጠች ጊዜ እንደዚህ እያለ ይመክራት ጀመር።

ለወደፊት ፊቱ ልጅ በወለድሽ ጊዜ ልጁን ዘወትር ጧትና ማታ ለብ ባለ ውኃ ማጠብ ነው። ከታጠበም በኋላ በፍጥነት በፎጣ አብሶ ማድረቅ ነው እንጂ እንደዚሁ የቆየ እንደ ሆነ በቅዝቃዜ በሽታ ይይዘዋል። ከዚህም በኋላ የሚሞቅ ልብስ አልብሶ አልጋ ላይ አስተኝቶ እንቅልፍ እንዲወስደው ማድረግ ነው።

ጡትሽ እንዳይደርቅ ሆምጣጣ ነገር አትቅመሽ፤ ነገር ግን ውኃ የሚያስጠማ ምግብ እየተመገብሽ ቢገኝ ወተት ባይገኝም ፈልቶ የበረደና የጠራ ውኃ በብዙ ጠጭ። ምናልባትም በማናቸውም በሽታ የታመምሽ እንደ ሆነ ልጁ የላም ወይም የፍየል ወተት እያፈሉ ሲበርድ ይስጡት እንጂ አንች እንዳታጠቢው፤ ተጠንቀቂ። የላም ወይም የፍየል ወተት ባይገኝ እንኳን እንደ ገንፎ ወይም እንደ ሙቅ የመሰለ የእህል ምግብ ወይም የሥጋ መረቅ መስጠት ነው።

በልብሱ ላይ ሽንቱን የሸናበት እንደ ሆነ ወይም ሌላ እድፍ ነገር ያየሸበት እንደ ሆነ ልብሱን ለውጠሽ ሌላ የታጠበ ልብስ አልብሽው። ለመቸውም ቢሆን ቢገኝ አራት ባይገኝም ሁለት ጥብቆ እያሰፋሽ እያለዋወጥሽ ማልበስ ነው።

በሳምንት በሳምንት አንዳንድ ማንካ የጉሎ ዘይት ወይም ሌላ የሚያስቀምጥ መድኃኒት ማጠጣት ነው። መድኃኒቱ ግን ሀኪም ያልፈቀደውና ያልተፈተነ እንዳይሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

ደግሞም ባለቀሰ ቁጥር ጡት አትስጭው፤ ነገር ግን ጧት አንድ ጊዜ፤ ደግሞ በሦስት ሰዓት አንድ ጊዜ፤ በስድስት ሰዓት አንድ ጊዜ፤ በዘጠኝ ሰዓት አንድ ጊዜ፤ ፀሐይ ሲጠልቅ አንድ ጊዜ አጥቢው፤ ሌሊትም እንደዚሁ ሁለት ጊዜ ብቻ አጥቢው።

ከአታክልትም ሙዝ፣ ባህረ ሎሚ፣ ድንች ይህን የመሰለ ሁሉ ለልጅ መልካም ነው። ለማናቸውም ቢሆን በወር በወሩ አንችን ልጅሽንም ሀኪም ቢመረምራችሁ መልካም ነው።

ይህንም የመከርርሁሽ ሁሉ ብታደርጊ ልጅሽ በጤና ያድግልሻል፤ አንችም ያለ ኀዘን ትኖሪያለሽ እያለ እጅግ ደስ በሚያሰኝና ወደ ልብ የሚገባ ምክር መከራት።

ጽዮን ሞገሳም ከወንበር ላይ ተነሥታ ቆማ ሀኪሙ ስለ መከራት ምክር ሁሉ አመስግኖ ወደ ቡልጋ ሔደች።

ቡልጋም በደረሰች ጊዜ የሀኪሙን ነገር ለዘመዶችዋ ነገረቻቸው። እነርሱም ሕፃኑ በስምንት ቀን እንደ ዳነ መልኩም እንደ ተለወጠና እንዳማረበት አይተው ሀኪም ማለት እንደ እግዚአብሔር ነውን እያሉ አደነቁ።

ጽዮን ሞገሳም ባልዋ ብርሃኔ ለቅበላ ወደ ተጉለት እንድትመለስ አስታውቋት ነበርና ቅበላ መድረሱን አይታ ከዘመዶችዋ ተሰናብታ ወደ ተጉለት ወጣች። ልጅዋም በአንቀልባ የታዘለ እንደ ሆነ እንደ ፊተኛው እንዳይታመም ስለ ፈራች ወደ አዲስ አበባ በወሰደችው ቅርጫት ውስጥ አግብታ ወንዶች አሽከሮች እየተፈራረቁ ተሸክመውት ወጡ።

ብርሃኒም ሚስቱ ጽዮን ሞገሳ የባልዋን ትእዛዝ ፈጻሚ መሆኗን ያውቅ ነበርና ለቅበላ ስምት ቀን ሲቀረው እስከ ደብረ ብርሃን ወጥቶ ተቀበላት። የተወደደች ሚስቱንና ልጁንም በማየቱ እጅግ ደስ አለው።

ወደ ቤታቸው በደረሱ ጊዜ ዘመድ አዝማዱ ሁሉ ተሰብስበው እንኳን ደህና ገባሽ እያሉ ሰላምታ አቀረቡላት።

ሁለት ቀንም ካረፈች በኋላ በየጎረቤትዋ እየሔደች የባሏን ዘመዶች ሽማግሎችንና ባልቴቶችን ስትጠይቅ ሰነበተች።

ከዚህም በኋላ ብርሃኔና ጽዮን ሞገሳ በደስታ ነዋሪዎች ስለ ሆኑ በኵረ ጽዮንን በወለደች በሦስተኛው ዓመት ሴት ልጅ ወለደችና የክርስትና ስምዋ ወለተ ጽዮን ተባለ። ደግሞ ወለተ ጽዮንን በወለደች በሁለተኛው ዓመት ሌላ ወንድ ልጅ ወለደችና የክርስትና ስሙ ተክለ ጽዮን ተባለ።

ቀጥላ ደግሞ በሦስተኛው ዓመት ሌላ ሴት ልጅ ወለደችና የክርስትና ስምዋ በአባትዋ በብርሃኔ ወገን ሞገሰ ብርሃን ተባለች። ከዚህ በኋላ ግን መውለድ ተዋትና እነዚያኑ አራቱን ልጆችዋን ታሳድግ ጀመር።

ልጆችዋም ካደጉ በኋላ ሁለቱ ወንዶች ልጆች ወደ ደብረ ብርሃን እየወጡ ተምረው ዳዊት ደገሙ። ሁለቱን ሴቶች ልጆች ግን እናታቸው ጽዮን ሞገሳ በቤትዋ እያስተማረች ዳዊት አስደገመቻቸው። የእጅ ሥራም ተምረው አወቁ። በቤትም ውስጥ በሚሆነው ሥራ ሁሉ እናታቸውን እየረዱና እያገለገሉ በማደጋቸው የአባታቸውም የእናታቸውም ወገኖች ሁሉ እጅግ ደስ አላቸው።

## ምዕራፍ ፳

# ስለ ሥላሴ በዓል ዝክርና ስለ ብርሃኔ ሞት

ብርሃኔ ጽዮን ሞገሳ ለሥላሴ በዓል ዝክር ያዘክሩ ነበርና ለጥር ሥላሴ ቤት ሙሉ ድግስ ስለ ደገሱ የደብረ ብርሃን ካህናት ወደ ተጉለት ወርደው ዝክሩን ሲበሉና ሲጠጡ ውለው በዚያው አድረው ነበር። በማግሥቱም ብርሃኔና ጽዮን ሞገሳ ከልጆቻቸው ጋራ ባንድ ገበታ ተቀምጠው ሲበሉ የደብረ ብርሃን አለቃወደ እልፍኝ ተጠርተው ገብተው ነበርና ብርሃኔና ጽዮን ሞገሳን ልጆቹንም ባንድ ገበታ ተቀምጠው ሲበሉ ባዩ ጊዜ ፊታቸው ወደ ብርሃኔ አዙረው ከዳዊት መዝሙር ፻፳፯ኛውን ፍሬ ጸማከ ተሴሰይ።

ብፁዕ አንተ ወሠናይ ለከ።

ብእሲኢትከ ከመ ወይን ሥሙር ውስተ ጽርሐ ቤትከ።

ወውሉድከ፤ ከመ ተከለ ዘይት ሐዲስ፤ ዐውደ ማዕድከ።

ናሁ ከመዝ ይትባረክ ብእሲ ዘይፈርሆ ለእግዚአብሔር።

ይባርከ እግዚአብሔር እምጽዮን።

ወትሬኢ ሠናይታ ለኢየሩሳሌም።

በኵሉ መዋዕ ሕይወትከ።

ወትሬኢ ውሉደ ውሉድከ።

ሰላም ላዕለ እስራኤል እያሉ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ቃል ተናገሩ።

ከዚህም በኋላ ብርሃኔና ጽዮን ሞገሳ የልጅ ልጆች አይተው ሸምግለው ዕድሜ ጠግበው በፍቅርና በደስታ ከኖሩ በኋላ ብርሃኔ በድንገት በሽታ ታመመና ሞተ። ጽዮን ሞገሳም አርባውን አውጣ በባልዋ ናፍቆትና ኃዘን ሰውነቷ ስለ ደከመ በቶሎ አረፈችና ሁለቱም በደብረ ብርሃን ተቀበሩ።

ይህንም በመሰለ ጋብቻ ተጋብተው፤ ልጆች ወልደው፤ የልጅ ልጆች አይተው የሚሞቱ ባልና ሚስት እጅግ የታደሉ ናቸው።

ተጨረሰ፤ አሜን።

# ክፍል ፫ አዲስ ዓለም

## የቅኖችና የደግ አድራጊዎች መኖሪያ

### መቅድም

ሰው በዚህ ዓለም በሚኖርበት ዘመን ሁሉ ለሕይወቱ እንጀራ፣ ውኃ፣ ልብስ ካገኘ ይበቃው ነበር። ነገር ግን ለእንጀራው ወጥ፣ ለውኃውም ማር፣ ወይም ወይን እየተሰናዳ መጨመሩ መብሉና መጠጡ ጣዕም ያለው እንዲሆን ነው። ለልብሱም ሐር ወይም ጥለት መጨመሩ ማየት ደስ እንዲያሰኝ ነው እንጂ ሌላ ምክንያት የለውም።

ደራሲም ድርሰት እየደረሰ መጽሐፍ ሲጽፍ ከመላእክትና ከሰው፤ ከእንስሳና ከአራዊት፤ ከአዕዋፍና ከተንቀሳቃሽ፤ ከተረትና ከጫዋታ፤ ከደታና ከኃዘን ከሌላውም ይህን ከመሰለው ነገር ሁሉ ምሳሌ እያመጣና እየጨመረ መጻፉ ለአንባቢው እንዳይሰለቸውና ለሰሚውም እንዲገባው ነው እንጂ ሌላ ምክንያት የለበትም።

አሁን ዛሬ በባቡር ወይም በመርከብ ለመሔድ ያሰቡ ሰዎች አስቀድመው ልዩ ልዩ የሆኑ መጻሕፍትንና ጋዜጦችን እየገዙ ይይዙና በየተራ እያነበቡ ሲጓዙ ረጅሙን ጉዞዋቸውን ያለድካምና ያለመሰልቸት ያሳልፉታል።

በመንፈሳዊም ነገር ቢሆን በገዳምና በሌላም ስፍራ የሚኖሩ ሰዎች የሚፈልጉትን ነገር ከእግዚአብሔር ለማግኘት ዳዊትና ውዳሴ አምላክ፤ አርጋኖንና መልክአ ጉባኤ፤ ይህንም የመሰለውን የጸሎት መጽሐፍ እየለዋወጡ መድገማቸው እዳይሰለቻቸው ልባቸው እንዳይዘነጋ፤ የጸሎት ቃል በአነጋገር ሲለዋወጥ ደስ እያላቸው ከጸሎት እንዳያቋርጡ ረጅሙም ሰዓታቸው ሳይታወቅ እንዲያልፍላቸው ነው በአቡነ ዘበሰማያት ውስጥ ይገኛል አቡነ ዘበሰማያትን ብቻ መድገም ይበቃ ነበር። ነገር ግን አንዱን ቃል ቀኑን ሁሉ እየመላለሱ ቢናገሩት መሰልቸቱ አይቀርም ተብሎ ሌሎችንም የጸሎት መጻሕፍት መድገም የሚያስፈልግ ሆነ።

በዚህም መጽሐፍ የሚገኙ ፍሬ ነገሮች ምንም ጥቂቶች ቢሆኑ ነገሩን ገልጦ ማስረዳት የሚያስፈልግ መስሎ ስለ ታየኝ ያልተደረገውን ነገር በልብ አሳብ ብቻ እንደ ተደረገ አስመስዬ በአንድ በተማረ ልጅና ሳይማሩ በልማድ በሚኖሩ በአንድ ቄስ መካከል የተነሣውን ክርክር ምሳሌ እያደረግሁ በረጅሙ ጽፌዋለሁና አንባቢዎቹ ሳይሰለቹ ያነበቡት እንደ ሆነ ከፍሬ ነገሩ ሲደርሱ ደስ ይላቸዋል።

ገብሬ እንኳ አስቀድሞ ሳያርስና ሳያርም ሳይኮተኩትና ውኃ ሳያጠጣ የዘራውን ፍሬ ለማግኘት አይችልም። ፍሬውን ካገኘ በኋላ ግን ደስ ይለዋል እንጂ ያለፈውን ድካሙን ሁሉ አያስበውም።

መጽሐፍ የሚያነብ ሰውም ባለመሰልቸት ሲያነብ ለአሳቡ የሚስማማውን ምሥጢር ያገኘ እንደ ሆነ ደስ ይለዋል እንጂ የንባቡን መርዘምና በማንበብ መድከሙን አያስበውም።

ደግሞ አሳቡ ጥቂት ጥቂት ይለዋወጥ እንጂ የዚህ መጽሐፍ ዋናው ጥቅሙና ፍሬ ነገሩ የተሳሳተውንና በልማድ የቆየውን ነገር በማሻሻል ለማደስ ነው እንጂ ሌላውን ሰው ለመጉዳት ራስን ብቻ ለመጥቀም የታሰበ ነገር የለበትም።

አንዳንድ ሰዎች ብዙ ዘመን የኖረውን ልማድ ማሻሻል ማደስ እንደ ነውር ይመስላቸዋል። ይኸውም የቀድሞውንና የዛሬውን ታሪክ ካለማንበባቸውና ካለመረዳታቸው የተነሣ ነው እንጂ ታሪክ አንበበው በነበሩ ዛሬ በዓለም ላይ ልማዱን ያላሻሻለና ያላደሰ ሕዝብ አለመኖሩን ያገኙት ነበር።

ሌላውስ ይቅርና ሕዝበ እግዚአብሔር፤ ውሉደ እግዚአብሔር የተባሉት የእስራኤል ካህናት እግዚአብሔር በሙሴና በአሮን አድሮ በሠራላቸው ሕግ የተጻፈውን ልማድ እያሻሻሉ አድሰውታል። በቀድሞ ዘመን የእስራኤል ካህናት ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ነው እያሉ በግና ፍየል፤ ጊደርና ወይፈን፤ ርግብና ዋኔ እያረዱ ደሙን እየረጩ ስቡንና ሞራውን እያጤሱ ይኖሩ ነበር። ዛሬ ግን በማናቸውም አገር የሚኖሩ የእስራኤል ካህናት የበግና የፍየል፤ የጊደርና የወይፈን መሥዋዕት እየሠዉ ደም ይረጫሉ፤ ስብና ሞራ ያጤሳሉ ተብሎ አይወራባቸውም።

የመሐመድ ልጆች እስላሞች እንኳ ከሃይማኖት በቀር የምግባርና የልማድን ነገር ሁሉ እያሻሻሉና እያደሱ መሔዳቸው በዓለም ሁሉ ተሰምቶ በታሪኢክ ተጽፏል።

ስለዚህ የዘመነ ሐዲስ ካህናትም በሕገ ወንጌል ያልተጻፈውን በስሕተት እየገባ ልማድ ሆኖ የቀየውን አንዳንድ የምግባር ነገር ቢያሻሽሉና ቢያድሱ ያስመሰግናቸዋል እንጂ አያስነቅፋቸውም በምሳሊኤ እየሆነ በልብ ሐሳብ የተጻፈውን ይህን መጽሐፍ በቅን ልቡና ቢያነቡት ለማሻሻሉ ሥራ እንዲረዳቸው እርግጥ ነው።

እግዚአብሔር የልጁን የኢየሱስ ክርስቶስን ብርሃን ለሁላችንም ያብራልን አሜን።

## ምዕራፍ ፩

# ስለ ዓወቀ ትውልድና ወደ ፓሪስ ስለ መሔዱ

በተጉለት አውራጃ የሚኖሩ አቶ እንደ ልቡ የሚባሉ ሰው ነበሩ። እርሳቸውም የወግዳዋን እመየት እንደሻሽን አግብተው ዓወቀን ወለዱ። ዓወቀም ከልጅነቱ ጀምሮ ብልህ ነበረና የአውሮጳን ወሬ ሁሉ እየሰማ ወደ አውሮጳ ሔዶ ጥበብና እውቀትን ለመማርና እንደ አውሮጳ ሕዝብ ለመሠልጠን ይመኝ ነበረ።

ነገር ግን አባትና እናቱን ስለ ፈራ ይህን ምኞቱን ለማንም አልገለጠም። ይህም አሳቡ በፍርሐት ምክንያት የማይፈጸም መሆኑን ልቡ በተረዳው ጊዜ ለአባትና ለእናቱ ሳያስታውቅ ኮብልሎ ለመሔድ ቁርጥ አሳብ አደረገ። ዋናውም ችግሩ ስለ ገንዘብ ነበረና ሙሴ ላኑስ የሚባል ፈረንሣዊ በመጣ ጊዜ ለእርሱ ሎሌነት ተቀጥሮ ወደ ጅቡቲ ወረደ።

ጅቡቲም በደረሰ ጊዜ አሳቡን ሁሉ ለሙሴ ላኑስ አጫወተው። ሙሴ ላኑስ የዓወቀን አሳብ በሰማ ጊዜ የኢትዮጵያ ወዳጅ ነበርና እጅግ ደስ አለው። የመርከቡንም የባቡሩንም ኪሣራ እኔ እከፍልልሃለሁ ብሎ ይዞት ወደ ፓሪስ ተሻገረ።

በፓሪስም ወደ ትምሕርት ቤት ገብቶ ይማር ጀመረ። በዚያም ያሉት የፓሪስ ልጆች ሁሉ በመልኩና በጥቁረቱ ይስቁበት ነበረ። እሱር ግን እንደ ልቡ ወደ ትምህርቱ ነውና ውርደቱንና ችግሩን ታግሦ በትምህርት ቤቱ ሰባት ዓመት ተቀመጠ። ቋንቋም፣ የእጅ ሥራም ተማረ። አገሩንም ለመደው። እነዚያም በመልኩና በጥቁረቱ የሚስቁበት ልጆች ከመላመድ የተነሳ ሊወዱትና ሊያከብሩት ጀመሩ።

ነገር ግን ማንም ሰው ቢሆን ምንም በውጭ አገር ደስ ቢለው ልቡ ካገሩ አይለይምና ዓወቀ ወደ አገሩ ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ ያስብ ጀመረ። ይህም አሳቡ እየበረታበት ስለ ሔደ በቶሎ ተነሥቶ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ።

ዓወቀ ዘወትር በአውቶሞቢልና በሠረገላ በትራይሞ እንደ ነት በለሰለሰ በፓሪስ መንገድ መመላለስ ለመደና አሁን ያንን የተጉለትን ዳገትና ቁልቁለት እንደ ምን ያድርገው። በበቅሎም እንዳይቀመጥ ቁልቁለት ሆነበት። በእግሩ እንዳይሔድ ያንን የፓሪኢስ ጫማ ሰክቷልና ድንጋዩ እየገጨው፤ ሱፋጩ እየቆረጠው አስቸገርወ። ግን ምን ይደረጋል፤ መቸም የፓሪስ መንገድ አልተገኘም። እንዲሁ ሲወድቅ ሲነሣ በብዙ ጭንቀት ከአባቱ ቤት ደረሰ።

አቶ እንደ ልቡም ባለ ብዙ ወገን ነበሩና የጠፋው ልጃቸው ተመልሶ መጣ ተብሎ በተወራ ጊዜ ዘመድ አዝማዱ ሁሉ ከየስፍራው ተሰበሰበ።

ዓወቀም ዘመዶቹ መሰብሰባቸውን በሰማ ጊዜ ከፓሪስ ይዞት የመጣውን ማለፊያ ኮት ለበሰና ሊገናኛቸው ወጣ።

ነገር ግን ከተለያዩ ሰባት ዓመት ሆኖ ነበርና ደግሞ እንደ ፈረንጅ ኮት በመልበሱ ወንድማቸው መሆኑን አጡት። ይልቁን ደግሞ ዓወቀ እንደ ፓሪስ ሰዎች ጢሙን ሁሉ በሙሉ ላጭቶት ነበረና በጦርነት ውስጥ የተጎሳቆለ መስሏቸው ደነገጡ። እርሱም እኔ ወንድማችሁ ዓወቀ ነኝ እያለ ሁሉንም በየተራ ይስማቸው ጀመረ።

ዘመዶቹም በእርግጥ እርሱ መሆኑን ከተረዱ በኋላ ምነው ምን ሆነሃል አብደሃል፤ ወይስ በጤናህ ነውን፤ እንዴት እንደ እብድ ጥብቆ ብቻ ለብሰህ ትሔዳለህ አሉት።

ዓወቀም መለሰ፤ ዘመዶቼ ሆይ፤ እናንተ ባትለምዱት የእብደት ልብስ መሰላችሁ እንጂ ይህስ የሥልጣኔ ልብስ ነው።

ያገራችን ልብስ በትልልቅ ሰዎች ፊት ለመቆም ቢሆን ካላደረጉት አይሆንም። ለእርሻ ሥራ ቢሆን ጠቅልሎ በድምበር ላይ ካላስቀመጡት ይህን አጣፍቶ ለማረስ አይቻልም።

ለንግድም ሥራ ቢሆን ጠቅሎ በኢጋሠሥ ላይ ካልጫኑት የበረሃ ቆንጥርና ቀንተፉ ይቀደዋል። ደግሞ መጫኛ ለመሳብ፤ ጭነት ለማደላደል ይህን ለመሰለው ሥራ ሁሉ የማይመች ነው። በጦርነትም ጊዜ ቢሆን ይህን ሸማ አጣፍቶ ለመዋጋት እጅግ ያስቸግራል። ያገራችን ልብስ ጥቅምነቱ ለሴሊትና ለጧት ብርድ ብቻ ነው።

ደግሞ ቀለም ያልገባ በነጭነቱ የቆየ ስለ መሆኑ በአራት ቀን፤ በአምስት ቀን ካላጠቡት እድፍ ይይዛል። ያደፈ ልብስም መልበስ ለሚያየው ሰው ሁሉ ያስጠይፋል። የኮት ልብስ ግን ለማናቸውም ሥራ ሁሉ የተመቸ ነው። በኮትና ባንገት፤ በደረት ጌጥ ቢያጌጡበት ያሣምራል። በብሩሽ ቢጠርጉት እድፉ ይለቃል። ልብስ ማለት ይህ ነው። ደግሞ የልብስና የምግብ ነገር ባለቤቱ እንደ ወደደ ቢያደርግ አይከለከልምና ለኔ ይህ የለበስሁት መልካም ነው። ለእናንተም የለበሳችሁት መልካም ነው እንጂ የሚያነቃቅፍ ነገር የለበትም። አውሮጶችም ቀድሞ እንደኛ ሀገር የመሰለ ልብስ ይለብሱ ነበረ። ሕንድም፤ ቻይናም፤ ጃፓንም፣ ምስርም፣ ልዩ ልዩ ልስብ ነበራቸው። ነገር ግን አሁን የሚበዙት የአውሮጳን ልብስ መርጠው ኮት ይለብሳሉ። ስለዚህ እኔም ይህን ልብስ ወድጄዋለሁና መርቁልኝ አላቸው።

ዘመዶቹም ይህን በሰሙ ጊዜ ወንድማችን በእርግጥ አብዶአልና አሥረን ወደ ጠበል እንውሰደድው ብለው መከሩበት። አቶ እንደ ልቡም ሰባት ዓመት ሙሉ ዓይኑን ሳያዩት የኖሩትን ልጃቸውን ዘመዶቻቸውን ደስ ለማሰኘት ሲሉ አሥረው ወደ ጠበል ሰደዱት።

ዓወቀ እውቀቱ በትምህርት የጸና ስለ ሆነ በዘመዶቹ ማስፈራራት የለበሰውን ኮት ለመለወጥ አልወደደምና አንድ ወር ሙሉ ከታሠረ በኋላ ዘመዶቹ አሳቡ የማይለወጥ ብርቱ መሆኑን አይተው ስንት ወር ታሥሮ ይቀመጣል ይፈታና እንደ ፈቃዱ ይሁን ብለው ፈቱት።

ዓወቀም በተማረው ትምሕረት ለመግሥቴ አገልግላለሁ፣ ሰውነቴን ደስ አሰኛለሁ እያለ ሲያስብ ገና በመጀመሪያ እንደዚህ ያለ ሁከት ስለ አገኘው እጅግ አዘነ። ከፓሪስም ወደ ሀገሩ ለመመለስ ያሰበበትን ቀን ይረግም ጀመረ። ቢቻለውም ወደ ፓሪስ ለመመለስ ይመኝ ጀመረ።

## ምዕራፍ ፪

# ስለ አቶ እንደ ልቡ መታመምና መሞት

ዓወቀም ይህን በመሰለ አሳብ ተጨንቆ ሳለ አባቱ አቶ እንደ ልቡ በድንገት ታመሙና ተኙ። በሁለተኛውም ቀን ፈረሱን ጭኖ ሀኪም ለመፈለግ ወደ አዲስ አበባ ጋለበ። አዲስ አበባም በደረሰ ጊዜ ከሀኪሙ ጋራ ተነጋግሮ ሀኪሙን ይዞ ወደ ተጉለት ተመለሰ። ዘመዶቹም አቶ እንደ ልቡን ለመጠየቅ ተሰብስበው መጥተው ነበረና ዓወቀ ሀኪሙን ይዞ ሲመጣ ባዩ ጊዜ እጅግ ተቆጡና ዓይናቸውን ወደ አቶ ዓወቀ አፍጥጠው መቸስ አንተ የማታመጣው ነገር አለን። ደግሞስ የፈረንጅ መድኃኒት አጠጥተህ አጐታችንን ለመግደል አስበሃልን፤ ከዚህ ይልቅ ወደ ደብተራ ገብረ ጻድቅ ዘንድ ሔደህ መጽሐፍ አታስገልጥላቸውምን። የመንዙ ደብተራ ወልደ ሐና መጽሐፍ እየገለጡ መድኃኒቱን በቀንድ ቢላዎ እየቆረጡ እነመየት ወላንሳን፤ እንየሻቃ በድሉን አድነዋቸው የለምን። የሀገራችን መድኃኒት ሳለ ሀኪም የሚሉ ለምን አመጣህብን። አሁንም ለአባትህ አዝነህ እንደ ሆነ ደብረ ብርሃን ወይም ወደ አንኮበር ውጣና መጽሐፍ አስገልጥላቸው። የሀኪም መድኃኒት ግን ምንም ቢሆን አናቀምሳቸውም አሉት።

ዓወቀም ይህን ህ ኡሉ በሰማ ግዚኤ እጅግ አዘነ። አሳቡና አሳባቸውም ባለመጋጠሙ እጅግ ተበሳጨ። ወደ ፓሪስም ለመመለስ ቁርጥ አሳብ ካደረገ በኋላ አባቱ በእግዚአብሔር ዳኛ፤ ባልጋ ቁራኛ ተይዘው ሳሉ ትቶ ለመሔድ ኃፍረት ሆነበት። ለሀኪሙ ግን ከአዲስ አበባ እስከ ተጉለት የደከመበትን የኪሣራውን ከፍሎ መለሰው።

አቶ እንደ ልቡም በሽታቸው እየጠነከረ ይሔድ ጀመረ። ከዚህም በኋላ ያቶ እንደ ልቡ ዘመድ አዝማድ ተሰብስበው ያጐታችን በሽታቸው እየጠነከረ ይሔድ ጀመረ። አሁንም ሁለቱ ሴቶች ልጆቻቸው ቤጌምድር ናቸውና ለመቃብር እንኳ ቢደርሱ መላክተኛ እንላክ ብለው መከሩ።

ዓወቀም እንደዚህ ሲማከሩ በሰማ ጊዜ ለዚህስ አታስቡ፤ እኔ እልካለሁ ብሎ አሽከሩን ጠርቶ በቶሎ ዳለቻውን ፈረስ ጫነና ወደ አንኮበር ወጣ። አንኮበርም ስትደርስ ወደ ስልክ ቤት ሔደህ የአባታችንን መታመም ለእኅቶቼ በስልክ ንገር አለው። አሽከሩም እንደ ታዘዘ በቶሎ አሎ፤ ጐንደር አሉ ብሎ ጠራ። አልከኛውም በቀረበ ጊዜ ለከንቲባ እንግዳዬ ሚስትና ላለቃ ሣህሉ ሚስት አባታችሁ አቶ እንደ ልቡ በጠና ታመዋልና በነፍሳቸው ድረሱ ብለህ ንገር ብሎ ወደ ተጉለት ተመለሰ። ስልከኛውም ሔዶ በነገራቸው ጊዜ ተልኮ የመጣው ማነው? ብለው ጠየቁት።

እርሱም በስልክ ነው እንጂ መላክተኛስ አልመጣም ብሎ መለሰላቸው።

ስልክ ማለት ምንድነው? አሉት።

በነሐስ ሽቦ ላይ ቃሉ ሁሉ ይመላለሳል። ያንዱን ወር ጐዳና ባንድ አፍታ ይደርሳል። ከፈረንጅ አገር የመጣ ብልሃት ነው አላቸው።

ወይ መሰንበት ሆይ፤ ከቶ እያደረ ምን ይመጣ ይሆን። የሰው ቃል በሽቦ ላይ ይሔዳል የሚባል ጉድ አለ ዛሬ ሰምተን አናውቅም ብለው ዝም አሉ። ወደ ማታም ባሎቻቸውም ይህን በሰሙ ጊዜ አዎን የዚህን የስልክ ነገር እኛም ሰምተናል። ነገር ግን ቃሉን የሚያመላልሰው ሰይጣን ነው አሉ። ስለዚህ የስልክ ወሬ ምንም ቢሆን አይታመንም። ሰይጣኑ ያልሞተውን ሰው ሞተ፤ ያልታመመውን ሰው ታመመ፤ እያለ ይናገራልና አይዟችሁ አትደንግጡ አሏቸው። ከዚህ በኋላ እንደ ገና ልባቸውን አጽናንተው ዝም ብለው ተቀመጡ። አቶ እንደ ልቡ ግን በሽታቸው እየጠነከረ፤ ሰውነታቸው እየመነመነ ይሔድ ጀመረ።

በቤጌምድር ላሉት ልጆቻቸው በስልክ ተልኮ ነበረና ሠላሳ ቀን ሙሉ ምንም ምላሽ ስላልመጣ ዘመድ አዝማዱ እንደ ገና ተሰብስበው ያቶ እንደ ልቡ ሴት ልጆች በቶሎ እንዲመጡ ተልኳል ተብሎ ነበረ። ነገር ግን እስከ ዛሬ ድረስ መላክተኛው እንኳ አልተመለሰም። አሁንም ሳይደርሱ መቅረታቸው ነው። እንደምን እናድርግ ይሆን እያሉ ሲጨነቁ ዓወቀ በሰማ ጊዜ ምናልባት የስልኩ ቃል ባይደርስላቸው ይሆናል ብሎ መለሰ።

በዚያ ጊዜ ሁሉም ዓይናቸውን ወደ እርሱ አፍጥጠው ስልክ ማለት ምንድን ነው አሉት። ስልክማ ስልክ ነው። ያባታችንን መታመም ለእኅቶቼ ንገር ብዬ አሽከሬን ወደ አንኮበር መላኬ በስልክ እንዲነግራቸው ነው እንጂ በእግረኛማ ቤጌምድር ደርሶ እስቲመለስ አንድ ወር ያስፈልገው የለምን ብሎ ነገሩን ገለጠላቸው።

በዚያ ጊዜ ወንዶቹም ሴቶቹም እየተነሡ እጃቸውን ማጨብጨብ፤ ከንፈራቸውን መንከስ ሆነ። ፓሪስ ደርሶ የተመለሰ ሁሉ ራሱ እየዞረ መበላሸቱን ስናውቅ አንተን አምነን መላክተኛ ስናልክ መቅረታችን እብዶቹ እኛ ነን አሉት። ነገር ግን በትምሕህርት ቤት ያደገ ሰው ጊዜ ሲመቸው ምንም ቢሆን የፖለቲካ ነገር መናገሩ አይቀርምና እብዶቹ እኛ ነን ማለታቸውን ሰምቶ ይህ እርግጥ ነው ከናንተ የበለጠ ዕብድ የለም ብሎ ሳቀባቸው። ወደ ቤትም በገቡ ጊዜ አቶ እንደ ልቡ ደክመው ኑረው ለኑዛዜ ቄስ ጥሩልኝ አሉ። ዓወቀም ይህን በሰማ ጊዜ የነፍስ አባታቸው መምሬ ሰባጋዲስን በቶሎ አስጠራላቸው። አቶ እንደ ልቡም ኑዛዜያቸውን ጀመሩ። የተጉለቱን መሬቴን ሚስቴ እንደሻሸ ትጦርበትና በኋላ ለልጄ ለዓወቀ ይሁን። የመንዙን ርስቴን ቤጌምድር ላሉት ለሁለት ሴት ልጆቼ ሰጥቻለሁ። የደብረ ብርሃኑም መሬት ለዓወቀ የጦር ማቋሚያ

ይሁነው። ለነፍስ አባቴ ቁርበቴን፤ የጎሽ ዋንጫዬን፤ የታመምሁበትን ልብሴን ሰጥቻለሁ ብለው ኑዛዜያቸውን ጨረሱ።

ኑዛዜያቸውንም ከጨረሱ በኋላ ሁለት ሰዓት ያህል ቆይተው አረፉ። ወዲያው በተጉለት ዙሪያ የሚኖሩት ዘመድ አዝማዳቸው ሁሉ እየተጠሩ መጡ። ሴቶቹ ፊታቸውን እየነጩ፤ ቀሚሳቸውን እየቀደዱ፤ ደረታቸውን እየመቱ ያለቅሱ ጀመሩ።

ደግሞ በተጉለት አውራጃ ያሉት ካህናት ሁሉ ጥናችሁን እያያዛችሁ ኑ ተብለው ነበርና ፲፰ ጥና መጣ። ደብረ ብርሃኖችም መጥተው ነበረ። ከዚህም በኋላ ቄሱ፣ ዲያቆኑ፣ ሳታት፣ ቋሚው ባንድ እውገን ሆኖ እግዚአታውን፣ ሃሌታውን፣ ግንዘቱን፣ ነአኩቶውን ያደርስ ጀመረ። ደብተራ ደብተራውም ባንድ ወገን ሆኖ ዳዊቱን፣ መሥዋዕቱን ያደርስ ነበረ።

አቶ ዓወቀ ግን ወደ እልፍኙ ገባና ዘወትር ልብሱን አወለቀና ጥሩ ጥሩ ኮትና ሱሪ ለበሰና፤ በግራ ክንዱ ላይ ትንሽ የጥቁር አጥላስ ቅዳጅ በመርፌ ሰፋና ዓይኑን በመሐርም ጠረግ ጠረግ እያደረገ በአባቱ ሬሳ አጠገብ ቆመ። በዚያ ጊዜ ቀሳውስቱም ግንዘት መድገማቸውን ትተው፤ ደብተሮችም መዋሥዕት መምራታቸውን ትተው፤ ዘመድ አዝማዱም ልቅሷቸውን ትተው ዓወቀን ያዩ ጀመረ።

ከመካከላቸውም አንዱ ዘመዱ ወደ ዓወቀ ቀረበና ምነው ወንድሜ አቶ እንደ ልቡን ያህል አባት ሲሞት ፊትህን ነጭተህ፣፤ ዝተህ ታጥቀህ ታረግድ ነበረ። ይህ እንኳ ቢቀር የዘወትር ልብስህን ለብሰህ አባቴ፤ አባቴ፤ እያልህ ማልቀስ ነበረ እንጂ የክት ልብስህን ለብሰህ በአባትህ ሬሣ አጠገብ እንደ ጅብራ ትገተራለህን። ይህንስ በማድረግህ ለየሰው ሁሉሑ መሳቂያ ከመሆን በቀር ሌላ ምንም ትርፍ አለህ። ለካ የፈረንጅ ሀገር ትምሕርት እንደዚህ ያሞቃልላልን እያለ ይቆጣው ጀመረ።

ዓወቀም ይህን በሰማ ጊዜ እንዲህ ብሎ መለሰ። ከእንግዲህ ወዲህ እኔ ወደ አባቴ እሔዳለሁ እንጂ አባቴ ወደ እኔ አይመለሱም። ወደ እኔ የሚመለሱ ቢሆን እንኳ ፊቴን መንጩት፤ እንኳን ዝተት መታጠቅ ሌላም ከዚህ የበለጠ ነገር ባደረግሁ ነበረ። ደግሞስ አባቴ ወደ ጌታቸው ወደ ክርስቶስ፤ ወደ ዘላለም ሀገራቸው ወደ ሰማይ ቢሔዱ ደስ ያሰኛል እንጂ ምን ያሳዝናል። አባቴ በሰማይ ላይ ከአብርሃምና ከይስሐቅ ከያዕቆብም ጋራ ተቀምጠዋል። በዚያ ከቅዱሳን መላእክት ጋራ በጌታቸው ፊት ይመላለሳሉ። ስሙን ይቀድሳሉ። በዚያ ጻድቃን ሰማዕታትን ያያሉ። አባቴ ይህን ሁሉ የደስታ ዓለም ሲያገኙ ጊዜ ምን ያሳዝነኛል። እኔስ ክርስቶስ እንደ ሞተና እንደ ተነሣ አምናለሁና ይህም መዋቲ ሥጋቸው በኋለኛው ቀን እንዲነሳ፤ እኛም ሁላችንም በሰማይ እንድንገናኝ

አልጠራጠርም። ስለዚህ ለጊዜው ስለ ተለዩኝ ብቻ አዝናለሁ እንጂ ትንሣኤ ሙታንን እንደማያምኑ እንደ አረማውያን የቀቢፀ ተስፋ ኃዘን አላዝንም አለው።

እንደዚሁ ካህናቱ ሁሉ እኩሉ ሲፈቱ እኩሉ ሲስቁ ፍታቱ አለቀና አቶ እንደ ልቡ ተቀበሩ። ዓወቀም የጉዞውን ሰባት አሞሌ አምጥቶ ለካህናቱ ሰጠ።

## ምዕራፍ ፫

# ስለ አቶ እንደ ልቡ ተዝካር

አቶ እንደ ልቡ በሞቱ በሦስተኛው ቀን መምሬ ሰባጋዲስ ወደ ዓወቀ ዘንድ መጥተው ልጄ ሆይ፤ በተጉለት ወረዳ አቶ እንደ ልቡን የመሰለ ጌታና ሽማግሌ የለም። አሁንም በየዘመዳቸውና በየወዳጃቸው እርዱኝ እያልህ እያለክህ ገባሮቹንም እያዘዝህ ያርባቸው ድግስ እንዲጀመር ይሁን አሉት።

ዓወቀም እንደዚህ ብሎ መለሰ። አባቴ ሆይ፤ እባክዎ በዚህ ነገር አያስቸግሩኝ። ላባቴ ተዝካር ጌዞ ውቀጡልኝ፣ ብቅል አብቅሉልኝ፣ ጋን ተሸከሙልኝ፣ እንጨት ስበሩልኝ፣ ጠላ ጥመቁልኝ፣ ጠጅ ጣሉልኝ፣ አረቄ አውጡልኝ፣ እንጀራ ጋግሩልኝ፣ ወጥ ስሩልኝ፣ እያልሁ ዘመድ አዝማዴን አላስቸግርም። በዚህ ላይ ደግሞ እገሌ ረዳኝ፣ እገሌ አልረዳኝም በማለት ከወዳጅና ከዘመድ ጋር መቀያየም ይመጣል። ገባሮቹንም እንዳላዛቸው ዛሬ ወራቱ ሰኔ ስለ ሆነ ዋና የዘር ወራት ነውና መሬታቸው ሳይታረስ የከረመ እንደ ሆነ በሚመጣው ዓመት በረኃብ ያልቃሉ። ወደ እግዚአብሔርም ቢያዝኑ ያስፈርዱብኛል። ነገር ግን ከራሴም ከአባቴም ገንዘብ ያገኘሁትን ያህል ለቤተ ክርስቲያንም፤ ለካህናትም፣ ለነዳያኑም ምጽዋት እሰጣለሁ አላቸው።

መምሬ ሰባጋዲስም ይህም በሰሙ ጊዜ እጅግ ተቆጡ። መቸም መች ቢሆን እንደዚህ ያለ ሥራ ተሠርቶ አያውቅም። በአቶ እንደ ልቡ ተዝካር ካህናቱ ካልተሳከሩበትና በዋንጫ ካልተማቱበት ምን ተዝካር ወጣ ይባላል። እናንተ የኋላ ልጆች ወደ ፓሪስ መሻገር ከጀመራችሁ ወዲህ የምታመጡት ፈሊጥ ሁሉ ለእኛ አይገባንም። አሁንም ቢያንስ ፴ ጋን ጠላ፤ ፳ ጋን ጠጅ ፳ ጠርሙስ ያህል አረቄ ሳትደግስ የቀረህ እንደ ሆነ እገዝትሃለሁ አሉት።

ዓወቀም በዚህ ነገር እጅግ ስለ አዘነ እባክዎ አባቴ አያስቸግሩኝ። ሰውን አለልክ አጠጥቶ ማስከር የማይገባ መሆኑን አያውቁትምን። ደግሞስ ስካር ትልቅ ኃጢአት መሆኑን፤ የሚሰክርም ሰው ሁሉ ካህን እንዳሆን በመጽሐፍ መከልከሉን አልሰሙምን። በአለፈው ዘመን ሁሉ በአዲስ አበባ ካህናቱ ከተዝካር ቤት ሲመለሱ እየሰከሩ በመንገድ

ላይ እየወደቁ የውጭ አገር ሰዎች ፎቶ ግራፍ እያነሡ ወደ ሀገራቸው እየሰደዱ መሳቂያ እንዳደረጓቸው አልሰሙምን። በልክ በልተው በልክ ጠጥተው እንዳይወጡ ምንም ቢሆን የማይቻል ነገር ነው። እንዲያውም አንዱን ሰው ባንዳንድ ዋንጫ መጠጥ ሰክሮ ይገኛል። ስለዚህ አዕይንተ እግዚአብሔር የተባሉትን ካህናት በጠጅና በአረቄ አስክሬ መሣቂያ ለማድረግ አሳብና ምኞት የለኝም። ደግሞም ተዝካር ደግሶ ሰውን ማስከር የሞተውን ሰው ነፍሱን ያጸድቀው እንደ ሆነ አሰዱልኝና ልደግስ። ገንዘብ መስጠት ግን እንዲያጸድቅ ለማስረድታ ምጽዋተ አበድር እመሥዋዕት ተብሏል አላቸው።

መምሬ ሰባጋዲስም ካህናቱ፣ ነዳያኑ እስኪሰክሩ ቢጠጡ ተዝካር ከወጣ አይወር እንደዚህ ነው ያሰኛል እንጂ ምን ያስጐዳል። ደግሞም እኔ ይህን ጭቅጭቅ አላውቅምና አንኮበር ወጥተህ ከሚካኤልና ከጊዮርጊስ፣ ከማርያንና፣ ከመድኃኔ ዓለም አለቆች ጠይቅ አሉት። እንደዚህም ሲጨቃጨቁ ከቆዩ በኋላ በመጨረሻው እኔ ምንም ቢሆን ጠጅና አረቄ አጠጥቼ ካህናተ እግዚአብሔርን ለማስከር አልደግስም። ነገር ግን እንደ እቻለኝ ገንዘብ አውጥቼ ለአባቴ ተዝካር እመጸውታለሁ ቁርጥ ነገር ነገራቸው።

ከዚህም በኋላ በየገጠሩ ሁሉ ሀያ ሀያ ብር እየላከ ያባቱን ሰዓተ ሌሊት እስጀመረ። እነዚያም በቤጌምድር የሚኖሩ ያቶ እንደ ልቡ ሴት ልጆች ያባታቸውን ሞት እዚያው ተረዱና ለአርባቸው መጡ። መጥተውም ከወንድማቸው ጋራ ተላቅሰው ሲጨርሱ መምሬ ሰባጋዲስ ቀርበው ወንድማችሁ ለአቶ እንደ ልቡ አርባ ለካህናትና ለነዳያን ገንዘብ እሰጣለሁ እንጂ ድግስ አልደግስም ብሎ ተቀምጧል። የናንተሳ አሳብ እንደ ምን ነው? ብለው ጠየቁ። ዓወቀም የመብልና የመጠጥ ድግስ አልደግስም ያለበትን ምክንያት ሁሉ ለእኅቶቹ ገልጦ ነገራቸው። እኅቶቹ ግን አሳቡን አልተቀበሉትምና በመካከላቸው ትልቅ ሁከት ተነሳ። በማግሥቱም ወደ ዳኛ ሔደው ወንድማችን ያባታችንን ተዝካር በገንዘብ እንጂ በድግስ አላወጣም ብሎ አርባቸው ሊያልፍ ነው።

ነገር ግን አልደግስም ካለ ያባታችንን ገንዘብ ያካፍለንና እኛ በሰማንያቸው እንደግሳለን አሉ። ዳኛውም ዓወቀን አስጠርቶ እኅቶችህ ያባታችንን ገንዘብ ያካፍለን ይሉሃል አለው። ዓወቀም እኔ የኑዛዜውን ነገር መቸ ሰማሁትና አካፍላቸዋለሁ። ወይ ለነርሱ ብቻ ተናዘውላቸው ይሆናል፤ ወይም ደግሞ ለኔ ብቻ ተናዘውልኝ ይሆናል፤ ወይም ደግሞ ለእናታችን ብቻ ተናዘውላቸው ይሆናል፤ ብሎ መለሰ።

ከዚህ በኋላ ሁለቱም ሴቶች ልጆች ወደ መምሬ ሰባጋዲስ ሔደው መምሬ ሆይ፤ ወንድማችንን ያባታችንን ገንዘብ አካፍለንና ለሰማንያቸው ተዝካር እንድንደግስ ብንለው የኑዛዜውን ቃል አልሰማሁትም ብሎ በእርስዎ አመካኝቶ እምቢ አለ። አሁንም የኑዛዜውን ቃል አሳዩንና ወደ ፊት ድግሱን እንድንደግስ አሏቸው። መምሬ ሰባጋዲስም

በነገሩ ተናደዋልና ለእናንተ ምን ኑዛዜ አላችሁ፤ ያላቸውን ገንዘብና ማለፊያ ማለፊያውን ርስት የተናዘዙት ለሚስታቸውና ለዓወቀ ነው። ለናንተ ግን የተናዘዙላችሁ ያንን የመንዙን ቆዳ መሬት ነው ብለው ነገሩዋቸው።

ሴቶቹም ልጆች ይህን በሰሙ ጊዜ አባታችን ምንም ቢሆን እንደዚህ ያለ ኑዛዜ አይናዘዙም። አልበደልናቸው፤ አላስቀምናቸው። እርሳቸው በፈቃዳቸው ለሩቅ ሀገር ለጐንደር ሰዎች ድረውን እንኖራለን። ምን ባጠፋን እንዴህ ያለ ኑዛዜ ይናዘዙብናል። ነገር ግን ይኸው ወንድማችን ፈረንጅ ዕፀ መሰውር በራሳቸው ላይ አዙሮባቸው ይሆናል እያሉ እየተናደዱ ሰንብተው በሰማንያቸው ተዝካር መደገሳቸው ይቅርና እስከ አርባቸውም ሳይቆዩ እየተቆጡ ወደ ቤጌምድር ሔዱ።

ዓወቀም ያባቱ አርባ በደረሰ ጊዜ ስለ ተዝካሩ ፈንታ አሥር አሥር ብር እሰጣለሁና ፍቱልኝ እያለ ለየገጠሩ ይልክ ጀመረ። ካህናቱም በፀሐይ ሙቀት ተጉለት ድረስ ከመውረድና ተዝካር ከመብላት አሥሩ ብር ይሻለናል እያሉ እያመሰገኑ ተቀበሉ። ለአጥቢያው ካህናት ግን ሀያ ሀያ ብር ደረሳቸው። በዚሁም እኩሉ ኩታ እየገዙ ለበሱበት። እኩሉም ለሚስቶቻቸው ቀሚስ ገዙበት። እኩሉም ለልጆቻቸው ጥብቆ ገዙበት።

ካህናቱም ይህን ባገኙ ጊዜ የጠጅና የጠላን ተዝካር ነገር ቢያስቡት ትርፉ ስካርና ከባልንጀራ ጋራ መጣላት ይልቁንም በሽታ ሆኖ አገኙት። የገንዘብ ተዝካር ግን ስካርና በሽታ የሌለበት ልብስ ቢገዙበት፤ ሥጋ ቢገዙበት፤ ቅቤ ቢገዙበት ሌላውንም ይህን የመሰለውን ሁሉ ቢገዙበት ንብረት ችግር ያድናል።

ደግሞ የተዝካሩን ገንዘብ እያጠርቀሙ በመንፈቅ ባመት ቢካፈሉት ብዙ ብር ይሆናል። የጠጅና የጠላ ተዝካር ግን ከምሳና ከእራት አያድንም። እንደምን ማለት ተዝካር እበላለሁ ብሎ ምሳውን ሳይበላ ከቤቱ የሚነሣ የለም። ማታም ተዝካር በልቻለሁና ብሎ ራቱን ሳይበላ የሚያድር የለም። የገንዘብ ተዝካር ግን ለተዝካር አውጭውም ብዙ ድካም የሌለበት ቀላል ሥራ ነው። ለካህነቱም ብዙ ጥቅም ያለበት ነው።

ስለዚህ ጌታም እንደ ጌትነቱ፤ ድኃም እንደ ድኅነቱ የሚቻለውን ያህል ገንዘብ እየሰጠ እንዲያስፈታ ደንብ ቢደረግ እጅግ መልካም በሆነ ነበረ እያሉ እርስ በርሳቸው መነጋገር ጀመሩ።

## ምዕራፍ ፬

# ስለ ተዝካር የተደረገ ጉባዔ

ይህም ዓወቀ ስለ አባቱ ተዝካር ያሰበው አሳብና የሠራው ሥራ ከመምሬ ሰባጋዲስም ጋራ የተነጋገረው ነገር ሁሉ በሸዋም፣ በጐጃምም፣ በጐንደር፣ በትግሬም፣ በወሎም፣ በዳር ሀገርም ተሰማ። ስለዚህም ነገር ሊቃውንቱ ሁሉ እኩሉ የዓወቀ አሳብ መልካም ነው እያሉ እኩሉም እስከ ዛሬ የቆየው አሳብ መልካም ነው እያሉ እኩሉም እስከ ዛሬ የቆየው ልማዳችንን ለመተው እንደምን ይችላል እያሉ በሚገናኙበት ስፍራ ሁሉ ክርክር ያነሡ ጀመሩ።

ይህም ነገር ካንዱ ወዳንዱ ሲተላለፍ በዘመኑ ወደ ነበሩት እጨጌ ጆሮ ደረሰ። እጨጌም ይህን ነገር በሰሙ ጊዜ ይህማ ትልቅ ነገር አይደለምን። አሁንም ሊቃውንቱ ይሰበሰቡና ነገሩን በጉባዔ እንጨርሳለን ብለው ሊቃውንቱ ሁሉ እንዲሰበሰቡ አዘዙ። ሊቃውንቱም በዚሁ በጉባዔው ነገር እጅግ ደስ አላቸው። ይልቁንም ካህናት በተዝካር ቤት በብዙ እየጠጡ በየመንገዱ ላይ እየወደቁ የውጭ ሀገር ሰዎች ለመሳቂያ ፎቶ ግራፍ እያነሱ ወደ ሀገራቸው መስደዳቸው በተሰማ ጊዜ ሊቃውንቱ ሁሉ በዚህ በትንሽ ነገር የካህናት ስም በመጥፋቱ እጅግ አዘኑ። ኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖታችንን የሚነቅፍ ጠላት ሲመጣብን በቅዱስ ማርቆስ ኃይል ፊት ለፊት ቀርበን እንከራከራለን። በተዝካር ቤት ስለ መስከር ግን ምንም የለንምና ጉባዔው በቶሎ ይሁንልን እያሉ ወደ እጨጌው ላኩ። እጨጌም ይህ ጉባዔ በሰኔ ፳ ቀን በእንጦጦ ራጉኤል (በእንተ ይእቲ ደብረ ኃይል) እንዲሆን አዘዙ።

የቀጠሮውም ቀን በደረሰ ጊዜ ሊቃውንቱ ሁሉ ተሰበሰቡ። ከእነዚሁም የዋነኞቹ ስም ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነ። መልአከ ገነት እንግዳ፣ መልአከ ብርሃን ኃይሉ፣ መልአከ ፀሐይይ ክንፉ፣ መልአከ ሰላም ምህርካ፣ መልአከ ኃይል ተስፋዬ፣ በትረያርክ ጎሹ፣ ቄስ አጼ ገብረ ሚካኤል፣ አቃቤ ሰዓት ዘወልደ ማርያም፣ ከነዚኢሁም ጋራ በየአድባራቱ የብሉይና የሐዲስ መጻሕፍት የሚያስተምሩ ብዙ መምሕራት ነበሩ።

እነዚህም ሁሉ ቀን ቀን በጉባዔው ባንድነት እየዋሉ ማታ ማታ በየሰፈራቸው ይሔዱ ነበረ። እጨጌውም ለነዚህ ሁሉ ሊቃውንቶች በየሰፈራቸው ድርጐ ይልኩላቸው ነበሩ። በሰኔ ፳ ቀን ይህን ነገር ለመጨረስ ጉባዔው በተጀመረ ጊዜ መልአከ ኃይል ተስፋዬ እንደ አፈ ጉባዔ ሆነው የሆነበትን ነገር ለመናገር ጀመሩ።

አባቶቼና ወንድሞቼ ሆይ፤ አንደኛ እንደ ኢትዮጵያ ካህናት የታደለ የለም። እነሆ በኦሪት እንደ ተጻፈ በብሉይ ዘመን የአሮን ልጆች ካህናት ከወንድሞቻቸው ጋር ርስት እንዳይካፍሉ ተከልክለው ነበሩ። ነገር ግን ሕዝቡ አሥራትና በኩራት እየሰጡዋቸው

ለቤተ እግዚአብሔርም የሚገባውን መባና ስለት እየተካፈሉ መሥዋዕቱንም እየበሉ ይኖሩ ነበሩ።

ይህም ልማድ በዘመነ ብሉይ ከአሮን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ከባሕር ማዶ ባሉት ካህናት ሁሉ ጸንቶ ይኖራል። ከባሕርም ማዶ ያሉ መንግሥቶች ሁሉ የተቻላቸውን ያህል ለቤተ ክርስቲያን ምጽዋት ይሰጣሉ እንጂ ለካህናት ርስት ጉልት አይሰጡም።

ነገር ግን አንዳንድ ክርስቲያኖች ልጅ የሌላቸው እንደ ሆነ ርስትና ጉልታቸውን በኑዛዜ ለቤተ ክርስቲያን እያወረሱ ይሞታሉ።

ቤተ ክርስቲያንም ከምእመናን የወረሰችው ርስትና ጉልት የሚገኘውን የምድሩን ፍሬ ለካህናት ቀለብና ልብስ፤ ለድኆች ልጆች ማስተማሪያ፤ ለድኆች ሽማግሎች መጦሪያ፤ ታደርገዋለች እንጂ ለእያንዳንዱ ካህን ርስት ጉልት አድርጋ አትሰጥም። ስለ ግብሩም ትልቁ ቆስጠንጢኖስ ብቻ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠ መሬት ግብሩ ለቤተ ክርስቲያን ይሁን ብሎ መርቆላት ነበረ እንጂ ከርሱ በኋላ የተነሡት ነገሥታት በግድ ግብር ይቀበሏታል። እነሆ አባቶቻችን ግብጻውያን በገንዘባቸው በገዙትና ምእመናን ባወረሱዋቸው በገዳመ አስቄጥጽ፣ በገዳመ ጳኩሚስ፣ በገዳመ ጳውሊ፣ ይህንም በመሰለው በገዳም ርስትና ጉልት እስካሁን ለመንግሥት ግብር እየገቡ ይኖራሉ።

አሁን ግን በመጀመሪያ እንደ ተናገርሁት ቃል በዚህ ዓለም እንደኛ እንደ ኢትዮጵያ ካህናት የታደለ የለም ያልሁበትን ነገር ገልጬ እነግራችኋለሁ።

በዓለም ላይ በየመንግሥቱ የሚኖሩ ካህናት ሁሉ ርስት ጉልት ስለ ሌላቸው ሥራቸውም ማስተማር ብቻ ስለ ሆነ ከምእመናን በሚያገኙት በምጽዋት ገንዘብ ብቻ በችግር ይኖራሉ።

እኛ ግን በብዙ ከመታደላችን የተነሣ እግዚአብሔር በቸርነቱ የኢትዮጵያን ነገሥታት ሁሉ የሞቱትን ነፍሳቸውን ይማር፤ ያሉትንም መንግሥታቸውን ጽኑ ሰላም ያድርግላቸውና የኢትዮጵያን ምድር ከሦስት ከፍለው አንዱን እጅ ለነጋሽ፤ ሁለተኛውን እጅ ለአንጋሽ፤ ሦስተኛውን እጅ ለቀዳሽ እያሉ የመንግሥቱንም ግብር እየፋቁ ለእኛ ለካህናቱ ለእያንዳንዳችን ርስት እያደረጉ ሰጡት። እነሆ ባለ ርስቱ ካህን ሲሞት ርስቱን ለወንድ ልጁና ለሴት ልጁ ወይም ለዘመዶቹ አውርሶ ይሞታል እንጂ በተ ክርስቲያን እንደ ፈቀዳት ለማድረግ አትችልም።

መሳፍንቱና መኳንንቱ እንኳ የእኛን የካህናቱን ኑሮ ወደው ርስትና ጉልታቸውን የቅስና፣ የዲቁና፣ የግብዝና፣ የደብተርነት፣ እያሉ በቤተ ክርስቲያን መዝገበ ያስጠፉሉ። ነገር ግን ስሙን ብቻ የቤተ ክርስቲያን ብለው ያስጥፉታል እንጂ ቤተ ክርስቲያን ከዚያ

የምታገኘው ጥቅም እንጅ ጥቂት ነው። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቤት አቁማ አድኖችን ልጆች ለማስተማር የሚጦር ልጅ የሌላቸው ሽማግሎች ለመጦር አትችልም።

ለቤተ ክርስቲያንም የተባለውን ርስትና ጉልት መኳንንትና እኛ ካህናቱ ተካፍለን ከያዝን በኋላ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን ተብሎ ከምእመናን የሚመጣውን ምጽዋት እኛው ካህናትቱ እንካፈለዋለን። ሰለዚህ ቤተ ክርስቲያን ለድኆቿ ምንም ትርፍ አታገኝም።

በዚህም ላይ ደግሞ ሰው ሲሞት ለተዝካሩ ጠጅና ጠላ አረቄ ደግሱ እያልን ስካር እንደ ዝሙት ኃጢአት መሆኑን እያወቅን አለልክ እየጠጣን በየመንገዱ እየወደቅን አላፊ አግዳሚው መሳለቂያ አድርጐን ቀረ።

እንግዲህ እኛ በተዝካር ቤት ጠጥተን ከሰከርን አትስከሩ ብለን ለማስተማር እንደምን እንችላለን።

አሁንም ተዝካር ማለት የሞተውን ሰው ከኵነኔ ለማዳን ነው እንጂ ካህናትን ለማስከር አይደለምና ከእንግዲህ ወዲህ ተዝካር ሁሉ በገንዘብ ስጦታ ቢሆን ካህናትም ወደ ተዝካር ቤት ባይሔዱ ይሻላል። ካህናቱም የተዝካሩን ገንዘብ እየተቀበሉና እያጠራቀሙ ከተካፈሉ በኋላ ጠጅም ሥጋም ቢፈልጉ የወደዱትን እየገዙ በየቤታቸው ከሚስቶቻቸውና ከልጆቻቸው ጋራ ይጠቀሙበት። ይህም የእኔ አሳብ የሁላችሁ አሳብ እንዲሆን ተስፋ በማድረግ አመለከታችኋለሁ ብለው ነገራቸውን ጨረሱ።

ከዚህ ቀጥሎ መልአከ ሰላም ምህርካ ተነሥተው አባቶቼ ሆይ፤ መልአከ ኃይል ተስፋዬ የተናገሩትን ነገር ሁሉም መልካም ነው። ካህናትም ከመንግሥት ርስት ጉልት ስለ ተቀበሉ የዕለት ምግብ አይቸግራቸውምና ወደ ተዝካር ቤት ባይሔዱ ጉዳት የለባቸውም።

ነገር ግን የዕለት ምግብ የሌላቸው እኩሉ እየለመኑ እየበሉ በቤተ ክርስቲያን የሚማሩ፤ እኩሉም አካላቸው የጐደለ ሠርቶ ለመብላት የማይችሉ፤ እኩሉም የሚጦር ልጅ የሌላቸው ሽማግሎች በያገሩ እንደሚኖሩ ታውቃላችሁ። እንግዲህ እነዚህ በተዝካርና በድግስ ቤት ሔደው እንጀራ ካልበሉ ጠላ ካልጠጡ እንደምን ይኖራሉ? ብለው ጠየቁ።

መልአከ ብርሃን ኃይሉም እንዴህ ብለው መለሱ፤ አባቱ እናቱ ወይም ዘመዱ የሞተበት ሰው ፍታቱን አስፈትቶ ለካህናቱ ያገኘውን ያህል ገንዘብ ይስጥ። ለነዳያን ግን በመጠኑ ድግስ ደግሶ የነፍስ አባቱን አቁሞአ እያበላ የማያሰክር መጠጥም ያጠጣቸው።

ጌታችን በወንጌል ወአንተሰ ሶበ ትገብር በዓለ ዒትጸውዕ አዕርክቲከ፤ ወማኅፈረከ፤ ወአዝማዲከ፤ ወጎረከ፤ ወአብዕልተ፤ ከመ ይጸውዑከ። አላ ጸውዕ ነዳያነ ወምስኪናነ ብሎ የለምን። ለነዳያኑ እንደ ጌታችን ቃል ማድረግ ነው እንጂ ምንም የሚያስቸግር ነገር የለበትም። ብለው ጨረሱ።

ቀጥሎ መልአከ ገነት እንግዳ ተነሥተው መልአከ ብርሃን ኃይሉ የተናገሩት ነገር እጅግ መልካም ነው። ነገር ግን በሀገራችን በኢትዮጵያ የሕዝቡ ብልጥግና አሁንም ለጊዜው በእህልና በከብት ነው እንጂ የወርቅና የብር ብልጥግና በብዙ እንደ ሌለ የታወቀ ነው። አሁን ተዝካር በገንዘብ ይሁን ስንል ጊዜ ሕዝቡ ይቸገሩ የለንም? እንደምን ይሆናል? ብለው ጠየቁ። መልአከ ፀሐይ ክንፉም እንዴህ ብለው መለሱ፤ ምነው ትንሹን ነገር ትልቅ ታደርጉታላችሁ። ጌታችን በቤተ መቅደስ አጠገብ ተቀምጦ ሲያስተምር ብዙ ባለ ጠጐች እየመጡ ብዙ የወርቅና የብር መባ አገቡ። በኋላ ግን ሴት መጥታ ሁለት የነሐስ ቤሳ መባ አገባች።

በዚያ ጊዜ ጌታችን ብዙ ወርቅ ካገቡት ከባለጠጐቹ ይልቅ ሁለት ቤሳ ያገባችውን ድኃይቱን አመስግኖዋት የለምን።

አሁንም ገንዘብ ያለው ሰው እንደ ተቻለው ገንዘብ እየሰጠ ያስፈታ። ገንዘብ የሌለው ግን በቤቱ ያገኘውን እህልም ከብትም ቢሆን እያስገመተ ወይም እየሸጠ ይስጥ። በጭራሽም ገንዘብም፣ እህልም፣ ከብትም የሌለው ሰው ስለ ክርስቲያንነቱ ያለ ገንዘብ ይፈታ በለው ተናገሩ። ይህንም ቃል በጉባዔው የተሰበሰቡት ሊቃውንቶች ሁሉ በደስታ ተቀብለው ተስማሙበት።

ከዚህም በኋላ ለልጅ ልጅ ምስክር እንዲሆን ብለው የተቀበሉትንና የተስማሙበትን የጉባዔውን ቃል ጽፈው አትመው በየገዳማቱ በየአድባራቱ እንዲቀመጥ አደረጉ።

ይህም ሁሉ ከሆነ በኋላ ዓቃቤ ሰዓት ዘወልዳ ማርያም ተነሥተው አባቶቼና ወንድሞቼ ሆይ፤ እርጥቡ ሬሳ ደረቁን አስነሣ፤ የሚባል ተረት ዛሬ ሊደርስ ነው። ነገሩማ ከተጀመረ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ በስሕተት ገብቶ ልማድ ሆኖ የሚኖር ብዙ ነገር ያለ አይደለምን። አሁንም እግዚአብሔር በፈቃዱ ከሰበሰበን ዘንድ ይህን በስሕተት ገብቶ ልማድ ሆኖ የኖረውን ሁሉ ተማክረን ብናሻሽለው አይሻልምን ብለው ተናገሩ።

ጉባዔውም ይህን ነገር በሰሙ ጊዜ ነገሩን ያስታውቁንና የሚቻል ቢሆን ዛሬውኑ እንጨርሳለን። የማይቻል ቢሆን ግን ሁለተኛው ዓመት ተቃጥረን እንለያያለን አሏቸው። ዓቃቤ ሰዓትም ነገሩን ጀመሩ።

መጀመሪያ ነገር፤ ከእኛ ከካህናቱ ወገን አንዳንዱ ብእሲ ወብእሲት አሐዱ አካል። ዘእግዚአብሔር አስተጻመረ ሰብእ ኢይፍልጥ ተብሎ የተጻፈውን የመጽሐፍ ቃል እያወቁ ሚስቶቻቸውን እየፈቱ ሌላይቱን እያገቡ ይኖራሉ። ከእንግዲህ ወዲህ ግን ካህን የሆነ ሰው ሚስቱ በዝሙት ካልተጠረጠረቻን ካልተመሰከረባት በቀር፤ የፈታ እንደ ሆነ ካህን ተብሎ እንዳይጠራ፤ በቤተ ክርስቲያንም ገብቶ የክህነት ሥራ እንዳይሠራ ቢከለክል መልካም ነው። ሚስቱ የሞተችበትን ግን ብቻውን ለመኖር የማይቻለው ቢሆን ያግባ።

ሁለተኛ ነገር፤ ለቅስና የሚመረጥ ሰው የብሉይና የሐዲስ መጻሕፍት የተማረ ይሁን። ይህም ባይሆን አራቱን ወንጌል አንብቦ የማይተረጉም ቅስና አይሾም የተባለውን የመጽሐፍ ቃል እያወቁ ቀሳውስቶቻችን የብሉይና የሐዲስ መጻሕፍት ማወቃቸው ይቅርና ስተካከለው ንባብ ማንበብ አይችሉም። ከእንግዲህ ወዲህ ግን ግዕዝ ቋንቋ ያልተማረ ሰው ቅስና እንዳይሾም ቢከለክል መልካም ነው።

ሦስተኛ ነገር፤ በቤተ ክርስቲያን ላይ አለቃ የሚሆን ሰው ሁሉ የግዕዝ ቋንቋ ካልተማረ፤ በተክሊልና በቊርባን ከሚስቱ ጸንቶ ካልኖረ የአለቅነት ሹመት እንዳይሾም ቢከለክል መልካም ነው።

አራተኛ ነገር፤ ገንዘብ ሰጥቶ ዲቁና ወይም ቅስና የተቀበለ ሰጭውም ተቀባዩም ውጉዝ ነው ብለው ሐዋርያት አውግዘዋልና ከእንግዲህ ወዲህ የዲቁና ወይም የቅስና ሹመት በገንዘብ እንዳይሆን ቢከለከል መልካም ነው።

አምስተኛ ነገር፤ ኢታድልዉ ለገጸ ሰብእ የተባለውን እያወቅነ ድኃ ሲሞት አጭር ፍታት፤ ባለ ጠጋ ሲሞት ረጅም ፍታት እናደርጋለንና ከእንግዲህ ወዲህ ክርስቲያን ለሆነ ሰው ሁሉ ፍታቱ ትክክል ቢሆን መልካም ነው።

ስድስተኛ ነገር፤ የታመመ ሰው ወይም ያልታመመ ሰው ሥጋ ወደሙ አቀብሉኝ ባለ ጊዜ እርሱ በፈቃዱ ለቤተ ክርስቲያን ብሎ ምጽዋት ካልሰጠ በቀር በግድ የአቁራቢ ገንዘብ መቀበል ቢቀር መልካም ነው።

ሰባተኛ ነገር፤ ከቀሳውስቱና ከዲያቆናቱ፤ ከደብተሮቹም ሚስት ሲያገቡ ብዙዎቹ ተክሊልና ቊርባን አይደረግላቸውምና ከእንግዲህ ወዲህ የቤተ ክርስቲያን ወገኖች ሁሉ በተክሊልና በቊርባን ቢጋቡ መልካም ነው።

ስምንተኛ ነገር፤ ታቦት ማለት የእግዚአብሔር ቃል የተጻፈበት ሥጋ ወደሙ የሚቀመጥበት ነው። ነገር ግን ቄሱ፣ ወይም ዲያቆኑ በኃጢአት በወደቁ ጊዜ ታቦቱ ረከሰ እየተባለ እንደ ገና ይበረካል። ይልቁንም ቀሳውስቱ አነጋገር ካለማወቃቸው የተነሣ

ሥላሴ ረከሱ፤ ማርያም ረከሰች፤ ሚካኤል ረከሰ፤ ጊዮርጊስ ረከሰ፤ እያሉ በመናገራቸው ለመስማት እንኳ እጅግ ይከብዳልና ከእንግዴህ ወዲህ ታቦት ረከሰ ማለት ቢቀር መልካም ነው።

ዘጠነኛ ነገር፤ የቤተ ክርስቲያን ቋንቋችን ግዕዝ ስለ ሆነ እንኳን ሕዝቡ ቀሳውስቱ ምሥጢሩን አያውቁትም። ይልቁንም ሕዝቡ ሁሉ በቅዳሴ ጊዜ ታጥቀው ቆመው ከጌታችን መከራ ወይም በመልካም ሥራ የሚገኘው ከመንግሥተ ሰማይ ምሥጢር ወይም በክፉ ሥራ ከሚመጣው ከገሃነም ኵነኔ አንዲት ቃል ሳይሰሙ የመምሬ እገሌ ድምጡ ማለፊያ ነው፤ የመምሬ እገሌ ድምጡ መጥፎ ነው በማለት ብቻ ይለያያሉና ከእንግዲህ ወዲህ በቅዳሴ ላይ ወንጌል በተነበበ ጊዜ ቢሆን ቄሱ ባይሆን ከሊቃውንቱ አንዱ በወንጌሉ በአማርኛ ቋንቋ እየተረጐመ ለሕዝቡ በያሰማቸው መልካም ነው።

የቀረውን ትንንሹ ስሕተት ብዙ ነው። ነገር ግን ዋነኞቹ ስሕተቶች እነዚህ ከዚህ በላይ የተናገሩ ናቸው። ኃጢአትም ሲለመድ ጽድቅ ይሆናል ተብሎ እንደ ተጻፈ፤ እኛም እነዚህን ሁሉ ስሕተቶች እንደ ጽድቅ አድርገን ብዙ ዘመን አሣለፍን። አሁንም ይህን ሁሉ እያሻሻልን ብንጨርስ መልካም መሆኑን ለአባቶቼና ለወንድሞቼ አመለከታለሁ ብለው ነገራቸውን ጨረሱ።

ጉባዔውም ዓቃቤ ሰዓት ዘወልደ ማርያም የተናገሩትን በሰማ ጊዜ እስካሁን ድረስ ይህን ነገር ደፍሮ የሚናገረው ሰው ባይገኝ ነው እንጂ የስሕተት ሥራ መሆኑን የየሁላችን ልብ ያውቀዋል። አሁንም እግዚአብሔር ዓወቀን ምክንያት አድርጎ ይህን ሁሉ ለመነጋገር ካበቃን ዛሬ ክረምቱ እየገፋ ስለ ሔደ በሩቅ ሀገር ለሚመጡት ሊቃውንቶች ውኃ ይሞላባቸዋልና በሌላ ጊዜ እንዳሁኑ ጉባዔ ተደርጎ ነገሩኑን እንጨርሳለን። ሊቃውንቱም በየቤታቸው ነገሩን ሲያወጡና ሲያወርዱ ይከረሙ ብለው በሚመጣው ዓመት ለኅዳር ፳ ቀን ተቃጥረው ተለያዩ።

## ምዕራፍ ፳

# ዓወቀ በአባቱ መቃብር ላይ ጥርብ ድንጋይ ስለ ማቆሙ

ዓወቀ ከፓሪስ ከተመለሰ ጀምሮ በየጊዜው አንዳንድ ሁከት ያገኘው ነበር እንጂ ፍጹም የሆነ የደስታ ጊዜ አልነበረውምና በአባቱ ተዝካር ነገር የተነሣውን ጭቅጭቅ ከጨረሰ በኋላ ደግሞ እንደ ገና ዘመዶቹ ተሰብስበው መጥተው አቶ እንደ ልቡን ያህል አባት ሞተው ላርባቸው አንድ ጋን ጠላ እንኳ ሳታስጠምቅ ቀረህ። አሁን ደግሞ በመቃብራቸው ላይ አንድ ጕጆ ማቆም አቅቶህ በበጋ ፀሐይ በክረምት ዝናም

እያስደበደብሃቸው ትኖራለህ። አቶ እንደ ልቡ አንተን ከመውለድ መካን ሆነው ቢቀሩ ይሻላቸው ነበረ። አሁንም የሰው ሁሉ መሳቂያ እንዳትሆን እንደ ምንም ብለህ አንድ የመቃብር ቤት ሥራላቸው አሉት።

ዓወቀ ግን የዘመዶቹን ምክር ተወና ወደ ደንጊያ ጠራቢዎች ሰፈር ሔዶ ርዝመቱ አንድ ሜትር ተኩል ስፋቱ ፰ ሳንቲም የሆነ ደንጊያ በላዩም የመስቀል ምልክት ያለበት ለማስጠረብ ተዋዋለ። ደንጊያውም ተጠርቦ ከተጨመረሰ በኋላ አቶ እንደ ልቡ የተወለዱበትና የሞቱበትን ቀኑን ወሩን፣ ዓመተ ምሕረቱን በደንጊያው ላይ አስቀርጾ ወስዶ በአባቱ መቃብር ላይ አቆመው።

መምሬ ሰባጋዲስም አንድ ቀን በቤተ ክርስቲያን ዳሮ ሲያልፉ ባቶ እንደ ልቡ መቃብር ላይ የተጠረበ ነጭ ድንጋይ አዩና ቀርበው ቢመለከቱት አቶ እንደ ልቡ በዚህ ቀን ተወለዱ፤ በዚህ ቀን ሞቱ የሚል ጽሕፈት ያለበት ደንጊያ ሆኖ አገኙት። ከዚህ በኋላ እየተቆጡና እያጉረመረሙ ወደ ዓወቀ ቤት ሔዱ።

ዓወቀም መምሬ ሰባጋዲስ ሲመጡ ገና በሩቅ ባያቸው ጊዜ ነጭ ደንጊያ አሰጠርቦ በአባቱ መቃብር ላይ ስለ ማቆሙ ሊያመሰግኑት የመጡ መስሎት በደስታ ተቀበላቸው። መምሬ ሰባጋዲስ ግን ገና ሰላምታ ሳይሰጡት ዓወቀ መቸስ አንተ የማታመጣው ነገር አለን። አምስት ሺከም እንጨት፤ አምስት ሺከም ሣር አቅርበህ አንድ ጐጆ ማቆም ቸገረህና ባባትህ መቃብር ላይ ደንጊኢያ አቆምህበትን አሉት።

ዓወቀም ይህን በሰማ ጊዜ አባቴ ሆይ፤ በሆነው ባልሆነው ነገር ለምን ያስቸግሩኛል። በአባቴ መቃብር ላይ ቤት ብሠራ ከእንግዲህ ወዲህ አባቴ ተነሥተው አይበሉበት፤ አይጠጡበት፤ ተድላ ደስታ አያደርጉበት፤ ከዘመድና ከወዳጅ ጋር አይጫወቱበት፤ ለስማቸው መታሰቢያ እንደ ሆነ ያቆምሁት ደንጊያ እስከ ሺህ ዓመት ሳይጠፋ ይቆያል። የእንጨትና የሣር ጐጆ ባቆምበት ግን ባመቱ አርጅቶ ይወድቃል። ቤት ብሠራላቸው ትርፉ ምንድነው፤ ያውስ ቢሆን የእኔ አባት ንጉሥ ወይም ጳጳስ አይደሉም። ደግሞም ብዙ ገንዘብ አላወረሱኝም እንጂ ብዙ ገንዘብ አውርሰውኝ በሆነ በኖራና ባሸዋ መልካም የመቃብር ቤት በሠራሁላቸው ነበር። ነገር ግን ያወረሱኝ ገንዘብ ጥቂት ስለ ሆነ ከችግሬ አይተርፈኝም። ቢተፈኝም እንኳ ለድኃ እመጸውትላቸዋለሁ እንጂ የመቃብር ቤት አልሠራም አላቸው።

መምሬ ሰባጋዲስም ስለ አባትህ ነገር ከእንግዴህ ወዲህ ከአንተ ጋራ የምነጋገረው ነገር የለኝም ብለው ተቆጥተው ሔዱ። ቢሆንም ዓወቀ የሚነግራቸው ነገር ሁሉ ወደ

ልብ የሚገባ ስለ ሆነ ቁጣቸው ካንገት በላይ ነበርና አንዳንድ ቀን እየመጡ መጠየቃቸው አልቀረም።

## ምዕራፍ ፮

# ዓወቀ ዘመዶቹ ያጩለትን ሚስት አላገባም ስለ ማለቱ

ዓወቀ አባቱ ከሞቱ በኋላ በተጉለት ብዙ ዓመት ተቀመጠ። እርሱ አሳቡ በአዲስ አበባ ለመኖር ነበረ። ነገር ግን ኑሮው ሁሉ ከሀገሩ ሕዝብ ልማድ ልዩ ስለ ሆነ ያገሩንም ልማድ እንዳይከተል ዕውቀቱና ትምሕርቱ ስለ አስቸገረው ትልቅ ሥጋት ሆነበት። ሚኢስትም ለማግባት ፈቃዱ ሆኖ ሳለ ኑሮው በደስታ ስላልሆነ አሳቡን ለመፈጸም አልቻለም።

ዘመዶቹም ምንም በየትንንሹ ነገር ቢቀያየሙ ሥጋቸው ነውና ብቻውን እንዳይኖር ብለው ሚስት ሊያጩለት አሰቡ። እንደ ልማዳቸውም ከርሱ ባይማከሩና ሳያስፈቅዱ ያቶ በፈቃዱን ልጅ አጩለት። ከብዙ ቀንም በኋላ ዘመዶቹ ሁሉ ተሰብስበው መጥተው አባትህ ሞቱ አንተ ብቻህን ቀረህ። አሁንም ዘር እንዳይጠፋ ብለህ ሚስት አጭተንልሃልና ነገሩን እንድትሰማው ብለን ነው።

በፊትም ነገሩን ማስታወቃችን አንተ ከፓሪስ ከተመለስህ ወዲህ አመልህ ተለውጦአልና ብንፈራህ ነው እንጂ እንደ ሀገራችን ልማድ ቢሆን የሠርጉ ለት ብቻ ተነሣ በለን እንወስድህ ነበር አሉት።

ዓወቀም ይህን በሰማ ጊዜ በዘመዶቹ አሳብ እጅግ አድርጎ ተደነቀ። እንዲህም ብሎ መለሰላቸው፤ ዘመዶቼ ሆይ፤ እኔ የማገባት ሴት መልኳን ሳላይ፤ ጠባይዋን እውቀቷን ሳልመረምር፤ የማገባት ይመስላችኋል? እርሷስ መልኬን ሳታይ፤ ጠባዬንና እውቀቴን ሳትመረምር፤ እኔን ባል አድርጋ ለመኖር የምትችል ይመስላችኋል? የናንተ ዓይን ለእኛ ምናችን ነው? መልክ ለመልክ ሳንተያይ፤ ጠባይ ለጠባይ አንመራመር ከተጋባን በኋላ ከመካከላችን ጠብ የተነሳ እንደሆነ እንደምን እንሆናለን አላቸው።

እነርሱም እንዴህ ብለው መለሱ፤ ተብ የተነሣ እንደ ሆነ አንተ ምን አስፈራህ። ብትሆንህ ታኖራታልህ፤ ባትሆንህ ግን እጅዋን ይዘህ መንጭቀህ ታስወጣታለህ። ላንተ ለእንደ ልቡ ልጅ ሴት ትጠፋ ይመስልሃልን። እንዲያውስ በየሳምንቱ አንዲቱን እየፈታህ ሌላይቱን ብታገባ ማን ይከለክልሃል አሉት።

ዓወቀም ይህን በሰማ ጊዜ እጅግ አድርጐ ሳቀባቸው። እንዴህም ብሎ መለሰላቸው፤ ዘመዶቼ ሆይ፤ ጥንቱንም የፈራሁት ይህንኑ አሳባችሁን ነበር። ማንም ቢሆን ሚስት ካገባ በኋላ ከሞት በቀር የሚለየው የለም። ባልና ሚስት ሁለቱ ተዋደው ከተጋቡ በኋላ ተቻችለው ይኖራሉ እንጂ መፋታት አልተፈቀደላቸውም። ስለዚህ መልኳን አይቼ፤ ጠባይዋንና እውቀቷን መርምሬ እወድሃለሁ እወድሻለሁ ከተባባልን በኋላ በተክሊልና በቁርባን አገባለሁ እንጂ ምንም ቢሆን እናንተ ያጫችሁልኝን ሴት አላገባም ብሎ ቁርጥ ነገር ነገራቸው።

መልኳን ሳላይ፤ ጠባይዋንና እውቀቷን ሳልመረምር አላገባም የምትለን ሴት ፊት ናትን ወይስ ልጃገረድ ናት። ፊት ሴት ታገባ እንደ ሆነ በእርግጥ ለማማረጥ ትችላለህ። ልጃገረድ እንደ ሆነችማ እወድሃለሁ ማለቷ ቀርቶ ቀና ብላ እንኳ ፊትህን ለማየት ትፈራ የለምን። ብትደፍር እንኳ አባትና እናቴን ጠይቅ፤ እኔ አላውቅም ትልሃለች እንጂ ሌላ ምላሽ አትሰጥህም አሉት። ዓወቀም መልሰ፤ እኔም አባትና እናቴ ያውቃሉ የምትለውን ለማግባት አልፈልግም። ነገር ግን ብእሲ ያውቃሉ የምትለውን ለማግባት አልፈልግም። ነገር ግን በእሲ ወብእሲት አሐዱ አካል። ዘእግዚአብሔር አስተጻ፣እረ ሰብእ ኢይፍልጥ የሚለውን ቃል የተማረች፤ ይህንም ለመናገር የማትፈራውን ሴት ፍልጌ አገባለሁ አላቸው።

ዘመዶቹም ይህን በሰሙ ጊዜ ጥንቱንም ጥፋተኞቹ እኛ ነን። ይህን የፈረንጅ ጥብቆ መልበስ ከጀመርህ ወዲህ ዘመዶችህን ችላ እንዳልኸን ልባችን እያወቀ ላንተ ሚስት ማጨታችን ቅጣት ይገባናል። አሁንም በዚህች በታጨችው ልጅ የመጣውን ነገር እኛ እንደ ገባን እንወጣለን። አንተም የፈቀድኸውን አድርግ ብለው እየተቆጡ በየቤታቸው ገቡ።

በማግሥቱም ተሰብስበው እንግዴህ እንዴት እናድርግ። ያቶ በፈቃዱስ ፊት እንዴት አድርገን ነው የምናየው ይባባሉ ጀመር። ከመካከላቸውም አንዱ ተነሥቶ አይዟችሁ ምንም አትፍሩ። አቶ በፈቃዱ ደግ ሰው ናቸው። ጥንቱንም ቢሆን የኛን ዝምድና ፈልገው እሺ አሉን እንጂ እንኳን ልጃቸውን ዘመዳቸውንም ቢሆን ለዚህ ለጥብቆ ለባሽ አይሰጡትም ነበረ። አሁንም እንዲሁ ባንድነት ሆነን ነገሩን ሁሉ ከስር እስከ ጫፉ እንንገራቸው አላቸው። ከዚህም ነኋላ ባንድነት ሆነው ወደ አቶ በፈቃዱ ቤት ሔዱ። አቶ በፈቃዱም ገና በሩቅ ባያቸው ጊዜ ተመካክረው የሠርጉን ቀን ለመቁረጥ የመጡ መስሎት ደስ አለው። ወደ ቤትም በገቡ ጊዜ ሁሉም ደንጊያ እየተሸከሙ በእግሩ ላይ እየወደቁ ማረን ማረን አሉት።

አቶ በፈቃዱም ደነገጡና እባካችሁ አስቀድማችሁ ነገሩን ንገሩኝ። ነገሩስ ከሰማሁት በኋላ ምላሹን እነግራችኋለሁ አላቸው። እነርሱም ከስር እስከ ጫፉ ሊነግሩት ጀመሩ። አቶ እንደ ልቡ በተጉለት አውራጃ የታወቁና የከበሩ ሰው እንደ ነበሩ አንተም ራስህ ታውቃለህ። ነገር ግን ይህ ዓወቀ የሚባለው ልጃቸው በልጅነቱ ኮብልሎ ወደ ፓሪስ ሔዶ ነበረና ከዚያ ሲመለስ ዓመሉና ጠባዩ ሁሉ ተለዋውጦ አገኘው። አቶ እንደ ልቡም ከቶ ልጄ ምን ሆነብኝ ይሆን እያለ ሲጨነቁ በድንገት ታመሙና ሞቱ። ውቃቢህ ያጥፉን፤ የሞቱ ለት የከት ልብሱን ለብሶ፤ የአጥላስ ቁራጭ መሳይ በክንዱ ላይ ለጥፎ ዓይኑን በመሐረም እየጠራረገ ሲቀልድ ዋለ። ላርባቸውም አንድ ጋን ጠላ እንኳ ሳይስጠምቅ ብር እያፈሰሰ ለድኖች ሲሰጥ ዋለ። በመቃብራቸውም ላይ አንድ ጉጆ ማቆም አቅቶት አንድ ደንጊያ አስጠርቦ አቁሞበታል።

አሁን ደግሞ እኛ ምንም ቢሆን ሥጋው ሥጋችን ነው፤ ደሙ ደማችን ነው፤ ብለን ያንተን ልጅ አጭተን አግባ ብንለው አስቀድሞ መልኳን ያላየኋትን፤ ጠባይዋንና እውቀትዋን ያልመረመርኳትን ሴት አላገባም ብሎ አሳፍሮ ሰደደን። ያውም በተክሊልና በቁርባን ካልሆነ ሚስት አላገባም ብሎ መለሰልን። እኛም ይህን ሁሉ ነገር ከስማን በኋላ እንደ ፈቃድህ ሁን ብን ትተነው ሔድን። ስለዚህ በደፈርንህ ይቅርታ አድርግልን ብለን መጥተንብሃል አሉት።

አቶ በፈቃዱም ይህን በሰማ ጊዜ እኔ ሌላ ትልቅ ነገር መስሎኝ ተጨንቄ ነበረ እንጂ ይህማ እጅግ ትንሽ አይደለምን። እርሱ የኔን ልጅ ባይገባ ጉዳቱ ለራሱ ነው እንጂ የኔ ባል አጥታ የምትኖር መሰለውን። ደግሞስ በተክሊልና በቁርባን ካልሆነ አላገባም ማለቱ የኔ ልጅ እኔ እስታለሁ ድረስ ቀይና ጥቁሩን እያማረጠች ስታገባ ትኖራለች እንጂ ባንድ በርሱ ብቻ ታስራ ልትኖር ነውን። እናንተ ግን በዚህ ነገር ምንም አትዘኑ። በዚህም ምክንያት ወዳጅነታችን የሚቀር መስሏችሁ አትፍሩ አላቸው።

እነርሱም ይህን ነገር ካቶ በፈቃዱ ቃል ሰምተው ከተሰነባበቱ በኋላ እንግዲህ ለዘመድ ማሰብ እርም ነው እያሉ ዓወቀን እያሙ ወደ ቤታቸው ተመለሱ።

፯

# ዓወቀ ራሱ የመረጣትን ሚስት አጭቶ ስለ ማግባቱ

ዓወቀ በማናቸውም ምክንያት ስለ ተበሳጨ ወደ ፓሪስ እንዳይመለስ ያባቱ ቤት መፍረሱ ሆነ። አለሚስትም እንዳይቀመጥ ሕይወቱን ብቻውን ለመጨረስ የማይቻለው ሆነ። ስለዚህ ዘመዶቹ ሀይ ሀይ ብለው አዳፍረው የማትስማማኝን ሚስት ያጋቡኝ እንደ

ሆነ ፀፀት ይሆንብኛል ብሎ ሚስት ለመፈለግ ከተጉለት ወደ አዲስ አበባ ወረደ። በአዲስ አበባም ከቀበና እስከ ጉለሌ እየዞረ የተማረችና የሠለጠነች፤ መልኳ ያማረ፤ ጠባይዋና እውቀቷ የተመረመረ፤ በትምሕርት ቤት ያደገች አንዲት ልጃገረድ አገኘና ከርሷ ጋራ ቃል ለቃል ተነጋግሮ በምሥጢር ተማምሎ ሲጨርስ ለአባትና ለእናትዋ አስታወቀ። አባትና እናታዋም ፈቃድዋን ቢጠይቋት አዎን እርሱን አገባለሁ፤ ብላ ሳታፍር ሳትፈራ መለሰችላቸው።

ከዚህም በኋላ ዓወቀ የጋብቻውን ቀን ተቃጥሮ ወደ ተጉለት ተመለሰ። የጋብቻውንም ቀን በደረሰ ጊዜ ዓወቀ ድግስ ደግሱልኝ፤ ድንኳን ትከሉልኝ ብሎ ለማንም አልነበረም።

ነገር ግን በቤቱ ያገኘውን ያህል አሰናዱ ብሎ እርሱና አምስቱ ባልንጀሮቹ ብቻ ወደ አዲስ አበባ ወረዱ። አዲስ አበባም ቅዳሚት ማታ ገቡ። እሁድ ከሌሊቱ በ፲ ሰዓት ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሔዱ። ሚስቱም እንዴሁ ሁለት ባልንጀሮቿንና አባት እናቷን ቤተዘመዶቿንም አስከትላ መጣች።

ካህናቱም ተክሊሉን አድርሰው፤ ቅዳሴ ቀድሰው፤ ሥጋ ወደሙ አቀበሏቸው። ከዚህም በኋላ የሠርግ ልብሳቸውን እንደ ለበሱ ወደ ሠርጉ ቤት ሔዱ። ከሠርጉም ቤት ከወዳጆቻቸው ጋራ ተቀምጠው እስቲ ጸግቡ በሉ፤ እስቲረኩም ጠጡ። በማግሥቱም ሰኞ ጧት ተነሥተው ወደ ተጉለት ጉዞ ጀመሩ።

የዓወቀም ዘመዶች ተሰብስበው እንግዴህ እንዴት እናድርግ። ምንስ እነርሱ ቢጠላን ያቶ እንደ ልቡ ልጅ አይደለምን። እርሱ ሚስት ሲያገባ እኛ የቤታችን ብንቀር የሰማ ሰው ዓወቀ በፓሪስ ኖሮ ስለ መጣ ዕንደ ባዕድ አድርገው ሚስት ሲያገባ ወደ ቤቱ ሳይሔዱ ቀሩ ብሎ በእኛ ይፈረዳል እንጂ እርሱ እኛን ማስቀየሙን የሚያውቅልን የለም። በያገሩም እየዞርን እንዴህ አደረገን እያልን የርሱን ክፋት ለየሰው ሁሉ ለመናገር አይቻለንም። አሁንም ከሰው አፍ እንድንድን እየሔድን እንመለስ ብለው መከሩ። ወደ ዓወቀ ቤትም በደረሱ ጊዜ ወደ ዳስ እንዳይገቡ ዳስ አልተጣለምና እንዲያው በደጅ ቆመው ጉድ ሲሉ ቆዩ። ወዲያው ከአዲስ አበባ በተነሣ በአራተኛው ቀን በ፱ ሰዓት ሚስቱን ይዞ አባቱ ቤት ደረሰ። በቤቱም የተገኘውን ያህል ምግብም መጠጥም አቅርቡ ብሎ አዘዘ። ቤተ ዘመዱም ሠርገኞችም ሁሉም ባንድነት በአዳራሽ ተቀመጡ።

ሁሉም በልክ በልተው፤ በልክ ጠጥተው፤ ከአጠገቡ በኋላ ሽማግሎች እየተነሡ አንተን እንደ አብርሐም፤ እንደ ይስሐቅ እንደ ያዕቆብ ያድርግህ። አንችንም እንደ ሣራ፣ እንደ ርብቃ፣ እንደ ልያ፣ ያድርግሽ። ውለዱ፣ ከበዱ፤ ብለው መረቁ።

ዓወቀም ከራት በኋላ የቅርብ ዘመዱን አሰናበተ። የሩቅ የሩቁን ግን በአዳራሹ ውስጥ ምንጣፍ አነጥፎ እንግዲህ ብትተኙም ብትጫወቱም እንደ ፈቃዳችሁ ሁኑ ብሎ ሚስቱን ይዞ ወደ እልፍኙ ሔደ። ዘመዶቹም ይህ የጋብቻው ነገር ነገር እንዳለ ስለ ሆነባቸው ፈዝዘው ቆይተው ነበረና ዓወቀ ወደ እልፍኝ ከሔዱ በኋላ አዛዡን ጠርተው ቢገድልህም ይግደልህ አንድ ጋን ጠላ ስጠንና እንጠጣ አሉት። እርሱም ሲፈራ ሲቸር አንድ ጋን ጠላ ሰጣቸው።

አንዳንድ ዋንጫ ጠላ ከጠጡ በኋላ ግን የዓወቀ የእናቱ እህት አክስቱ ብቅሉ ወደ ራስዋ ሲወጣ ጊዜ ተነሣችና ያቶ እንደ ልቡ ልጅ ሚስት ሲያገባ ዘመድ እንደ ሌለው እንደ ድኃ ሠርግ መሆኑ ስለ ምን ነው። በሉ እጃችሁን አውጡና አጨብጭቡ። አታሞውንም ድልቅ ድልቅ አድርጉት፤ እያለች ዘመድ አዝማዱን አነሳሳችና እርሷ በመካከል ሆና ታወርድ ነበረ።

ጫጉላሽ አብቧል ዛሬ፣

እኸ፤ የሸንኰሬ፣

ጫጉላሽ አብቧል ዛሬ።

የብር አሎሎ መሳይ ዓይንሽ፣

እኸ፤ የሸንኰሬ፣

ጫጉላሽ አብቧል ዛሬ፣

አዳባይ ወርደሽ ትዋጊአለሽ።

እኸ የሸንኰሬ፣

ጫጉላሽ አብቧል ዛሬ።

ሴት ሴቱ እንደዚህ እየዘፈኑ ባንገት ሲወርዱ ደግሞ ወንድ ወንዱ ባንድ ወገን ሆነው እንደዚህ እያሉ ይጨፍሩ ጀመሩ።

፩ኛ. ሸቦዬ፤ ሸቦዬ፤ ሎጋው ሸቦዬ

ሀይ ሀይ ሀይ፤ ሎጋው ሸቦ።

ያችን ድንቡሎ ካስወደደህ፣

ሀይ ሀይ ሀይ፤ ሎጋው ሸቦ፣

አትወዳትሞይ ባሏን ነጥቀህ።

ሀይ ሀይ ሀይ፤ ሎጋው ሽቦ።

፪ኛ. አካልሽ ልስልስ እንዳመልማሎ፣

ሀይ ሀይ ሀይ፣ ሎጋው ሽቦ፣

አትፈችውሞይ ያንን መለሎ።

ሀይ ሀይ ሀይ፤ ሎጋው ሽቦ፣

፫ኛ. አንችን በማየት ፈዘዝሽ ዓይኔ፣

ሀይ ሀይ ሀይ፣ ሎጋው ሽቦ፣

አንድ ቀን ለርሱ አንድ ቀን ለኔ።

ሀይ ሀይ ሀይ፣ ሎጋው ሽቦ።

፬ኛ. ፈርተኸው ነወይ ያንን ኀብዳዳ፣

ሀይ ሀይ ሀይ፣ ሎጋው ሽቦ፣

አትወስዳትሞይ ውኃ ስትቀዳ።

ሀይ ሀይ ሀይ፣ ሎጋው ሽቦ።

ሴቶቹ ባንድ ወገን **ጫጉላሽ አብቧል ዛሬ** ሲሉ ወንዶቹ ደግሞ ባንድ ወገን **ሎጋው ሽቦ** ሲሉ ደብተሮች የሆኑ ዘመዶቹ ደግሞ ከበሮ አስመጥተው በአልባሰ ወርቅ ዑጽፍት፤ በአልባሰ ወርቅ። ዳዊትኒ ይቤላ ይቤላ በአልባሰ ወርቅ እያሉ ሲጨፍሩ ከመካከላቸው አንዱ ደብተራ ተነሥቶ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ግጥም እየገጠመ ያወርድላቸው ጀመረ።

፩ኛ. ሰላም ለኪ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፣

እንደ አድዋ ሥላሴ እንደ አክሱም ጽዮን።

፪ኛ. ፍቅርሽም ጽኑ ነው የጴጥሮስ ሥልጣን፣

መናፍቅ እኒ ነው ካንች የማይካን።

፫ኛ. መዓዛ አፉኪ ከመ መዓዛ ኮል፣

ክልኤ አጥባትኪ ከመ ዕጐለ ወይጠል።

፬ኛ. ከጧት እስከ ማታ ካንቺ ጋር መዋል፣

መመረጥ እንጂ ነው በብዙ መታደል።

እንደዚህ እየሆነ እልልታውም፣ ጭፈራውም፣ ከበሮውም ባንድነት በተቀላቀለ ጊዜ ዓወቀ ከእንቅልፉ ነቃና በቤቱ ውስጥ አምባ ጓሮ የተነሣ መስሎት በቶሎ ወደ ደጅ ብቅ ብሎ ቢያዳምጥ የዘፋኞች ድምጥ መሆኑን ተረዳው።

በዚያ ጊዜ ሙሽራዪቱን በእልፍኙ ትቶ እርሱ ብቻውን ወደ አዳራሹ እየሮጠ ገብቶ እጁን እያርገበገበ ኧረ ምን ማለታችሁ ነው። አብዳችኋልን። ኧረ እባካችሁ ዝም በሉ። ይህ አሁን የምትዘፍኑት ዘፈን የአረማውያን ጋብቻ ዘፈን ነው እንጂ የክርስቲያን ጋብቻ ዘፈን አይደለም።

ገና በጋብቻችን ቀን ጀምራችሁ የዝሙት ዘፈን ልታስተምሩን ትወዳላችሁን።

ደግሞም እነዚህ ያልተማሩት ዘመዶቼ እንኳ የዝሙት ዘፈን ቢዘፍን አይፈረድባቸውም። እናንተ ደብተሮቹማ በየሥርጉ ቤት እየገባችሁ የባልና የሚስትን አንድነት ለሠርገኞቹ መስበክ ነበረ እንጂ ይህን የመሰለ የዝሙት ዘፈን መዝፈን መቼ ይገባችሁ ነበረ።

አሁንም እስቲነጋ ድረስ አርፋችሁ ተኙ እንጂ አትዝፈኑ። ዘፈንም ለመስማት ፈልጋችሁ እንደ ሆነ ለክርስቲያን ጋብቻ የሚገባው ዘፈን እኔ አሰማችኋለሁ አላቸው። ወዲያውም በፍጥነት ወደ ዕቃ ቤቱገብቶ ግራማፎኑን ይዞ መጣ። ከዚህም በኋላ ሴቶች ዘመዶቹን ባንድ ወገን፣ ወንዶች ዘመዶቹን ባንድ ወገን፣ ካህናት ዘመዶቹን በመከላከል አስቀምጦ ግራማፎኑን እየዘወረ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ግጥም አሰማቸው።

፩ኛ. ጋብቻ ክብሩ ነው በጳውሎስ ስብከት፣

ወምስካቦሙኒ አልቦቱ ስእበት።

፪ኛ. ጋብቻን ለማክበር ሕጉን ለመቀደስ፣

በሠርጉ ቤት ገባ ኢየሱስ ክርስቶስ።

፫ኛ. ጥንቱንም ሲፈጠር ሲዘረጋ ዓለም፣

አንድ አዳም ለሔዋን ሒዋንም ለአዳም።

፬ኛ. ያዳም ልጆች ቀድሞ ዝሙትን ወደው፣

የጋብቻን ሥርዓት በማፍረሳቸው፣

ማየ አይኅ አዝንሞ አሰጠማቸው፣

፭ኛ. ደግሞም በሎጥ ጊዜ በዝሙታቸው፣

እሳቱን አውርዶ አቃጠላቸው።

፮ኛ. ሚስቱን የሚፈታ እንበለ ትዝሙ፣

በእግዚአብሔር ዘንድ መቸ ይረሳል ቂሙ።

፯ኛ. ጋብቻን ለማክበር ስለ ሚስቱም ደግሞ፣

የኃድግ ብእሲ አባሁ ወእሞ።

ይህንም ዘፈን በግራማፎኑ ካሰማቸው በኋላ

በዚያም ጊዜ ሁሉም ተነሥተው አሁን ይህን ሁሉ ጭቅጭቅ ያመጣኸው ለዚህ ለቁራሽ እንጀራና ለቅራሪ ጠላህ ነው እንጂ፤ በእውነት ለዘፈኑ ብለህ አይደለም።

እኛ ባገራችን ባልና ሚስት ሲጋቡ የሚዘፈን ዘፈን ጫጉላሽ አብቧል ዛሬ እየእባለ ነው። ከስብስቴና ከአብዬ ከአምኃ ኢየሱስ አስቀድሞ የነበረውን የሠርግ ዘፈን አሁን አንተ ልትለውጠው ነውን። ያንተ ሠርግ የሠርግ መጀመሪያ አይደለም። አሁንም አትጨቅጭቀን እንሔድልህለን። ዛሬ ሙሉ ጨረቃ ናትና እስቲነጋም አንቆይም ብለው እየተቆጡ ሔዱ። በመንገድም ሲደርሱ ያባቱ ያቶ እንደ ልቡ የወንድም ልጅ ሽሙጡን ጀመረ። ዘመዶቼ ሆይ፤ የእንደ ልቡ ልጅ ያደረገብንን ሁሉ አያችሁን። እኛን አትዝፈኑ ብሎ ከለከለና እርሱ ጋኔኑን በብረት ውስጥ አስገብቶ ያዘፍነው ጀመረ አላቸው። ምነው በፈረንጅ ሀገር ጋኔን የለም ይሉ የለምን አሉት።

በፈረንጅ ሀገር ጋኔን የለም መባሉ እኛን ለማታለል ነዋ። አሁን ዛሬ በሰማይ ላይ የሚሔዱት በምን መሰላችሁ። የአየሩን ጋኔን እየጐተቱ አይደለምን። እኛ ባገራችን ስንሰማ የበቁ ቅዱሳን በአየር ይሔዳሉ ይባል ነበረ። ዛሬ ግን በፈረንጅ ሀገር ማንም ሰው በአየር ይሔድ ጀመረ። የእንደ ልቡም ልጅ እንዳቅሙ ጋኔኑን በብረት አግብቶ ያዘፍን ጀመረ አላቸው።

ደግሞ የአከስቱ ልጅ እመየት ይጋርዱ እኔ ለራሴ በዚያ በብረቱ ያስለፈለፈውን ዘፈን አንዱንም አላውቀውም። እርም ያድርግብኝ፤ ከተወለድሁ ጀምሮ በሠርግ ቤት እንደዚህ ያለ ዘፈን ሲዘፈን አልሰማሁም ብላ ተናገረች።

ደግሞ አንዱ ዘመድዋ እንዲህ ብሎ መለሰላት። እቴ ሆይ፤ ኧረ እባክሽ ዝም ብለሽ ብትሔጅ አይሻልምን። የሞተ ሰው አታውቂምን። እንግዴህ ዓወቀን ከሞቱት ዘመዶቻችን እንደ አንዱ እንቁጠረውና እርም በለን እንተወው።

የጋብቻን ሥርዓት በማፍረሳቸው ማየ አይኅ አዝንሞ አሰጠማቸው ብሎ የዘፈነ ጊዜ በጭራሽ ራሱ የጠፋ መሆኑን አትረጅውምን። ስንት ሰዎች የጋብቻን ሥርዓት እያፈረሱ በደኅና ይኖሩ የለምን። የይፋቱ አቶ ዱባለ ይህች የዛሬዋ ሚስቱ ሰባተኛው ናት። ስድስቱን ሁሉንም አውቃቸዋለሁ። የዛሬዋን ግን በወሬ ነው። ደግሞ የአፍቀራው ደብተራ ደባልቄ መጽሐፍ ግለጥልኝ ለማለት ሔጄ ስንጫወት ይህች የዛሬዋ ሚስቴ አምስተኛዬ ናት ብሎ ነግሮኛል። ደግሞ የምጃሩ መምሬ ወልደ ሰንበት የሕግ ሚስታቸውን ከፈቱ ወዴህ ሚስት አልረጋልህ ብሏቸው እንዲሁ እንዳመላለሱ ይኖራሉ። እኔም ይኸው አንች እንደምታውቂው የሸዋ ጧፍ የምትባለዋ ሚስቴ ሦስተኛዬ ናት። አንችስ ይህ የዛሬው ባልሽ ስንተኛሽ ነው አላት።

ኡኡ፤ የእኔ ባሎች ስንቱን ልንገርህ። አባ በዝብዝ ዮሐንስ የመጡ ጊዜ ገና ልጃገረድ ነበርሁ። ግን ለከንፈር ወዳጅነት ደርሼ ነበረና ቆላ እንጨት ለመስበር ስወርድ ጕረምሶች ሁሉ እየተከተሉኝ ይወርዱ ነበረ።

የሰባት ወር (የእምባቦ) ዘመቻ ጊዜ የሕግ ባል አንድ ደብተራ አገባሁና ስልጠላው ጊዜ በመድኃኒት ተበተበኝ። በኋላ አባትና እናቴ ብትሞችም ሙቺ ብለው በግድ አፋትተው ወሰዱኝ። እርሱንም ከፈታሁት በኋላ ጤና አላገኘሁም። ባልም ሳገባ ጊዜ በሁለት በሁለት ወር ይፈቱኝ ጀመረ። ነገሩም እጅግ ሲቸግረኝ ጊዜ የመጣፍ ገላጭ ሁለት አሞሌ ይዤ ሔጄ በሞጃው በደብተራ አሻግሬ እግር ላይ ወደቅሁና ነገሩን ሁሉ ነገርኋቸው። እርሳቸውም ውቃቢ የቀርባቸው ደግ ሰው ስለ ሆኑ መጽሐፋቸውን ገልጠው አይተው ኮከቤንም ቆጥረው ሲጨርሱ የሕግ ባልሽ በመድኃኒት ተብትቦሻልና በጥቁር ፍየል ብራና መፍትሔ ሥራይ ጽፌ እሰጥሻለሁ ብለው ወዲያው ጽፈው ባንገቴ ላይ አሰሩልኝ።

ደብተራ አሻግሬም ይህን ሁሉ ካደረጉልኝ በኋላ ሰው መሆን አይቀርምና እደሪ ሲሉኝ ጊዜ እሺ ብዬ እዚያው አደርሁ። ያጋጣሚ ነገር ባንድ ጊዜ ውድቀት ቅሪት ሆንሁና

ቁጭ አልሁ። በዚያም ነገር እያዘንሁ ቆይቼ ሣለሁ በ፫ኛው ወር ውኃ ልቀዳ ወደ ወንዝ ወርጄ ስመለስ ካፊያ መሳይ አካፍቶ ነበረና አዳጠኝና ስወድቅ ጊዜ አስወረደኝ።

ከዚያም ወዲህ የዛሬውም ባሌን አቶ ሲሣይን አገባሁና ያ ደብተራ አሻግሬ ያደረጉልኝ መድኃኒት ተመስሎልኝ ይኸው ከተጋባን አሥር ዓመት ሆነ። እንግዴህ ሁለታችንም አርጅተናልና የምንፋታ አይመስለኝም ብላ መለሰች።

ይኸውልሻ፤ የጋብቻን ሥርዓት አፍርሶ የተጐዳ ማነው። የእንደ ልቡ ልጅ ብቻ የጋብቻ ሥርዓት በማፍረሳቸው ማየ አይኅ አዝንሞ አሰጠማቸው እያለ ይዘፍናል። አቶ እንደ ልቡ ይህን ሁሉ የልጁን ጉድ ሳያይ እንኳን ሞተ፤ አላት።

## ምዕራፍ ፳

# የዓወቀ ዘመዶች ከብዙ ቀን በኋላ አሳቡን ስለ መቀበላቸው

ይህንም ሁሉ ነገር እየተነጋገሩ ሲሔዱ የአቶ እንደ ልቡ የታላቅ ወንድም ልጅ ደብተራ አዳንቄ የሚባል ከእርሳቸው ጋራ አብሮ ነበረና ዘመዶቼ ሆይ፤ ተዉ፤ እጅግ ነገር አታብዙ። እንኜም ለጊዜው የዓወቀን ሥራ አልወደውም ነበር። ነገር ግን ይህን ያህል የሚያሳማው አይደለም። የጋብቻን ሥርዓት መጠበቅ ከብዙ ነገር ያድናል። መጀመሪያ፣ ባልና ሚስት የተፋቱ እንደ ሆነ ለልጆቻቸው ትልቅ ጭንቀት ነው። ልጆች ካባታቸው ጋር እንዳይኖሩ እናታቸውን ይናፍቃሉ። ከእናታቸው ጋር እንዳይኖሩ እባታቸውን ይናፍቃሉ። ሁለተኛም፤ ባል ሚስቱን በፈታ ጊዜ ከገንዘብ ሁሉ እየከፈለ ይሰጣልና በዚህ ምክንያት ለጊዜው እርሱ ራሱ ይደኸያል። በኋላም ለልጆቹ ምንም ገንዘብ ሳይተውላቸው ይሞታል። ሦስተኛም፤ ሚስት ያለችው ሰው ወደ ሌላይቱ ሴት ለመሔድ አይደፍርምና ከኃጢአት ይጠበቃል። አራተኛም፤ በሚስቱ ብቻ ጸንቶ የሚኖር ሰው ሥጋ ወደሙ አይከለከልምና ዘበልዓ ሥጋየ ወሰትየ ደምየ ይሄሉ ምስሌየ ያለውን ቃል ኪዳን ያገኛል። አምስተኛም፤ በሚስቱ ብቻ ፀንቶ የሚኖር ሰው ከቂጥኝ፣ ከጨብጥ፣ ይህንም ከመሰለ ሁሉ ይድናል። በቂጥኝና በጨብጥ ብቻ ያለቁት ዘመዶቻችንና በሌላ በሽታ ከሞቱት በሽታ ከሞቱት ዘመዶቻችን ይበዙ የለምን። ደግሞስ ሥርዓት የሚያፈርስ ሰው ሁሉ ምን ጉዳት አለበት ለምን ትላላችሁ። የመራቤቴው ደብተራ አጥላባቸው የሕግ ሚስቱን ፈትቶ ያቶ አብጤን ሚስቱ ውሽማ ቢይዝ አቶ አብጤ በድንገት ደርሶ በፎቁ ሽርክቶ አልገደለውምን። ፍትሐ ነገሥቱም በሚስቱ ላይ ከገድለው ይድን በቃ ብሎ ፈረደለት።

ደግሞስ የወግዳውን የሻላ ማመጫን ሁላችሁስ ታውቁት የለምን። እርሱ ሚስቱን ፈታና ሌላ ሴት ቢያገባ ሴት የቀድሞ ባሏን አለፈቃዱ ፈትታው ኑሮ ሁለቱም ባንድነት እንደ ተኙ ባንድ ጥይት ገድሏቸው አልሔደምን። በመጽሐፍም አመንዝሮች መንግሥተ ሰማያትን አይወርሱም ተብሎ ተጽፎአል። ይህስ ነገር ሁሉ ካነሣችሁ የኔም አሳብ እንደ አቶ ዓወቀ ነው አላቸው።

ከዚህ በኋላ ሁሉም እርስ በርሳቸው ክርክር ገጠሙ። ግማሾቹ የዓወቀ አሳብ መልካም ነው አሉ። ግማሾቹ ደግሞ አባቶቻችን እስከ ዛሬ እንዳቆዩን በየወሩ በያመቱ እያገባንና እየፈተን እንኖራለን እንጂ የተከሊል የቍርባን ጋብቻ አንፈልግም። እንደ ቄስ ባንዲት ሴት ብቻ ታስረን መኖራችን ምን በወጣን ነው አሉ።

ነገር ግን የተጉለት ሰው ላዩ ቆዳው ሞኝ መስሎ ልቡ እጅግ ብልህ ነውና በየቤታቸው ከገቡ በኋላ ተኝተውም፤ ቆመውም፤ ተቀምጠውም፣ ቢያስቡት የዓወቀ አሳብ እጅግ መልካም ሆኖ ታያቸው። ከዚህ በኋላ በተጉለት አውራጃ ያቶ እንደ ልቡ ዘመድ የተባለ የሩቁም የቅርቡም ቡሎ ወርቄ ገባያ ድረስ እንገናኝ ተባብሎ ተቃጠረ። ዓወቀ ምንም ብርቱ ጉዳይ አግኝቶናልና ቡሎ ወርቄ ገባያ ድረስ እንድትመጣልን ብለው ላኩበት።

ቀጠሮ ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም ባንድነት ተሰብስበው ከበርኖስ ተራ በስተቀኝ ባለው በጉብታው ሥር ተቀመጡ።

ገባያተኛው ሁሉ ባያቸው ጊዜ ስለ ብዛታቸውና ለብቻቸው ስለ መቀመጣቸው ያደንቅ ነበረ። ግማሹ በነፍስ ግዳይ ነገር የተጣለ ሰው ያስታርቃሉ ይሆናል አለ። ግማሹ ግን በርስት ነገር የተጣላ ሰው ያስታርቃሉ ይሆናል አለ። ከዚህ በኋላ ያቶ እንደ ልቡ ዘመዶች ባንድነት ተነሥተው ዓወቀ እግር ላይ ወድቀው ማረን ማረን እስከ ዛሬ ድረስ አሳብህን ሁሉ አንቀበልም ብለን በምትሠራው ሥራ ሁሉ፤ በትንሹም በትልቁም ስናስቀይምህ ኖርን። አሁን ግን አሳብህን ሁሉ ብናየውና ብንመረምረው ሰው ሲታመም በሐኪም ማሳከም፤ ቢሞትም በመቃብሩ ላይ ጽሕፈት ያለበት ጥርብ ደንጊያ ማስቀመጥ፤ ስለ ተዝካርም በጠላና በጠጅ፤ በአረቄ ፈንታ ገንዘብ መስጠት፤ የጋብቻንም ሥርዓት ማክበርና ሚስትን አለመፍታት እጅግ መልካም ነገር ሆኖ ስለ ታየን በዚህ ነገር አሳብህን ሁሉ ወደን ተቀብለናል። ባለፈው ነገር ብቻ ቂም አትያዝብን አሉት።

ዓወቀም ይህን በሰማ ጊዜ ከደስታው ብዛት የተነሣ ደነገጠ። ለጊዜውም የሚያላግጡበት መሰለው እንጂ እውነት አልመሰለውም። ነገሩንም መላልሰው ከነገሩትና እውነት መሆኑን ካወቀው በኋላ እኔ በናንተ ላይ ምንም ቂም የለኝም።

ነገር ግን አሳቤና አሳባችሁ ባለመጋጠሙ ብቻ እጅግ አዝኜ ነበር። አሁን እንደ አሳቤ መሆኑን እንዳውቀው እንማማል አላቸው።

እንዴት ብለን እንማማል አሉት። ዋናው ነገር ያለፈው ትንንሹ ነገር የሚያመጣ ጉዳት ቀላ ነውና የአባቴ የአቶ አንደ ልቡ ዘመድ አዝማድ የሆነ ሁሉ ከዚህ ቀድሞ ሚስት ያገባ እንዲሁ በጋብቻው ፀንቶ እንዲኖር። ወደፊትም ሚስት የሚያገባ በተክሊል እንዲያገባ የጋብቻንም ሥርዓት አክብሮ እንዲኖር በዚህ ተማምለን እንታረቅ አላቸው።

ዘመዶቹም ይህን ነገር በቃሉ በሰሙ ጊዜ በዚህ አሁን በተናገርኸው ነገር ሁሉ ተማምለን ለመታረቅ ፈቃዳችን ነው። ነገር ግን አንተም እኛ ሳናውቅ በስሕተት በሠራነው ሥራ ባለፈው ሥራችን ሁሉ ቂም ሳትይዝና ላትጐዳን ማልና እንታረቅ አሉት።

ዓወቀም የልቡ አሳብ መፈጸሙን ስለ ተረዳው ባለማወቅና በስሕተት በሠራችሁት ይቅርና በማወቅና በድፍረትም ብትሠሩት አሁን ንስሐ የምትገቡበት ከሆነ ባለፈው ሥራችሁ ሁሉ ቂም ይገቼ እንዳልጐዳችሁ እምላለሁ አላቸው።

ከዚህም በኋላ ሁሉም በግንባራቸው እየተደፉ ማረን አሉትና ይቅር ለእግዚአብሔር ባላቸው ጊዜ በየተራ እየተነሡ አንገቱን እያቀፉ ይስሙት ጀመር።

ዕርቃቸውም በመሐላ ከተጨረሰ በኋላ እንደ ገና በጉልበታቸው እየተንበረከኩ ወንድማችን ሆይ፤ መምሬ ሰባጋዲስ ካንተ ጋራ ደግና ክፉ እስከ መነጋገር የደረሱበት ምክንያቱ በአባትህ በሟቹ አቶ እንደ ልቡና በእኛው ምክንያት ነው እንጂ በራሳቸው ጉዳይ ካንተ ጋራ ምንም የሚያገናኝ ነገር አልነበራቸውም። ስለዚህ ዕርቃችን መሠረት ያለው ነገር እንዲሆን ከእርሳቸውም ጋራ ታረቅልን አሉት።

ዓወቀም ከዘመዶቹ ጋራ በመታረቁ ደስ ብሎት ሳለ አሁን ደግሞ ከመምሬ ሰባጋዲስ ጋር እንዲታረቅ ነገሩ ስለ ተጀመረ እጅግ ደስ አለውና ዘመዶቼ ሆይ፤ መምሬ ሰባጋዲስ አሮጌ ልማድ እየያዙና ባንዳንድ ተንኮለኛ ደብተራ ምክር እየተመከሩ ለጊዜው ይቆታሉ እንጂ ልባቸው ገርና ቅን ነው።

በየምክንያቱ እየተገናኘን ስንነጋገር ባንዳንድ ነገር በተቆጡ ጊዜ ሁለተኛ ፊቴን የሚያዩትና የሚያነጋግሩኝ አይመስለኝም። ነገር ግን በማግሥቱ ተመልሰው እየመጡ በትሕትና ቃል ሲያነግሩኝ በጣም አደንቅ ነበር። ስለዚህ በማናቸውም ቢሆን ከእርሳቸው ጋራ ለመታረቅ ፈቃዴ ነው።

*ነገር ግን ይህን የዕርቁን ነገር ያነሣችሁት ራሳችሁም አስባችሁ እንደ ሆነ ወይም እርሳቸው አስታርቁኝ ብለው ልከዋችሁ እንደ ሆነ ነገሩን ገልጣችሁ ንገሩኝና እታረቃለሁ አላቸው። ዘመዶቹም ባንድ ቃል ሆነው እኛ ግማሹን ተላጭታ ግማሹን ተቀብታ የሚባለው ተረት እንዳይደርስብን የሁላችንም የጠቡ ምክንያት አንድ ነውና ሁላችንም ታርቀን መንፈስ ቅዱስ እንዲወርድልን አስበን ነው እንጂ እርሳቸው አስታርቁኝ ብለው ልከውን እንደ ሆነ ውቃቢህ ያጥፋን፤ ያቶ እንደ ልቡን ቀን ይስጠን፤ እያሉ ይምሉ ይገዘቱ ጀመር።*

*እንግዲያውስ ከነገ ወዲያ አሙስ የሐምሌ ሥላሴ ስለ ሆኑ ወደ ደብረ ብርሃን እወጣለሁና ታቦት ዞሮ ሲገባ አንድ አፍታ በጥዱ ሥር ተገናኝተን ይቅር ለእግዚአብሔር እንድንባባል ይዛችኋቸው እንድትመጡ ይሁን አላቸው።*

## ምዕራፍ ፱

# ስለ ዓወቀና ስለ መምሬ ሰባጋዲስ የዕርቅ ነገር

*ያወቀ ዘመዶች የዕርቁን ነገር ተነጋግረውና መታረቂያቸውን ቀንና ሥፍራ ተቃጥረው ከተለያዩ በኋላ ከመካከላቸው ሺመልስ የሚባለውን ዘመዳቸውን ወደ መምሬ ሰባጋዲስ ቤት ልከው ይኸው እንግዲህ ስለ ዕርቁ ነገር ዓወቀን እሺ አሰኝተነዋልና እርስዎ ወቀሳና ረጅም ነገረ ሳያመጡ ባጭሩ ማረኝ ብለው እንዲወድቁ ይሁን። ወቀሳና ረጅም ነገር ያመጡ እንደ ሆነ ግን ዓወቀ ምላሽ የማያጣ ንቁና ፈጣን መሆኑን ያውቁታልና እርስዎ አንድ ነገር ሲናገሩ እርሱ አንድ ምላሽ ሲያመጣ በመካከሉ እንደ ገና ትጣሉና ዕርቁ ይፈርስብናል። ስለዚህ እንደ መከርንዎ ማረኝ ከማለት በቀር ሌላ ነገር እንዳያመጡ አደራ ብለንዎታል ብለህ ንገራቸው አሉት።*

*ሺመልስም ወደ መምሬ ሰባጋዲስ ቤት ሔዶ ከዘመዶቹ የተላከውን ሁሉ በነገራቸው ጊዜ ልጄ በምን ውቃቢ ቀረባችሁትና እሺ አሰኛችሁት። እኔ የፈራሁት ያንን እልኩን ያመጣና አልታረቅም ይላል ብዬ ነበረ እንጂ እርሱማ እሺ እታረቃለሁ ካለ በማን ዕድሌ። አሁንም እናንተ እንዳላችሁት ነገ ወደ ደብረ ብርሃን እመጣለሁና ታቦት ዞሮ ሲገባ በወንዶች መቋሚያ በኩል ፈልጉኝና ከጫምው ላይ ወድቄ ማረኝ እለዋለሁ። ከዚህ በቀር ሌላ ቃል የተናገርሁ እንደ ሆነ በአቡነ ሰላማ ቃል ነፍሴ ሲኦል ትውረድ በልህ ለዘመዶችህ ሁሉ ንገራቸው አሉትና ተመልሶ ቢነግራቸው እልልታ ብቻ ቀራቸው እንጂ ሁሉም ደስ አላቸው።*

ወይዘሮ ትሁን ዘር የምትባል አንዲቱ ዘመዳቸው መምሬ ሰባጋዲስ አንድ አጉል ነገር ተናግረው ዕርቁ ሳይፈርስ የቀረ እንደ ሆነ ምን አለች በሉኝ ብላ ተናገረችና ሴት ስሑት ነች አንች ምን ታውቂያለሽ እያሉ ተሳሳቁባት።

ከዚህም በኋላ በሐምሌ ሰባት ቀን ዓወቀ ከሌሊቱ በ፱ ሰዓት ተነሥቶ ሙሉ ጨረቃ ነበረችና ምንም ችግር ሳያገኘው ጧት ባንድ ሰዓት ደብረ ብርሃን ደረሰ።

ቅዳሴኢውም በሠለስት ነበረና ዕጣነ ሞገር ከተቆመና ታቦት ከዞረ በኋላ የዓወቀ ዘመዶች ሁሉ ከመምሬ ሰባጋዲስ ጋራ ሆነው በጥዱ ሥር ተቀምጠው ሲጠብቁ ዓወቀ በዚያው በቀጠሮ ሰዓት መጥቶ በመካከላቸው ተቀመጠ።

በዚያም ጊዜ አንዱ አቶ ይስማ ሸዋ የሚባለው ተነሥቶ ፊቱን ወደ ዓወቀ አቅንቶ ወንድማችን ሆይ፤ እስካሁን ድረስ ነገሩን አጋልጦ የሚያሳርቅ ሽማግሌ በመታጣቱ ብዙ ወራት ተኳርፈንና ተለያይተን ቆየን። አሁን ግን ያንተ ነገር ሁሉ እያደረ ወደ ልባችን እየገባ ስለ ሔደ በገዛ ራሳችን ማረን በለን ከመታረቅ ደረስን።

ደግሞ የሁላችንም የጠቡ መሠረት የሟቹ የአባትህን ያቶ እንደ ልቡን ተዝካር ነገር ስለ ሆነ ከነፍስ አባታቸው ከመምሬ ሰባጋዲስም ጋር እስከ መቀያየም ደረሳችሁ። ስለዚህ የጠቡ መሠረት አንድ ሆኖ ሳለ ከእኛ ጋራ ታርቀህ ከእርሳቸው ጋራ ሳትታረቅ ብትቀሩ የተጉለት ሰው ሁሉ ጉድ ይላል በማለት ሁለታችሁንም ታረቁ ብለን ብንጠይቃችሁ ለመታረቅ ፈቃዳችሁ መሆኑን አስታውቃችሁን። አሁንም ይቅር ለእግዚአብሔር ተባባሉና በየቤታችን እንሒድ ብሎ ተናገረ።

መምሬ ሰባጋዲስም አቶ ስማ ሸዋ የተናገረውን ነገር በፀጥታ ከሰሙ በኋላ ልጆቼ ሆይ፤ እኔና ዓወቀ የተቀያየምንበት ምክንያቱ ሁላችሁም እንደምታውቁት እኔ ለአባትህ ለአቶ እንደ ልቡ ተዝካር ድግስ ደግሰህ ካህናቱን አብላ፤ አጠጣ፤ በማለት፤ እርሱም ለተዝካራቸው ድግስ በመደገሴ ካህናቱ በመጠጥ እየሰከሩ የማይገባ ሥራ የሠሩ እንደ ሆነ ለሁላችንም ጉዳት ነውና የገንዘብ ምጽዋት ከመስጠት በቀር ድግስ አልደግስም በማለት ነው እንጂ ለራሴ የሚገባኝን ስጠኝ አልሰጥም በማለት አይደለም።

በማንም ሀገር ቢሆን የነፍስ ልጅ ሲሞት ሲጠጣበት የነበረው ዋንጫው፤ ሲተኛበት የነበረው አልጋውና ቁርበቱ፤ ሲለብሰው የነበረው ልብሱ የሚገባው ለነፍስ አባቱ ስለ ሆነ አቶ እንደ ልቡ ገና ሳይሞቱ ተናዘውልኝ ነበር። እኔ ግን ይህን ሁሉ ሳላነሣ መቆየቴ እርሱ አውቆ ያደርገዋል ብዬ ነበር።

አሁንም ታረቅ ካላችሁኝ ይቅር ለእግዚአብሔር ይበለኝ እንጂ ከርሱ የምፈልገው ሌላ ነገር የለኝም ብለው ማረኝ ለማለት ሲቀርቡ ዓወቀ በቁጣ ደሙ ፈላና ዘመዶቼ

ሆይ፤ ከመምሬ ሰባጋዲስ ጋራ ታረቅ ብትሉኝ እሺ ማለቴ ባለፈው ሥራቸው ሁሉ ንስሓ የገቡበት መስሎኝ ነበር እንጂ እንደዚህ የወቀሳ ቃል ይናገራሉ ብዬ አላስብሁም ነበር።

አሁንም ይህ አነጋገራቸው እኔን በደለኛ እያስመሰሉ ነውና የዚህ ነገር በሽማግሎች ሳይታይና ሳይጣራ ምንም ቢሆን ከእርሳቸው ጋራ አልታረቅም። ቃል ለምድር ለሰማይ ይሁንብኝ ብሎ ለመሔድ ተነሣ።

ወይዘሮ ትሁን ዘርም በዚያው ቆማ የዓወቀንና የመምሬ ሰባጋዲስን ንግግር ትሰማ ነበርና፤ ይኸውላችኍ፤ ትናንትና ይህን ስንነጋገር መምሬ ሰባጋዲስ አንድ አጉል ነገር ተናግረው ዕርቁ ያልፈረሰ እንደ ሆነ ምን አለኝ በሉኝ አላልኍችሁምን፤ እንግዲህ እረፉት አለችና ወደ ቤቷ የመሔድ ጉዞ ጀመረች።

ያወቀም ዘመዶች ሁሉ ወደ መምሬ ሰባጋዲስ ዓይናቸውን እያፈጠጡ ቀርበው ትናንትና የዕርቁን ነገር ስንነጋገር ማረኝ ከማለ በቀር ሌላ ቃል የተናገርሁ እንደ ሆነ በአቡነ ሰላማ ቃል ነፍሴ ወደ ሲኦል ትውረድ ብለው አልነበረምን፤ ምን ያለሁ ጉደኛ ነሁ እያሉ ዓይንሁ ላፈር ይሏቸው ጀመር።

መምሬ ሰባጋዲስ ግን ግድየለሽም መሳይ ነበሩና ሁላችሁም እንዲህ ልታወናብዱኝ አይገባም፤ አሁን የተናገርሁትን ሁሉ ሰምታችኍል። ታረቅ ብትሉኝ ሁሉም ይቅርብኝና ይቅር ለእግዚአብሔር ይበለኝ አልሁ እንጂ አባትህ የተናዘዙልኝ ለእኔ የሚገባኝ ለእኔ ካልሰሸኝ አልታረቅም አላልሁም። እርሱ ግን በዚህ አሁን በተናገርሁት ነገር አልታረቅም ካለ የዕርቁ ማፍረሻ ሰበብ መፈለጉ ነውና ይተወው፤ ይፈንጥረው ብለው በቁጣ ተነሡ።

ከዚህም በኋላ ያወቀ ዘመዶችና የመምሬ ሰባጋዲስ ወዳጆች ሁሉ ያሰቡት የዕርቁ ነገር ቀርቶ ያላሰቡት ጠብ ስለ ተነሣ አዝነው እንግዴህ ይህን ነገር እኛ የማንጨርሰው ከሆነ ሊቃውንቱ በእጨጌው ሰብሳቢነት ጉባዔ አድርገው የተዝካርን ነገር ከጨረሱ በኋላ በሌላውም ለየትንንሹ የመንፈሳዊ ጉዳይ ወደ ፊት ጉባዔ አድርገው ሊነጋገሩበት ቀን ወስነዋልና ይህም መምሬ ሰባጋዲስና ዓወቀ የተጣሉበትን የዋንጫና ያልጋ የልብስ ነገር ጉባዔ ቀርቦ ቢጨርስ ይሻላል በማለት ሁለቱም በጉባዔው እንዲገኙ አስማምተውና አፈጣጥመው በየቤታቸው ሔዱ።

## ምዕራፍ ፲

# ስለ መምሬ ሰባጋዲስ ድንጋጤና ጥንቃቄ

መምሬ ሰባጋዲስ ወደ ክፉ ይተረጒምብኛል ብለው ባላሰቡት ነገር ዓወቀ እንደ ተቆጣና ዕርቁ እንደ ፈረሰ አይተው እጅግ ደነገጡ። ይልቁንም ወደ ፊት በሊቃውንቱ ጉባዔ ቀርበው ከዓወቀ ጋራ እንዲነጋገሩ ነገሩ በመቆረጡ በፍርሐት ተርበደበዱ።

ቢሆንም መምሬ ሰባጋዲስ ቁርበታቸው ብቻ ሞኝ ይመስላል እንጂ ውስጠ ብልጥ ነበሩና እንግዴህ በጉባዔው ፊት ቀርበው ከዓወቀ ጋራ ተነጋግሬ የተረታሁ እንደ ሆነ ተንቄና ተዋርጄ ልኖር ነው። ይልቁንም ዓወቀ በዚኢህ ነገር እጅግ ተናዷልና ምናልባት ለስሚውና ለፈራጁ የሚያስቸግር አንድ የወንጀል ነገር አምጥቶ ሥልጣኑ ይያዝልኝ ብሎ የተናገረ እንደ ሆነ ለፋሲካ በዓል ከየነፍስ ልጆቼ የጦም ቆሎ እንኳ እንዳልቀበል ያደርገኛል። ለዚህም ነገር የሚጠቅም ምክር ከደብረ ብርሃን አለቃ እንዳልጠይቅ ለትጉለት ቅርስ ስለ ሆነ ወሬው በቶሎ ይሰማማብኛልና ወደ አንኮበር ወጥቼ የየደብሩን አለቆች ብጠይቅ ይሻላል ብለው በቶሎ ስንቃቸውን አሰናድተው ተጓዙ። አንኮበርም በደረሱ ጊዜ ከወዳጃቸው ከመምሬ አሰጋኸኝ ቤት ገብተው አደሩ። በማግሥቱኡም በማለዳ ተነሥተው ወደ ማርያም አለቃ ሔደው የዘመኑን አዲስ ሥልጣኔ ተምሬአለሁ የሚል ዓወቀ የሚባል በተጉለት ወረዳ ተነሥቶ የነፍስ ልጆችህ ሲሞቱ ልብስ መውሰድ አይገባህም ብሎ ክርክር ይዞኛል። ነገሩም ወደ ፊት ሊቃውንቱና መምሕራኑ ጉባዔ በሚያደርጉበት ጊዜ እንዲታይ ተቃጥረናልና እንደ ወዳጅ መክረው፤ እንደ ዳኛ ፈርደው በዚህ ነገር ግፉበትም ቢሉኝ፤ ይቀርብህም፤ ቢሉ ከፈቃድዎ አልወጣምና የሚያዋጣኝን እርግጡን ንገር እንዲነገሩኝ ተማጥኜብዎታለሁ ብለው ከጫማቸው ላይ ወደቁ።

አለቃም የመምሬ ሰባጋዲስን ነገር ከሰሙ በኋላ መምሬ ሆይ፤ ዘመኑም የሰውም እውቀት ተለዋውጧልና እንደ ዘመኑ መሥራት ይሻላል። ዘመን የማይለውጠው የሃይማኖትን ነገር ብቻ ነው እንጂኢ የልማድ ነገር ንጉሥንና መንግሥትን ወይም ሕዝብን የሚጐዳ ካልሆነ በቀር ጥቅሙን እያመዛዘኑ ቢለውጡት አያስቸገርም። ስለዚህ የነፍስ ልጃችሁ በሞተ ጊዜ ባለ ጠጋ እንደ ሆነ ልብሱንና አልጋውን ጀንዲውን ለነዳያን መመጽወት ነው። ድኃ የሆነ እንደ ሆነ ግን ለድኃይቱ ሚስቱና ለልጆቹ መተው ነው እንጂኢ እናንተ ቀሳውስቱ እየወሰዳችሁ ልትሰለብሱት የሚገባ አይመስለኝም። እንዲያውም እስከ ዛሬ ልብ አድርገን ባናስተውለው ነው እንጂ አንዳንዱ ሰው በሚጋባ በሽታ ተሰቦ ወይም በተቅማጥ ይሞታልና የዚያን ልብስ እየወሰዱ መልበስ ወይም ለሌላ ሰው መሸጥ ትልቅ ስህተት ነው።

ሀኪሞችማ በሚገባ በሽታ የታመመ ሰው ሲሞት የለበሰውን ልብስ በእሳት አቃጥሉ እያሉ ያዛሉ ሲሉ ሰምተናልና ይህን የመሰለውን ጉዳት የሚያመጣው ንገር ቢቀርብዎ ይሻላል። ደግሞ እርስዎ የሚቹን ልብስ መውሰድ ይገባኛል ብለው ሲከራከሩ ዓወቀ የሚች ልብስ ለነፍስ አባቱ ይገባል ተብሎ የታዘዘበትን መጽሐፍ ይንገሩኝ ያለዎ እንደ ሆነ አያገኙምና ትልቅ ኀፍረት ይሆንብዎታል።

ይልቁንም ዓወቀ አጽንቶ የያዘው ይህን የመሰለ ንገር በኦርቶዶክሳዊትና በእስክንድርያዊት ቤተ ክርስቲያን አይደረግም በማለት ነው ሲሉ ስምተናልና በዚህ ነገር በጣም ቢጠነቀቁ ይሻላል። እንግዲህ በእኔ ወገን የምመክርዎ በጉባዔው ፊት ሲቀርቡ አጥፍቻለሁ ማረኝ ብለው በዓወቀ እግር እንዲወድቁና ነገሩ እንዲቀር ነው ብለው ከልብ የሆነ እውነተኛ ምክር መከርዋቸው።

መምሬ ሰባጋዲስም መካሪና ዘመድ አያሳጣዎ ብለው መርቀው ተሰናበቱ።

ከዚያም ሲወጡ በየተራ እየሔዱ የሚካኤልን፣ የጊዮርጊስን፣ የመድኃኔ ዓለምን አለቆች ቢጠይቋቸው ከማርያም አለቃ ጋራ የተማከሩ ይመስል ቃላቸው አንድ ስለ ሆነ መምሬ ሰባጋዲስ ሳይጠራጠሩ ምክራቸውን ተቀበሉ።

ባራተኛውም ቀን ከወዳጃቸው ከመሬ አሰጋኸኝ ጋራ ተሰነባብተው ወደ ተጉለት ተመለሱ።

## ምዕራፍ ፲፩

# ስለ ሁለተኛው ጉባዔ ነገር

በዓወቀና በመምሬ ሰባጋዲስ መካከል በተነሣው በተዝካር ነገር ሊቃውንቱና መምሕራኑ ጉባዔ አድርገው የተዝካር ነገር ከጨረሱ በኋላ ዓቃቤ ሰዓት ዘወልደ ማርያም ሌላውንም በስሕተት የገባውን ለመሙላት አሳባቸውን ገልጠው ቢናገሩ በየቤታቸው ስናስብበት ከርመን ሁለተኛውን ጉባዔ በሚመጣው ዓመት በኅዳር ፳ ቀን እናደርጋለን ተባብለው ተለያይተው ነበርና አሁን ቀጠሮ ስለ ደረሰ ቀደም እያሉ በኅዳር ፩ ቀን እንጦጦ ራጉኤል (እንተ ይእቲ ደብረ ኃይል) ገቡ። መልአከ ፀሐይ ክንፉ ብቻ የልብ በሽታ ነበረባቸው ጾመ ፍልሰታን በጥሬና በውኃ እጾማለሁ ብለው የልባቸው በሽታ ተቀስቅሶባቸው ጳጉሜ ሲገባ አረፉና በደብረ ሊባኖስ ተቀበሩ።

እጨጌውም ሊቃውንቱና መምሕራኑ በዚያው በቀጠሮው ቀን መምጣታቸውን በሰሙ ጊዜ የደብረ ሊባኖስን ገዳም መጋቢና ፀባቲውን አስከትለው በኅዳር ፯ እንጦጦ

ራጉኤል ደረሱ። በማግሥቱም በማለዳ መጥተው በጉባዔው በተቀመጡ ጊዜ ሊቃውንቱና መምሕራኑ እየመጡ እንድ እማዕረጋቸው ተራ በየመንበራቸው ተቀመጡ።

ከዚህም በኋላ ፓትርያርክ ጐሹ ተነሥተው ከእጨጌው ፈቃድ ከተቀበሉ በኋላ ጉባዔ የሆነበትን ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ነገር ይናገሩ ጀመሩ።

አባቶቼና ወንድሞቼ ሆይ፤ አስቀድሞ የእግዚአብሔር ስሙ የተባረከ ይሁንና ከዚህ ቀንና ሰዓት ስለ ደረስን ባንድነትም ስለ ሰበሰበን እናመሰግነዋለን። አሁን በዚህ ጉባዔ የተሰበሰብንበት ምክንያቱ ከዚህ ቀድሞ በዓወቀና በመምሬ ሰባጋዲስ መካከል የተነሣውን የተዝካርን ነገር ተነጋግረን ስንጨርስ ዓቃቤ ሰዓት ዘወልደ ማርያም ተነሥተው በስሕተት ገብቶ ልማድ ሆኖ የኖረውን ትንንሹን የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት እንድናሻሽል ቢነግሩን በየቤታችን ሥናስብበ ከርመን ክረምት ውጭ በኅዳር ፳ ቀን ተገናኝተን እንድንጨርስ ተስማምተን ተለያይተን ነበርን። የዛሬው ጉባዔ ምክንያቱ ይህ ነው።

እኔ በበኩሌ የተማሩትን ወዳጆቼን ሰብስቤ ባማክራቸው ሁሉም የዓቃቤ ሰዓት ዘወልደ ማርያም አሳብ መልካም ነው ብለውኛልና ሌላ የምጨምርበት ነገር የለኝም። ስለዚህ እናንተ በየተራ እየተነሣችሁ ለዚሁ ነገር አሳባችሁን አስታውቁና በበዛው ወገን ነገሩ ይቆረጣል አሏቸው።

ከዚህም በኋላ መልአከ ገነት እንግዳ ተነሥተው እንደ እኔ አሳብ የሆነ እንደ ሆነ እስካሁን በልማድ ስንሠራው በኖርነው ባለፈው ሥራችን እግዚአብሔር ይቅር ይበለን እንጂ ለወደ ፊቱ ዓቃቤ ሰዓት ዘወልደ ማርያም እንደ ተናገሩት ቢሆን መልካም ነው አሉ።

ቀጥሎ መልአከ ብርሃን ኃይሉ ተነሥተው ዕውር ምን ትሻለህ ቢሉት ብርሃን አለ ይባላል። እኛስ በልማድ ከመኖር በመጽሐፍ ቃል መኖር ይሻላል ሲሉን ጊዜ ሌላ ምን ነገር ያስፈልገናል። በማናቸውም ቢሆን የዓቃቤ ሰዓት ዘወልደ ማርያም ነገር መልካም ነው ብለው ተቀመጡ።

ቀጥሎ መልአከ ስለማ ምርህካ ተነሥተው የእኛ ነገር በገዛ አረሟ እባብ ይዛ ታስፈራራ እንደሚባእልው ነገር ሊሆንብን ነው።

በልማድ መኖር ቀርቶ በመጽሐፍ ቃል መኖር ይሻላል ሲሉ ጊዜ ምን ነገር እንጨምርበታለን። የዓቃቤ ሰዓት ዘወልደ ማርያም ነገር መልካም ነው አሉ።

ቀጥሎም መልአከ ኃይል ተስፋዬ ተነሥተው ከዳቦ የተገኘ ወጥ አብረህ ግመጥ፤ እንደሚባለው ሁሉ አሁን በተዝካር ምክንያት ተነሳሥቶ በቤተ ክርስቲያናችን በስሕተት ገብቶ ልማድ ሆኖ የኖረው ነገር ሁሉ እየተሻሻለ ይታደስ ሲባል ጊዜ ወደን ተቀብለናል ከማለት በቀር ሌላ ምን እንጨምርበታለን። የዓቃቤ ሰዓት ዘወረደ ማርያም ነገር እጅግ መልካም ነውና እንቀበለዋለን አሉ።

ቀጥሎ ቄስ አጼ ገብረ ሚካኤል ተነሥተው እሳት ቢተኛ፤ ገለባ ሰደደ ጉበኛ የሚባለው ተረት በእኛ ደረሰ። ቢሆን ይህን የመሰለውን የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት መጀመሪያ እኛው አስበን ማሻሻልና ማደስ ይገባን ነበር። ባይሆንስ እግዚአብሔር ዓወቀንና መምሬ ሰባጋዲስን ምክንያት አድርጐ ሲያስነሣልን ጊዜ እሺ ወደናል ከማለት በቀር ሌላ ምን እንናገራለን። እኔ በፍፁም ልቤ የዓቃቤ ሰዓት ዘወልደ ማርያምን ነገር ተቀብያለሁ ብለው ተናገሩ ነገሩ በሁሉም ዘንድ መወደዱን ለማስረዳት በጉባዔው ያሉት ሁሉ በደታ አጨበጨቡ።

ከዚያም በኋላ የደብረ ኃይል አጋፋሪ ወደ ብፁዕ እጨጌ ቀርቦ ይህ በጉባዔ የተጨረሰው መንፈሳዊ ነገር ሁሉ ያገራችንን ሕዝብ በሙሉ ደስ የሚያሰኝ የደስታ ቀን ስለ ሆነ ነገ እሁድ ቅዳሴ ውጭ መዘምራኑ ገስግሰው ወረብ እንዲወርቡና በከበሮና በጸናጽል እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ለማስረገጥ ማሰባቸውን አመለከተ።

ብፁዕ እጨጌም ፈቃድ ባደረጉ ጊዜ ወደ ማታ ደወል ተደውሎ የየደብሩ መዘምራን ትልቁም ትንሹም ተሰበሰቡና በማግሥቱ የሚወርቡትን ወረብ ሲማከሩ የዜማው መምር ተነሥቶ በጉባዔው ስለ ተፈጸመው ስለ ሙሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደስታ በመጀመሪኢያ ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ስቡሐ ዘተሰብሐ ብለን ወረቡን ስለ አቡነ ተክለ ሃይማኖትና በወንበራቸው ስለ ተቀመጡት ስለ እጨጌው ክቡር አበ ኵልነ አባ ተክለ ሃይማኖት። አስታጋብእነ ለስብሐተ እግዚአብሔር እንላለን።

በጽፋትም ጊዜ ጉባዔው ስለ ተደረገበት ስለ ደብራችን ክብር ንፍሑ ቀርነ በጽዮን በደረብ ኃይል። ስብኩ በዓለ ራጉኤል ሊቀ መላእክት ብለን እንጨርሳለን ብለው ተናገሩና በዚህ ተስማምተው ሔዱ።

በማግሥቱም ስለ እሁድነቱ ቅዳሴው በነግህ ነበረና ጸሎተ ቅዳሴው ከተፈጸመ በኋላ ብፁዕ እጨጌ ቀሳውስቱ ላይ መንበራቸውን አስዘርግተው በተቀመጡ ጊዜ ሊቃውንቱና መምሕራኑ ሁሉ በቀኝና በግራ እንደ ማዕረጋቸው ተራ ተቀመጡ።

ደግሞ የጉባዔውን መጨረሻ ለማየት ብዙ መሳፍንትና መኳንንት ከአዲስ አበባ ወጥተው ነበርና እነርሱም እንደ ማዕረጋቸው ባንድ ወገን ተቀመጡ።

ከዚህም በኋላ መዘምራኑ ድርብ መርገፋቸውን፤ ግምጃ ቀሚሳቸውን እየለበሱ መጥተው ከሰቅሰቁ በታች ባለው ሜዳ ላይ ሆነው ንሴብሖ ብለው ሲጨርሱ አበ ኵልነ አባ ተክለ ሃይማኖት በሚለው ወረብ እያስረገጡ ቆይተው ሲደምቅ ንፍሐ ቀርነ በጽዮን በደብረ ኃይል የሚለውን እየጸፉ ያሸበሽቡ ጀመር፡

ከቶ ይህን የመሰለ የደስታ በዓል በመቸም ጊዜ ተደርጐ አያውቅም ይባላል።

ወረቡም ሲጨረስ ብፁዕ እጨጌ ተነሥተው ቆመው የጉባዔውን ነገር ሁሉ በፍቅርና በሰላም ስለ መጨረሳቸው ሊቃውንቱንና መምሕራኑን እያመሰገኑ መሳፍንቱና መኳንንቱም፤ ሕዝቡም ሁሉ የጉባዔውን መጨረሻ ለማየት ከአዲስ አበባ በመምጣታቸው እየመረቁ ካሳረጉ በኋላ ተቀመጡ።

ይህም ሁሉ ሲሆን ዓወቀ ከመምሬ ሰባጋዲስ ጋራ እርቅ የተፋረሱበትን ነገር ለጉባዔው ለማመልከት በዚያው ቆሞ ሲጠባበቅ ነበረና እጨጌውና ሊቃውንቱ ለመሔድ በሚነሡበት ጊዜ ድምጹን ከፍ አድርጐ አባቶቼ ሆይ፤ ከመምሬ ሰባጋዲስ ጋራ በፊታችሁ የምነጋገርበት ትንሽ ጉዳይ አለኝና ስለ ስባረ አጽሙ አንድ አፍታ ተቀምጣችሁ አድምጡኝ ብሎ የልመና ቃል ተናገረ።

አፈ ጉባዔውም መልአከ ኃይል ተስፋዬ ተነሥተው ቆመው ስለ ስባረ አጽሙ ብለህ ስትለምን እንኳን ትንሽና ትልቅም ጉዳይ ቢሆን እንሰማሃለንና ተናገር አሉት።

መምሬ ሰባጋዲስ ግን የአንኮበር አለቆች እንደ መከሩዋቸው ዓወቀ ለጉባዔው የሚናገርባቸውን ነገር ለሙተውና ማረኝ ለማለት ቁርጥ አሳብ አድርገው ነበርና ገና መናገር ሳይጀምር ታላቅ ድንጋይ ተሸክመው በእግሩ ሥር ወድቀው እስካሁን በአባትህ ተዝካርና በመቃብር ቤታቸው፤ በሙት ልብሱም ነገር ስለ አስቸገርሁህ ንስሐ ገብቻለሁና አንተም ስለ ስባረ አጽሙ ብለህ ማረኝ አሉት።

ዓወቀም ለመማሩ እምረዎታለሁ። ነገር ግን የተጣላንበትን ነገር ሊቃውንቱ ቢሰሙት ምን ቸገርዎ እያለ ቢያመለክታቸው፤ እኔ አጥፍቻለሁ፤ ንስሓ ገብቻለሁ ሊቃውንቱ እንዲሰሙት ምን ያስፈልጋል። አሁን እኔን ይቅር ካላልኸኝ አንተንም ሰማያዊ አባትህ ይቅር አይልህም እያሉ ያንኑ የሚያውቁትን የአቡነ ዘበሰማያትን ጥቅስ እየጠቀሱ ያስፈራሩት ጀመር።

ዓወቀም ነገሩ በሊቃውንት ፊት ይገለጥ ማለቱ የእርቁ መሠረቱ እንዲጸና ነበር እንጂኢ እርቁን እምቢ ለማለት አልነበረምና መምሬ ሆይ፤ አሳብዎ እንደዚህ ከሆነ አጥፍቻለሁ ማረኝ ማለት ብቻ የሚበቃ አይደለምና ስለ ተዝካርና ስለ መቃብር ቤት፤

ስለ ሙት ልብስ መውሰድ ነገር የአንተ አሳብ ሁሉ ገብቶኛል ብለው በነዚህ በሊቃውንቱና በመምሕራኑ ፊት ይናገሩና ይቅር ለእግዚአብሔር እላለሁ አላቸው።

ልጄ ሆይ፤ ለምን እንደ ሦስት ዓመት ሕፃን ታደርገኛለህ። ምንስ ቢሆን ነገር ሳይገባኝና ሳልረዳው አጥፍቻለሁና ማረኝ እላለሁን። ተዝካር በጠላ፣ በጠጅ፣ በአረቄ፣ ከሚሆን በገንዘብ ወይም በእኽልና በከብት ምጽዋት ቢሆን መሻሉን አንተው አስረድተኸኛል። የመቃብር ቤትም በእንጨትና በሣር ከሚሆ፤ በጥርብ ደንጊያ ቢሆን ለብዙ ዘመን የሚቆይ መሆኑን አንተው አስረድተኸኛል። የሙት ልብስም ለነዳያን ቢመጸውት መልካም መሆኑን፤ የአንኮበር አለቆች አስረድተውኛልና ሁሉም ገብቶኛል፤ እያሉ እየተንገፈገፉ ይናገሩ ጀመር። ዓወቀም መምሬ ሰባጋዲስ ባለፈው ሥራቸው ሁሉ በእርግጥ ንስሐ መግባታቸውን ከተረዳ በኋላ መምሬ ሆይ፤ እንደዚህስ ከሆነ ይማሩኝ የምልዎ እኔ ነኝ ብሎ ተሽቀዳድሞ በጫማቸው ላይ ወደቀ። መምሬ ሰባጋዲስም በራሱ ላይ ወድቀው ሁለቱም ድምጣቸውን እያሰሙ ይቅር ለእግዚአብሔር ተባባሉ።

## ምዕራፍ ፲፪

# ስለ መምሬ ሰባጋዲስ ስብከት

የእርቁም ነገር ከተጨረሰ በኋላ መምሬ ሰባጋዲስ ወደ እጨጌው ቀርበው ብፁዕ አባታችን ሆይ፤ ከዓወቀ ጋራ እስከ መቀያየምና ይቅር ለእግዚአብሔር እስከ መባባል የደረስንበትን ነገር ሁሉ በሊቃውንቱና በመምሕራኑ ፊት ለመስበክ አስቤአልሁና ፈቃድዎን እለምናለሁ።

ይልቁንም ዋናው አሳቤ የጉባዔውን ፍጻሜ ለማየት ከአዲስ አበባ የመጡት መሳፍንቱና መኳንንቱ ሳይበታተኑብኝ አሁን ለመጀመር ነው ብለው ተናገሩ።

ብፁዕ እጨጌም ከሊቃውንቱና ከመምሕራኑ ጋራ ከተማከሩ በኋላ ፈቅደንልሃልና ስብከትህን ጀምር አሏቸው።

መምሬ ሰባጋዲስም ከፍ ባለ ሥፍራ ላይ ቆመው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ስብከት ጀመሩ።

ጌቶችና አባቶቼ፤ ወንድሞቼም ሆይ፤ ዛሬ ጊዜ አጋጥሞኝ እናንተ ክቡራን ሊቃውንትና መምሕራን፤ ይልቁንም ብፁዕ እጨጌ ጉባዔ ባደረጋችሁበት ቀን በፊታችሁ ቆሜ የልቤን አሳብ ለመናገር ስለ ተፈቀደልኝ እጅግ መታደል ነውና በሙሉ ሰውነቴ ደስታ ይሰማኛል።

ቀሳውስት ያልፋሉ፤ ቀሳስት ይተካሉ። ቤተ ክርስቲያን ግን ለዘላለም እርስዋ ናት። ከዚህም ቀድሞ ይህን ካለማወቄ የተነሣ በየምክንያቱ ከየነፍ ልጆቼ በሰበሰብሁት ገንዘብ ሰፊ ርስት ገዛሁ። ቤትም ሠራሁ። የደስታ ገነትም አድርጌ ልዩ ልዩ ፍሬ የሚያፈራ ተክልና ዛፍ ተከልሁ። የላምና የበግም መንጋ አበዛሁ። ታላቅና የተፈራም ሆንሁ። ከእኔም አስቀድሞ በተጉለት ከነበሩት ቀሳውስት ይልቅ ከበርሁ። ዓይኔ ያየውን፤ ልቤም ያሰበውን ሁሉ በማግኘት ሰውነቴን ደስ አሰኘኋት።

አሁን ግን ለሁሉ ጊዜ አለውና በአቶ እንደ ልቡ ተዝካር ነገር በልጃቸው ከዓወቀ ጋራ መነጋገር ከጀመርሁበት ቀን ወዲህ ያለፈውን ሥራዬን ሁሉ ብመለከተው ከንቱና የከንቱ ከንቱ ሆኖ አገኘሁት። ከንቱ ነፋስም እንደ መከተል ቆጠርሁት።

ጨው ሆኜ ሳልሁ አንድ ቀን እንኳ አልጫ የሆነውን የሰውን ልብ አላጣፈጥሁም። መብራት ሆኜ ሳለሁ አንድ ቀን እንኳ በጨለማ ውስጥ አላበራሁም። የተራራ ላይ መንደር ሆኜ ሳለሁ አንድ ቀን እንኳ አልታየሁም።

አሁን ግን እናንተ ሊቃውንቱና መምሕራትኑ በደብረ ኃይል ጉባዔ አድርጋችሁ መንፈሳዊውን የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት ሁሉ እያሻሻላችሁ በማደሳችሁና በመወሰናችሁ ወደ ፊት የሚነሡ ቀሳውስትና ዲያቆናት በሠራችሁትና በወሰናችሁት ሥርዓት ጸንተው የኖሩ እንደ ሆነ እንደ እኛ ከመወቀስ ይድናሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

ይህንም መንፈሳዊውን ነገር ሁሉ ለመወሰን ላሳሰባችሁ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባዋል። ስሙም ለዘላለም የተባረከ ይሁን። ጌቶችና አባቶቼ ሆይ፤ እንደዚህም ስላልኋችሁ ይህ ያለፈው ስሕተት ሁሉ የእናንተም ጭምር ነው እንጂ የእኛ የቀሳውስቱና የዲያቆናቱ ብቻ አለመሆኑንን ማወቅና መረዳት ይገባችኋል። ይህንኑም አሁን በየተራው እያደረግሁ እነግራኋለሁ ብለው ገና ለመናገር ሳይጀምሩ፤ ብፁዕ እጨጌ ወደ መምሬ ሰባጋዲስ ፊታቸውን አዙረው አንተ ቄስ ምነው እንግዴህ አይበቃህምን። ደግሞ እነዚህን ሊቃውንቱን ምን አደረጉ ልትላቸው ይሆን አላቸው።

መምሬ ሰባጋዲስም ለጊዜው ደንገጥ ካሉ በኋላ እንደ ገና አንሰራሩና ፊታቸውን ወደ እጨጌ አቅንተው ብፁዕ አባታችን ሆይ፤ ባልፈው ነገር ሁሉ እንደ ንፍሮ ተቀቅያለሁ፤ በስያለሁና እባክዎ ይተውኝ እንፏሎቴ ይውጣልኝ። አለዛሬም እነዚህ ሊቃውንቱና መምሕራኑ ባንድነት ተሰብስበው አይገኙምና የልቤን እንድናገር በተክለ ሃይማኖት በስባረ አጽሙ ይፍቀዱልኝ እያሉ ይውለበለቡ ጀመር።

በዚህም ጊዜ ዓቃቤ ሰዓት ዘወልደ ማርያም ተነሥተው እውነት ነገር የሚናገር ከሆነ ቢናገር እኛ ምን ቸገረን ብለው ለእጨጌ በቀስታ አመለከቱና ተፈቅዶልሃልና ተናገር አሏቸው።

መምሬ ሰባጋዲም ስለ ተፈቀደላቸው እያመሰገኑ፤ እጅ ከነሡ በኋላ ተናገርማ ካላችሁኝ መልአከ ኃይል ተስፋዬና ዓቃቤ ሰዓት ዘወልደ ማርያም በጉባዔው ፊት ቆመው ጥፋቱን ሁሉ በእኛ በቀሳውስቱ ላይ እያስመሰሉ ለተናገሩት ሁሉ ምላሹን እንዳልሰጥ ያለቀውን ነገር እንደ ገና መጀመር ይሆንብኛልና ሳያውቁብን ቀሩ እንዳትሉ ብቻ ባጭሩ አድርጌ እናገራለሁ።

ባለፈው ዘመን ስንሠራቸው ከነበረው ሥራዎች ሁሉ እንደ ነውር ሆነው የተቆጠሩብን አሥር ነገሮች ናቸው።

፩ኛ. በየድግስና በየተዝካሩ ቤት ስለ መስከር፤

፪ኛ. ቀሳውስት ሚስቶቻቸውን ስለ መፍታት፤

፫ኛ. ቀሳውስት ንባብና ትርጓሜ ሳይማሩ ስለ መቀሰስ፤

፬ኛ. የቤተ ክርስቲያን አለቃ የግዕዝ ቋንቋ ስለ አለማወቁ፤

፭ኛ. ቀሳውስት ብር እየሰጡ ቅስና ስለ መሾማቸው፤

፮ኛ. ለድኃ ትንሽ ፍታት፤ ለባለ ጠጋ ትልቅ ፍታት ስለ መደረጉ፤

፯ኛ. ቀሳውስት በሽተኛ አቁርበው ገንዘብ ስለ መቀበላቸው፤

፰ኛ. ቀሳውስት በተክሊል ሚስት ስለ አለማግባታቸው፤

፱ኛ. ቀሳውስት ታቦት ረከሰ እያሉ ስለ ማስባረካቸው፤

፲ኛ. ቀሳውስት በቅዳሴ ጊዜ ወንጌል እየተረጐሙ ስለ አለማስማታቻቸው ነው።

እንግዴህ ምናልባት በነዚህ ባለፉት ነገሮች ሁሉ በእለተ ምጽአት በክርስቶስ በጌትነቱ ዙፋን ጌት በምንቆምበት ጊዜ የሚፈርድብን የሆነ እንደ ሆነ አላፊዎች የምናደርገው ጳጳሳቱንና እናንተን ሊቃውንቱን መሆኑ የማይጠረጠር ነው ብለው ሌላ ነገር እጀምራለሁ ሲሉ ዓቃቤ ሰዓት ዘወልደ ማርያም ተነሥተው ምነው መምሬ፤ እንዲያው ያለ ልጓም ልትጋልበን ጀመርህና ባልተናዘዙትና ንስሐ ባልገቡ ሰዎች ቤት እየገባህ አንድ ዋንጫ ጠላ በጠጣህ ቁጥር በሐልዮ፣ በነቢብ፣ በገቢር፣ የሠራችሁትን

ኃጢአት ሁሉ እግዚአብሔር ይፍታ እያልህ የምትሒደው ለካ እኛን ሊቃውንቱን አላፊዎች አደርጋለሁ እያልህ ኖርዋል።

በል እስቲ በማናቸውም ቢሆን እኛን አላፊዎች የምታደርጉበትን ምክንያቱን ሁሉ ገልጠህ ተናገርና እንስማው አሏቸው።

አላፊዎች የምናደርግበት ምክንያቱማ እስከ ዛሬ ድረስ በስሕተት የገባውን ሁሉ ልማድ አድርገን ስንኖር ባይናችሁ እያያችሁ፤ በጆሮአችሁ እየሰማችሁ እንደ መጻሕፍት ቃል ኑሮ እንጂ በልማድ መኖር አይገባችሁም ብላችሁ ስላልመከራችሁን እምቢ ብንልም በቤተ ክርስቲያን ፊት ስላልገሠፃችሁን ነው።

ይልቁንም እኛ ያልተማርነው ቀሳውስቱና ዲያቆናቱ ብናጠፋ እንኳ እናንተ የተማራችሁት ሊቃውንቱ እንደ መጻሕፍቱ ቃል እየሠራችሁ ለእኛ አብነት መሆን ይገባችሁ ነበርና እየሠራችሁ አብነታችሁን ባለማየታችሁ ነው። እስቲ እንደ እኛ በልማድ የማይኖሩ ሊቃውንቶች በሙቶ ስንት የሚገኙ ይመስልዎታል። ጠባቂ የሌላቸው እብጎች እንዲጠፉና ተኵላ እንዲበላቸው የታወቀ አይደለምን፤ ምንስ በጎቹን ተኵላ ቢበላቸው ጠባቂው ቅጣት ይቀርለታልን።


እንግዴህ ይህን ሁሉ ጥፋት በእኛ በቀሳውስቱ ላይ ብቻ ለማድረግ በጉባዔ ተሰብስባችሁ መታረቂያ ብታደርጉን እግዚአብሔር ይወድላችኋልን እያሉ የልባቸውን ተናግረው ሲጨርሱ አባቶቼ ሆይ፤ እርጥቡ ሬሳ፤ ደረቁን አስነሣ እንደሚባል ዓቃቤ ሰዓት ዘወልደ ማርያም ጥፋቱን ሁሉ በቀሳውስት ላይ ብቻ እያደረጉ ስለ ተናገሩ ተናድጄ ያለፈውን ነገር ተናገርሁ እንጂ ለወደ ፊቱማ ሁሉንም የተወሰነውን ሥርዓት አጽንተን ለመጠበቅ ያብቃን እንጂ ምንም የሚያከራክር ነገር የለበትም። ስለ ሆነም ነገሩ ከልቤ እየገንፈለ በድፍረት ይህን ሁሉ ነገር በመናገሬ ማሩኝ ብለው አንገታቸውን ሲደፉ፤ መልአከ ስለማ ምህርካ ተነሥተው መምሬ ሰባጋዲስ ሆይ፤ እኛ ዛሬ የተሰበሰብነው ለእውነት ነገር ነው እንጂ ለሐሰትና ውዳሴ አይደለምና አሁን እርስዎ የተናገሩት ሁሉ እውነቱን ነገር ስለሆነ ከእኛ ወገን በድፍረት የሚቆጥርብዎ አንድም ሰው አይገኝም፤ ብለው ቢናገሩ በጉባዔው የተቀመጡት ሊቃውንቶችና መምሕራኑ ቃሉ ቃላችን ነው በማለት ሁሉም በደስታ አጨበጨቡ።

ከዚህም በኋላ በመጀመሪያው ጉባዔ የተስማሙበት ነገር ሁሉ በመዝገብ ተጽፎ በእጨጌውና በሊቃውንቱ ማኅተም ታትሞ ነበርና ይህም በሁለተኛው ጉባዔ የተስማሙበት ነገር ሁሉ ተጨማሪ ሆኖ በዚያው በፊተኛው መዝገብ ተጽፎ እንደ ገና ሁሉም አትመውበት ኋላ ለሚነሣው ትውልድ ምስክር ሆኖ እንዲቆይ ዋናው መዝገብ

በደብረ ሊባኖስ ይቀመጥ። ከዚያው በትክክል አንዳንድ ግልባጭ እየተጻፈ በሸዋ አውራጃ በዝቋላና በፍርኩታ፤ በትግሬ አውራጃ በአክሱምና በደብረ ቢዘን፤ በቤጌምድር አውራጃ በጣና ባሕር ቂርቆስ፤ በሳይንት አውራጃ በተድባበ ማርያም በጐጃም አውራጃ በመርጡለ ማርያምና፣ በዲማ፤ በወሎ አውራጃ በሐይቅና በግሼን ገዳማት እንዲቀመጥ ፈቅደናልና የብፁዕ እጨጌ ዳብዳቤ እየተጨመረ እንዲላክ ይሁን በማለት ተስማምተው ጉባዔ ተጨረሰ።

**ተፈጸመ።**

# ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ



በመርሐቤቴ ረመሽት ቀበሌ ደን አቦ በሚባል አካባቢ የተወለዱት ኅሩይ በወጣትነት ዕድሜያቸው ያሳዩት በነበረው ትጋትና ቅልጥፍና ፀሐፌ ትዕዛዝ ገብረሥላሴ ቀድሞ ይጠሩበት የነበረውን ገብረመስቀልን በመቀየር ኅሩይ አሏቸው።

ለዓፄ ኃይለሥላሴ የቅርብ አማካሪ በመሆን የሃይማኖትና የአስተዳደር ሕጎች እየተረጎሙና የአርትኦት ሥራዎቻቸውን እያጠናቀቁ እንዲወጡ ያደረጉት ብላቴን ጌታ ኅሩይ ታሪክ፣ ማኅበራዊ ጉዳይንና ፍልስፍናን ያካተቱ 42 የሚደርሱ መጻሕፍትን አሳትመዋል፡፡ ከሥራዎቻቸው መካከል **“ወዳጄ ልቤ”** የሚባለው መጽሐፍ ታዋቂነትንና ተወዳጅነትን አትርፎላቸዋል።።

## የደራሲው ሥራዎች

1. ከንግሥተ ሳባ እስከ ታላቁ ዐድዋ ዘመቻ**(ታሪክ)**
2. ኢትዮጵያና መተማ(ታሪክ)
3. ዳግማዊ ቴዎድሮስ**(ታሪክ)**
4. ደስታና ክብር**(ታሪክ)**
5. የሕይወት ታሪክ**(ትምህርት)**
6. ዋዜማ**(ታሪክ)**
7. ማኅደረ ብርሃን ሀገረ ጃፓን**(ታሪክ)**
8. በዕድሜ መሰንበት ሁሉን ለማየት**(ታሪክ)**

9. መጽሐፈ ቅኔ **(ግጥምና ቅኔ)**
10. ወዳጄ ልቤ**(ልብወለድ)**
11. የልብ ሐሳብ**(ልብወለድ)**
12. ዐዲስ አለም**(ልብወለድ)**
13. ጎሐ ጽባሕ **(መልክ፥ ገድልና: ነገረ መለኮት)**
14. ጥሩ ምንጭ **(መልክ፥ ገድልና ነገረ መለኮት)**
15. ስኳርና ወተት **(ተረቶችና ቀልዶች)**
16. ለልጅ ምክር ላባት መታሰቢያ**(ትምህርት)**